ለ. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተሰባበሩትን ነገሮች መጠጋገን።

20ኛ ጥያቄ፡- ሁለት ዓምዶች ያሉት ሠንጠረዥ አዘጋጅ። ሀ) በአንደኛው ዓምድ ውስጥ ከላይ የተጠቀሱትንና ሌሎችም ለቤተ ክርስቲያናችሁ ጤናማነትና መንፈሳዊ ብስለት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ የምትላቸውን አገልግሎቶች ዘርዝር። ለ) ከእያንዳንዱ አገልግሎት አጠገብ አገልግሎቱን በጥሩ ሁኔታ ሊከታተል ይችላል የምትለውን መሪ (ለምሳሌ፣ ሽማግሌ፣ መጋቢ፣ ወንጌላዊ፣ ዲያቆን) ጻፍ።

## ለአገልግሎት ድልደላ የሚያግዙ መሠረታዊ መርሖዎች

1. ቤተ ክርስቲያን ምንም ዓይነት የአመራር መዋቅሮችና ከላይ የተጠቀሱትን ዓይነት አገልጋዮች ብትቀጥርም፣ መንፈሳዊ እድገት እንዲመጣ ከተፈለገ፣ ከላይ የተገለጹት አገልጋዮች ተግባራቸውን የሚወጡበትን መንገድ መፈለጉ የግድ ይሆናል። ከላይ የተገለጹት አገልግሎቶች በአግባቡ እንዲከናወኑ ካልተደረገ፣ በሳል ክርስቲያኖችን ማፍራት አስቸጋሪ ይሆናል።

2. ሽማግሌዎች ከሌሎች ሥራዎቻቸው ጎን ለጎን (እርሻ ወይም የቢሮ ሥራ፣ የቤተሰብ እንክብካቤ፣ ወዘተ. . .) የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎቶች በሙሉ በብቃት ለመወጣት ከቻሉ፣ ሌሎች አገልጋዮችን መፈለጉ አስፈላጊ አይሆንም። በተግባር ሲታይ ግን፣ ሽማግሌዎች ሥራ ስለሚበዛባቸው፣ ከላይ የተጠቀሱትን አገልግሎቶች በሙሉ ሊወጡ አይችሉም። በመሆኑም፣ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ባልሆኑት ምእመናን አማካኝነት አገልግሎቶችን ለማካሄድ ጥረት ማድረግ ይኖርባታል።

ብዙውን ጊዜ ሰዎች በተወሰነ አገልግሎት ላይ ትኩረት በማድረግ ይህንኑ አገልግሎት በሚገባ ለማከናወን በሚጥሩበት ጊዜ ውጤታማ ይሆናሉ። ስለሆነም፣ አንድ ሰው በወንጌል ስርጭት ላይ ስጦታ ካለው፣ ትኩረቱን እዚያው ላይ ማድረግ አለበት። የማስተማር ስጦታ ያላቸው ሰዎች ደግሞ፣ በዚሁ አገልግሎት ላይ ቢሰማሩ የተሻለ ይሆናል። ሰዎችን ያለ ስጦታቸው ወይም ያለ ፍላጎታቸው በምናሠራበት ጊዜ፣ የእግዚአብሔርን እንጎዳለን።



እንዲሁም ደግሞ ለአንድ ሰው ካለው ጊዜ የበለጠ ኃላፊነት በምንሰጥበት ጊዜ፣ የእግዚአብሔርን ሥራ እናደናቅፋለን።

በሽማግሌዎች፣ ደመወዝ በሚከፈላቸው መጋቢዎችና ወንጌላውያን ብቻ በመጠቀም እያንዳንዱን አማኝ በእረኝነትና በደቀ መዝሙርነት ማገልገል አይቻልም። ስምንት ሽማግሌዎች 1000 ምእመናንን በሚገባ ሊያውቁና እያንዳንዱ አማኝ በመንፈሳዊ ብስለት እንዲያድግ ሊረዱት አይችሉም። ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ወይም ወንጌላዊ ብትቀጥርም፣ ጥቂት ሰዎች እጅግ ብዙ ምእመናንን መድረስ መቻላቸው አጠራጣሪ ነው። አንድ መጋቢ ለ1000 ምእመናን አገልግሎት በመስጠት እያንዳንዱ አማኝ በእምነቱ እንዲያድግ ሊያደርግ አይችልም። አንድ ወይም ሁለት ወንጌላውያን ወንጌሉን በማኅበረሰቡ ውስጥ ላሉት ሰዎች ሁሉ ሊያዳርሱ አይችሉም። ስለሆነም፣ አብያተ ክርስቲያናት የተወሰኑ ሰዎችን ቀጥረን ሁሉንም ሥራ ልናሠራ እንችላለን የሚል እሳቤ ሊኖራቸው አይገባም። እነዚህ አገልግሎቶች ሊፈጸሙ የሚችሉት ሁሉም ምእመናን እግዚአብሔር የሰጣቸውን የጸጋ ስጦታ ተጠቅመው ሲያገለግሉ ነው። ሽማግሌዎችና መጋቢው በሳልና ልምድ ያላቸው ምእመናን ጊዜያቸውን በመስጠት የሚያገለግሉበትንና ሰዎች በእምነታቸው እንዲያድጉ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ የሚያበረክቱበትን መዋቅር ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል።

5. መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመራር መሪዎች የእያንዳንዱን አማኝ መንፈሳዊ ሕይወት የሚንከባከቡበት ነው። ኢየሱስ ከ100 በጎቹ ውስጥ አንዱ ስለ ጠፋበት 99ኙን ትቶ አንዱን ፍለጋ ስለ ሄደ ሰው የተናገረው ምሳሌ አለ (ማቴ. 18:12-14)። እንደ እረኞች፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከትንሹ እስከ ትልቁ፣ ከድሀው እስከ ሀብታሙ፣ ምንም ትምህርት ከሌላት ሴት እስከ ከፍተኛ ትምህርት ያለው ወንድ ድረስ ለሁሉም ምእመናን እንክብካቤ ማድረግ ይኖርባቸዋል። የሰዎችን አካላዊ ችግሮች ለመፍታት ጥረት ማድረግ ቢኖርብንም፣ በመንፈሳዊ ሕይወታቸውም እንዲያድጉ መርዳት ይኖርብናል።

6. የቤተ ክርስቲያን አመራር ግብ እያንዳንዱን አማኝ በክርስቶስ ወዳለው መንፈሳዊ ብስለት ማምጣት ነው። ይህ ማለት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምእመኖቻቸውንና መንፈሳዊ ደረጃቸውን በማወቅ መንፈሳዊ እድገታቸውን ለማፋጠን የሚያስችሉትን መንገዶች መፈለግ አለባቸው ማለት ነው። ማንም ሰው ስማቸውን፣ ባሕርያቸውን፣ ቤተሰባቸው ያለበትን ሁኔታ፣ የመንፈሳዊ እድገት ደረጃቸውን፣ ወዘተ. . . ሳያውቅ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ሊንከባከብ አይችልም። አንድ እረኛ በሚያገለግላቸው ሰዎች ሕይወት ውስጥ የግል ተሳታፊ መሆን አለበት።

7. እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመንከባከብ የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችንና አገልጋዮችን ይጠቀማል። ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር ወደሚፈልገው ደረጃ እንድትደርስ ጠቃሚ ሚናዎችን የሚጫወቱ ሽማግሌዎች፣ ዲያቆናት፣ ወንጌላውያን፣ መጋቢያን፣ አስተማሪዎች፣ ወዘተ. . . አሉ። ከላይ የተጠቀሱት አገልግሎቶች እውን ሊሆኑ የሚችሉት እነዚህ አገልጋዮች መንፈሳዊ ስጦታዎቻቸውን ተጠቅመው በስምምነት ሲያገለግሉ ነው።

> 21ኛ ጥያቄ፡- ከላይ የተጠቀሱትን አገልግሎቶችና መሠረታዊ መርሖዎች እንደ መመሪያ በመጠቀም ለቤተ ክርስቲያናችሁ የእግዚአብሔርን ዕቅድ እውን ለማድረግ ምን ዓይነት መዋቅር ልታዘጋጅ ትችላለህ?

## የልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አገልግሎቶች

እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በሳሎች እንዲሆኑ የሚያግዙትን አገልግሎቶች ማዘጋጀት አለባት። ለምሳሌ፣ አንድ ወንጌላዊ ለአዳዲስ አማኞች የደቀ መዝሙርነት ትምህርት በመስጠት ለጥምቀት እንዲያዘጋጃቸው መጠየቅ ይቻላል። ከዚያ በኋላ መጋቢው ለምእመናን ቀጣይነት ያለው ትምህርት ሊሰጥ ይችላል። ከላይ የተገለጹትን አገልግሎቶች ለማሟላት የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች ምን ዓይነት ተግባራት ማከናወን እንዳለባቸው ከዚህ በታች አንዳንድ ሐሳቦች ቀርበዋል።



> 22ኛ ጥያቄ፡- 1ኛ ቆሮ. 3፡5-15ን አንብብ። ሀ) ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን ተከላ ውስጥ ድርሻዬ ምንድን ነው አለ? ለ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሐዋርያው ሚና ምን ነበር? ሐ) ቤተ ክርስቲያን እንድታድግ የሚያደርገው ማን ነው?

## የውጭ ወንጌላዊ፣ የቤተ ክርስቲያን ተካይ ወይም የወንጌል መልእክተኛ አገልግሎት፡-

እግዚአብሔር ለአንዳንድ ሰዎች ከሚሰጣቸው ስጦታዎች አንዱ ቤተ ክርስቲያን በሌለባቸው ስፍራዎች ቤተ ክርስቲያን የመትከል ስጦታ ነው። ይህንን ከጳውሎስ ሕይወት ውስጥ እንመለከታለን። ጳውሎስ እግዚአብሔር ወንጌል ወዳልደረሰባቸው ስፍራዎች ወንጌሉን እንዲያደርስ እንደ ጠራው ተገንዝቦ ነበር። ራሱን የተመለከተው እንደ አትክልተኛ፣ ማለትም ዘር በሌለባቸው ቦታዎች የወንጌሉን ዘሮች የመትከል ኃላፊነት እንደ ተሰጠው ሰው ነበር። ወይም ደግሞ እርሱ መሠረትን እንደሚጥል ሰው ነበር። ነገር ግን ጳውሎስ ችግኙን ውኃ ማጠጣት ወይም በመሠረቱ ላይ ጡቦችን መደርደር እንደ አጵሎስ ያሉት የሌሎች ሰዎች ኃላፊነት እንደ ሆነ ተረድቶ ነበር። አስተማሪ፣ ሰባኪ ወይም ሽማግሌ የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማር ቤተ ክርስቲያንን የሚያሳድጉ ውኃ አጠጪዎች ነበሩ። ጳውሎስ በዚህ ሁሉ ላይ የቤተ ክርስቲያን እድገት የሚወሰነው በእግዚአብሔር መሆኑን አመልክቷል። ይህ ቤተ ክርስቲያንን የምንተክለው ወይም እንድታድግ የምናደርገው እኛው ነን ብለን እንዳናስብ የሚጠቅመን ጥሩ ማስጠንቀቂያ ነው። እኛ በእግዚአብሔር እጆች ውስጥ ያለን መሣሪያዎች ነን። በአማኞች ሕይወት ውስጥ የቁጥርም ሆነ መንፈሳዊ እድገት እንዲመጣ የሚያደርገው እግዚአብሔር ነው።

በአንድ አዲስ ስፍራ እግዚአብሔርን የምታመልክ ጠንካራ ቤተ ክርስቲያን እንድትኖር ሥራውን የሚጀምር ሰው መኖር አለበት። ይህ «የውጭ ወንጌላዊ» ተብሎ የሚጠራው ሰው ሥራውን ይጀምራል። የአዲስ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረሰብን መሠረት ይጥላል። ሌሎች በኋላ እርሱ በሠራው መሠረት ላይ ተጨማሪ ተግባራትን ያከናውናሉ። ነገር ግን የሥራው ጀማሪ እርሱ ነው።

ለመሆኑ አንድ የውጭ ወንጌላዊ ሊያውቃቸውና ሊያከናውናቸው የሚገባቸው ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?

1. አንድ የውጭ ወንጌላዊ እግዚአብሔር ለአገልግሎት እንደ ጠራው ማወቁ በጣም አስፈላጊ ነው። ይህ ከቤተ ክርስቲያን ከባባድ አገልግሎቶች አንዱ ነው። ወንጌላዊው ከዘመዶቹና ጓደኞቹ ተለይቶ ወደ አዲስ አካባቢ ስለሚሄድ፣ ብቸኝነት ይሰማዋል። ሰዎቹ የሌላ ጎሳ አባላትና የተለየ ቋንቋ የሚናገሩ ሊሆኑ ስለሚችሉ፣ በአሳብ መግባባት ራሱ ሊያስቸግር ይችላል። ኢየሱስና በኋላም ጳውሎስ፣ ወንጌላውያንን ሁለት ሁለት እያደረጉ የላኩት ብቸኝነትንና ተስፋ መቁረጥን ለማስወገድ ነበር።

2. ወንጌላዊው ራሱን የሚገዛ ሰው መሆን አለበት። የሚቆጣጠረው ሰው ሳይኖር አገልግሎቱን ለማካሄድ የሚችል ሰው መሆን አለበት። መቼ መመስከር እንዳለበት ወይም መቼ ወደ ቤቱ መመለስ እንዳለበት የሚነግረው ሰው አይኖርም። በዚህ በኩል ራሱን ለመቆጣጠር ካልቻለ፣ ብዙ ጊዜ ያባክናል።

| |
|---|
| 23ኛ ጥያቄ:- ፊልጵ. 2:5-8 እና 1ኛ ቆሮ. 9:19-23ን አንብብ። ሀ) ኢየሱስ ሰዎችን ለማዳን ምን አደረገ? ለ) ጳውሎስ ወንጌሉን ከተሰያዩ ባህሎች ለመጡት ሰዎች በሚያካፍልበት ጊዜ ምን አደረገ? ሐ) ጳውሎስ ለሕዝቡ ሲል አኗኗሩን የቀየረው ለምን ነበር? መ) የውጭ ወንጌላውያን ይህ አመለካከት ለምን እንደሚያስፈልጋቸው አብራራ። |

ለውጫዊ ወንጌላዊነት መሠረቱ ወንጌሉን ለሌላ ጎሳ ለማዳረስ አኗኗራችንንና አነጋገራችንን መቀየርና ሰዎች ወንጌሉን እንዲረዱና እንዲቀበሉ ማገዝ ነው። ኢየሱስ በመንግሥተ ሰማይ ሰማያዊ ቋንቋ እየተናገረ አምላክ ሆኖ ይኖር ነበር። በቤተልሔም በተወለደ ጊዜ ግን፣ ባህሉን በመቀየር እን፤ አይሁዶች የዕብራይስጥ ቋንቋ መናገርን፣ እንደ አይሁዶች መልበስን፣ የአይሁድን ባህል መረዳትን፣ ወዘተ. . . ተማረ። የሚያገለግላቸውን ሰዎች ባህልና ቋንቋ ተማረ። አይሁዶች ልክ እንደ እርሱ ለመሆን እንዲቀየሩ አልጠበቀም። ጳውሎስ ከአይሁዶች ጋር በሚሆንበት ጊዜ እንደ አይሁዶች፣ ከአሕዛብ ጋር በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ እንደ አሕዛብ መኖሩን ተናግሯል። ይህንን ያደረገው ሰዎች ኢየሱስን በመከተ



ላችን ምክንያት ባህላችንን መተው ይኖርብን ይሆናል ብለው እንዳይሰጉ ለማሳየት ነው። ደኅንነት የአለባበስ፣ የአመጋገብ፣ ወዘተ. . .ጉዳይ ሳያሆን፣ ከሐሰተኛ አምላክ ወደ እውነተኛ አምላክ የመመለስ ጉዳይ ነው። ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል የማይጥሱ ባህሎቻቸውን እንዲተዉ መጠየቅ ወንጌሉን እንዳይቀበሉ በማድረግ አላስፈላጊ መሰናክሎችን ይፈጥራል።

እንደ ኢየሱስና ጳውሎስ፣ ውጫዊ ወንጌላዊ መሆን ከሰዎች ጋር በግልጽ ለመግባባት እንድንችል አዲስ ቋንቋ መማርን ይጨምራል። አንድ ወንጌላዊ ወደ አዲስ አካባቢ በሚደርስበት ጊዜ ማድረግ ያለበት የመጀመሪያው ጉዳይ ይህ ነው። የሕዝቡን ቋንቋ አለመማራችን ለእነርሱ ግድ እንደሌለን ያሳያል። እኛ እነርሱን ከመምሰል ይልቅ፣ እነርሱ እኛን እንዲመስሉ እየፈለግን ነው ማለት ነው። ወንጌላዊው የአካባቢውን ባህል በመገንዘብ ወንጌሉን በሚገባቸው መንገድ ለማብራራት የሚያስችሉትን ነገሮች መፈለግ ይኖርበታል፡ ይህ ማለት ከዚህ በፊት የማንመገባቸውንና በባህላችን ጸያፍ ናቸው የሚባሉትን ነገሮች መብላትን ሊጨምር ይችላል። ነገር ግን ወንጌሉን የምንመሰክርላቸው ሰዎች አገልጋዮች መሆናችንን ማስታወስ አለብን። የእነርሱን ምግብ ለመመገብ ፈቃደኛ መሆናችን ለእነርሱ አክብሮት እንዳለን የሚያሳይ ነው። ሰይጣን በወንጌላውያን አእምሮ ውስጥ ከሚያስቀምጣቸው ነገሮች መካከል አንዱ የእነርሱ ባህልና ነገሮችን የሚያከናውኑበት መንገድ ከሚያገለግሏቸው ሕዝብ የተሻለ መሆኑን ማሳየት ነው። እንዲህ ዓይነት ትዕቢት በልባችን ውስጥ እንዳያቆጠቁጥ ጥንቃቄ ማድረግ አለብን። የተጠራነው ሌሎችን በትሕትና እንድናገለግል ነው። ይህ ማለት ደግሞ እነርሱን፣ ቋንቋቸውንና ባህላቸውን ማክበር ማለት ነው። ባህላችን ከእነርሱ የተለየ ሊሆን ቢችልም፣ የግድ ከእነርሱ የተሻለ ላይሆን ይችላል።

4. የአንድ ወንጌላዊ ትልቁ ምስክርነት ፍቅርን የሚያሳይ ሕይወት ነው። አንዳንድ ጊዜ ለሰዎች ስብከትን ልናቀርብና ለእነርሱ እንደምናስብ የሚያሳይ ግንኙነት መመሥረት የማያስፈልገን ይመስለናል። በአንድ አካባቢ የሚኖር አንድ የሌላ

ሃይማኖት መሪ፣ «እናንተ ጴንጤዎች በኢየሱስ ካላመናችሁ ወደ ሲኦል ትወርዳላችሁ እያላችሁ ስታልፉ ሳይ ታስጠሉኛላችሁ:: ነገር ግን ለእኔ እንደሚያስብ ሰው መጥታችሁ ብትጎበኙኝ ደስ ይለኝ ነበር፣» ሲል ተናግሯል:: ወንጌሉን ለመቀበል የማይፈልጉ ሰዎች ወደ ክርስቶስ የሚመጡት እንደምናስብላቸው ሲያውቁ እንጂ፣ ስለ እግዚአብሔር እውነት ክርክር ስለ ገጠምናቸው አይደለም:: ስለሆነም፣ አንድ ወንጌላዊ እግዚአብሔር ለሰዎች ያለውን ፍቅር በሚገባ ማሳየት አለበት:: የገንዘብ ችግር ያለባቸውን ሰዎች መርዳቱ ጠቃሚ ነው:: የታመሙትን፣ ወዘተ. . . መጎብኘት ያሻል:: ሰዎች የወንጌላዊውን ሕይወት ካከበሩ፣ መልእክቱን ለመስማት ልባቸውን ይከፍቱለታል::

5. ውጤታማ የውጭ ወንጌላዊ ለመሆን ልዩ ሥልጠና ማግኘት ያስፈልጋል:: የአዲሱ አካባቢ ሰዎች ሌላ ቋንቋ ስለሚናገሩ፣ አዲስ ቋንቋ ለመማር የሚያስችል ክህሎት ማወቅ አለበት:: ከእርሱ የተለየ ባህል ስለሚኖራቸው፣ እንዴት ባህላቸውን እንደሚረዳ መማር አለበት:: ከራሱ ባህል አንጻር በግሱ የሚጠላቸውንና መጽሐፍ ቅዱስ «ስሕተት» ናቸው የሚላቸውን ነገሮች እንዴት እንደሚለይም ማወቅ አለበት:: የውጭ ወንጌላዊው ጥንቃቄ ካላደረገ፣ ሳያውቅ ሰዎች የእርሱን ባህል እንዲከተሉ ሊያስገድዳቸው ይችላል:: በአንዳንድ አካባቢዎች (ለምሳሌ፣ በዘላን ማኅበረሰቦች አካባቢ) አማኝ መሆን አማራ እንደ መሆን የሚታይበት ሁኔታ አለ:: እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ወንጌሉን መቀበል ከአማራነት (በደጋማዎቹ የኢትዮጵያ አካባቢዎች የሚኖሩ ሰዎች) ጋር የሚገናኝ ነገር አይደለም:: ስለሆነም፣ ሰዎች ከትምህርታችን የሚረዱት ይህንን ከሆነ፣ ወንጌሉን በትክክል አላስተማርናቸውም ማለት ነው:: ወንጌላዊው የማያውቀው ሃይማኖትም ሊገጥመው ይችላል:: በዚህ ጊዜ ሰዎች ኢየሱስን መከተል ለምን እንደሚያስፈልጋቸው ለሚታቸውን በማይጎዳ መንገድ የሚያብራራበትን ዘዴ መፈለግ አለበት::

6. ወንጌላዊው ቀላሉን አማራጭ በመከተል በሚኖርበት አካባቢ ካሉት ሰዎች ይልቅ የራሱ ባህል አባላት ለሆኑት ሰዎች



ለመመስከር መፈለግ የለበትም:: በሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢዎች ማለት ይቻላል ከተለያዩ ባህሎች የመጡ ሰዎች ይኖራሉ:: እነዚህ ከሌላ አካባቢ የመጡት ሰዎች ከወንጌላዊው ጋር አንድ ዓይነት ባህል ሊኖራቸው፣ ከአብዛኛው የአካባቢው ሕዝብ ተነጥለው የሚኖሩ ሊሆኑ ይችላሉ:: ብዙ ወንጌላውያን የሚፈጥሩት አንዱ ስሕተት በእነዚህ ሰዎች ላይ ትኩረት ማድረግ ነው:: የመንግሥት ሠራተኞች ወይም ነጋዴዎች ባሉበት አካባቢ ቤተ ክርስቲያን ይከፍታሉ:: የአምልኮው ቋንቋ ደግሞ በአካባቢው ሕዝብ የሚገለጽ አይሆንም:: ወንጌላውያን በአካባቢው ሕዝብ ላይ ትኩረት በማያደርጉበት ጊዜ፣ ወንጌሉ ወደ እነዚህ ሰዎች እንዳይደርስ እየጋረዱ ናቸው ማለት ነው:: በአንዳንድ አካባቢዎች የፕሮቴስታንት ክርስትና የደቡቦች ሃይማኖት ነው ይባላል:: ይህም ሊሆን የቻለው ወንጌላውያን ከደቡብ አካባቢ ከመጡት ሰዎች ጋር ኅብረት ስለሚያደርጉ ነው:: ያለኸው አዲስ አበባ ነው እንበል:: ሚሲዮናውያን ወንጌል ለመመስከር ከውጭ አገር መጥተዋል:: ነገር ግን ሚሲዮናውያን የሚናገሩት ከሌሎች የውጭ አገር ሰዎች ጋር ብቻ ቢሆንና፣ አምልኮው የሚካሄደው በእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቻ ቢሆን፣ ለማመን ከፈለግክ፣ የግድ እንግሊዝኛ መማር ሊኖርብህ ነው:: የምታመልከውም የአንተን ባህል ያላገናዘበ አምልኮ ነው የሚሆነው:: ይህ በክርስቶስ ማመንን ቀላል ያደርግልሃል? አያደርግልህም:: በዚህ ጊዜ፣ «ይህ ለፈረንጆች ነው:: ለእኛ አይደለም፣» ትላለህ:: ትኩረታችንን በእናሳዎቹ ባህል ላይ በማድረግ የአካባቢው ሕዝብ እኛን እንዲመስል በምንጠይቅበት ጊዜ የሚሆነው እንዲህ ዓይነት ነገር ነው::

> 24ኛ ጥያቄ:- የሐዋ. 20:20-21፣ 30-31 እና ቈላ. 1:28-29ን አንብብ:: ሀ) ሰዎች መዳን ብቻ ሳይሆን፣ ወደ መንፈሳዊ ብስለት እንዲደርሱ ለማገዝ ጳውሎስ ምን አድርጌአለሁ አለ? ለ) ይህ ለምን አስፈላጊ እንደ ሆነ አብራራ::

ሰዎች ወደ እምነት ከመምጣታቸው በፊት የውጭ ወንጌላዊው ላልዳኑት ሰዎች በስፋት ይመሰክራል:: ነገር ግን ሰዎች በኢየሱስ ማመን በሚጀምሩበት ጊዜ፣ የወንጌላዊው ሥራ ይቀየራል:: በማኅበረሰቡ ውስጥ ላሉት ሰዎች ሁሉ ይመስክራል:: ከዚህ በተጨማሪ

ያመኑትን ሰዎች ደቀ መዝሙር ማድረግ አለበት:: ኢየሱስ ያዘዘን እንድንመሰክር ብቻ ሳይሆን፣ እርሱን ለመከተል የሚያስፈልጋቸውን ትምህርት ሁሉ እንድናስተምራቸው ነው:: (ማቴ. 28:19-20ን አንብብ::) ጳውሎስ ሰዎች በሳል እንዲሆኑ እንዳስተማረ ይናገራል:: ለኤፌሶን ሽማግሌዎች ሲናገር፣ ቀንና ሌሊት በእንባ ሲያስተምራቸው መቆየቱን ገልጾአል:: እያንዳንዱ የውጭ ወንጌላዊ አማኞች በሳል የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች እንዲሆኑ ለማስተማር ዕቅድ ማውጣት አለበት:: በጥንቃቄ ማስተማር ይኖርበታል:: እስኪጠመቁ ብቻ ሳይሆን፣ ኢየሱስን ለመከተል ማወቅ ያለባቸውን ነገሮች ሁሉ ማስተማር ይኖርበታል:: አንዳንድ ወንጌላውያን ብዙ ጊዜያቸውን ለምስክርነት ይለጡና አማኞችን ለማስተማር ጥቂት ጊዜ ብቻ ይጠቀማሉ:: ይህ ደግሞ አዳዲስ አማኞች ወደ መንፈሳዊ ብስለት እንዳያድጉ ያደርጋል:: አዳዲስ አማኞች ኢየሱስን እንደ ጌታቸው ለመከተል በቂ ትምህርት የማግኘት ጉጉት አላቸው:: በዚህ ጊዜ ትምህርት ካልሰጠናቸው፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ የአኗኗር መንገዶችን ሊያጎለብቱ ይችላሉ:: ከዚህ በኋላ ልማዳቸውን እንዲቀይሩ ማድረግ በጣም ከባድ ነው::

8. ባልና ሚስት ሰዎችን ለክርስቶስ ለመማረክ ራሳቸውን እንደ አንድ ቡድን መመልከት አለባቸው:: ይህ ማለት ሁለቱም እግዚአብሔር ለወንጌል አገልግሎት እንደ ጠራቸው ማመን አለባቸው ማለት ነው:: ሚስት እግዚአብሔር ለዚህ አገልግሎት ጠርቶኛል የሚል እምነት ከሌላት፣ ቤተሰቦቿንና ጓደኞቿን ትታ ወደ ሌላ ቦታ ለመሄድ ደስተኛ ልትሆን አትችልም:: ይህ ደግሞ የባሏን ውጤታማነት ይቀንሳል:: ቤተሰቡን ለመንከባከብ ብቻ ሳይሆን፣ ለአገልግሎትም የተጠራች መሆኗን ካላመነች፣ በቂ አገልግሎት መስጠቱ አስቸጋሪ ይሆናል:: በማኅበረሰቡ ውስጥ ላሉት ሴቶች ለመመስከር እርሷ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ልታደርግ ትችላለች:: ወደ ገበያ ስትሄድ፣ ውኃ ልትቀዳ ወይም ልብስ ልታጥብ ወደ ወንዝ ስትወርድ፣ እንዲሁም ወደ ለቅሶ ቤት ስትሄድ ለሴቶች ስለ ክርስቶስ የመመስከር ዕድል ሊኖራት ይችላል:: ባሏ ግን ይህንን ዕድል ሊያገኝ አይችልም::



**25ኛ ጥያቄ:-** የሐዋ. 2:14፤ 15:13፤ 21:18፤ 11:30፤ 15:6፤ 22ን አንብብ:: ሀ) መጀመሪያ የኢየሩሳሌምን ቤተ ክርስቲያን መምራት የማን ኃላፊነት ነበር? ለ) ከጥቂት ጊዜ በኋላ ማን ነበር የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪ የሆነው? ሐ) ሐዋርያት የቤተ ክርስቲያን አመራርን ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች የሰጡት ለምን ይመስልሃል?

**26ኛ ጥያቄ:-** የሐዋ. 14:23፤ ቲቶ 1:5ን አንብብ:: ሀ) አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተች በኋላ ጳውሎስ ምን እንዳደረገ ግለጽ:: ለ) ቤተ ክርስቲያኒቱ እስክትመሠረት ድረስ ሥልጣን የያዘው ማን ይመስልሃል?

9. እግዚአብሔር በረከቱን ሲያፈስና ሰዎች ማመን ሲጀምሩ፣ የውጭ ወንጌላዊ ለምችን ለቤተ ክርስቲያን መሪነት ማዘጋጀት አለበት:: በኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያንም ሆነ በጳውሎስ አገልግሎት ውስጥ የምንመለከተው አንድ ዓይነት የቤተ ክርስቲያን አመሠራረት ነው:: የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኒቱ በሳል ሽማግሌዎችን እስክታፈራ ድረስ፣ ሐዋርያትና ጳውሎስ መንፈሳዊ ሥልጣኑን ይዘው ይቆያሉ:: የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን በተጀመረች ጊዜ ሐዋርያት የማስተማርና የመስበክ፣ አለመስማማቶችን የመቅረፍ፣ እንዲሁም ለአማኞች መንፈሳዊ ምሪት የመስጠት ኃላፊነት እንደ ነበረባቸው እናነባለን:: ነገር ግን ቤተ ክርስቲያኒቱ እያደገች ስትመጣ፣ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አመራሩ ከሐዋርያት ወደ ሽማግሌዎች ተላለፈ:: ከእነዚህ ሽማግሌዎች መካከል አንዱ የጌታችን ወንድም የነበረው ያዕቆብ ነበር::

ይህ የተደረገው ለምን ነበር? ሐዋርያት የተባሩት ልክ እንደ ውጫዊ ወንጌላዊ አብያተ ክርስቲያናትን እንዲመሠርቱና ሰዎች የእግዚአብሔርን እውነት ይረዱ ዘንድ እንዲያስተምሩ ነበር:: አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ከመምራት ይልቅ፣ በቤተ ክርስቲያን ላይ ተጽዕኖ ያስከተሉትን አጠቃላይ ነገሮች በማረም ላይ ነበረ ትኩረት ያደረጉት:: በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን በሚመሠርትበት ጊዜ በመጀመሪያው አካባቢ (ከበርናባስ ጋር) መንፈሳዊ አመራር ይሰጣል:: ቤተ ክርስቲያኒቱ እየጠነከረች በምትሄድበት ጊዜ ግን፣ ሽማግሌዎች ለአጥቢያው አማኞች መንፈሳዊ መሪነት እንዲሰጡ ነበር የሚያደርገው:: ከዚያ በኋላ ወደ ሌሎች አካባቢዎች በመሄድ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናትን

ይመሠርታሉ። ጳውሎስና በርናባስ ለቃሉ ታማኞች ለመሆን ባላቸው ፍላጎት ከመሠረቷቸው አብያተ ክርስቲያናት ጋር ያላቸውን ግንኙነት በዘላቂነት ጠብቀዋል።

ከዚህ ውስጥ ሁሉም ወንጌላውያንና በቤተ ክርስቲያን ተከላ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ሊገነዘቡ የሚገባቸውን ሦስት እውነቶች መመልከት ይቻላል።

ሀ. ምንም እንኳን በቤተ ክርስቲያን ተከላ ውስጥ ትልቁ ነገር አጥቢያዊ የሽማሌዎችን አመራር ማደራጀት ቢሆንም፣ ይህ ሂደት በችኮላ መከናወን የለበትም። ብስለት የሌላቸውንና የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመምራት ያልተዘጋጁትን ሽማግሌዎች ከመሾም ይልቅ ቤተ ክርስቲያኒቱ ለተወሰነ ጊዜ በሳል በሆነ ቤተ ክርስቲያን ተካይ አመራር ሥር እንድትቆይ ማድረጉ መልካም ነው። መንፈሳዊ ብስለት ከሌላቸው የአጥቢያ መሪዎች በላይ ቤተ ክርስቲያንን የሚጎዳ ነገር የለም። ሐዋርያትም ሆኑ ጳውሎስ ለአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ወዲያውኑ ሽማግሌዎችን አይሾሙም ነበር። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መንፈሳዊ ብስለት ያላቸው ሰዎች እስኪገኙ ድረስ ይጠብቁ ነበር። ከዚያ በኋላ ነበር ሽማግሌዎችን የሚመርጡት። ጳውሎስ ለቲቶ ደብዳቤ የጻፈበት ትልቁ ምክንያት መንፈሳዊ ብስለት ያላቸውን ሰዎች መርጦ አመራሩን እንዲያስረክብ ነበር (ቲቶ 1:5)። ነገር ግን ሽማግሌዎቹን በጥንቃቄ እንዲመርጥ አሳስቦታል። ተገቢውን መንፈሳዊ መመዘኛ ማሟላት ያስፈልጋቸው ነበር። ይህ ካልሆነ፣ መንፈሳዊ መሪዎች ሊሆኑ አይችሉም ነበር።

ሽማግሌዎች የቤተ ክርስቲያናቸውን መንፈሳዊ ደረጃ ለመወሰን ወሳኝ ሚና ስለሚጫወቱ፣ መምራት ያለባቸው እነዚህን መንፈሳዊ መመዘኛዎች የሚያሟሉ ሰዎች መሆን አለባቸው። ቤተ ክርስቲያን ተቅበዝባዥ ከሆነች፣ ይህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መንፈሳዊ አለመሆን ችግር ነው። እግዚአብሔር ለአመራር የሰጠንን መመዘኛ ብናሟላ፣ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ የምንመለከታቸው አብዛኞቹ ችግሮች ይወገዳሉ። ሰዎች መንፈሳዊ ብስለት ስለሌላቸው፣ ጳውሎስ የሽማግሌዎችን መመዘኛዎቹን ለማላላት የፈቀደበት ሁኔታ መኖሩን የሚያሳይ መረጃ የለንም። እንዲሁም ደግሞ ሰባት ወይም ዘጠኝ ሽማግሌዎችን ለመምረጥ የተገደደበት ሁኔታ መኖሩን አንመለከትም። መንፈሳዊ ብቃት ከቁጥር በላይ አስፈላጊ ነው። መንፈሳዊ ብስለት የሌላቸውን ሰዎች ጨምሮ ሰባት ሽማግሌዎችን ከመምረጥ ይልቅ፣ ብስለት ያላቸውን ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች መምረጡ የተሻለ ነው።

ለ. የቤተ ክርስቲያን ተካይ/ወንጌላዊ ቀዳሚ ትኩረት ከሚሰጣቸው ነገሮች አንዱ እግዚአብሔርን የሚወዱትን ሰዎች በማፈላለግ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተዘረዘሩትን መንፈሳዊ የመሪነት መመዘኛዎች እንዲያሟሉ ማገዝ ነው። ወንጌላዊው እነዚህ አዳዲስ መሪዎች እንዴት እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ እንደሚመሩ ማሠልጠን አለበት። ልክ ጳውሎስ የኤፌሶንን ሽማግሌዎች እንዳስተማረ ሁሉ፣ ወንጌላዊውም ይህንኑ ተግባር ማከናወን ይጠበቅበታል። (የሐዋ. 20:25-32ን አንብብ።)

ሐ. እነዚህ አማኞች እግዚአብሔርን የመስማትና የመከተል፣ እንዲሁም መንፈሳዊ ምሪት መስጠት በሚጀምሩበት ጊዜ፣ ወንጌላዊው የቤተ ክርስቲያን አመራሩን ለእነዚሁ ሽማግሌዎች ማስረከብ አለበት። መንፈስ ቅዱስ በመንፈሳዊ መንገድ እንዲመሩ እንደሚያስችላቸው መተማመን አለበት። ከዚያም ወደ ሌላ ቦታ መሄድ አለበት። እርሱ እዛ እስካለ ድረስ ሽማግሌዎቹ ቤተ ክርስቲያንን ለመምራት በመንፈስ ቅዱስ ላይ ከመደገፍ ይልቅ በእርሱ ላይ ሊደገፉ ይችላሉ።

ብዙውን ጊዜ ወንጌላውያን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለረዥም ጊዜ በመሪነት ሲሠሩ ይቆያሉ። ብዙዎቹ አዳዲሶቹን አማኞች መንፈስ ቅዱስ ይመራቸዋል የሚል እምነት የላቸውም። ጳውሎስ ሽማግሌዎች ለመሆን የተስማሙትንና ከጥቂት ወራት በኋላ መንፈሳዊ ብስለት ያገኙትን ሽማግሌዎች እንደሚመራ እምነት ነበረው። እነዚህ ሰዎች ጠንካራ እምነት እንዳላቸውና መሪነት የሚጠይቃቸውን ነገሮች መረዳታቸውን ለማረጋገጥ ብዙ ሰዓታት አብሯቸው እንዳሳለፈ ጥርጥር የለውም። አንዳንድ ወንጌላውያን መንፈሳዊ የሆነ አጥቢያዊ አመራር አይመሠርቱም። በዚህም

ምክንያት ወንጌላውያኑ ወደ ሌላ ቦታ በሚሄዱበት ጊዜ የመሪነቱን ሥራ ለማካሄድ የሚያስችል ሥልጠናም ሆነ ዝግጁነት ያለው ሰው ማግኘት አስቸጋሪ ይሆናል:: በአንዳንድ አካባቢዎች ወንጌላውያን ለዓመታት ሲሠሩ ይቆዩና ወደ ሌላ ቦታ በሚሄዱበት ጊዜ የመሪ እጥረት ያጋጥማል:: ሰዎች እሑድ ቀን ይሰባሰቡና መጽሐፍ ቅዱስ አንብበውና ጥቂት መዝሙሮች ዘምረው ይበታተናሉ:: አንድ ወንጌላዊ ሥራውን ለመንፈሳዊ መሪዎች ካልሰጠ፣ ድካሙ ሁሉ መና ሊቀር ይችላል::

27ኛ ጥያቄ:- ሀ) እግዚአብሔርን የሚወዱና እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ የሚመሩ ወንጌላውያን የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ ደረጃ ሲለውጡ የተመለከትከው እንዴት ነው? ለ) በተሳሳቱ መመዘኛዎች (በሀብት፣ በትምህርት፣ ወዘተ. . .) የተመረጡ ሽማግሌዎች በቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ደረጃ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩት እንዴት ነው? ሐ) ይህ መሪዎችን በጥንቃቄ መምረጥ አስፈላጊ መሆኑን የሚያሳየው እንዴት ነው? መ) ይሀ መሪዎች ለአመራር በብቃት መሠልጠን እንዳለባቸው የሚያሳየው እንዴት ነው?

10. ቤተ ክርስቲያንን በመጋቢነት ለማገልገል አንድ ወይም ሁለት ሰዎች መዘጋጀት አለባቸው:: ወንጌላዊው ሽማግሌዎችን በማስተማር አገልግሎቱን ለእነርሱ ማስረከብ ብቻ ሳይሆን፣ ከእነርሱ ጋር በመሆን ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቀጣይነት ያለው አገልጋይ የሚሰጥ የእግዚአብሔር ሰው መፈለግ አለበት:: በጎች በየቀኑ ካልተመገቡ፣ ተዳክመው ይሞታሉ:: በተመሳሳይ ሁኔታ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ከቃሉ በሚገባ ካልተመገቡ፣ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ይዝሉና ለዓለማዊነትና ለሐሰተኛ ትምህርት እልፈው ይሰጣሉ:: እያንዳንዷ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለምእመናን ተከታታይነት ያለው ትምህርት መስጠት የሚችል ቢያንስ አንድ ሰው ያስፈልጋታል:: በአብዛኛው ይህ ማለት አንድ ሰው ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት በመግባት የእግዚአብሔርን ሕዝብ መምራት ማለት ምን እንደ ሆነ መማር አለበት ማለት ሊሆን ይችላል::

ሀ. ይህ ግለሰብ በጥንቃቄ መመረጥ አለበት:: ቤተ ክርስቲያንን ሙሉ ጊዜ ለማገልገል እንደ ተጠራ ማሳየት አለበት:: ጊዜውን



ለጥቶ ሕዝቡን በእረኝነት ለማገልገልና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ መርዳት ይኖርበታል:: ለመንፈሳዊ አመራር የሚያስፈልጉትን መንፈሳዊ ባሕርያት ማጎልበት ይጠበቅበታል:: የመጽሐፍ ቅዱስ ተምህርት ቤት ሥልጠና መንፈሳዊ ባሕርይ ወይም መንፈሳዊ ስጦታና ጥሪ አያጎናጽፈውም:: ይህ እንዴት ይበልጥ ውጤታማ አገልግሎት እንደሚሰጥ የሚያግዘው ነው::

ለ. ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር በመሥራት ሥልጠና የሚሰጠው ሰው ተስማሚ ትምህርት ቤት መምረጥ አለበት:: ለመጋቢነት አገልግሎት የሚዘጋጅ ከሆነ፣ ሰዎች በብቃት የመጋቢነትን አገልግሎት እንዲሰጡ ወደሚያሠለጥን ትምህርት ቤት መግባት አለበት:: በወንጌላዊነት አገልግሎት የሚሰማራ ከሆነም፣ ሰዎች ጥሩ ወንጌላውያን እንዲሆኑ ወደሚያዘጋጅ ትምህርት ቤት መሄድ አለበት:: የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሰዎች የተለያዩ ክህሎቶች እንዲኖራቸው የግድ ይላል:: ይህም የተለያዩ ዓይነት ሐኪሞች እንዳሉ ማለት ነው:: አንዳንዶች በልጆች ሕክምና፣ ሌሎች ደግሞ በዓይን ሕክምና፣ ወዘተ. . . ልዩ ሥልጠና ያገኛሉ::

ሐ. ቤተ ክርስቲያን አገልጋዩን ለሙሉ ጊዜ አገልግሎት ለመቀበል መዘጋጀት አለባት:: ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን በማስተማር ለሚያገለግሉ ሰዎች ደመወዝ መክፈል እንዳለባት አስጠንቅቋል (1ኛ ቆሮ. 9:7-11፤ 1ኛ ጢሞ. 5:17-18):: ቀደም ሲል በኢትዮጵያ የገጠር አብያተ ክርስቲያናት በሽማግሌዎች አገልግሎት በብቃት ተግባራቸውን ሲወጡ ቆይተው ሊሆን ይችላል:: አሁን ባሉት ለፋፊ አብያተ ክርስቲያናት ግን ሽማግሌዎች ብቻቸውን ለወጣቶችና ለልጆች በቂ ትምህርትና የእረኝነት አገልግሎት በመስጠት ወደ ብስለት ሊያደርሷቸው አይችሉም:: እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊና ስጦታ ያላቸውን ሰዎች በመምረጥ ሥልጠና ልትሰጣቸውና ቤተ ክርስቲያንን እንዲያገለግሉ ደመወዝ ልትከፍላቸው ይገባል:: ደመወዙ ደግሞ የአገልጋዩን ወጪዎች ለመሸፈን የሚችልና ስለ ገንዘብ ሳይጨነቅ ትኩረቱን በአገልግሎት ላይ እንዲያደርግ የሚያስችለው መሆን አለበት::

መ. ሽማግሌዎችና መጋቢው በቡድን በመሥራት ቤተ ክርስቲያንን መምራት አለባቸው። ቤተ ክርስቲያን መጋቢውን እንደ ቅጥር ሠራተኛ የምትመለከት ከሆነ፣ ተገቢውን መንፈሳዊ ምሪት ለማግኘት አትችልም። ቤተ ክርስቲያን ጤናማ ልትሆን የምትችለው ሽማግሌዎችና መጋቢው በቅርብ በመሥራት እግዚአብሔር የሚፈልገውን አመራርና እረኝነት የሚሰጡ ከሆነ ብቻ ነው።

11. የውጭ ወንጌላዊው ሌላ ቤተ ክርስቲያን ለመመሥረት ወደ ሌላ አካባቢ በሚሄድበት ጊዜ የሚረከቡትን ሽማግሌዎች ማዘጋጀት አለበት። ወንጌላዊው እረኞችን ካሠለጠነና ከእነርሱ ጋር በመሆን መጋቢን ካዘጋጀ በኋላ፣ ወደ ሌላ ቦታ መሄድ አለበት። ለወንጌላዊ የእግዚአብሔር ፈቃድ አብያተ ክርስቲያናትን እንዲተክል እንጂ በመጋቢነት እንዲያገለግል አይደለም። ሁልጊዜም የቤተ ክርስቲያኒቱ «አባት» ሆኖ መሥራቱን ይቀጥላል። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያኒቱን ለእግዚአብሔር በአደራ ሰጥቶ ወደፊት መቀጠል አለበት።

12. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በውጭ ወንጌላውያን ላይ የሥልጣን መዋቅር በሚያዘጋጁበት ጊዜ መጠንቀቅ አለባቸው። እንደ ሁሉም ሰው፣ የውጭ ወንጌላውያንም ለአገልግሎታቸው በኃላፊነት መጠየቅ አለባቸው። ሌሎች ሰዎች የሚሰጧቸውን ምሪቶችና ጥበብ መጠቀም ይኖርባቸዋል። የእግዚአብሔርን ጥሪ ሊያከናወኑ የሚችሉት በተጠያቂነት እንዲሠሩ ሲደረግ ነው። ነገር ግን የውጭ ወንጌላውያን ተጠሪዎች የአገልግሎቱን ባሕርይ የሚያውቁ መሆን አለባቸው። በወንጌላዊነት አገልግለው የማያውቁ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ለዚህ ተጠሪነት ብቁ አይሆኑም። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወንጌላውያኑን በቀጥታ የሚቆጣጠሯቸው ከሆነ፣ ሁለት ችግሮች ሊፈጠሩ ይችላሉ።

ሀ. ብዙውን ጊዜ እነዚህ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች የወንጌላውያንን ጥሪ አይረዱም። ስለዚህ፣ እንደ ወንጌላውያን ሳይሆን፣ እንደ መጋቢዎች እንዲሠሩ ኃላፊነቶችን ይሰጧቸዋል።



ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ወንጌላውያን ለማኅበረሰቡ የሚመለክሩ ሳይሆኑ፣ በመጋቢነት የሚሠሩ አገልጋዮች እንዲሆኑ ይፈልጋሉ። ይህ ወንጌሉ ወደ አዳዲስ አካባቢዎች እንዳይዳረስ ከማድረጉ በተ ጨማሪ፣ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን እድገት ይገድባል። ይህም የሚሆነው መሪዎች ሥራውን ለመረከብ ራሳቸውን ስለማያዘጋጁ ነው። አንድ ሰው ቤተ ክርስቲያኒቱን በመጋቢነት እንዲያገለግል ለማድረግ ዝግጅት አያደርጉም። ሁልጊዜም፣ «ምንም የሠለጠነ ሰው የለንም። የሠለጠነ ሰው ለመቅጠር ደግሞ ገንዘብ የለንም፣» ይላሉ። እነዚህ ማመኻኛዎች ለወንጌሉ መስፋፋት ትልቅ እንቅፋቶች ናቸው።

ለ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የጠፉትን ከማዳን ይልቅ፣ በቤተ ክርስቲያኒቱ ጉዳዮች ላይ ያተኩራሉ። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች በውጭ ወንጌላውያን ላይ ሥልጣን ሲሰጣቸው፣ ወንጌላዊው ጥሪውን እውን ከማድረግ ይልቅ፣ በቤተ ክርስቲያን ሥራዎች ላይ እንዲያተኩር ይጫኑታል። በአንዳንድ አካባቢዎች የውጭ ወንጌላውያን እንግዶችን እንዲቀበሉ፣ እምልኮውን እንዲያዘጋጁ፣ ለሚናሮችን እንዲያዘጋጁ፣ ወዘተ. . . ይጠየቃሉ። ይህ ደግሞ ደኅንነትን ካላገኙት ሰዎች ጋር የሚያሳልፉት ጊዜ እንዳይኖርና ስለ ክርስቶስ ለመመስከር እንዳይችሉ ያደርጋቸዋል።

> 28ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ቤተ ክርስቲያናችሁ ምእመናን የውጭ ወንጌላውያን እንዲሆኑ ለማዘጋጀት ምን እያደረገች ነው? ለ) የውጭ ወንጌላውያን ከላይ የተዘረዘሩትን ነጥቦች ማወቃቸውና መተግበራቸው ምን ጥቅም ይኖረዋል ብለህ ታስባለህ?

## ሦስተኛ ቀን

# የሽማግሌዎች አገልግሎት፡-

ምንም እንኳን አንድ ዓይነት የቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ መዋቅር መከተሉ አስፈላጊ ላይሆን ቢችልም፣ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን አስፈላጊ አገልግሎቶች ሁሉ ተግባራዊ የሚያደርግ ሰው መኖሩ የግድ ነው። ሽማግሌዎች እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲከናወን የሚፈልጋቸው ነገሮች ሁሉ

ለማከናወን ከቻሉ፣ ወንጌላውያንን፣ መጋቢያንን ወይም ዲያቆናትን መጠቀም አያስፈልጋቸውም:: ነገር ግን ቤተ ክርስቲያኒቱ በጣም ትንሽ ካልሆነች በስተቀር፣ ሽማግሌዎች ሁሉንም አገልግሎት ለመፈጸም እንደማይችሉ ግልጽ ነው:: ስለሆነም፣ ሽማግሌዎች የትኞቹን አገልግሎቶች ሊያከናውኑ እንደሚችሉና የትኞቹን አገልግሎቶች ሌሎች ሰዎችን በማሠልጠን እንደሚያካሂዱ መወሰን አለባቸው:: እግዚአብሔር ሽማግሌዎች ለምእመናኑ ተገቢውን የእ ረኝነት አገልግሎት እንዲሰጡ በኃላፊነት ይጠይቃቸዋል::

1. በአዲስ ኪዳን ውስጥ ቤተ ክርስቲያን በሽማግሌዎች ነበር የምትመራው:: የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ነበሯት (የሐዋ. 11:30፤ 15):: ጳውሎስ የጀመራቸው አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሽማግሌዎች ነበሯቸው (የሐዋ. 14:23፤ 20:17፤ ፊልጵ. 1:1፤ ቲቶ 1:5):: እነዚህ ሰዎች እንደ መጋቢ ባለ አንድ ሰው ቁጥጥር የሚንቀሳቀሱ አልነበሩም:: አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በአንድ ሽማግሌ ስትመራም አንመለከትም:: ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አመራር ኃላፊነቱ የሚያርፈው አያሌ ሽማግሌዎች ለሚገኙበት ቡድን ነበር::

29ኛ ጥያቄ፡- 1ኛ ጢሞ. 3:17፤ ቲቶ 1:5-9፤ 1ኛ ጴጥ. 5:1-3፤ የሐዋ. 20:28ን አንብብ:: ሀ) ሰዎች ለሽምግልና ከመመረጣቸው በፊት ምን ዓይነት መመዘኛዎችን ማሟላት አለባቸው? ለ) መመዘኛዎችህን በሦስት ቡድኖች ክፈላቸው - 1) የግል ባሕርይ፣ 2) ከሌሎች ጋር ያለ ግንኙነት፣ እና 3) ችሎታ:: ሐ) ዛሬ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ሽማግሌዎችን በሚመርጡበት ጊዜ አምብዛም ትኩረት የማያደርጉት በየትኞቹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባሕርያት ላይ ነው? መ) ሰዎችን ለሽምግልና በሚመርጡበት ጊዜ ሰዎች የሚጠቀሙባቸው ተጨማሪ መመዘኛዎች ምን ምንድን ናቸው?

እያንዳንዱ ሽማግሌ በመመዘኛው መሠረት በጥንቃቄ ይመረጥ ነበር:: ብዙውን ጊዜ ሰዎች ሽማግሌዎችን በሚመርጡበት ጊዜ ፈቃደኛ የሆኑትን ሰዎች ይመርጣሉ:: አስፈላጊውን መመዘኛ ባያሟሉም እንኳን፣ ፈቃደኛ የሆኑትን ሰዎች መርጠው ይሾማሉ:: ብዙውን ጊዜ እነዚህ አዲስ የሚመረጡ ሰዎች የሚችሉትን ያህል ጥረት ማድረጋቸው አይቀርም:: ነገር ግን በአዲስ ኪዳን ውስጥ



የተዘረዘሩትን የመሪነት መመዘኛዎች ስለማያሟሉ፣ የመሪነቱን ተ ግባር የሚወጡት በዓለም ውስጥ በለመዱበት መንገድ ነው:: በመሆኑም፣ አመራሩ አይሳካላቸውም፣ ቤተ ክርስቲያንም ለችግር ትጋለጣለች:: ሌላ ጊዜ ሰዎች በተሳሳቱ ምክንያቶች ይመረጣሉ:: የተወሰነ ጎሳ አባል በመሆናቸው፣ ለቤተ ክርስቲያን መሥሪያ ቦታ የሰጡ በመሆናቸው፣ በመንግሥት ቢሮ ውስጥ ያላቸው ሥልጣን ቤተ ክርስቲያኒቱን ይጠቅማል ተብሎ በመታሰቡ፣ ወይም ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን ብዙ ገንዘብ ሊሰጡ የሚችሉ ታዋቂ ነጋዴዎች በመሆናቸው ለአገልግሎት ይታጫሉ:: የሚያሳዝነው፣ ሰዎች እነዚህን በመሳሰሉት የተሳሳቱ ምክንያቶች ለመሪነት በሚመ ረጡበት ጊዜ፣ በመንፈሳዊ መንገድ ለመምራት የሚያስችል ስጦታ ከሌላቸው፣ እንደ ዓለም ሥርዓት መምራታቸው የማይቀር ነው:: ይህ ደግሞ ቁሳዊ ጥቅም ወይም ክብር ለማግኘት ሲባል በሰዎች ላይ ከፍተኛ ቁጥጥር ማድረግን ያካትታል::

አዲስ ኪዳን ምን ዓይነት ሰዎች ለሽምግልና መመረጥ እንዳለባቸው በግልጽ አስፍሯል:: ዛሬ ለሽምግልና የምንፈልጋቸው እንደ ትምህርት፣ በመንግሥት የተከበረ መሆን፣ ከትክክለኛው ጎሳ መወለድ፣ ወዘተ. . . በዝርዝሩ ወስጥ አልተካተቱም:: ይህ እኛ ስለ አመራር ያለን ግንዛቤ ከአዲስ ኪዳን የመሪነት ግንዛቤ የተለየ መሆኑን ያሳያል:: መጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት የሚሰጠው በባሕርይ ብቃቶች ላይ ነው:: ትልቁ የክህሎት ብቃት ለማስተማር መቻል ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ያስፈራቸው የብቃት መለኪያዎች ቢቻል የምንፈጽማቸው ነገሮች አይደሉም:: የማያምኑ ሰዎች መጥፎ ስም ባተረፉባት በቀርጤስ እንኳን ጳውሎስ ሽማግሌዎች በሚመረጡበት ጊዜ መደበኛ የብቃት መመዘኛዎች መጠበቅ እንዳለባቸው ገልጾአል:: እንዲሁም ደግሞ ጳውሎስ ሰዎቹ ሁሉንም ባይሆን የተ ወሰኑትን መመዘኛዎች ካሟሉ ሊመረጡ ይችላሉ አላለም:: ይህ ተ ማሪዎች 50 በመቶ አምጥተው የሚያልፉበትን የትምህርት ቤት ሥርዓት የሚከተል ነገር አይደለም:: ጳውሎስ መመዘኛው መቶ በመቶ መሟላት አለበት ይላል:: ጳውሎስ ብቃት ያላቸው ሰዎች ብቻ በሽምግልና እንዲመሩ ነው የገለጸው:: መጽሐፍ ቅዱስ ያስፈራቸውን መመዘኛዎች ካላሟሉ ግን፣ በሽምግልና ሊመሩ

አይችሉም። እርሱ የተናገረው እንደ ሐዋርያ በመሆኑ፣ ጢሞቴዎስ፣ ቲቶ እና ዛሬም እኛ ይህንን የመታዘዝ ኃላፊነት አለብን።

3. በአዲስ ኪዳን ሽማግሌዎች የሚከተሉትን አገልግሎቶች አከናውነዋል፡-

«ሽማግሌ» የሚል ቃል በምትሰማበት ጊዜ ወደ አእምሮህ የሚመጣው ነገር ምንድን ነው? የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ምን ዓይነት ሥራዎችን መሥራት አለበት? ብዙውን ጊዜ ይህ ቃል ሲጠራ ወደ አእምሯችን የሚመጣው አንድ ሽምገል ያለ ወይም ከፍተኛ ትምህርት ያለውና በጣም ሥራ የሚበዛበት ሆኖ ሳለ፣ በሽማግሌዎች ቦርድ ላይ ለመቀመጥ ፈቃደኛ የሆነ ሰው ነው። በወር አንድ ጊዜ ከሌሎች ሰዎች ጋር በመገናኘት የቤተ ክርስቲያንን የአስተዳደር ጉዳዮች በመገምገም ስለ ገንዘብ፣ የሕንጻ ግንባታና አገልግሎት ጠቃሚ ውሳኔዎችን የሚሰጥ ነው። ሽማግሌ አስተዳዳሪ ነው።

ይሁን እንጂ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሽምግልና ምን እንደ ሆነ ለመረዳት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህንኑ ቃል ለመግለጽ የተጠቀሱትን ቃላት መመርመሩ ጠቃሚ ይሆናል። የሚገርመው መጽሐፍ ቅዱስ ከተጠቀመባቸው ቃላት አንዳቸውም ስለ አስተዳደራዊ ሥራዎች ወይም ምእመናንን ስለ መቆጣጠሩ የሚናገሩ አለመሆናቸው ነው።

*ሀ. እረኛ (የእረኛ-መሪን አገልግሎት በስፋት ለመመልከት ትምህርት አሥራ ዘጠኝን ተመልከት።)*

*30ኛ ጥያቄ፡- 1ኛ ጴጥ. 5፡1-3ን አንብብ። ሀ) ጴጥሮስ ሽማግሌዎች ምን እንዲያደርጉ ይመክራል? ለ) የሽማግሌዎች ተጠሪነት ለማን ነው? ሰዎችን በእረኝነት ለማገልገል ምርጥ ምሳሌያችን ማን ነው? ሐ) ስለ ሽማግሌዎች አገልግሎት «እረኛ» የሚለው ቃል ምን ያስተምራል? መ) የሐዋ. 20፡25-31ን አንብብ። ከዚህ ምንባብ ስለ እረኛ ተግባር ምን እንማራለን?*

ምናልባትም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምንመለከተው እጅግ የታወቀ የመሪ ምሳሌ እረኛ የሚለው ሳይሆን አይቀርም።



እግዚአብሔር የሕዝቡ እረኛ ነው። እርሱ ለበጎቹ ይጠነቀቃል (መዝ. 23፤ ኢሳ. 40፡11)። ኢየሱስ ለበጎቹ እጅግ የሚያስብ እረኛ በመሆኑ ከ100 በጎቹ አንዱ ቢጠፋ 99ኙን ትቶ አንዱን ፍለጋ ይሄዳል (ዮሐ. 10፡1-16፤ ሉቃስ 15፡3-7)። በብሉይ ኪዳን፣ መሪዎች እረኞች ተብለው ይጠሩ ነበር (ሕዝ. 34)። የሚያሳዝነው፣ በብሉይ ኪዳን አብዛኞቹ መሪዎች ሥልጣናቸውን አላግባብ በመጠቀም ለመንጋው እንክብካቤ ያላደረጉ ነበሩ። በአዲስ ኪዳን የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች የእረኞች አለቃ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ሥር የሚሠሩ እረኞች መሆናቸው ተመልክቷል (1ኛ ጴጥ. 5፡4)። ሁሉም ሽማግሌዎች እረኞች ናቸው። ጥያቄው እንግዲህ፣ «የእግዚአብሔርን መንጋ የሚጠብቁ መልካም እረኞች ናቸው ወይ? ወይስ ለበጎቹ እምብዛም የግል እንክብካቤ የማያደርጉ ግድየለሽ እረኞች ናቸው? ወይስ ለግል ጥቅማቸው ብቻ የሚሮጡ ክፉ እረኞች ናቸው?» የሚለው ነው።

የእረኛ መሪ ምሳሌ እግዚአብሔር ሽማግሌዎች እንዴት እንዲመሩ እንደሚፈልግ ብዙ ነገሮችን ያሳየናል። ይሁን እንጂ፣ እረኛ መሪ ምን እንደሚመስል ለመረዳት፣ የአይሁድ እረኞችን ሁኔታ ማወቅ ይኖርብናል። በኢትዮጵያ ውስጥ እረኞች በጎቻቸውን እየገረፉ ሲነዱ እንመለከታለን። አይሁዳውያን እረኞች ግን በጎቻቸው እንዲታዘዙላቸው ጉልበት አይጠቀሙም። ድንጋይ በመወርወር ወይም በዱላ በጎቻቸውን አይመቷቸውም። ከዚህ ይልቅ፣ አይሁዳውያን እረኞች ከበጎቻቸው ጋር የግል ግንኙነት ይመሠርቱ ነበር። በጉ ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮ እረኛው በጣም ያቀርበዋል። ገና ሲወለድ ጀምሮ በጉን ይንከባከበዋል። በጎቹን ሣር ወይም ውኃ ወዳለበት ቦታ በሚወስድበት ጊዜ፣ በደንብ መሄድ የማይችሉትን ትንንሽ በጎች በጫንቃው ወይም በክንዶቹ ላይ አድርጎ ይሸከማቸዋል። ለእያንዳንዱ በግ ልዩ ስም ይሰጠዋል። በጉ ይህን ስሙን ያውቀዋል። በጉ በራሱ ርቀት መሄድ በሚችልበት ጊዜ እረኛው የበጉን ፍላጎቶች ለማሟላት ጥረት ማድረጉን ይቀጥላል። እረኛው ሁልጊዜም ጥሩ ውኃና ሣር ወዳለበት ስለሚመራቸው፣ በቁስላቸው ላይ ዘይት ስለሚጨምራላቸው፣ ወዘተ. . . በጎቹ ሁልጊዜም እረኛቸው እንደሚያስብላቸው

ያውቃሉ። ግንኙነታቸው በጣም የተቀራረበ በመሆኑ፣ እረኛው እዚህ አገር እንደሚታየው ከበጎቹ ኋላ ሆኖ በበትር ከመደብደብና ድንጋይ ከመወርወር ይልቅ፣ ፊት ፊት እየሄደ በጎቹ እንዲከተሉት በስማቸው ይጠራቸዋል። ማታ እረኞች ሕይወታቸውን ለበጎቻቸው ይሰጣሉ። ይህንንም የሚያደርጉት በጎቻቸውን ለመጠበቅ ሲሉ ከበሩ ላይ በመተኛት ነው። በጎቹን አውሬ ሊያጠቃ የሚችለው መጀመሪያ እረኛው ላይ ጉዳት ካደረሰ በኋላ ብቻ ነበር።

| |
|---|
| *31ኛ ጥያቄ፦ መዝ. 23ን አንብብ። ሀ) ይህ መዝሙር እረኛችን የሆነውን እግዚአብሔርን ከገለጸበት መንገድ ስለ እግዚአብሔር ልዩ እንክብካቤ ምን እንማራለን? ለ) ከዚህ ታሪክ እረኞች ለምእመናን ማድረግ ስላለባቸው ልዩ እንክብካቤ ምን እንማራለን? ሐ) ብዙ ሽማግሌዎች ስለ እረኝነት የሚያስቡትን ከላይ ከተገለጸው ጋር አነጻጽር።* |

እግዚአብሔር ሽማግሌዎችን «እረኞች» ብሎ በመጥራቱ፣ ስለ አገልግሎታቸው የሚከተለውን ለማስተማር ፈልጓል፦

1) የሽማግሌዎች ቀዳሚ ተግባር የምእመናንን ፍላጎት ማሟላት ነው። ቀዳሚው ጭንቀታቸው ቤተ ክርስቲያንን ማስተዳደር ሳይሆን፣ የምእመናንን መንፈሳዊ ሕይወት መንከባከብ ነው። የአንድ እረኛ ግብ የበጎቹን ጤንነት መጠበቅ እንደ ሆነ ሁሉ፣ የእረኛ መሪ ግብ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ጤናማ የሆኑትን አማኞች ማፍራት ነው።

2) ሽማግሌዎች ከእያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን አባል ጋር ግንኙነት ይመሠርታሉ። የአይሁድ እረኞች መጀመሪያ የግል ግንኙነት በመመሥረት በጎቻቸውን እንደሚመሩ ሁሉ፣ ሽማግሌዎችም ምእመኖቻቸውን ማወቅ ይኖርባቸዋል። ሽማግሌዎች ምእመናንን በማዘዝ ወይም የሚፈልጉትን እንዲያደርጉ በማስገደድ ሳይሆን፣ የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር ለመምራት መጣር አለባቸው። ምእመናን ሽማግሌዎቹን የሚለዩት የግል ፍላጎታቸውን ለማሟላት ሲጥሩ ነው። ይህ ደግሞ በፈቃደኝነት እረኞቹን እንዲከተሉ ያስችላቸዋል።



3) ሽማግሌዎች ቀደም ሲል ለምእመናን ፍላጎቶች የፍቅር ምላሽ በመስጠት ስላሳዩ፣ ምእመናን ሽማግሌዎቹ የሚናሩትን ይሰማሉ። አንድ ሰው የእረኝነት በትር መያዙ ብቻ እረኛ እያሰኘ ውም። አንድ ሰው እረኛ ሊሆን የሚችለው ድምጹን ሰምተው ለመከተል ፈቃደኛ የሆኑ በጎች ሲኖሩት ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ አንድ ሰው ሽማግሌ ወይም መሪ መባሉ ብቻ ግለሰቡን እረኛ አያሰኘውም። እረኛ ባለመሆናቸው ምክንያት ማንም ሰው የማይሰማቸው፣ ወይም የማይከተላቸው ብዙ ሰዎች አሉ። ይሁን እንጂ፣ ሽማግሌዎች እረኞች መሆን ይጠበቅባቸዋል። ስለሆነም፣ ለሽምግልና የሚመረጡ ሰዎች ለሰዎች ፍላጎቶች የሚጨነቁ መሆናቸውን ያሳዩ ሊሆኑ ይገባል። የሽምግልና ማዕረግ ባይሰጠውም፣ አንድ ምእመን ለምክር ሲመጣ፣ ወይም ደግሞ ራሱ የተቸገረ ሰው በመመልከት በፈቃደኝነት የረዳ ሰው መሆን አለበት። የሽማግሌዎች ምርጫ ምእመናን ለምክር የሚቀርቧቸውንና ሌሎችን ለመርዳት ራሳቸውን የሚሰጡትን ሰዎች መለየት ነው።

4) እረኞች መንፈሳዊና ቁሳዊ ፍላጎቶቻቸውን በማሟላት ለምእመናን የእረኝነት አገልግሎት ይሰጣሉ። በጎች እረኛቸውን የሚያምኑበት ብቸኛው ምክንያት ፍላጎታቸውን ለማሟላት ደፋ ቀና የሚሉ መሆናቸውን ከልምድ ስለሚያውቁ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ መንፈሳዊ እረኞችም የምእመናንን እመኔታ የሚያገኙት ሁኔታው ምንም ያህል አስቸጋሪ ቢሆን፣ ለሕዝቡ ፍላጎቶች ራሳቸውን በመስጠታቸው ነው። የምእመናንን እመኔታ ለማግኘት ቁልፉ ሽማግሌዎች በተከታታይ በሚያከናውኗቸው ተግባራት ታማኞች መሆናቸውን ማስመስከራቸው ነው። ምንም ቢሆንም ምንም፣ እነዚህ ቃላቸውን የሚጠብቁ ሰዎች መሆን አለባቸው። ሁኔታው ባይመች እንኳን፣ የምእመኖቻቸውን ጉዳት ለመቀነስ የሚጥሩ መሆን አለባቸው።

5) ሽማግሌዎች ከምእመኖቻቸው ጋር አብረው የሚታዩ እንጂ የተለዩ ወይም የበለጡ መሆናቸውን ለማሳየት የሚሞክሩ መሆን የለባቸውም። እረኞቹ የሚገኙት በጎቻቸው በሚገኙባቸው ስፍራ

ምች ሁሉ ነው። እረኛው ከበጎቹ የተሻለ ሕይወት አይኖረውም። በበጎች ላይ ዝናብ ቢወርድ፣ እረኛውም ይበሰብሳል። አየሩ ቀዝቃዛ ቢሆን፣ በጎቹም እረኛቸውም ለብርድ ይጋለጣሉ። በተመሳሳይ፣ እውነተኛ እረኞች ከምእመኖቻቸው የራቁ አይደሉም። ምእመናን የሚጋፈጧቸውን የድህነትና የሥራ አጥነት ችግሮች ይረዳሉ። ራሳቸውን የተሻሉ፣ የበለጠ የተማሩ፣ ወይም ትልቅ ኃይል ያላቸው አድርገው ከመመልከት ይልቅ፣ እውነተኛ እረኛ ሽማግሌ ዎች የሰዎችን ችግሮች ለመቅረፍ ጥረት ያደርጋሉ።

6) ሽማግሌዎች የቤተ ክርስቲያንን ጉዳዮች ከማስተዳደር ይልቅ፣ አብዛኛውን ጊዜያቸውን ማሳለፍ የሚገባቸው ምእመናን ለመርዳት በመምከር ነው። እረኞች ከበጎች ጋር የቅርብ ግንኙነት ለመመሥረት ጊዜ እንደሚፈጅ ያውቃሉ። ይህ በአንድ ወይም በሁለት ሳምንታት ውስጥ የሚከናወን ጉዳይ አይደለም። በተ መሳሳይ መንገድ፣ ሽማግሌዎች የእግዚአብሔርን መንጋ በእረኝነት ለማገልገል ከፈለጉ፣ ለፊ ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውንና ራሳቸውን በመስጠት የሕዝቡን ፍላጎቶች ማሟላት አለባቸው። ምእመናን ካወቋቸውና ከተማመኑባቸው በኋላ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ሊያግዟቸው ይችላሉ።

32ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች እንደ እውነተኛ «እረኞች» ቢሠሩ አገልግሎታቸው እንዴት የሚለወጥ ይመስልሃል? ለ) ሕዝቡ ለአመራር ያለውስ አመለካከት እንዴት የሚቀየር ይመስልሃል?

እንዳለመታል ሆኖ፣ እውነተኛ እረኛ ሆነው የሚያገለግሉ ሽማግሌዎች ብዙ አይደሉም። ሽማግሌዎችና አገልጋዮች ከዚህ የተ ለዩትን ሦስት ምሳሌዎች የሚከተለው ሆነው ተገኝተዋል።

በ<u>መጀመሪያ</u>፣ እንደ ቅጥር ሠራተኞች የሚያገለግሉ ብዙ ሰዎች አሉ። ኢየሱስ ቅጥረኛ ለበጎች መልካም እንክብካቤ እንደማያደርግ ተናግሯል (ዮሐ. 10:1-13)። ቅጥረኛ የሚያስበው ለራሱ ደህንነትና ፍላጎቶች ብቻ ነው። ከሕዝቡ ፍላጎቶች በላይ ለራሱ ሕይወት የሚጨነቅ ሽማግሌ ወይም መጋቢ እንደ ቅጥር ሠራተኛ ነው። ብዙውን ጊዜ ሽማግሌዎች የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን እንደ ቅጥር ሠራተኞች ይመለከቷቸዋል። ከዚህም



የተነሣ፣ አገልጋዮቹ አገልግሎታቸውን የሚመለከቱት እንደ ሥራ ነው። ለምእመናን እምብዛም ሳይጨነቁ ተግባራቸውን ያከናውናሉ። አገልግሎቱን የሚመለከቱት እንደ ሥራ በመሆኑ፣ የሚያስቀድሙት የራሳቸውን ጥቅም እንጂ የቤተ ክርስቲያን አባላትን ጥቅም አይደለም።

ሁለተኛ፣ በበጎ ፈቃደኝነት የሚሠሩም አሉ። እግዚአብሔር ምንም ነገር እንድናደርግ አያስገድደንም። እንዲያውም፣ እረኞች እንድንሆን አያስገድደንም። እንድንረዳው ይጠይቀናል፤ እኛም ይህንኑ ለማድረግ እንስማማለን። የሚያሳዝነው፣ ሽማግሌዎች ለመሆን ፈቃደኞች ሆነን ስለ ተገኘን፣ መጽሐፍ ቅዱስ ሽማግሌ ዎች ማድረግ አለባቸው የሚላቸውን ነገሮች ሁሉ ማከናወን ያለብን ይመስለናል። ብዙውን ጊዜ ሽማግሌዎች በበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት እንደሚሰጡ ያስባሉ። ሁኔታው አመቺ በሚሆንበት ጊዜ ወደ ስብሰባዎች ወይም ወደ ሥራ ለመምጣት ፈቃደኞች ይሆናሉ። ሳይመች ሲቀር ደግሞ፣ ይተዉታል። «እኛ ሥራ የሚበዛብን ሰዎች ነን። የምንችለውን ያህል እንሠራለን፤ ነገር ግን ያንን ሁሉ ሰዓት እንድንሠራ አትጠብቁ» ይላሉ።

<u>ሦስተኛ</u>፣ ብዙ ሽማግሌዎች ራሳቸውን እንደ «ቦርድ አባላት» ይመለከታሉ። ቀዳሚው ተግባራቸው በሽማግሌዎች ቦርድ ላይ መቀመጥ ነው። በወር አንድ ጊዜ መጥተው ሰዎች ስለሚጋፈጧቸው ችግሮች ተወያይተውና አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን ሰጥተው ይሄዳሉ። እንዲህ ዓይነት ሽማግሌዎች የቤተ ክርስቲያኒቱ ሥራዎች መከናወናቸውን እንጂ ከምእመናን ጋር የግል ግንኙነት ማድረጋቸውን እንደ አስፈላጊ ነገር አይመለከቱም። ሰዎች እንክብካቤ ሊደረግላቸው የሚገቡ የእግዚአብሔር በጎች መሆናቸው ይዘነጋና፣ ቤተ ክርስቲያኒቱን ለማንቀሳቀስ የሚያስችሉ መሣሪያዎች ተደርገው ይቆጠራሉ።

33ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ከእነዚህ ሦስት የተሳሳቱ የሽማግሌነት ግንዛቤዎች የትኞቹን እንደ ተመለከትክ ግለጽ። ለ) እረኛ ሽማግሌ የሚመራበትን ሁኔታ እነዚህን ሦስት የተሳሳቱ መንገዶች ከሚከተሉ ሰዎች የሚለየው እንዴት ነው?

እግቢአብሔር ሽማግሌዎች ሕዝቡን በእረኝነት እንዲያገለግሉ ይፈልጋል:: ነገር ግን እኛ ሽማግሌዎችን ወደ አስተዳዳሪነት የሚቀይር የቤተ ክርስቲያን መዋቅር የምንከተል ከሆነ፣ የእግዚእብሔርን ሕዝብ በእረኝነት ለማገልገል ሌሎች መንገዶችን መፈለግ እለብን:: እግዚአብሔር ሰዎችን በእረኝነት ሳያገለግል የማስተዳደር ተግባር ብቻ የሚያከናውን መዋቅር እንድንመሠርት አይፈልግም::

ለ. አስተማሪ:- (1ኛ ጢሞ. 3:2፤ ቲቶ 1:9ን አንብብ)

የጳውሎስ ፍላጎት ምእመናን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በሳሎች እንዲሆኑ ነው:: (ቈላ. 1:28-29ን አንብብ::) ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ከሚያስችሉት ዋና ዋና መሣሪያዎች አንዱ ማስተማር ነው:: ጳውሎስ ሰዎችን ለማረም፣ ለመገሠጽ፣ ለማበረታታት፣ ወዘተ. . . (2ኛ ጢሞ. 4:2) መጽሐፍ ቅዱስን መጠቀም እንዳለብን ይናገራል:: እብያተ ክርስቲያኖቻችን በሳል ባልሆኑ አማኞች እንዲሞሉ ካደረጉት ነገሮች አንዱ የትምህርት ማነስ ነው:: የሰዎች መዳን ብቻ በቂ ነው ብለው ያስባሉ:: መንፈሳዊ ልጆችን እንወልድና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ላንረዳቸው እንቀራለን:: ይህ ልጅን ወልዶ ትምህርት፣ ምግብ ወይም ሥልጠና እንደማይሰጥ ወላጅ መሆን ማለት ነው:: ሌላው በሳል ያልሆኑ አማኞች እንዲበዙ ያደረገው መጽሐፍ ቅዱስን ሥርዓታዊ በሆነ መንገድ ለማስተማር ዕቅድ እለማውጣታችን ነው:: ተጋብዘው የሚያስተምሩ ሰዎች ስብከቶችን ያቀርባሉ እንጂ፣ የተደራጀ ትምህርት እይሰጡም:: እማኞች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በሳል የሚሆኑበት ብቸኛው መንገድ ከእግቢእብሔር ቃል የሚመጣውን ትምህርት በማወቅና በመታዘዝ ነው::

ማስተማር ሽማግሌዎች አማኞች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በሳሎች እንዲሆኑ ለማድረግ ከሚጠቀሙባቸው ዐበይት መሣሪያ ዎች አንዱ በመሆኑ፣ ጳውሎስ ሽማግሌዎች የማስተማር ብቃት እንዲኖራቸው ይገባል ይላል:: ጳውሎስ በሁለቱም የሽምግልና የብቃት ዝርዝሮች ውስጥ ሽማግሌዎች የእግዚእብሔርን ቃል



ማወቅና ማስተማር እንዳለባቸው እመልክቷል:: እንዲያውም፣ ሽማግሌ ከዲያቆን በዋናነት የሚለየው የማስተማር ብቃት ሊኖረው ስለሚገባ ነው:: ይህ ማለት ከሽማግሌ ዋና ዋና ኃላፊነቶች እንዱ የእግቢአብሔርን ቃል ለምእመናን ማስተማር ነው:: ስለሆነም፣ በማስተማር አገልግሎት ላይ በስፋት የማይሳተፍ ሽማግሌ የሽማግሌነት ተግባሩን እያከናወነ አይደለም ማለት ነው::

ይህ ማለት ግን አንድ ሽማግሌ ለሕዝብ የመናገር ከፍተኛ ችሎታ ሊኖረው ይገባል ማለተ አይደለም:: በየእሑዱ ምእመናንን ሁሉ የማስተማር ችሎታ ሊኖረው ይገባል ማለት አይደለም:: ነገር ግን የወንጌሉን እውነቶች በሚገባ ሊያውቅና እነቢህኑ እውነቶች በሕይወቱ ሊያሳይ ይገባል ማለት ነው:: ለአንድ ወይም ሁለትና ሦስት ሰዎች ለሚገኙበት አነስተኛ ቡድን የወንጌሉን እውነታዎች ማካፈል መቻል አለበት::

አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት «አስተማሪ ሽማግሌ»ን ከተራ ሽማግሌ ይለያሉ:: አስተማሪ ሽማግሌ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል:-

1) ምእመናንን በይፋ የማስተማሩን ተግባር በአብዛኛው ያከናውናል:: በአብዛኞቹ እሑዶች ከምስባክ ትምህርት ያቀርባል:: አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት እንዲህ ዓይነቱን አስተማሪ ሽማግሌ «መጋቢ» ብለው ይጠሩታል:: በኋላ የመጋቢን ልዩ ተግባራት እንመለከታለን::

2) ብዙውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ሆኖ ይሠራል:: ስዚህ አገልግሎቱም ደመወዝ ይከፈለዋል::

«አስተማሪ ሽማግሌ»ን ከመደበኛ ሽማግሌ የሚለየው የአገልግሎቱ ልክ ነው:: ሁለቱም የእግቢአብሔርን ቃል ማስተማር ቢኖርባቸውም፣ አስተማሪው ሽማግሌ ከመደበኛው በበለጠ የማስተ ማር ተግባራትን ያከናውናል:: አብዛኞቹ መደበኛ ሽማግሌዎች ሙሉ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት በዓለማዊ ሥራቸው ላይ ስለሚሆን፣ የአስተማሪ ሽማግሌን ያህል ጊዜ ሰጥተው ሊያገለግሉ እይችሉም:: ይህ ማለት ግን አስተማሪ ሽማግሌ ከሌሎች ሽማግሌ

ዎች የበሰጠ ሥልጣን እሰው ማሰት አይደሰም:: «ቅጥር ሠራተኛ» ነው ማሰትም አይደሰም:: እርሱም እንደ ሌሎቹ ሁሉ ሽማግሌ ነው:: ነገር ግን ከሌሎች በበሰጠ ሰቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ጊዜ ይሰጣል::

መጽሐፍ ቅዱስ ማስተማርን የሚመሰከትበት መንገድ እኛ ክምንመሰክትበት የተሰየ ነው:: ሰእኛ ማስተማር መረጃ የማስተላሰፍ ጉዳይ ነው:: ስሰዚህ በስሚናሪ ወይም በሥነ መሰኮት ኮሌጅ መረጃ የተሰጣቸው ሰዎች ሌሎችን እንዲያስተምሩ ይነገራቸዋል:: እነርሱም የተቀበሉትን መረጃ ሰሌሰች ያስተላልፋሉ:: ብዙውን ጊዜ ስሰሚያስተምሩት ነገር የግል ተሞክሮ የላቸውም:: በመሆኑም፣ ወንጌልን መስክረው የማያውቁ ስዎች ስሰ ወንጌል ስርጭት ያስተምራሉ፣ ያላገቡት ስሰ ጋብቻ ያስተምራሉ:: የዚህ ዓይነቱ ሥነ መሰኮታዊ ትምህርት ሰቤተ ክርስቲያን እምብዛም ጠቃሚ አይሆንም:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እስተማሪ ክሕይወት ልምዱ የሚያስተምር ሰው ነው:: ከሌሎች የሰማውን ብቻ ሳይሆን፣ እነዚያ እውነቶች በእውነተኛ ሕይወት ውስጥ እንዴት እንደሚዛመዱም ያስተምራል:: ተማሪዎቹም ቢሆኑ መረጃውን ብቻ ሳይሆን የሚማሩት፣ እውነቱ በአስተማሪው ሕይወት ውስጥ ተግባራዊ የሚሆንበትን መንገድ ጭምር ነው:: እውነተኛና ውጤታማ ትምህርት ሦስት ነገሮችን ይጠይቃል:-

1) ጥሩ የመረጃ እውቀት:: ሽማግሌ የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅ አሰበት:: መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት የመግባት ዕድል ሳይኖረው ቢችልም፣ በግል ጥናት፣ መንፈሳዊ መጻሕፍትን በማንበብና የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት የሚያስተምሩትን ሰዎች በጥንቃቄ በማዳመጥ መጽሐፍ ቅዱስን በሚገባ ሊያውቅ ይችላል:: ቃሉን በሚገባ ሳያውቅ ሰማስተማር በሚሞክርበት ጊዜ፣ የሰይጣን መሣሪያ በመሆን የሐስት ትምህርቶችን ሊያስፋፋ ይችላል:: ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክምንመሰከታቸው ከባባድ አደጋዎች አንዱ የቃሉን እውነት ጥርት አድርገው የማያውቁ ሽማግሌዎች መኖራቸው ነው:: ጳውሎስ ሰኤፌሶን ሽማግሌዎች ሲናገር የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ እንደ ነገራቸውና ከዚህ በኋላ ሌሎችን



ሲያስተምሩ እንደሚችሉ ገልጾሳቸዋል (የሐዋ. 20:17-21፣ 26-31):: እኛስ በቤተ ክርስቲያናችን ሽማግሌዎችን ልክ እንደ ጳውሎስ ሰአገልግሎት አዘጋጅተናል ሊንል እንችላሰን? ጳውሎስ ሐስተኛ አስተማሪዎች ክው-ጭ ብቻ ሳይሆን፣ ክቤተ ክርስቲያን ውስጥም ሊፈልቁ እንደሚችሉ ተናግሯል::

2) እውነት ከሰዎች ሕይወት ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ማብራራት:: መጽሐፍ ቅዱስ የተሰጠን የንድፈ-አሳብ እውቀት ሰማስተማር አይደሰም:: ይልቁንም፣ አስተማሪዎች ቃሉን በመጠቀም የወንጌሉን እውነት ከሰዎች ሕይወት ጋር ማዛመድ አሰባቸው:: ይህንን ከጳውሎስ መልእክት ውስጥ እናገኛሰን:: ጳውሎስ ስሰ ደኅንነት አስተምህሮ ማብራሪያ ባቀረበበት የሮሜ መጽሐፍ ውስጥ ሳይቀር የመጨረሻዎቹን ምዕራፎች የቋጨው ሰዎች ከወንጌሉ የተነሣ እንዴት አኗኗራቸውን መቀየር እንዳሰባቸው በማሳየት ነው:: ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔር ቃል እንዴት ከግል ሕይወታቸውና ካሉበት ሁኔታ ጋር እንደሚዛመድ ሰማወቅ ይቸገራሉ:: እስተማሪዎች እውነቱን ብቻ ሳይሆን፣ እውነቱ ከሕይወታቸው ጋር የሚዛመድበትን ሁኔታ በማሳየት ጭምር ሊረዷቸው ይገባል:: መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን መንፈሳዊ እውነትን በዕለት ተዕለት የመኖርን ሁኔታ ጥበብ ሲል ይጠራዋል:: እውነቱ ደስ ብሏቸውና የስሙትም ነገር ጥሟቸው ይወጡና እግዚአብሔር ምን እንዲያደርጉ እንደ ጠየቃቸው ሳያውቁ ይቀራሉ:: ሰዚህ ይሆን ብዙ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን እየተመላሰሉ፣ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የማይኖሩት?

3) ማስተማር የመጽሐፍ እውቀት ሳይሆን፣ በልምድ ላይ የተመሠረተ ነው:: የመጽሐፍ እውቀትን ብቻ ማስተላለፍ የተወሰነ ጥቅም ነው ያሰው:: ነገር ግን አንድ ሰው ከልምዱ ተነሥቶ በሚያስተምርበት ጊዜ፣ ሰዎች ሰመስማት ይዘጋጃሉ:: ሰዎች አንድን አስተማሪ የሚሰሙት ግሰሰቡ «ተእማኒነት» አሰው ብሰው ሲያስቡ ነው:: ይህ ማሰት የሚናገረው በሕይወቱ ውስጥ ያሰፈ መሆኑን ሲያረጋግጡ ነው:: ብዙውን ጊዜ የሕይወት ልምድ ሳይኖረው ዲግሪ ይዞ የመጣን ሰው ምእመናን እምብዛም አይሰሙትም::

ትልቁ ትምህርት የግለሰቡ ሕይወት ነው። «ድርጊታችን ከቃላችን በላይ ጮክ ብሎ ይናራል» የሚል አባባል አለ። ስለሆነም፣ ሰዎች ቃላችንን ቢሰሙም፣ አኗኗራችንንም እየተከታተሉ መሆናቸውን መዘንጋት የለብንም። ሽማግሌዎች ስለ ወንጌሉ መናገር ብቻ ሳይሆን፣ ለምእመናን እግዚአብሔርን የሚያስከብር ሕይወት ምን እንደ ሆነ ለማሳየት በሚያስችል ሕይወትም መመላለስ አለባቸው። የምናስተምረውና የምንኖረው ሕይወት የሚቃረን ከሆነ፣ ምናልባትም ግብዞች ነን ማለት ነው። ሰዎች ግብዝነትን በሕይወታችን ውስጥ በሚመለከቱበት ጊዜ፣ የምናስተምራቸውን እሳብ ክልባቸው አይሰሙም። ድርጊታችን ከቃላችን በላይ ትልቅ መልእክት ያስተላልፋል፣ ሰዎችም ከምንናገረው በላይ የምንኖረውን ሕይወት ይኮርጃሉ።

34ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ከቤተ ክርስቲያናችሁ ሽማግሌዎች አብዛኞቹ «ለማስተማር የሚበቃ» የሚለውን መስፈርት ያሟላሉ? መልስህን አብራራ። ለ) እነዚህ ሽማግሌዎች በትጋት ሕዝቡን ያስተምራሉ? እንዴት እንደሚያስተምሩ ለማሳየት አንዳንድ ምሳሌዎችን ስጥ። አብዛኞቹ የማያስተምሩ ከሆነ፣ ምክንያቱ ምንድን ነው? ሐ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ያሉት አብዛኞቹ አስተማሪዎች ወይም ሰባኪዎች የመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተማሪነትን ሦስት መስፈርቶች ያሟላሉ? ካልሆነ፣ ችግሩ ያለው የቱ ጋ ነው? መ) ሰዎች ግለሰቡ 1) የሚያስተምረውን በሕይወቱ ስላልተለማመደው፣ ወይም 2) ቃሉ ከሕይወቱ ስለ ተፋታ የአንድን ሰው ትምህርት አንለማም ያሉበት ሁኔታ ነበር?

አንድ ሽማግሌ ከሚያከናውናቸው አገልግሎቶች አንዱ ቃሉን በግልጽና ቀጣይነት ባለው መንገድ ለምእመናን ማካፈል መሆኑ አሌ አይባልም። እያንዳንዱ ምእመን ቃሉን ካልተማረ፣ በመንፈሳዊ ሕይወቱ በሳል ሊሆን አይችልም። ስለሆነም፣ ሽማግሌዎች እያንዳንዱ ምእመን ቃሉን እንዴት እንደሚማር ዕቅድ ማውጣት አለባቸው። ልጆች፣ ወጣቶችና አዋቂዎች በተገቢው መንገድ የእግዚአብሔርን ቃል መማር አለባቸው። አዳዲስ አማኞች የቃሉን እውነት መማር አለባቸው። ሽማግሌዎች ይህንን ለማድረግ ካልቻሉ፣ ምእመናን ሁሉ ቃሉን በአጥጋቢ ሁኔታ የሚማሩበትን ዕቅድ ማውጣት አለባቸው።



35ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በመንፈሳዊ እድገትህ ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገልህ ማን ነው? ግለሰቡ ይህንን እድገት እንድታገኝ ምን እንዳደረገልህ ግለጽ። ለ) ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሰው ቀረብ ብሎ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን እንዲያይ የሚፈልጉት ለምንድን ነው? ሐ) 1ኛ ቆሮ. 11:1፣ ፊልጵ. 3:17ን አንብብ። ጳውሎስ ይህንን ትእዛዝ የሰጠው ለምን ይመስልሃል? መ) ሽማግሌዎች ዛሬ ለቤተ ክርስቲያን እንዲህ ዓይነት ትእዛዝ ለመስጠት ፈቃደኞች የሚሆኑ ይመስልሃል? መልስህን አብራራ።

*ሐ. አሠልጣኝ (ደቀ መዝሙር እንደሚያደርግ መምህር)፡-*

የምናውቃቸው ሰዎች ከፍተኛ የሆነ ተጽዕኖ ያሳድሩብናል። ብዙውን ጊዜ እነዚህ ሰዎች ተጽዕኖ የሚያሳድሩብን መደበኛ ትምህርት በመስጠት ሳይሆን፣ በሕይወታቸው በሚያሳዩን ነገር ነው። አብዛኞቹ ምእመናን በቃል ትምህርት ብቻ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነቶች ተግባራዊ ለማድረግ መቸገራቸው የማይቀር ነው። የሚቀልላቸው የእግዚአብሔርን እውነት የሚኖርን ሰው ሕይወት ማየትና ከዚያ በኋላ የእርሱን ሕይወት የሚመስል ኑሮ መምራት ነው። ጳውሎስ ይህንን በመረዳቱ፣ ሕይወቱን በግልጽ ለሌሎች ምሳሌ አድርጎ እንደሚኖር አመልክቷል (የሐዋ. 20:18-21)። እንዲያውም፣ «እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ» እስከ ማለት የደረሰ አገልጋይ ነበር። ምሳሌ መሆን ሰዎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ለማገዝ የሚያስችል የሥልጠና መንገድ ነው።

1) ሽማግሌዎች ምእመናን እንዴት ክርስቶስን እንደሚከተሉ በምሳሌ ማሳየት አለባቸው። አንድ ሽማግሌ በምእመናን ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊያደርግና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ሊያደርግ የሚችልበት ትልቁ መንገድ ኢየሱስን እንዴት እንደሚከተሉ ምሳሌ መሆን ነው። ይህ ማለት ሰዎች ሕይወቱን ማየት መቻል አለባቸው ማለት ነው። ከእግዚአብሔር፣ ከቤተሰቡ፣ ከሥራው፣ ከማያምኑ ሰዎች፣ ከድሆች፣ ወዘተ. . . ጋር ያለውን ግንኙነት መመልከት ይኖርባቸዋል። ሰዎች እርሱን ካዩት በኋላ፣ ይኮርጁታል። በዚህ ዓይነት በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እየበሰሉ ይሄዳሉ።

ይህ ባህላዊ የመሪነት ግንዛቤያችንን እንድንለውጥ የሚጠይቅ ነው:: ብዙውን ጊዜ መምህር ወይም መሪ ከተራ አማኞች ጋር አብሮ ከመሆን እንዲታቀብ ይፈለጋል:: ይህ የሚሆነው ምናልባትም ሰዎች የመሪውን የጸሎት ሕይወት፣ የቤተሰብ ሕይወት፣ ወዘተ. . . ቀረብ ብለው ካዩ፣ አክብሮት አይሰጡኝም ብሎ በማለቡ ምክንያት ይሆናል:: ነገር ግን በኢትዮጵያ ውስጥ መንፈሳዊ ምሳሌ መሆን ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ በግልጽ ሳናሳይ፣ መንፈሳዊ ክርስቲያኖችን ማፍራት አይቻልም:: ሽማግሌዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመንፈሳዊነት ምርጥ ምሳሌዎች መሆን ስላለባቸው፣ ወደ ምእመናን ቀረብ ብለው ሕይወታቸውን ማስነበብ አለባቸው:: የሽማግሌዎችና የምእመናን ቁጥር ስለማይመጣጠን፣ ምእመናን የመሪዎችን ሕይወት በቅርብ እንዲመለከቱ ማድረጉ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል:: ስለሆነም፣ ሽማግሌዎች ክርስቶስን መከተል ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ ምእመናን እንዲያውቁ የሚረዱ አሠልጣኞችን መመደብ አለባቸው::

36ኛ ጥያቄ፡- 2ኛ ጢሞ. 2:2ን አንብብ:: ሀ) ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የሰጠው ትእዛዝ ምን ነበር? ለ) ጳውሎስ ራሱ ይህንን ትእዛዝ የፈጸመው እንዴት ነበር? ሐ) አብዛኞቹ ሽማግሌዎች ይህንን ትእዛዝ ይፈጽማሉ? መልስህን አብራራ::

2) ሽማግሌዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልጋዮች በሥራቸው እንዲረዱ በማድረግ ሊያዘጋጁቸው ይገባል:: «ሰዎችን የሚያሳድግ መሪ የእግዚአብሔርን መንግሥት ያሰፋል:: ነገር ግን ሌሎች መሪዎችን የሚያሳድግ መሪ ውጤታማነቱን ይጨምራል» የሚል አባባል አለ:: ይህ ማለት ሰዎችን ብቻ በማስተማር ሥራ ላይ የሚያተኩሩ ሽማግሌዎች ግለሰቦቹ እንዲያድጉ ይረዳሉ ማለት ነው:: ነገር ግን አገልግሎቱ በአንድ ሰው ላይ ብቻ የተመሠረተ ይሆናል:: የሰዎቹ እድገት መሪው ሊሰጣቸው በሚችለው ጊዜ፣ ባሉት ስጦታዎችና ችሎታዎች የተገደበ ነው:: ነገር ግን ሌሎች መሪዎችን በሚያሳድግበት ጊዜ፣ ሥራውና ተጽዕኖው በሌሎች አገልግሎት ይስፋፋል:: ሽማግሌዎች ከሰዎች ጋር ሲሠሩና ሌሎች



መሪዎችን ሲያዘጋጁ፣ የወንጌሉ የመሮጥ ብቃት በከፍተኛ ደረጃ ይጨምራል::

ይህ ማለት እያንዳንዱ ሽማግሌ አንድ ወይም ሁለት ወጣቶችን ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ማዘጋጀት አለበት ማለት ነው:: ኢየሱስ 12 ተተኪዎችን አፍርቷል:: ጳውሎስ ደግሞ እንደ ቲቶና ጢሞቴዎስ (ምናልባትም ሌሎች ብዙ) የመሳሰሉትን አገልጋዮች አፍርቷል::

ይህም ቢሆን ባህላዊ አመለካከታችንን እንድንቀይር የሚጠይቅ ነገር ነው:: ብዙውን ጊዜ መሪዎች ወጣቶቹ ወደ አመራር እንዲመጡ አይፈልጉም:: «ከፍተኛ ትምህርት ስላላቸው ሰዎች ከእኛ አስበልጠው ሊወዷቸው ይችላሉ» በሚል ፍርሃት ተሸብበን በርቀት እንገፋቸዋለን:: የዚህ ዓይነቱ አመለካከት ስለ አመራር የተሳሳተ ግንዛቤ እንዳለን ያሳያል:: እንዲህ የምናስብ ከሆነ፣ የኢየሱስ ወይም የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች አይደለንም:: የምናገለግለው የራሳችንን ጥቅማ ጥቅምና ክብር ብቻ ነው ማለት ነው:: ወጣት መሪዎችን በማራቅ ለረዥምም ጊዜ በመሪነት ላይ ለመቆየት እንፈልጋለን:: ስለ እግዚአብሔር መንግሥት፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን እድገትና ስለ ኢየሱስ ክብር ከልባችን የሚገድደን ከሆነ፣ የመጥምቁ ዮሐንስ ዓይነት አመለካከት ይኖረን ነበር:: የኢየሱስ ዝና እየገነነ ሲመጣ ዮሐንስ፣ «እኔ ላንስ እርሱ ሊልቅ ያስፈልጋል» ነበር ያለው (ዮሐ. 3:30):: እግዚአብሔር ከእኛ የተሻለ አገልጋይ ቢያስነሣ፣ ለእርሱ የአገልግሎት በሮችን ከመከርቸም ይልቅ፣ በደስታ በሩን ወለል አድረገን ልንከፍትለት ይገባል::

37ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ሽማግሌዎች ምእመናንን የማሠልጠን ተግባራቸውን በተሻለ መንገድ እንዴት ሊያከናውኑ እንደሚችሉ ግለጽ:: ለ) ሽማግሌዎች ስጦታ ያላቸው ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲያገለግሉ በተሻለ ሁኔታ እንዴት ሊያዘጋጁቸው እንደሚችሉ ግለጽ::

መ. የእውነት ጠባቂዎች:-

38ኛ ጥያቄ፡- የሐዋ. 20:28-31ን አንብብ:: ሀ) ጳውሎስ የኤፌሶን መሪዎች እንዲጠብቁ የተናገራቸውን ነገሮች ዘርዝር:: ለ) ይህ አገልግሎት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለምን ያስፈልጋል? ሐ) ሽማግሌዎች ይህንን

አገልግሎት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን ያህል ጥሩ አድርገው እያከናወኑ ነው?

ጳውሎስ ለኤፌሶን ሽማግሌዎች የመጨረሻ ምክሩን በሚሰጥበት ጊዜ፣ ሽማግሌዎች የእውነት ጠባቂዎች መሆናቸውን ጠንከር ባለ መንገድ ገልጾላቸዋል:: ከእውነት እንዳይወድቁ የገዛ ሕይወታቸውን መጠበቅ ያስፈልጋቸው ነበር:: ከሽማግሌነት ኃላፊነቶች አንዱ በጎችን ከተኩላዎች መጠበቅ እንደ ሆነም አመልክቷል:: ጳውሎስ ተኩላዎች ከቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደሚወጡም ተናግሯል:: ይህን ሲል በሁሉም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የእግዚአብሔርን ሕዝብ መንፈሳዊ ሕይወት ለማጥፋት የሚፈልጉ ሰዎች መኖራቸውን ማመልከቱ ነበር:: ይህንን የሚያደርጉት ሥልጣን የጠማቸው መሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ:: ነገር ግን ብዙውን ጊዜ ትልቅ ስም ያላቸው ክርስቲያኖች ናቸው የሐሰት ትምህርትን የሚጀምሩት:: ሰይጣን ምእመናን የሐሰት ትምህርት እንዲከተሉ፣ ወንጌሉን ከማዳረስ ይልቅ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ብቻ እንዲጠመዱ ወይም የተወሰኑ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮዎችን በመያዝ ሌሎችን እንዲተዉ (ለምሳሌ፣ ከሁሉም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ይልቅ ልሳን በመናገር ላይ ማተኮር)፣ ምእመናን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ሳያድጉና ለእግዚአብሔር ውጤታማ ሳይሆኑ ይቀራሉ:: ሽማግሌዎች ቃሉን ካላወቁ፣ ወይም እውነትን ብናገር ሰው ምን ይለኛል? የሚል ፍርሃት ከነገሠባቸው፣ ተኩላዎች የምእመናንን ሕይወት እንዲያወድሙ እየፈቀዱ ነው ማለት ነው:: ሽማግሌዎች ከሚያከናውኗቸው ከባባድ አገልግሎቶቸ አንዱ የወንጌሉን እውነትና የአገልግሎቶችን ሚዛናዊነት መጠበቅ ነው:: ይህ ደግሞ ከአንዳንድ ምእመናን ጋር አለመስማማትን የሚያስከትል ነው::

ሠ. ጳጳስ:-

ዛሬ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ይህን ቃል የሚጠቀሙት የብዙ አብያተ ክርስቲያናት የበላይ የሆነን ሰው ለማመልከት ነው:: በአዲስ ኪዳን ግን ይህ ቃል ሽማግሌን ለመግለጽ ያገለገለ ሌላው አማራጭ ቃል ነበር:: ይህንን በሐዋርያት ሥራ 20:17-18 እና ቲቶ



1:5-7 ውስጥ እንመለከታለን:: ሽማግሌ የሚለው ቃል ብዙውን ጊዜ ከእድሜ ጋር የሚመጣውን መንፈሳዊ ብስለትና ጥበብ የተጎናጸፉትን ሰዎች ያመለከታል:: ጳጳስ የሚለው ቃል ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን የመከታተሉን ተግባር ያሳያል:: ይህ ደግሞ የሽማግሌ ዎች ተግባር ነው:: ጳጳስ የሚለው ቃል ማስተዳደርን ወይም መቆጣጠርን አያሳይም:: ነገር ግን የሰዎችን ፍላጎት ማሟላትን የሚያሳይ ነው:: አንድ አባት ልጆቹን በግል ደረጃ እንደሚያውቅና ከግል ማንነታቸው አንጻር ለእድገታቸው የሚያስፈልገውን ነገር እንደሚያደርግ ሁሉ፣ ጳጳስ/ሽማግሌም ሕዝቡን ማወቅ አለበት:: የግል ፍላጎታቸውን ስለሚያውቅ፣ እነዚህን ፍላጎቶች ለማሟላት እንዲችሉ ይረዳቸዋል::

39ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያናችሁ ሽማግሌዎች እያንዳንዱን ምእመን የሚያውቁ ይመስልሃል? ካልሆነ፣ ለምን? ለ) ሽማግሌዎች ምእመናንን በሚገባ ማወቃቸው ለምን ያስፈልጋል? ሐ) ሁሉም ምእመናን የሚገባቸውን ያህል መንፈሳዊ ክትትል እንዲያገኙ ምን ቢደረግ መልካም ነው?

40ኛ ጥያቄ:- 1ኛ ቆሮ. 4:1-5ን አንብብ:: ሀ) ጳውሎስ ሰዎች እርሱን (ሽማግሌዎችን) እንዴት እንዲመለከቱ ይፈልጋል? ለ) ይህ ስለ ሽማግሌዎች አገልግሎት ምን ያስተምረናል? ሐ) ጳውሎስ እንዲህ ዓይነቱ ሰው እግዚአብሔር እንዳይፈርድበት ምን ሊያደርግ ይገባል አለ?

ረ. የእግዚአብሔር ቤተሰብ ባለ አደራዎች:-

በጥንት ዘመን ሀብታሞች ብዙ ባሪያዎች ይኖሯቸው ነበር:: ከእነዚህ ባሪያዎች መካከል ትጉሕ ሠራተኛ፣ አስተዋይና ታማኝ የሆነው ባሪያ የጌታውን ንብረት በሙሉ በኃላፊነት እንዲያስተዳድር ይደረጋል:: ይህን ኃላፊነት የያዘው አገልጋይ «ባለ አደራ» ይባላል:: ዮሴፍ በጲጥፋራ ቤት ውስጥ ባለ አደራ ነበር:: ባሪያ ቢሆንም፣ ዮሴፍ የጲጥፋራንና ቤትና ሀብት በሙሉ ያስተዳድር ነበር (ዘፍጥ. 39:2-6፤ ማቴ. 20:1-8፤ ሉቃስ 16:1-9):: በ1ኛ ቆሮንቶስ 4:1-5 ጳውሎስ የማስተማር አገልግሎት የሚሰጡትን ሽማግሌዎች ጨምሮ መሪዎች ሁሉ ባለ አደራ መሆናቸውን ይናገራል:: የቤተ ሰቡ (የአማኞች ማኅበረሰብ) ባለቤት እግዚአብሔር ነው:: ቤተሰቡ

በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ምእመናን በሙሉ ያካትታል:: ሽማግሌው እንደ ሌሎች አማኞች ሁሉ የእግዚአብሔር ባሪያ ነው:: ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር ሽማግሌዎች ቤቱን እንዲያስተዳድሩ መርጧቸዋል::

ሽማግሌዎች በባለ አደራነት የሚያስተዳድሯቸው አያሌ ነገሮች አሉ::

በመጀመሪያ፣ ሽማግሌዎች የእግዚአብሔርን ቤተሰብ የሚያስተዳድሩበት ዋንኛው መንገድ ለሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር ነው:: እግዚአብሔር ሽማግሌዎች የእግዚአብሔርን ቃል ሀብቶች በታማኝነት የማስተላለፍ ኃላፊነት እንዳለባቸው ይገልጻል:: እንዲሁም ደግሞ ወንጌሉን ማንም ሰው እንዳይለውጥ መጠበቅ ይኖርባቸዋል (1ኛ ጢሞ. 1:11፤ 6:20፤ 2ኛ ጢሞ. 1:14):: ይህ ማለት ሽማግሌዎች የእግዚአብሔርን ቃል በጥንቃቄ በማጥናት እውነትን ሁሉ ለሕዝቡ ማስተማር አለባቸው::

ሁለተኛ፣ ሽማግሌዎች እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጠውን ንብረት ይጠብቃሉ:: ይህ ንብረት ደግሞ ገንዘብን የሚጨምር ነው:: ስለሆነም፣ ሽማግሌዎች ምእመናን አሥራትና መባ እንዲሰጡና ይህም የክርስቶስን መንግሥት ለማስፋት እንዲውል ማድረግ ይጠበቅባቸዋል:: ሁሉም ሰው የአቅሙን ያህል እግዚአብሔርን እንዲያገለግል ለማስቻል የሰዎችን ሀብትና መንፈሳዊ ስጦታዎች በአግባቢ ሁኔታ ከጥቅም ላይ ማዋል ይኖርባቸዋል::

ባለ አደራነት ተጠያቂነትን ያስከትላል:: የቤቱ ባለቤት መጋቢው ሌሎች ባሪያዎችንና የጌታውን ንብረት ስላስተዳደረበት ሁኔታ ተጠያቂ ያደርገዋል:: በተመሳሳይ ሁኔታ፣ እግዚአብሔር ሽማግሌዎች ቤቱን ስላስተዳደሩበት ሁኔታ ይጠይቃቸዋል:: በተጨማሪም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ያስተዳደሩበትን ልባዊ አሳብም ይገመግማል::



41ኛ ጥያቄ:- ኤፌ. 4:11-16ን አንብብ:: ሀ) ይህ ምንባብ አስተማሪዎች ምን ማድረግ አለባቸው ይላል? ለ) ይህ በቤተ ክርስቲያናችሁ እየተከናወነ ያለው እንዴት ነው? ካልሆነ፣ ለምን?

ለ. የእግዚአብሔር ሕዝብ አሠልጣኞች:-

እግዚአብሔር የሰውን አካል የፈጠረው በተለያዩ ክፍሎች በመከፋፈል ነው:: እነዚህ ሁሉ ክፍሎች የተለያዩ ዓላማዎች አሏቸው:: ይሁን እንጂ፣ ጠቃሚ የሚሆኑት ሲሠሩ ብቻ ነው:: ብዙዎቻችን ሽባ የሆኑትን ሰዎች አይተናል:: እነዚህ ሰዎች ጣቶችና እግሮች ቢኖሯቸውም፣ አይንቀሳቀሱላቸውም:: እነዚህ የአካል ክፍሎቻቸው እምብዛም አይጠቅሟቸውም ማለት ነው:: ሰውነት በጥሩ ሁኔታ የሚሠራው ደግሞ ሁሉም የሰውነት ክፍሎች ሲሠሩ ነው:: እግሮቹና ዓይኖቹ ካልሠሩ አንድ ሰው ሊራመድ አይችልም:: የክርስቶስ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያንም ጉዳይ እንዲሁ ነው:: እያንዳንዱ አማኝ የክርስቶስ አካል ክፍል ነው (1ኛ ቆሮ. 12:12-26):: እነዚህ ሰዎች የቤተ ክርስቲያን አካል በመሆናቸው ደስ ሊለን ቢችልም፣ እያንዳንዱ አማኝ እግዚአብሔር የሰጠውን ድርሻ መወጣት አለበት:: ሁሉም ሰው በስምምነት በሚሠራበት ጊዜ፣ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ውጤታማ ይሆናሉ:: አዲስ ኪዳን መንፈስ ቅዱስ ለእንድ ሰው የሰጣቸውን አገልግሎቶች «መንፈሳዊ ስጦታዎች» በማለት ይጠራል (1ኛ ቆሮ. 12):: አብዛኞቹ አማኞች እግዚአብሔር የሰጣቸውን መንፈሳዊ ስጦታዎች በብቃት ከሥራ ላይ በማያውሉበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ጤናማ ልትሆን አትችልም:: ሁሉም ምእመናን በንቃት የማያገለግሉ ከሆነ፣ የትኛውም ምእመን እግዚአብሔር የሚፈልገውን ያህል ሊያድግ አይችልም፤ ቤተ ክርስቲያንም እግዚአብሔር የሚፈልግባትን ተግባር ሁሉ ልትወጣ አትችልም::

ከሽማግሌ ዐበይት ተግባራት አንዱ እያንዳንዱ አማኝ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ በንቃት እንዲሳተፍ ማበረታታት ነው:: እግዚአብሔር ሽማግሌዎች ለማኅበረ ምእመናኑ ሁሉንም ነገር እንዲያደርጉ አይፈልግም:: ነገር ግን እያንዳንዱን መሪ ብቁ በማድረግ በአገልግሎት ላይ እንዲያሰማሩ ይጠብቅባቸዋል:: ይህ ደግሞ

ስአማኙም ሆነ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ጠቃሚ ይሆናል፡፡ ሽማግሌዎች የማስታጠቅ ተግባራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ፣ የሚከተሉትን ነገሮች ማስታወስ ይኖርባቸዋል፡-

1) የቤተ ክርስቲያኒቱ አስተዳደራዊ መዋቅር እያንዳንዱ አማኝ ግልጽ አገልግሎት እንዲያገኝ የሚያግዝ ሊሆን ይገባል፡፡ መዋቅሩ አብዛኞቹ ሰዎች ምንም ዓይነት ተሳትፎ ሳያደርጉ ቁጭ ብለው እንዲስተናገዱ የሚያደርግ ወይም አማኞች የት ቦታ ማገልገል እንዳለባቸው በሚገባ የማያሳይ ከሆነ፣ መዋቅሩ መስወጥ አለበት፡፡

2) የሽማግሌዎችና የአገልጋዮች ተግባር ምእመናን እንዴት ቤተ ክርስቲያንን እንደሚያገለግሉ ማሠልጠን ሲሆን ይገባል፡፡ ምእመናን እግዚአብሔርን ለማገልገል ትክክለኛ አመለካከት እንዲኖራቸውና ለማገልገል የሚያስችል ክህሎት እንዲኖራቸው ማገዝ ይኖርባቸዋል፡፡ ሽማግሌዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልግሎት በመስጠት ላይ ብቻ ትኩረት ማድረግ የለባቸውም፡፡

3) ሽማግሌዎች እያንዳንዱ አማኝ መንፈስ ቅዱስ የሰጠውን ስጦታ እንዲለይ ማገዝ ይኖርባቸዋል፡፡ የምእመናንን መንፈሳዊ ስጦታዎች ለማሳደግና ከስጦታቸው ጋር የተገናዘበ አገልግሎት ላይ ለመመደብ ሽማግሌዎች ከምእመናን ጋር አብረው መሥራት አለባቸው፡፡

4) ሽማግሌዎች ምእመናን ሰልታዊ በሆነ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ላይ እንዲሳተፉ መምራት አለባቸው፡፡ ምእመናን በጽዳት ሥራ ላይ ብቻ እንዲሳተፉ ከማድረግ ይልቅ፣ በምስክርነት፣ በማስተማር፣ ድሆችን በመርዳት፣ ወዘተ. . . ላይ እንዲሰማሩ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

5) ሰዎች አገልግሎቶችን በጥሩ ሁኔታ ሊያከናውኑ የሚችሉት በጥሩ ግንኙነቶች አማካኝነት ነው፡፡ የመንፈሳዊ ስጦታ ዎች ዓላማ አንዱ አማኝ ሌላውን እንዲያገለግል በማስቻል ምእመናንን ማነጽ ነው (1ኛ ቆሮ. 14:26)፡፡ ስለሆነም፣ ሽማግሌ ዎች መንፈሳዊ ሕይወታቸውን በሚያሳድጉና አንዱን ሌላውን እንዲያገለግል በሚያስችሉ ግንኙነቶች ማደጋቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ ስለሆነም፣ ቤተ ክርስቲያን አማኞች እርስ በርሳቸው የሚተዋወቁባቸው፣ አገልግሎት የሚሰጡባቸው ትናንሽ ቡድኖች እንዲመሠረቱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያን እርስ በርሳቸው የማይተዋወቁ ብዙ ሰዎች የሚገኙባት ከሆነች፣ አማኞች ሌሎችን ለማገልገል ሰፊ ዕድል ሊያገኙ አይችሉም፡፡ ይህ ሰዎች ቤቱ በጥሩ ይዞታ እንዲቀጥል ከሚጥሩ የቤተሰብ አባላት ይልቅ፣ በስፖርት ሜዳ ላይ እንደ ተሰባሰቡ ተ መልካቾች እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡

6) ሰዎች ሁሉ ልዩ ስለሆኑና የሚማሩትና የሚያገለግሉት በተ ለየ መንገድ ስለሆነ፣ የሁሉንም ሰው ፍላጎት የሚያሟላ አንድ አገልግሎት ወይም መንገድ የለም፡፡ ስለሆነም፣ መዋቅሩ ሰዎችን ሁሉ ለማሳተፍ የሚችል መሆን አለበት፡፡

7) ከሁሉም የተሻለ የማስታጠቅ ተግባር የሚከናወነው ሽማግሌ ዎች ምእመናን አብረዋቸው እንዲያገለግሉና እንዲሠሩ ሲያደርጉ ነው፡፡ መሪዎች ለምእመናኑ አገልግሎት ምን እንደ ሆነ በመናገር፣ እንዴት እንደሚያገለግሉ በማሳየት፣ አገልግሎት ሲጀምሩ በመመ ልከት፣ ሲወድቁ በማበረታታት፣ ወዘተ. . . ውጤታማ እንዲሆኑ ይረዷቸዋል፡፡

> 42ኛ ጥያቄ፡- የሐዋ. 15:4-21ን አንብብ፡፡ ሀ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተነሣው የሥነ መለኮት ክርክር ውስጥ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሚና ምን ነበር? ለ) ይህ ስለ ሽማግሌዎች አገልግሎት ምን ያስተምረናል?

ሸ. ስመንፈሳዊና ሥነ መለኮታዊ ጉዳዮች ፍርድ መስጠት፡-

ሽማግሌዎች አልፎ አልፎ ፍርድ የመስጠት አገልግሎትም ያከናውናሉ፡፡ ይህ አገልግሎት በሦስት ሁኔታዎች ውስጥ የሚከናወን ነው፡፡ በመጀመሪያ፣ ምእመናን በአንድ ጉዳይ ሳይስማሙ ሲቀሩና ይህም የግንኙነት መሻከርን ሲያስከትል፡፡ ጳውሎስ አማኞች እነዚህን ጉዳዮች ወደ ፍርድ ቤት እንዳይወስዱ

ያዝዛል (1ኛ ቆሮ. 6:1-8)። ይህ ራስ ወዳድነታቸውን ለማሸነፍ የሚያስችል መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው ከመኖሩ በተጨማሪ፣ አንድ ቀን ገዥዎች ለሚሆኑት አማኞች ነውር የሆነ ነገር ነው። አንድ አማኝ የክርስቶስን ስም በዓለም ውስጥ ከሚያሰድብ ይልቅ፣ ቢበደል የተሻለ ነው። ስለሆነም፣ ቤተ ክርስቲያን ችግሩን ብትፈታ መልካም ነው። ጳውሎስ ለችግሩ እልባት እንዲሰጡ የጠበቀው ሽማግሌዎችን ሳይሆን አይቀርም። ሽማግሌዎች የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ ስለሚያውቁ፣ በጉዳዩ ላይ ቃሉ ምን እንደሚል ሊናገሩ ይችላሉ። በመንፈሳዊነታቸው የተከበሩ በመሆናቸውም፣ ሰዎች ምክራቸውን ይሰማሉ።

ሁለተኛ፣ ክርስቲያኖች በግልጽ የእግዚአብሔር ትእዛዛት ላይ የማያምፁባቸው ጊዜያት አሉ። ለምሳሌ፣ በ1ኛ ቆሮንቶስ 5 ከአባቱ ሚስት ጋር ዝሙት እየፈጸመ የሚኖር ሰው እንደ ነበረ እናነብባለን። ጳውሎስ ከኃጢአታቸው ንስሐ በማይገቡት ሰዎች ላይ ቤተ ክርስቲያን ቅጣት እንድትሰጥ ያዝዛል። የቅጣት ሥነ ሥርዓቱን የሚያስፈጽሙት ሽማግሌዎች ሳይሆኑ አይቀሩም። ጉዳዩ በሚገባ ከተመረመረና ኃጢአተኛው ንስሐ እንዲገባ ዕድል ከተሰጠው በኋላ ፈቃደኛ በማይሆንበት ጊዜ፣ ሌሎች አማኞች ጋር ኅብረት እንዳያደርግ ይደረግ ነበር።

ሦስተኛ፣ ሥነ መለኮታዊ ወይም ባህላዊ ጉዳዮችን ማብራራት አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ፣ ሽማግሌዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ የመወሰኑን ሂደት ይመራሉ። በሐዋርያት ሥራ 15 አሕዛብ ይገረዙ አይገረዙ የሚል ጥያቄ ነበር። ስለዚህ፣ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ስብሰባ ጠሩ። ሽማግሌዎች ትክክል ወይም ስሕተት የሆነ ነገር ምን እንደ ሆነ ስመለየት ተሳትፎ አድርገው ነበር። በዘመናችን ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች (ለምሳሌ፣ በልሳናት ስለ መናገር፣ የትንቢት ቃል፣ የፈውስ አገልግሎት) እና ስለ መናፍቃን (ለምሳሌ፣ «ኢየሱስ ብቻ») ቢመረምሩ መልካም ነው። ወይም ደግሞ ጎጂ እንደ መሆናቸው መጠን፣ በቤተ ክርስቲያን ሊወገዙ ስለሚገባቸው እንደ ውድ ባህላዊ የሙሽራ ዋጋ፣ የሴት ልጅ ግርዛት፣ ወዘተ. . . ግምገማ ቢያደርጉ መልካም ነው። ዓለም



ጥሩ የሆነውንና ያልሆነውን ነገር እንድትነግራቸው ከመጠበቅ ይልቅ፣ በእግዚአብሔር ዓይን የትኞቹ ባህላዊ ልማዶች ጎጂ እንደ ሆኑና የትኞቹ እንደማይጎዱ በመግለጽ ዓለምን ሊመሩ ይችላሉ።

43ኛ ጥያቄ፡- ሀ) እንዲህ ዓይነቱ አገልግሎት እንዴት ጠቃሚ እንደ ሆነና በቤተ ክርስቲያናችሁ እንዴት እየተከናወነ እንዳለ ግለጽ። ለ) ከሦስቱ የፍርድ አሰጣጦች የትኛውን ተመልክተሃል? ሐ) ሦስተኛው ዓይነት የፍርድ አሰጣጥ ለዘመናችን እንዴት አስፈላጊ እንደሚሆን ግለጽ።

ቀ. የቤተ ክርስቲያንን ራእይ መምራት፡-

ሽማግሌዎች የሚያገለግሉት የቤተ ክርስቲያን ራስ በሆነው በክርስቶስ ሥር ነው። ኢየሱስ ሽማግሌዎች ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር የሚፈልገውን ተግባር እንድትፈጽም ይረዷት ዘንድ ኃላፊነት ሰጥቶአቸዋል። እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በማንም ተጠቅሞ ሊናገር ቢችልም፣ ቤተ ክርስቲያን የምትሳተፍባቸውን ተግባራት በዋናነት በጸሎት የሚወስኑት ሽማግሌዎች ናቸው። የሽማግሌዎች ምሪት ሳይኖር ሁሉም ምእመናን የእግዚአብሔርን ራእይ ሰመወሰን ይቸገራሉ። ይህ እግዚአብሔር ለሽማግሌዎች ከሰጣቸው የመሪነት ኃላፊነቶች አንዱ ነው።

በ. የቤተ ክርስቲያንን ሥራዎች ማስተዳደር፡-

በባህላችን ሽማግሌዎች ቤተ ክርስቲያንን በማስተዳደር በኩል ቀዳሚውን ሚና መጫወት አለባቸው ብለን እናስባለን። በአዲስ ኪዳን ሐዋርያት የአስተዳደር ሥራዎችን ለማከናወን የዲያቆናትን ዓይነት አገልግሎት እንደ ጀመሩ እንመለከታለን። ሐዋርያት ሥራችን መጸለይና የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት ነው የሚል አቋም ነበራቸው። ከላይ የተጠቀሱት 9 ሚናዎች በእግዚአብሔር ዓይኖች ሽማግሌዎች ሊያከናውኑ የሚገባቸው ናቸው። ይሁን እንጂ፣ ሽማግሌዎች በአስተዳደራዊ ሥራዎች መሰማራታቸው ስሕተት አይደለም። ይህ አንድ ሰው ሊያከናውነው የሚገባው ተግባር ነው። ነገር ግን ሽማግሌዎች አብዛኛውን ጊዜያቸውን ለአስተዳደራዊ ጉዳዮች ከሰጡ፣ ለማስተማር፣ ለጸሎትና የእግዚአብሔርን ሕዝብ በእረኝነት ለማገልገል የሚያስችል ጊዜ አይኖራቸውም። ይህ ደግሞ የተሰየ መዋቅር ማዘጋጀትን ይጠይቃል። ሽማግሌዎች

በአስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ በማተኮራቸው ምክንያት የማስተማርና የእረኝነት አገልግሎት ከተስተጓጎለ፣ ሰይጣን መሪዎች ከዋናዎቹ ይልቅ በአነስተኛዎቹ ጉዳዮች ላይ እንዲያተኩሩ ሊያደርግ ይችላል። አብያተ ክርስቲያናት የአዲስ ኪዳንን ምሳሌነት ተከትለው አስተዳደራዊ ጉዳዮችን ለዲያቆናት ቢሰጡ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

44ኛ ጥያቄ፡- ከላይ የተጠቀሱትን የሽማግሌዎችን አገልግሎቶች ከልስ። ሀ) ለአንድ አዲስ ሽማግሌ የሚያከናውናቸውን አገልግሎቶች የምታብራራ ብትሆን፣ ምን ትለዋለህ? ለ) እነዚህ ኃላፊነቶች ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው አገልግሎቱን እንዴት እንዲያደራጅ ትነግረዋለህ?

## አራተኛ ቀን

45ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ቤተ ክርስቲያናችሁ መጋቢ አላት? ለ) ከሆነ፣ አገልግሎቶቹ ምን ምንድን ናቸው? ሐ) ከቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ጋር ያለው ግንኙነት ምንድን ነው? በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚታየው በሽማግሌዎች እንደ ተቀጠረ አገልጋይ ነው ወይስ ከሽማግሌዎች እንደ አንዱ? ሐ) የሙሉ ጊዜ መጋቢ መኖሩ ለቤተ ክርስቲያን ምን ምን ጥቅሞችን ያስገኛል? መ) የሙሉ ጊዜ መጋቢ ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት አንዳንድ ድክመቶች ምን ምንድን ናቸው? ሠ) ምእመናን በመንፈሳዊ ብስለታቸው እንዲያድጉ ለማስቻል መጋቢ በምን በምን አገልግሎቶች ላይ ትኩረት ማድረግ አለበት?

## የመጋቢ አገልግሎቶች

የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መጋቢዎችን አይጠቀሙም ነበር። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በየአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናቱ የሙሉ ጊዜ መጋቢዎች በመሥራት ላይ ይገኛሉ። ስለሆነም፣ የትኛው ዓይነት የመጋቢ አገልግሎት ግንዛቤ ለቤተ ክርስቲያናችን ጠቃሚ ይሆናል? የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ ከውሳኔ መድረስ የሚያስፈልገው አሁን ነው። ትልቁ ጥያቄ፣ «መጋቢ ሊኖረን ይገባል ወይ?» የሚለው አይደለም። ትልቁ ጥያቄ፣ «ቤተ ክርስቲያን ወደ መንፈሳዊ ብስለት እንድታድግ የሚያግዙትን አገልግሎቶች እንዴት ልናካሂድ እንችላለን?» የሚለው ነው። ይህን ጥያቄ ለመመለስ መጋቢዎችን መጠቀም አንደኛው መንገድ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን መጋቢዎችን



ለአገልግሎት መሾም ከመቅጽበት ምእመናን በመንፈሳዊ ብስለት እንዲያድጉ ላያደርግ ይችላል። ከዚህ በታች አንድ መጋቢ ሊያከናውናቸው የሚገቡ ተግባራት ተዘርዝረዋል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የመጋቢዎችን አገልግሎቶች በሚመለከት በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ቢሰጡ መልካም ነው፡-

1. ስለ መጋቢ አገልግሎት ጤናማ ያልሆነ ግንዛቤ በሚኖርበት ጊዜ የሚፈጠሩ አደገኛ ሁኔታዎች። በኢትዮጵያ ብዙ አብያተ ክርስቲናት የመጋቢ አገልግሎት ምን እንደ ሆነ በሚገባ አያውቁም። ነገር ግን ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ሙሉ ጊዜውን ሰጥቶ የሚያገለግል መጋቢ እንዲኖራቸው ይፈልጋሉ። ይሁን እንጂ፣ አብያተ ክርስቲያናት መጋቢዎችን ከመቅጠራቸው በፊት ስለ አገልግሎቱ በጥንቃቄ ቢያስቡ መልካም ነው። ሙሉ ጊዜውን ሰጥቶ ምእመናንን የሚንከባከብና የሚያስተምር አገልጋይ መመደቡ አስፈላጊ ቢሆንም፣ ልንጠነቀቅባቸው የሚገቡን አንዳንድ ነገሮች አሉ።

አንደኛ፣ ለመጋቢው ብዙ ሥልጣንና ክብር የመስጠት አደጋ። በታሪክ ሁሉ አብያተ ክርስቲያናት የተወሰኑ አገልጋዮችን ልዩና ቅዱስ አድርገው የተመለከቱባቸው ሁኔታዎች ነበሩ። አንዳንድ መጋቢዎች የአገልግሎትና የመሪነት እውቀት ያላቸው ራሳቸው ብቻ እንደ ሆኑ ያስባሉ። ተጠሪነታቸው ለሽማግሌዎች ሳይሆን፣ ለእግዚአብሔር እንደ ሆነ ያስባሉ። እንዲህ ዓይነት ሰዎች በቀላሉ የቤተ ክርስቲያን «ነገሥታት» ሊሆኑ ይችላሉ። ከዚህ የሚከፋው ደግሞ፣ ምእመናን እነዚህን መጋቢዎች «የቤተ ክርስቲያን ራስ» እና የችግሮች ሁሉ መፍቻ ቁልፎች አድርገው መመልከታቸው ነው። ይህንን ስፍራ መያዝ ያለበት ግን ክርስቶስ ብቻ ነው።

ሁለተኛ፣ ሽማግሌዎች መጋቢውን ቅጥር ሠራተኛ አድርገው ሊመለከቱ ይችላሉ። አንዳንድ ሽማግሌዎች የራሳቸውን ሥልጣን ለመጠበቅ ስለሚፈልጉ፣ መጋቢው ሥልጠናውንና መንፈሳዊ ስጦታዎቹን በብቃት እንዲጠቀም አያደርጉትም። መጋቢው ምእመናንን ወደ መንፈሳዊ ብስለት ለመውሰድ የሚያስችል እውቀት ቢኖረውም፣ ሽማግሌዎች ሀሳቡን አይቀበሉም።

«እንድታደርግ የምንፈልገው አዳዲስ አማኞችን እንድታስተምርና ምእመናን በሚጣሉበት ጊዜ እንድታስታርቅ ብቻ ነው። የቀረው የእኛ ሥራ ነው፣» ይሉታል። እንዲህ ዓይነቱ አመለካከት እግዚአብሔር ለግለሰቡ የለጣቸውን መንፈሳዊ ስጦታዎችና ሥልጠና የሚያንቋሽሽ ነው። ይህ የግለሰቡን ሥልጠና የሚያባክን ነው። ምክንያቱም ሽማግሌዎች እኛው ብቻ ነን ጥሩ ውሳኔ መስጠት የምንችል ብለው ያስባሉ። አንድ መጋቢ እንደ ቅጥር ሠራተኛ በሚሆንበት ጊዜ፣ ስጦታዎቹንና ሥልጠናውን ተጠቅሞ በቤተ ክርስቲያን ላይ ለውጥ ሊያመጣ አይችልም። አገልግሎቱን የሚመለከተው እንደ ቅጥር ሥራ ስለሆነ፣ የፈጠራ ችሎታውን ተ ጠቅሞ ጥሩ ዕቅዶችን ሊያወጣ ወይም ሕዝቡን በእረኝነት ለማገልገል ረዥም ሰዓት ሊሠራ አይችልም። ከዚህ ይልቅ፣ በተቻ ለ መጠን ብዙ ገንዘብ አያገኝ ትንሽ አገልግሎት ብቻ የሚያበ ረክትበትን መንገድ ይፈልጋል።

ሦስተኛ፣ ሽማግሌዎች ውሳኔዎችን ብቻ መስጠት እንዳለባቸውና መጋቢው ሁሉንም ተግባር ማከናወን እንዳለበት ሊያስቡ ይችላሉ። መጋቢውን በሚቀጥሩበት ጊዜ፣ «አሁን ችግራችን ሁሉ ተቀርፏል። መጋቢው ለምእመናን የእረኝነትና የማስተማር አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል። እኛ በየወሩ እየተሰባሰብን ጥሩ ሥራ እያከናወነ መሆኑን ማረጋገጥ ብቻ ነው የሚኖርብን፣» የሚል ግንዛቤ ሊይዙ ይችላሉ። ሰባት ወይም ዘጠኝ ሽማግሌዎች እያንዳንዱን አማኝ በግል በማወቅ ወደ መንፈሳዊ ብስለት ለመምራት የሚቸገሩ ከሆነ፣ አንድ መጋቢ ምንም ያህል ጊዜ ቢሠራ ይህን ሁሉ ተግባር ሊወጣ እንደማይችል ግልጽ ነው። የቤተ ክርስቲያን አመራር ግብ እያንዳንዱን አማኝ በእረኝነት ማገልገል ነው። መጋቢው በዚህ በኩል ቁልፍ ሚና መጫወት አለበት። ነገር ግን ይህንን እውን ለማድረግ የብዙ ሰዎች ድጋፍ ወሳኝ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ሽማግሌዎች እረኞች እንዲሆኑ ያዝዛል። ስለዚህ፣ ሁሉንም የእረኝነት ተግባር ለመጋቢው ብቻ የምንሰጥ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ያዘዘንን ነገር እለመታዘዛችን ነው። መጋቢ መቅጠር የቤተ ክርስቲያኒቱን የእረኝነት ችግር ሙሉ በሙሉ አይቀርፍም።



አራተኛ፣ መጋቢ በሚኖርበት ጊዜ፣ ምእመናን ሁሉን ሥራ እርሱ እንዲያከናውን በመጠበቅ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ከመሳተፍ ይቆጠባሉ። ይህም መንፈሳዊ ስጦታቸውን እንዳይጠቀሙ ያደርጋል። በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ የማይሳተፉ ከሆነ፣ ምእመናን በመንፈሳዊ ብስለት ሊያድጉ አይችሉም።

ለዚህ ነው «መጋቢው ችግራችንን ሁሉ ይቀርፋል» የሚለው አሳብ እውን የማይሆነው። አንድ ሰው ቤተ ክርስቲያንን በእረኝነት ለማገልገል የሚያስፈልጉትን ስጦታዎች ሁሉ ይዞ አይገኝም። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንዳንድ ሰዎች ከሌሎች ጋር በቅርበት በመሥራት ችግር የደረሰባቸውን የማበረታታትና በሕይወታቸው እንዲያድጉ የማገዝ ስጦታ አላቸው። እነዚህ መልካም እረኞች ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቃል የማስተ ማር ብቃት ያላቸው ደግሞ አሉ። በአመዛኙ አንድ ሰው እነዚህን ሁለት ስጦታዎች ይዞ አይገኝም። ስለዚህ፣ ብዙውን ጊዜ መጋቢው በእረኝነቱ ጎበዝ ሊሆንና በማስተማሩ ደካም ሊል፣ ወይም ደግሞ ጥሩ አስተማሪ ሆኖ ሳለ፣ በእረኝነት አገልግሎት ደክም ሊል ይችላል። ነገር ግን ሌሎች መንፈሳዊ ስጦታዎች ያሏቸው ሰዎች አብረውት በሚሠሩበት ጊዜ፣ የእነርሱ ጥንካሬ ድክመቱን ይሸፍናል። ስለሆነም፣ ቤተ ክርስቲያን መደራጀት ያለባት የእያንዳንዱን አማኝ መንፈሳዊ እድገት ለማፋጠን እገዛ በሚሰጥበትና ስምእመናን ጥልቅ የእግዚአብሔር ቃል ትምህርት በሚሰጥበት መንገድ መሆን አለበት። መጋቢው በራሱ እነዚህን ሁሉ በብቃት ሊወጣ ስለማይችል፣ ሽማግሌዎች በሁለተኛው ቀን ትምህርት ውስጥ እንደተጠቀሰው፣ እነዚህን ሁሉ ፍላጎቶች ለማሟላት በጥንቃቄ ማቀድ አለባቸው።

46ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ቤተ ክርስቲያናችሁ መጋቢ አላት? ከሆነ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚያከናውናቸው ተግባራት ምን ምንድን ናቸው? ለ) አንዳንድ ሰዎች ከመጋቢው የሚጠብቋቸው የተሳሳቱ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?

**2. የመጋቢው የተወሰኑ ተግባራት፡-**

ሀ. በአዲስ ኪዳን ውስጥ መጋቢው ከሽማግሌዎች አንዱ ይመስላል:: በ1ኛ ጢሞቴዎስ 5:17-18 በማስተማር የሚተጉ ሽማግሌዎች ልዩ ክብርና ደመወዝ ሊከፈላቸው እንደሚገባ ተ መልክቷል:: ስለዚህ፣ በኤፌሶን 4:11 የተጠቀሰው መጋቢ/አስተማሪ ይህ አስተማሪ ሽማግሌ ይመስላል:: በመሆኑም፣ መጋቢውን እንደ ቅጥር ሠራተኛ ከመመልከት ይልቅ፣ አዲስ ኪዳን መጋቢ ሙሉ ጊዜውን ለአገልግሎት በመስጠቱ ምክንያት ደመወዝ እንደሚከፈለው ሽማግሌ አድርጎ ይገልጻል::

ለ. መጋቢ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊያከናውን የሚገባቸውን ተግባራት በሙሉ መዘርዘሩ በሁለት ምክንያቶች አስቸጋሪ ነው:: አንደኛ፣ እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን መጋቢዋ እንዲያከናውን የምትፈልጋቸውን ልዩ ልዩ አገልግሎቶች የማዘጋጀት ነጻነት አላት:: በዚህ ትምህርት ሁለተኛ ቀን ውስጥ የተዘረዘሩትን ተግባራት በሚመድቡበት ጊዜ፣ ተግባሮቹ ከቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ:: ሁለተኛ፣ እግዚአብሔር ለተለያዩ ሰዎች የተለያዩ ስጦታዎችን ይሰጣል:: ስለዚህ፣ አንደኛው መጋቢ የሚችለውን ነገር ሌላኛው መጋቢ አይችለውም ይሆናል:: ለምሳሌ፣ አንደኛው መጋቢ ለሕዝብ የማስተማር/የመስበክ አገልግሎት ሊሰጥና አማኞችን በግል በማማከርና በመርዳት ረገድ እምብዛም ስጦታ ላይኖረው ይችላል:: ይህ እንግዲህ አንድን ሰው ቀደም ሲል በተወሰነ ኃላፊነት ላይ ማስቀመጥ እንደሌለብን የሚያሳይ ነው:: ከዚህ ይልቅ፣ የመጋቢውን ደካማና ጠንካራ ጎኖች በመገምገም፣ እርሱ የማይችላቸውን ነገሮች ሌሎች ሰዎች እንዲያከናውኑ ማድረጉ ጠቃሚ ነው::

ሐ. መጋቢው በተቻለ አቅም ብዙ ምእመናንን በግል ለማወቅ መጣር ይኖርበታል:: ይህ ማለት ወደ ቤታቸው በመሄድ ምእመናንን መጎብኘት፣ ስማቸውን፣ የልጆቻቸውን ስሞች ማጥናት አለበት ማለት ነው:: ይህ ሰዎች መጋቢው ያስብልናል የሚል ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያደርጋል:: መንፈሳዊ ሁኔታቸውን፣ ልማዳቸውን፣ ለፈተና ሊጋለጡ የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች፣



እንዴት በሕይወታቸው እያደጉ እንደ ሆነ፣ ወዘተ . . . ማወቅ ይኖርበታል:: ከዚያ በኋላ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የሚያድጉባቸውን ዘዴዎች ይቀይሳል:: አንድ ሐኪም ብዙ ሰዎችን በአንድ ላይ ሊያክም አይችልም:: መጋቢውም ምእመናንን በአንድነት ለመርዳት ከመሞከር ይልቅ፣ እያንዳንዱን ሰው በመነጠል ከግሉ ሁኔታው ጋር የሚዛመዱ ድጋፎችን መስጠት ይኖርበታል:: ጳውሎስ «ከቤት ወደ ቤት» እየሄደ ያስተምር ነበር (የሐዋ. 20:20):: ይህ ለአማኞች በግለሰብ ደረጃ እንክብካቤ ማድ ረጉን የሚያሳይ ነው:

ይሁን እንጂ፣ ብዙ ሕዝብ ባለባቸው ትላልቅ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ለእያንዳንዱ አማኝ እንክብካቤ ማድረግ ቀላል ነገር አይደለም:: ስለሆነም፣ አንድ መጋቢና ጥቂት ሽማግሌዎች ባሉባቸው አብያተ ክርስያቲያናት ለእያንዳንዱ አማኝ እንክብካቤ ለማድረግ እንዲቻል በሳል አማኞችን መጠቀም የሚቻልበትን ዕቅድ ማውጣቱ ጠቃሚ ነው::

> 47ኛ ጥያቄ:- ሀ) መጋቢው ወይም ሽማግሌዎች የቤተ ክርስቲያናችሁን አባላት በግል ደረጃ በሚገባ የሚያውቋቸው ይመስልሃል? ካልሆነ፣ ለምን? ለ) ሕዝቡን በጥንቃቄ በእረኝነት እያገለገሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ መጋቢውና ሽማግሌዎች ምን ሊያደርጉ ይገባል?

መ. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወንጌላዊ ከሌለ፣ መጋቢው ወደ ማኅበረሰቡ ጎራ በማለት ስለ ክርስቶስ መመስከር አለበት:: መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥተው እንዲድኑ ከመጠበቅ ይልቅ፣ ወንጌሉን እንድንወስድላቸው ያዝዘናል:: ስለዚህ፣ መጋቢው ወዳልዳኑት ሰዎች ቤት በመሄድ ሊጎበኛቸው ይገባል:: ወንጌሉንም በገርነትና በጥልቀት ሊያብራራላቸው ይገባል:

ሠ. በኃጢአት የወደቁ ሰዎች ካሉ፣ መጋቢው ሊጎበኛቸው ይገባል:: ይህም ወደ ንስሐና ለክርስቶስ ወደ መታዘዝ ይመልሳቸዋል:: ንስሐ ለመግባት ካልፈለጉ፣ በማቴዎስ 18:15-17 የተጠቀሱትን ደረጃዎች ካሟላ በኋላ ከሽማግሌዎች ጋር በመተባበር የቅጣት ሥነ-ሥርዓት መስጠቱ አስፈላጊ ይሆናል::

ረ. የታመሙትን መጠየቅ ነ ነበት። በያዕቆብ 5:14-16 የተ ስጡትን መመሪያዎች በመጠቀም ስታመሙት መጸለይ ይኖርበታል። ስሥጋዊ ሕመማቸው መጸለይ ብቻ ሳይሆን፣ በሽተኞች እግዚአብሔር ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ባሕርያቸውን እንዲቀርጽ እንዲጸልዩ ሊያበረታቱቸው ይገባል።

ስ. ወደ ቤተ ክርስቲያን ስሚመጡ ልጆችና አዳዲስ አማኞች የደቀ መዝሙርነትን ትምህርት መስጠት ይጠበቅበታል። ይህንን በግሉ ስማከናወን ሊቸገር ቢችልም፣ ሥራው እየተከናወነ መሆኑን ማረጋገጥ አስበት። በዚህ እጅግ አስፈላጊ በሆነው የደቀ መዝሙርነት አገልግሎት ላይ ይስማሩ ዘንድ ሌሎች ሰዎችን ሊያሠስጥን ይችላል። የክርስቲያኖች ልጆች ወላጆቻቸው ክርስቲያኖች በመሆናቸው ምክንያት ያስ ጥያቄ ክርስቲያኖች ሆነናል የሚል አቋም ከመያዝ ይልቅ፣ በግላቸው በኢየሱስ ሊያምኑና እንዴት እንደሚከተሉት ሊማሩ ይገባል።

ሸ. መጋቢው ስቤተ ክርስቲያን የማስተማር ወይም የስብከት ፕሮግራም ዕቅድ ማውጣት አስበት። ስስንበት እምልኮ ልዩ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል። የተሰያዩ ብዙ ሰዎች ስስሚያውቋቸው ጉዳዮች ትምህርት እንዲስጡ የማድረግ ልምድ አስን። ይህ ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወጥነቱን የጠበቀ ትምህርት እንዳይኖር ያደርጋል። ከሚያስተምሩት ሰዎች አብዛኞቹ በቂ የእግዚአብሔር ቃል እውቀት ስስሌላቸው፣ የሚያስተምሩት ነገር ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር አይጣጣምም። ሁሉም ምእመናን የእግዚአብሔርን ቃል ስመማር የሚሰባሰቡበት አንድ ቀን ቢኖር እሑድ ጠዋት ነው። ምንም ያህል ጥረት ብናደርግ፣ አብዛኞቹ አማኞች ወደ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ፕሮግራሞች አይመጡም። እንዲህ ከሆነ እንግዲህ እሑድን በመጠቀም ስእግዚአብሔር ሕዝብ የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ ማስተማር አስብን ማስት ነው። ጳውሎስ ስኤፌሶን ሽማግሌዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ በሙሉ እንዳስተማረ ተናግሯል (የሐዋ. 20:27)። እኛ በእብያተ ክርስቲያኖቻችን ይህንን ልንል እንችላስን? አይመስልም። ብዙውን ጊዜ ስሕዝብ የእግዚአብሔርን ቃል ሰማስተማር የሚያስችል ሥልጣና ያገኘው



መጋቢው ነው። መጋቢው በየእሑዱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስስሚገኝ፣ ወጥነት ባስው መንገድ በማስተማር የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ ስምእመናን ሊያሳውቅ ይችላል። መጋቢው አብዛኞቹን ስብከቶች ቢሰብክ ሳምእመናን መንፈሳዊ ሕይወት እድገት የተሻለ አስተዋጾኦ ይኖረው ይሆን? ሽማግሌዎችና ተጋባዥ ሰዎች አልፎ አልፎ ሊሰብኩ ቢችሉም፣ በየእሑዱ መጋቢው ስምእመናን ብቃት ያስው የማስተማር አገልግሎት ቢሰጥ የተሻለ ይሆናል። (ማስታወሻ:- ይህ መጋቢዎች ራሳቸው ከአንዱ ወደ ሌላው ቤተ ክርስቲያን ሳይዞሩ በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ እግዚአብሔር የሰጣቸውን መንጋ መመገብ እንዳለባቸው የሚያሳይ ነው።) የመጋቢውና የመሪዎች ግብ ሰዎችን በክርስቶስ በሳል ማድረግ ነው። ይህ እውን ሊሆን የሚችስው ሰስዎች የእግዚአብሔርን ቃል በግልጽ ስናስተምር ነው። ስሜት ቀስቃሽ ስብከቶች ሰዎችን ደስ ሊያሰኙ ቢችሉም፣ ከፍተኛ መንፈሳዊ እድገት የማምጣት ብቃት የላቸውም። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቃል በግልጽ መስበክ ሕይወትን ይሰውጣል።

ቀ. መጋቢው ሌሎች ሰዎች በብቃት እንዲያገለግሉ ማሠልጠን አስበት። ሰዎች ሳልዳኑት እንዴት ውጤታማ ምስክርነት እንደሚሰጡ ማስተማር ይኖርበታል። ወንጌልን የሚመሰክረው መጋቢው ብቻ ከሆነ፣ ብዙ ሰዎች ስለ ክርስቶስ ሊሰሙ አይችሉም። ነገር ግን ብዙ ምእመናን በትጋት የሚመሰክሩ ከሆነ፣ ብዙ ሰዎች ወንጌሉን የመስማት ዕድል ይኖራቸዋል። መጋቢው ከችግሮቻቸው ጋር የሚታገሉትን ሰዎች የሚመክሩትን ሰዎች ሊያሠስጥን ይችላል። ይህ ምእመናን እርስ በርሳቸው የሚረዳዱበትን መንገድ ያመቻቻል። እንዲሁም ደግሞ መጋቢው ሰዎች እንዴት እንደሚያስተምሩ፣ በኃይል እንዴት እንደሚሰብኩ፣ ወዘተ. . . የተሰያዩ ሰዎችን ሊያሠስጥን ይችላል። መጋቢው ምእመናን መንፈሳዊ ስጦታቸውን እንዲጠቀሙ በይበልጥ በሚያሠስጥንበት ጊዜ፣ በርካታ ሥራዎች ይከናወናሉ። ይህ ደግሞ የራሱን መንፈሳዊ ስጦታዎች ስመጠቀም ጊዜ እንዲኖረው ይረዳዋል።

48ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ መጋቢው እነዚህን ሁሉ ኃላፊነቶች እየተወጣ ነው? ካልሆነ፣ ለምን? ለ) ከእነዚህ አገልግሎቶች በቤተ ክርስቲያናችሁ ውብጥ የማይከናወኑት የትኞቹ ናቸው? ለምን? ሐ) አንድ ሰው በእነዚህ አገልግሎቶች ላይ ትኩረት ቢያደርግ፣ ምእመናን እንዴት በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ እንደሚያስችል ግለጽ።

**ዲያቆናት፡-**

የዲያቆናት አገልግሎት የተጀመረው በኢየሩሳሌም ውስጥ በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነበር። ይህ አገልግሎት ምናልባትም በብሉይ ኪዳን ሌዋውያን የቤተ መቅደሉን አምልኮ ዝርዝር ጉዳዮች በመፈጸም፣ ካህናት በማስተማርና በአምልኮ ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ከሚደረግበት ሁኔታ የተወሰደ ይሆናል። «ዲያቆን» የሚለው ቃል የተወሰደው ከግሪክ ቃል ሲሆን፣ የቤተ ሰቡን ፍላጎቶች የሚያሟሉትን የቤት ሠራተኞች የሚያመለክት ነው።

ቤተ ክርስቲያን ለመጀመሪያ ጊዜ ሰዎችን ለድቁና አገልግሎት የሾመችው በሐዋርያት 6፡1-7 ነው። (ማስታወሻ፡- የሐዋርያት ሥራ 6 እነዚህን ሰዎች ዲያቆናት ብሎ አይጠራቸውም። ነገር ግን ሐዋርያት እግዚአብሔር «የምግብ አገልጋዮች» እንድንሆን አልጠራንም ብለዋል። ይህ ዲያቆናት የሚል ፍች የሚሰጥ ሐረግ ነው። ስለሆነም፣ እነዚህን ሰዎች እንደ ዲያቆናት መመልከቱ ጠቃሚ ነው። በኋላ ጳውሎስ በመሠረታቸው ትላልቅ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ዲያቆናት የአገልግሎት ድርሻ እንዲኖራቸው ደንግጓል።) የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን በከፍተኛ ደረጃ በማደግ ሐዋርያት የጸሎትና የማስተማር አገልግሎት እየሰጡ ለድሆች ምግብ እንደ ማደል ያሉትን አስተዳደራዊ ሥራዎች ለማከናወን ተቸግረው ነበር። ችግሮች መፈጠር ሲጀምሩ፣ ምእመናን ሰባት ሰዎችን በመምረጥ የምግብ ስርጭቱን እንዲከታተሉ አደረጉ። ይህም ሐዋርያት በዋናው የመንፈሳዊ አመራር ተግባራቸው እንዲቀጥሉ የሚያስችል ተግባር ነበር።

በትላልቅ አብያተ ክርስቲያናት ጳውሎስ ሽማግሌዎችን ብቻ ሳይሆን ዲያቆናትንም የሾመ ይመስላል። (1ኛ ጢሞ. 3፡1-3ን



አንብብ።) ይሁን እንጂ፣ አነስተኛ አብያተ ክርስቲያናት ሽማግሌዎች ብቻ የነበሯቸው ይመስላል። ጳውሎስ የትልቅ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የነበረው ጢሞቴዎስ ሽማግሌዎችንና ዲያቆናትን እንዲሾም ጠይቋል። በአነስተኛ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያገለግል የነበረው ቲቶ ግን (1፡5-9) ሽማግሌዎችን እንዲሾም አዝዞታል። ዲያቆናት ግን በዚህ ክፍል አልተጠቀሱም።

የዲያቆናትና የሽማግሌዎች መስፈርቶች አንድ ዓይነት ናቸው። ሁለቱም መንፈሳዊና በገንዘብ አያያዛቸው ታማኞች መሆን ይጠበቅባቸዋል። ነገር ግን ሽማግሌዎች የማስተማር ችሎታ ሊኖራቸው ሲገባ፣ ይህ መስፈርት ለዲያቆናት አልተጠቀሰም። በገንዘብ ጉዳይ ላይ ትኩረት መስጠቱ፣ ዲያቆናት የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ እንዲያስተዳድሩ ስለ ተፈለገ ይመስላል።

አዲስ ኪዳን ዲያቆናት ምን ያደርጉ እንደ ነበረ በግልጽ አይነግረንም። የዲያቆናትን የአገልግሎት ፍንጭ የምናገኘው ከሐዋርያት ሥራ 6 ውስጥ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ሆነው በማገልገል ላይ የነበሩት ሐዋርያት በዝርዝር አስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ ለመሳተፍ አለመፈለጋቸውን እንመለከታለን። እነርሱ የፈለጉት በመንፈሳዊ አገልግሎት (በጸሎትና በማስተማር) መቀጠልን ነበር። የዲያቆናት አመራር የተጀመረው ሽማግሌዎችን በአስተዳደራዊ ሥራዎች ለማገዝ ነበር። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ቤተ ክርስቲያን እያደገች በመምጣቷ፣ ሽማግሌዎች የመንፈሳዊ አመራርና የማስተማር አገልግሎቱን ከአስተዳደራዊ ሥራዎች ጋር አጣምረው ለማካሄድ በማይችሉበት ጊዜ፣ አስተዳደራዊ ተግባራት ለማከናወን ዲያቆናት ይመረጡ የነበረ ይመስላል።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት ማገልገል እንዳለባቸው ከሐዋርያት ጠቃሚ ትምህርቶችን ማግኘት ይኖርባቸዋል። ቤተ ክርስቲያኖቻቸው እያደጉ ሲሄዱ፣ ሽማግሌዎች በአስተዳደራዊ ጉዳዮች ሲጠመዱና መንፈሳዊ አገልግሎት ለመስጠት የሚችሉበትን ጊዜ ሲያጡ ይችላሉ። ችግሩ ሽማግሌዎች ብዙውን ጊዜ በአስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ በማተኮር

መንፈሳዊ አገልግሎቱን ችላ ወደ ማለቱ ያዘነብላሉ። ይህ ግን ሐዋርያት የመረጡት ነገር ተቃራኒ ነው። ለአስተዳደራዊ ጉዳዮች ብለው መንፈሳዊ ሥራዎችን ቸል ማለት የሰባቸውም። ይበልጥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሚሆነው ሽማግሌዎች በመንፈሳዊ አገልግሎት (በማስተማር፣ በጸሎትና በማማከር) ላይ ቢያተኩሩና ዲያቆናት አስተዳደራዊ ጉዳዮችን እንዲያካሂዱ ቢተዉላቸው ነው። ሥራ ለሚበዛባቸው መሪዎች አዲስ ኪዳን የሚሰጠው መፍትሔ ዲያቆናት መባ በመሰብሰብ፣ ወንበሮችን በማስተካከል ወይም ለድሆች ገንዘብን በመስጠት ሳይወሰኑ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱን አስተ ዳደራዊ ሥራዎች እንዲያከናውኑና ሽማግሌዎች ደግሞ ለቤተ ክርስቲያኒቱ መንፈሳዊ እድገት ጠቃሚ የሚሆኑትን ተግባራት እንዲያከናውኑ ነው።

*49ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ዲያቆናት አብዛኞቹን አስተዳደራዊ ሥራዎች እንዲያከናውኑ የሚያደርገውን የአዲስ ኪዳን ምሳሌነት ብንከተል፣ ይህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ኃላፊነቶች እንዴት ይለውጣል? ለ) ይህ ሽማግሌዎች በይበልጥ በመንፈሳዊ አገልግሎት ላይ እንዲያተኩሩ ሊያደርግ የሚችለው እንዴት ነው?*

## ውስጣዊ ወንጌላዊ፡-

አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ከመጋቢ ይልቅ «ወንጌላዊ» የመቅጠር ልምድ አላቸው። ብዙውን ጊዜ እነዚህ ውስጣዊ ወንጌላውያን የመጋቢን አገልግሎት የሚያከናውኑ ናቸው። እዚህ ላይ የመጋቢንና የወንጌላዊን ሥራዎች ልዩነቶች መረዳቱ ጠቃሚ ነው። ልክ እንደ ፊልጶስ፣ ወንጌላዊ ያልዳኑትን ሰዎች ወደ ክርስቶስ በማምጣቱ ሥራ ላይ የሚያተኩር ነው (የሐዋ. 8)። መጋቢ ግን አማኞችን በእረኝነት በማገልገልና በብስለት እንዲያድጉ በመርዳት ላይ ያተኩራል። ወንጌላዊና መጋቢ መሆን ሁለት የተ ለያዩ መንፈሳዊ ስጦታዎችና የአገልግሎት ዓይነቶች ናቸው።

## የውስጥ ወንጌላዊ ሥራዎች፡-

1. ማኅበረሰቡን በወንጌል የመድረስን ሥራዎች የማስተባበር ኃላፊነት አለበት። እያንዳንዷ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ወንጌሉን



ላለችበት ማኅበረሰብ ማካፈል አለባት። ይህንን እውን ለማድረግ አብዛኛው ኃላፊነት የሚወድቀው በእያንዳንዱ አማኝ ላይ ቢሆንም፣ ወንጌላዊው ከአማኞች ጋር በመሆን የወንጌል ምስክርነቱን ሥራ ያስተባብራል።

2. አዳዲስ አማኞችን የማስተማር ተግባራትን ያካሂዳል። መጋቢው ለዚህ ሥራ ኃላፊነት ሊወስድ ቢችልም፣ በአብዛኛው አማኞችን በማስተማሩ ሥራ መጠመዱ የማይቀር ነው። በመሆኑም፣ ወንጌላዊ ክርስቶስን መከተልና እውነተኛ አማኝ መሆን ምን ማለት እንደ ሆነ ለአዳዲስ አማኞች ማስረዳት አለበት። ምናልባትም እነዚህ አዳዲስ አማኞች ጥምቀትን እስኪወስዱ ድረስ ወንጌላዊው ሊያስተምራቸው ይችላል። ከዚያ በኋላ ወደ ብስለት እንዲያድጉ መርዳት የመጋቢው ኃላፊነት ሊሆን ይችላል።

3. ምእመናን እንዴት በብቃት እንደሚመሰክሩ ማሠልጠን አለበት። ምእመናን የቤተ ክርስቲያናቸውን ትውፊት ብቻ ሳይሆን፣ እውነተኛው ወንጌል ምን እንደ ሆነ እንዲረዱ ሊያግዛቸው ይገባል። እያንዳንዱ አማኝ እምነቱን በትክክል መግለጽ መቻል አለበት።

4. ምእመናን ለሌላ እምነት ተከታዮች ወንጌሉን እንዲያካፍሉ ማሠልጠን አለበት። ክርስቲያኖች ለሁሉም ሰው እምነታቸውን በጨዋነት የሚያካፍሉበትን መንገድ ማወቅ አለባቸው። ጴጥሮስ እንደተናገረው፣ እያንዳንዳችን በክርስቶስ ስላለን ተስፋ በምንጠየቅበት ጊዜ መልስ መስጠት አለብን (1ኛ ጴጥ. 3፡15)።

5. የመናፍቃንንና የሌሎች ሃይማኖት ተከታዮችን ጥያቄዎች እንዲመልሱ ማሠልጠን። ይህ ወንጌላውያን የሌሎች ሃይማኖቶችን አስተምህሮዎች እንዲያውቁ የግድ ይላል። ከዚያም መጽሐፍ ቅዱስን በመጠቀም አማኞች እንዴት በፍቅርና በጸጋ እንደሚመልሱላቸው ያስተምራል።

6. ውስጣዊ ወንጌላዊ ማኅበረሰቡን ለመድረስ የሚያስችሉትን ስልቶች ይነድፋል። በእያንዳንዱ የእድሜ ክልል፣ ጎሳና የምጣኔ ሀብት ደረጃ ውስጥ የሚገኝ እያንዳንዱ ሰው ወንጌሉን መስማቱን

ይገመግማል። ይህንን ለማረጋገጥ ከምእመናን ጋር አብሮ ይሠራል።

| |
|---|
| 50ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ቤተ ክርስቲያናችሁ የውስጥ ወንጌላዊ አሳት? በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን ምን ተግባራትን ያከናውናል? ይህ ከላይ ከተዘ ረዘሩት ተግባራት ጋር የሚመሳሰለው ወይም የሚለያየው እንዴት ነው? ለ) ከላይ የተዘረዘሩት አምስት ነገሮች ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አስፈላጊ የሚሆኑት እንዴት ነው? |

## የሴቶችና የወጣቶች መሪዎች፡-

አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ማኅበረ ምእመኖቻቸውን በመከፋፈላቸው ወጣቶችና ሴቶች በልዩ ቡድኖች ይደራጃሉ። በአዲስ ኪዳን ውስጥ እንዲህ ዓይነት ክፍፍሎች ስላልነበሩ፣ ምሳሌ ዎችን ማግኘት አይቻልም። ዛሬ እነዚህ ቡድኖች የተፈጠሩት ለሴቶችና ወጣቶች ተጨማሪ ትኩረት ለመስጠት ሲባል ነው። አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወንዶች በመሆናቸውና አገልጋዮቹም እንዲሁ በወንዶች የሚከናወኑ በመሆናቸው፣ የሴቶች ቡድኖች የተመሠረቱት ሴቶች ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኙ በማሰብ ነው። እንደዚሁም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አብዛኞቹ አገልግሎቶች በአዋቂዎች ላይ የሚያተኩሩ ናቸው። ነገር ግን ወደ ቤተ ክርስቲያን ከሚመጡት ሰዎች አብዛኞቹ ወጣቶች ናቸው። አብዛኞቹ ክርስቲያኖች በክርስቶስ የሚያምኑት በወጣትነት ጊዜ ያቸው ነው። ስለዚህ፣ ለወጣቶች ልዩ ትኩረት መስጠቱ አስፈላጊ ይሆናል።

የሴቶችና የወጣቶች መሪዎች የድርጅታቸውን ዓላማዎች ጠንቅቀው ሊያውቁ ይገባል። ትልቁ ዓላማ የሴቶች ወይም የወጣቶች ቡድን መመሥረት አይደለም። ብዙ ጊዜ አብያተ ክርስቲያናት የወጣቶች ወይም የሴቶች ማኅበር መሥርተናል ብለው ይመካሉ። ነገር ግን የማኅበር አባል መሆን ምንም ለውጥ ላያመጣ ይችላል። ሰዎች እግዚአብሔርን በበለጠ እንዲያውቁት እያደርግም። እያንዳንዱ ቡድን ወንጌሉን እንዲያዳርስም አይ ረዳውም። ሴቶች ሌሎች ሴቶችን ለክርስቶስ አይማርኩም።



ወጣቶችም በአካባቢያቸው ላሉት ወጣቶች የወንጌል ስርጭት ፕሮግራም አይቀይሱም። እንዲያውም፣ ሰይጣን እነዚህ ቡድኖች ከሽማግሌዎች ጋር ግጭት እንዲፈጥሩ ሊያደርግ ይችላል። ወጣቶች ለቤተ ክርስቲያን አጠቃላይ ወጪ አስተዋጽኦ ሳለማድረግ ሊሉ፣ «አሥራት የምለጠው ለራሴ ማኅበር ነው» የሚል አሳብ ይዘው ይገኛሉ። እንዲህ ዓይነቱ መንፈስ ቤተ ክርስቲያን ውጤ ታማ አገልግሎት እንድትሰጥ ከማድረግ ይልቅ ክፍፍል እንዲፈጠር ያደርገል።

የሴቶችና የወጣቶች ማኅበራት ለሽማግሌዎችና ለመጋቢው አጋዦች ሆነው መሥራት አለባቸው። ከመጋቢውና ከሽማግሌዎቹ አገልጋዮች እንዳንዶቹን በመካፈል ምእመናን በመንፈሳዊ ብስለት እንዲያድጉ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። የእያንዳንዱ ማኅበር ዋና ዓላማ የቡድናቸው አባላት በመንፈሳዊ ብስለትና በውጤታማ አገልግሎት እንዲያድጉ ማስቻል ነው። የሴቶች መሪ ዎች ሽማግሌዎችና መጋቢው ሴቶች በመንፈሳዊ አገልግሎት እንዲያድጉ ያበረታቷቸው ዘንድ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችላሉ። የወጣቶች መሪዎች ሽማግሌዎች ወጣቶችን ለአገልግሎት እንዲያነቃንቁ እገዛ ሊያደርጉ ይችላሉ።

ሴቶች ትኩረት ሊያደርጉባቸው የሚገቧቸው ልዩ ጉዳዮች አሏቸው። (ለምሳሌ፣ የቤት አመቤትነት፣ የሥራና የአገልግሎት ጊዜያቸውን እንዴት ሚዛናዊ እንደሚያደርጉ።) ሌሎች ሴቶችን በወንጌል ለመድረስ ከፍተኛ እገዛ ሊያደርጉ የሚችሉት ሴቶች ናቸው። በብዙ አገሮች በጸሎትና ለውጭ ወንጌላውያን ገንዘብ በመስጠት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርጉት የሴቶች ማኅበራት ናቸው። ወጣቶችም የተለዩ ፍላጎቶች አሏቸው። ለምሳሌ ያህል፣ ወጣት ወንዶችና ሴቶች በአንድነት ተሰባስበው በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የሚያድጉባቸውን እጋጣሚዎች ሊያመቻቹ ይችላሉ፣ ነገር ግን ይህ በዓለም ውስጥ ያሉትን እደገኛ ልምምዶች እንዲያደርጉ የሚገፋፋቸው ሊሆን አይገባም። (ለምሳሌ፣ ለዓለማዊ ፊልሞች እንዳይጋለጡ ማድረግ።) በተጨማሪም ወጣቶች ወንጌሉን ለማስፋፋቱ ተግባር ሊውል የሚችል ትልቅ ጉልበት አላቸው። ወጣቶች ሌሎች ወጣቶችን በወንጌል ለመድረስ ምርጥ መሣሪያዎች

ናቸው:: እነዚህ ልዩ መሪዎች ምእመናን በመንፈሳዊ ብስለትና በወንጌል ስርጭት እንዲያድጉ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችላሉ::

51ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በቤተ ክርስቲያናችሁ የሴቶችና የወጣቶች ማኅበራት አሉ? ካሉ፣ ዓላማቸው ምንድን ነው? ለ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የእነዚህ መሪዎች ተግባር ምንድን ነው? ሐ) የሴቶችና የወጣቶች መሪ ዎች ሽማግሌዎች ምእመናንን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ለማሳደግና ለማኅበረሰቡ ወንጌል የማዳረስ ተግባራቸውን እንዲያከናውኑ በማድረግ በኩል አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉት እንዴት ነው?

## የመዘምራን አባላት

መሪዎች በሌሎች ሰዎች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ናቸው ብለናል:: ይህ ማለት ዛሬ ካሉን ኃይለኛ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል የመዘምራን አባላት ይገኙበታል ማለት ነው:: ስለሆነም፣ የመዘምራን አባላት የሚያከናውኗቸውን ተግባራት (ለምሳሌ፣ በጸሎት ጊዜ መንቀጥቀጥ፣ «ሃሌሉያ» ማለት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶችን ማካሄድ፣ ወዘተ. . .) ወጣቶችም ያከናውናሉ:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መዘምራን በወጣቶች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ እንደሚችሉ በመረዳት አዎንታዊ የመንፈሳዊነት ምሳሌ ዎች እንዲሆኑ ማስቻል አለባቸው:: ስለ መዘምራን የሚከተሉትን ነገሮች ማስታወስ አለብን፡-

1. በመልካምም ሆነ በመጥፎ ጎኑ ለወጣቶች ጠንካራ ተጽዕኖ ስለሚፈጥሩ፣ የመዘምራን አባላትን በጥንቃቄ መምረጡ አስፈላጊ ነው:: የመዘመር ስጦታ ብቻ ሳይሆን፣ መንፈሳዊ ብስለትም ሊኖራቸው ይገባል:: መዘመር መንፈሳዊነታቸውን የሚያሳዩበት ስፍራ ሳይሆን፣ የአገልግሎት በር መሆኑን መረዳት አለባቸው:: ኢየሱስ ከልጆቹ አንዱን ማሰናከል ከፍተኛ ቅጣት እንደሚያስከትል ተናግሯል:: እግዚአብሔር ወደ ቤተ ክርስቲያን ለሚያመጡት ማንኛውም ዓይነት ጤናማ ያልሆነ ልምምድ ወይም ኢየሱስን ስለ መከተል መጥፎ ምሳሌዎች ለመሆናቸው ተጠያቂ እንደሚያደርጋቸው መረዳት አለባቸው::



2. የመዘምራን ቡድን አባላት መጸለይ ወይም መዘመር ብቻ ሳይሆን፣ በመደበኛነት የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት አለባቸው:: ጤናማ ባልሆኑ ልምምዶች እንዳያዘፈቁ የሚጠብቃቸው የእግዚአብሔር ቃል ነው:: የእግዚአብሔርን ቃል በበለጠ በሚ ረዱበት ጊዜ መዝሙሮቻቸውም በባለጠ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይሆናሉ::

3. የመዘምራን ቡድን አባላት ለሽማግሌዎች መታዘዝ አለባቸው:: እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያንን አመራር ለሽማግሌ ዎች እንጂ ለመዘምራን አልሰጠም:: ስለሆነም፣ ሽማግሌዎችን አለማዳመጥና አለመታዘዝ ማለት የቤተ ክርስቲያን ኃላፊዎች አድርጎ በሾማቸው በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ ነው:: ይህም ሽማግሌው ወይም የፕሮግራም መሪው መዘምራን አንድ መዝሙር ብቻ እንዲዘምሩ ቢጠይቃቸው፣ ሳያቅማሙ እሺ ማለትን ይጨምራል:: ሽማግሌዎች የመዘምራን አባላት የሚያሳዩአቸውን አንዳንድ ድርጊቶች (መጮህ፣ ወለል ላይ መውደቅ፣ ወዘተ. . .)፣ የስፒከሩን ወይም የሙዚቃውን ጩኸት የማይወዱ ከሆነ፣ ማስተካከል አለባቸው:: ሽማግሌዎችም በበኩላቸው የወጣቶችን ለየት ያለ ባህል በመረዳት አንዳንድ ፍላጎቶቻቸውን እንዲያሟሉ መፍቀድ አለባቸው:: በፍቅር መኖር ማለት ወጣቶች ሽማግሌዎችን፣ ሽማግሌዎች ደግሞ ወጣቶችን ለመረዳት ይሞክራሉ ማለት ነው:: አንዱም ሌላውን ያከብራል:: እግዚአብሔርን ልናስከብር የምንችለው በፍቅር አብረን ለመኖር ስንችል ብቻ ነው::

4. ቤተ ክርስቲያን መዘምራን በአምልኮ ውስጥ ያላቸውን ሚና ማጥናት አለባት:: መዘምራን ለአምልኮ ጠቃሚ መሣሪያዎች ናቸው:: ነገር ግን ሰይጣን ምእመናን በጋራ እንዳያመልኩ ሊያደርጋቸው ይችላል:: ለመጀመሪያ ጊዜ መዘምራን በቤተ መቅደስ ውስጥ አምልኮውን እንዲያካሂዱ ያደረገው ዳዊት ነበር (1ኛ ዜና 15:16):: ነገር ግን በምኩራቦችም ሆነ በአዲስ ኪዳን አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ መዘምራን አልነበሩም:: አዲስ ኪዳን ሁሉም አማኞች በጋራ በማምለክ ነጻነታቸው ላይ ትኩረት ያደርጋል (1ኛ ቆሮ. 14:26):: መዘምራን በአምልኮ ውስጥ

ስለሚኖራቸው ድርሻ የሚከተሉትን ነገሮች ማስታወሱ ጠቃሚ ነው።

ሀ. እግዚአብሔር ለአንዳንድ ሰዎች መዝሙር የመጻፍ፣ የመዘመርና የሙዚቃ መሣሪያዎችን የመጫወት ስጦታ ስጥቶአቸዋል። እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ስጦታ ያላቸውን ሰዎች በመጠቀም አምልኮዋን ለማሳደግ መጣር አለባት።

ለ. በታሪክ እግዚአብሔር ጠቃሚ እውነቶችን ለማስተማርና ሕዝቡን ለማበረታታት ሶሎ ዘማሪዎችንና መዘምራንን ሲጠቀም ኖሯል። ብዙውን ጊዜ መዝሙር ከሰብከት የበለጠ ለሕዝብ ጆሮ ቅርብ ነው። ስለሆነም፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መዘምራንን በጥበብና በውጤታማነት ለአገልግሎት ማስማራት አለባቸው። መዘምራን እዝማቾችን እየደጋገሙ በመዘመር የሰ ዎችን ስሜት ከማነሣሣት ይልቅ፣ በተመረጡ ቃላት እማካኝነት ምእመናን የእግዚአብሔርን እውነቶች እንዲያሰላስሉ ማድረግ አለባቸው። እውነተኛ እምልኮ እንዲኖር የሚዘምሩትም ሆነ የሚሰሙት ሰዎች የቃላቱን ትርጉም ማወቅ አለባቸው።

ሐ. ምእመናን ወደ ቤተ ክርስቲያን ከሚመጡባቸው ዐበይት ምክንያቶች አንዱ እግዚአብሔርን ለማምለክ ነው። ዋና ዓላማቸው ሌሎች ሲያመልኩ መስማት አይደለም። እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ከሰጣቸው የአምልኮ መሣሪያዎች አንዱ መዝሙር ነው። (በኤፌ. 5፡19 አማኞች በአንድነት መዘመራቸው የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ምልክት ተደርጎ ታይቷል።) መዘምራን የምእመናኑን የጋራ ዝማሬ ጊዜ መሻማት የለባቸውም። አንዳንድ ጊዜ መዘምራን ከአንድ ሰዓት በላይ ይዘምራሉ። ነገር ግን ምእመናን ለጥቂት ደቂቃዎች ብቻ በጋራ እየዘመሩ እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ ይደረጋል። ይህ አማኞች ሁሉ የእግዚአብሔር ካህናት መሆናቸውን ከሚናገረው የአዲስ ኪዳን ትምህርት ውጭ ነው። አምልኮ ምእመናን የሚተገብሩት እንጂ፣ የሚታዘቡት ነገር አይደለም።



5. ሽማግሌዎች ወጣቶች ሌሎች አገልግሎቶችንም ጭምር እንዲያከብሩ መርዳት አለባቸው። ብዙ ወጣቶች ሊሳተፉ የሚችሉበት ብቸኛው አገልግሎት መዘምራን ቡድን ውስጥ መግባት ብቻ ይመስላቸዋል። የመዘምራን አገልግሎት ጠቃሚ መሆኑ እሙን ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር ወጣቶች ልጆችን በማስተማር፣ ቤተ ክርስቲያንን በማጽዳት፣ ለሌሎች ወጣቶች በመመስከር፣ ወዘተ. . . እንዲያገለግሉ፣ ይፈልጋል። ጥቂት ወጣቶች ብቻ በመዘምራን ቡድን ውስጥ እያገለገሉ፣ አብዛኞቹ መንፈሳዊ ስጦታዎቻቸውን የማይጠቀሙባት ቤተ ክርስቲያን ጤናማና ሚዛናዊ አይደለችም።

> 52ኛ ጥያቄ፦ ሀ) እግዚአብሔር ጠቃሚ መንፈሳዊ እውነቶችን ለማስተ ማርና ምእመናን እርሱን እንዲያመልኩ ለማስቻል መዘምራንን የተ ጠቀመባቸውን መንገዶች ዘርዝር። ለ) መዘምራን ምእመናን በጋራ ከማምለክ ይልቅ አዳማጮች እንዲሆኑ ሊያደርጉ የሚችሉት እንዴት ነው? ሐ) ከመዘመር ውጭ ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊያከናውኑ የሚችሏቸው ሌሎች አገልግሎቶች ምን ምንድን ናቸው? ወጣቶች በእነዚህ መንገዶችም እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ ለማበረታታት ሽማግሌዎች ምን ሊያደርጉ ይችላሉ?

## አምስተኛ ቀን፦ ለሳምንታዊ ስብሰባ በመዘጋጀት የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስ።

## ሳምንታዊ ስብሰባ

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ሀ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ያሉትን የተለያዩ አስተ ዳደራዊ መዋቅሮች ግለጽ። ለ) የእያንዳንዱ ደረጃ ዓላማ ምንድን ነው? ሐ) አንድን መዋቅር ለመገምገም የሚያስችሉትን ሦስት መመዘኛዎች በመጠቀም እያንዳንዱን አስተዳደራዊ መዋቅር ገምግም። መ) እያንዳንዱ የመዋቅር ክፍል ምን ያህል ዓላማውን እያሳካ ነው? ሠ) ከእነዚህ መዋቅሮች ሰዎች ያልተረዷቸው የትኞቹ ናቸው? ረ) እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን መዋቅር እና

ማኅበር (የወጣቶች ማኅበር፣ የሴቶች ማኅበር፣ ወዘተ. . .) ግልጽ ዓላማ ሊኖረው የሚገባው ስምንድን ነው?

2. ሀ) መሪዎች በተለምዶ በቤተ ክርስቲያን መዋቅር ውስጥ ያላቸውን ሚና በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከተጠቀሰው ጋር አነጻጽር:: የሚመሳሉትና የሚለያዩት እንዴት ነው? ለ) የላይኞቹ አመራሮች ከታች ያሉትን አመራሮች በጥሩ ሁኔታ ቢመሩ፣ እንዴት ነገሮች ሊለወጡ እንደሚችሉ ግለጽ:: ሐ) አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ስለ ማዋቀር በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱትን አሳብ አንሥታችሁ ተወያዩ:: የመዋቅሩ አዎንታዊና አሉታዊ ገጽታዎች ምን ምንድን ናቸው? የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን መዋቅር የበለጠ ጠቃሚ ለማድረግ (እያንዳንዱን አማኝ በእረኝነት ለማገልገል) ምን ቢደረግ መልካም ይሆናል ትላለህ?

3. ጊዜው እየገፋ ሲሄድ፣ አብዛኞቹ ድርጅቶች ግትርና ትውፊታዊ እየሆኑ ይሄዳሉ:: ሀ) ይህ በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ሊከሰት የተመለከትከው እንዴት ነው? ለ) ምእመናን አሁን ከክርስቶስ ጋር ካላቸው ግንኙነት ይልቅ በቀድሞ ትውፊቶቻቸው ላይ ትኩረት በሚያደርጉበት ጊዜ የሚከሰቱት አሉታዊ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? ሐ) ረዥም ታሪክ ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች አዳዲስ ነገሮችን ለመቀበልና የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ ለመስማት ይችሉ ዘንድ ምን ማድረግ ይችላሉ?

4. ሀ) አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በብስለት እንድታድግ የሚያስፈልጉትን አገልግሎቶች ዘርዝር:: ለ) በዝርዝሩ ውስጥ መጨመር ያለባቸው ሌሎች ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? ሐ) የማያስፈልጉና በዝርዝሩ ውስጥ ያሉት ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? መ) የዝርዝሩ የተለያዩ ገጽታዎች ተግባራዊ በማይሆኑበት ጊዜ የሚከሰቱት አንዳንድ አሉታዊ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? ሠ) በአሁኑ ሰዓት በቤተ ክርስቲያናችሁ እነዚህን ነገሮች እያከናወነ ያለው ማን ነው? ረ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካሉት የተለያዩ መሪ ዎች ወይም አገልጋዮች እያንዳንዱን አገልግሎት ለማከናወን ከሁሉም የበለጠ ተስማሚ የሆነው ሰው ማን ነው?



5. ሀ) በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉትን የተለያዩ ዓይነት መሪዎች ወይም አገልጋዮች ዘርዝር:: ለ) የእያንዳንዱን ዓይነት አገልጋይ ዐበይት ኃላፊነቶች ዘርዝር:: ሐ) በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱትን የአገልጋዮች ኃላፊነቶች በቤተ ክርስቲያናችሁ ካለው ሁኔታ ጋር አነጻጽር:: ሁለቱ የሚለያዩባቸውንና የሚመሳሰሉባቸውን መንገዶች ግለጽ:: መ) አገልጋዮች ተ ግባራቸውን በግልጽ ማወቃቸው አገልግሎታቸውን እንዴት እንደሚያሳድግ ግለጽ::

# ትምህርት ሃያ ሁለት

## አንደኛ ቀን:- ከሽማግሌዎች ጋር የሚዛመዱ ሌሎች ጉዳዮች

| |
|---|
| 1ኛ ጥያቄ:- ዘጸአ. 18:13-26ን አንብብ:: ሀ) ሙሴ የተጋፈጠው የአመራር ችግር ምን ነበር? ዛሬ አብዛኞቹ ሽማግሌዎች እንዴት ተመሳሳይ ችግር እንደሚገጥማቸው ግለጽ:: ለ) የዮቶር መፍትሔ ምን ነበር? ዛሬ ይህንን መፍትሔ እንዴት ለቤተ ክርስቲያን ልንጠቀም እንደምንችል አብራራ:: ሐ) ዘኁል. 11:10-17ን አንብብ:: ሙሴ ስለ መሪነት አገልግሎቱ ለእግዚአብሔር ያቀረበው ቅሬታ ምን ነበር? እግዚአብሔር ምን እንዲያደርግ ፈለገ? መ) እግዚአብሔር ሙሴን በመሪነቱ ለመርዳት ምን አደረገ? ሠ) ስለ ሽማግሌዎች አገልግሎትና የቤተ ክርስቲያን አደረጃጀት ከእነዚህ ሁለት ምሳሌዎች ምን ልንማር እንችላለን? |

## በእያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ስንት ሽማግሌዎች ሊኖሩ ይገባል?

እግዚአብሔር ከሽማግሌዎች ስለሚጠብቃቸው ኃላፊነቶች ሁሉ ካነበብንና በብዙዎቹ ትላልቅ አብያተ ክርስቲያኖቻችን ውስጥ ስላለው ሁኔታ ካሰብን በኋላ፣ «ይህ ሊሆን የሚችል ነገር አይደለም:: ስምንት ወይም ዘጠኝ ሽማግሌዎች እስከ አንድ ሺህ ያህል ምእመናን ባሉባቸው አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ እንዴት አድርገው ነው እያንዳንዱን አማኝ በግል ሊያውቁ የሚችሉት?

ስምንት ሽማግሌዎች ለእነዚህ ሁሉ ሰዎች በግል ደረጃ የሽምግልና አገልግሎት ሊሰጡም ሆነ የግል ፍላጎቶቻቸውን ሊያሟሉላቸው አይችሉም:: ጥቂት መሪዎች ሁሉም ምእመናን በአገልግሎት ውስጥ ገብተው እንዲሳተፉ ለማድረግ፣ የማስተማር አገልግሎት ለመስጠትና የበሰል ክርስትናን ሕይወት በምሳሌነት ሊያሳዩ የሚችሉት እንዴት ነው? ሽማግሌዎች የሚችሉትን ያህል ጥረት ያደርጋሉ:: በአስተዳደራዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ለማድረግና በደቀ መዝሙርነት ፕሮግራሞችን ለብዙ ምእመናን የመንፈሳዊ እረኝነት አገልግሎት ለመስጠት እንሞክራለን:: ይሁን እንጂ፣ አዲስ ኪዳን ሽማግሌዎች እያንዳንዱን አማኝ በእረኝነት እንዲያገለግሉ ይጠይቃል:: እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ አማኝ መንፈሳዊ እድገት ሽማግሌዎችን ተጠያቂ ያደርጋቸዋል::

በአስተዳደራዊ ችግሮች ላይ ትኩረት በማድረግና የእረኝነትን አገልግሎት ባለመስጠት ችግሩን ለመፍታት ከመሞከር ይልቅ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ሌላ መፍትሔ ይሰጠናል:: መፍትሔውም ምእመናንን የሚመሩትን ሰዎች ቁጥር ማብራከት ነው:: የሽማግሌዎችን ቁጥር ልንጨምርና እያንዳንዱ ሽማግሌ አነስተኛ ቁጥር ያላቸውን ምእመናን በእረኝነት እንዲያገለግል ማድረግ ይቻላል:: ወይም ደግሞ ሽማግሌዎቹ ክትትል እያደረጉ ከእነርሱ ሥር ሆነው ምእመናንን የሚንከባከቡ ረዳት ሽማግሌዎችን መሾም ይቻላል::

በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሽማግሌዎች ቁጥር የተገደበበት ቦታ አይገኝም:: ይህ ማለት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተፈለገውን ያህል የሽማግሌዎች ቁጥር መጠቀም ይቻላል ማለት ነው:: የሽማግሌዎችን ቁጥር በትንሹ የሚቀጨው ቤተ እምነታዊ ሕግ ብቻ ነው:: እነዚህ በቁጥር አነስተኛ የሆኑ ሽማግሌዎች ብዙውን ጊዜ መንጋውን በእረኝነት ከማገልገል ይልቅ፣ በአስተዳደራዊ ሥራዎች ይጠመዳሉ:: አዲስ ኪዳን እግዚአብሔር ሌሎችን የመንከባከብ ሸክም የሰጠውና መንፈሳዊ መመዘኛዎችን የሚያሟላ ማንኛውም በሳል አማኝ ሽማግሌ ሊሆን እንደሚችል ያሳያል (1ኛ ጢሞ. 3:1):: የሽማግሌዎች አካል ለጥቂት ግለሰቦች ብቻ የተወሰነ አይደለም:: ምን ያህል ሽማግሌዎች ሊኖሩን ይገባል? ለሚለው



ጥያቄ መሠረቱ «እያንዳንዱን አማኝ በአግባቡ በእረኝነት ለማገልገል ምን ያህል እረኞች ያስፈልጉናል?» የሚለው ነው:: ቀደም ሲል ከተወሰነው ቁጥር በላይ አስፈላጊ ሊሆን የሚገባው የቤተ ክርስቲያናችን ፍላጎት ነው::

ምናልባት ዮቶር ለሙሴ የሰጠው ምክር ብዙ ትምህርት ሳይሰጠን አይቀርም (ዘጸአ. 18:17-23):: ከሁለት ሚሊዮን በላይ የሆኑትን ሰዎች ለመምራት መጣር ለሙሴ ሸክም ሆኖበት ነበር:: ለረዥም ሰዓታት የሕዝቡን ችግሮች ያዳምጥ ነበር:: ችግራቸውን በመቅረፍ ሊረዳቸው ቢፈልግም፣ በቂ ጊዜ ሊያገኝ አልቻለም:: ችግራቸው በጊዜው ስለማይፈታላቸው፣ ሕዝቡ ያጉረመርሙ ነበር:: ቀኑን ሙሉ ተሰልፈው ነበር የሚውሉት:: ተራቸው ከመድረሱ በፊት ሙሴ ደክሞት ይነሣል:: ስለዚህ፣ በቀጣዩ ቀን መመለስ የግድ ይሆናል:: ስዚህ መፍትሔው የሕዝቡን ችግር ቸል ማለት አልነበረም:: ይህ ጥሩ አመራር አልነበረም፣ ሕዝቡን በእረኝነት ማገልገልም አልነበረም:: መፍትሔው የተሻለ አደረጃጀት በማካሄድ የመሪዎችን ደረጃዎች ማዘጋጀት ነበር:: በመሆኑም፣ ዮቶር ሙሴ አስተዳደራዊ መዋቅር በማዘጋጀት 10 ሰዎችን በእረኝነት የሚያገለግሉትን የበታች አመራሮች እንዲያስናዳ መከረው:: ከእነርሱ የተሻለ ብቃት ያላቸው ሰዎች 50፣ 100 እና 1000 ለዎችን በእረኝነት የማገልገል ኃላፊነት ተሰጥቶአቸው ነበር:: በሌላ አባባል፣ የ50 ሰዎች መሪ የሆነው አገልጋይ የ10 ሰዎችን መሪዎች የመከታተል ኃላፊነት ይኖርበታል ማለት ነው:: የ100ዎች መሪ የ50ዎቹን፣ የ1000ዎቹ መሪ ደግሞ የ100ዎቹን መሪዎች ይረዳል:: ይህ አሠራር እያንዳንዱ አማኝ ችግሮቹን ለመርዳትና በመንፈሳዊ ሕይወቱ እድገት እንዲያሳይ የሚረዳው ሰው እንዲኖረው ያደርግ ነበር:: ከፍተኛ የኃላፊነት ደረጃዎች ያሏቸውና መሪዎች ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ የሚረዷቸው እረኞች ነበሩ:: ዮቶር ዕቅዱ ተግባራዊ እንዲሆን ከተፈለገ፣ እያንዳንዱ መሪ በጥንቃቄ መመረጥ እንዳለበት አስረድቷል:: ሁሉም እግዚአብሔርን መፍራት፣ ቃሉን ማወቅ፣ ጥበቡን መከተል፣ እንዲሁም ያለ አድልዎ በፍቅር ማገልገል ያስፈልጋቸው ነበር::

በአዲስ ኪዳን ዘመን የቤተ ክርስቲያን ሕንጻዎች ስላልነበሩ፣ ሰዎች በግለሰቦች ቤቶች ውስጥ ነበር የሚሰባሰቡት። የቤተ ክርስቲያን ምእመናንም ቁጥር ከ50 ሰዎች አይበልጥም ነበር። ለእነዚህ 50 ሰዎች ብቃት ያለው የእረኝነት አገልግሎት ለመስጠት ሁለት ወይም ሦስት ሽማግሌዎች ይበቁ ነበር። ዛሬ ግን በአያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች አሉ። ጥቂቶቹ ሽማግሌዎች መንፈሳዊ ክትትል ማድረግ ይቅርና የምእመኖቻቸውን ስም ለማወቅ ይቸገራሉ። ይህ ማለት ለምእመናን እንክብካቤ የሚያደርጉትን ሰዎች ቁጥር መጨመር አለብን ማለት ነው።

ሽማግሌዎች ለሁሉ ምእመናን መንፈሳዊ የእረኝነት አገልግሎት ለመስጠት መቻላቸው ወሳኝ ነገር ነው። 1000 ምእመናን ያሏት ቤተ ክርስቲያን በ8 ሽማግሌዎች ብቻ የምትመራ ከሆነና አያንዳንዱ እማኝ በበቂ ሁኔታ የእረኝነት አገልግሎት የማያገኝ ከሆነ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር 8ቱን ሽማግሌዎች በኃላፊነት እንደሚጠይቅ ይናገራል። የእረኝነት ዓላማው ሕዝቡን በእረኝነት ማገልገል ነው። መከተል ያለብንም ይህንኑ ዓላማ የሚያሳካውን መዋቅር ነው። ምናልባትም ልክ እንደ እስራኤል ብዙ ሽማግሌዎች ሊኖሩን ይገባ ይሆናል። ምእመናን 25 ሰዎች ባሉባቸው ቡድኖች ቢከፋፈሉና እነዚህን ሰዎች የሚመሩ አገልጋዮች ለሽማግሌዎች ተጠሪዎች ቢሆኑስ? ለእነዚህ የበታች መዋቅር መሪዎች የማስተማርና የሥልጠና አገልግሎት የሚሰጡ 8 ወይም ከዚያ የሚበዙ ሽማግሌዎች ቢኖሩስ? ጥቂት ሽማግሌዎችን ለመምረጥ ብቻ ስንል መንፈሳዊ ምሪትንና እረኝነትን ከመገደብ ይልቅ፣ እግዚአብሔር በሰጠን ምእመናን ቁጥር መዋቅራችን ይስፋል ማለት ነው።

> 2ኛ ጥያቄ፡- እያንዳንዱ እማኝ በቂ የእረኝነት አገልግሎት እንዲያገኝ በሚያስችል መንገድ ቤተ ክርስቲያናችሁን እንዴት ልታደራጅ ትችላለህ? ምን ዓይነት መዋቅር ታዘጋጃለህ? በእያንዳንዱ ደረጃ ላይ ያሉት መሪዎች ምን ዓይነት አገልግሎቶችን ያከናውናሉ?



## መጽሐፍ ቅዱስ ሽማግሌ ቤተ ክርስቲያንን «ያስተዳድራል»፣ ምእመናን «ሊገዙላቸው» ይገባል ሲል ምን ማለቱ ነው?

> 3ኛ ጥያቄ፡- 1ኛ ጢሞ. 5:17፤ 1ኛ ተሰ. 5:12-13፤ ዕብ. 13:17ን አንብብ። ሀ) እነዚህ ጥቅሶች ሽማግሌዎች ከምእመናን ጋር ስላላቸው ግንኙት ምን ያሳሉ? ለ) ምእመናን ከመሪዎች ጋር ስላላቸው ግንኙነትስ?

ኢየሱስ በመንግሥቱ ውስጥ መሪዎች ለአመራር የተለየ አመለካከት እንዲኖራቸው አስተምሯል። በሕዝቡ ላይ በሥልጣንና በኃይል ከመግዛት ይልቅ፣ መሪዎች የእግዚአብሔር ሕዝብ አገልጋዮች መሆን አለባቸው። ነገር ግን በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሽማግሌዎች ሕዝቡን እንደሚያስተዳድሩና ሕዝቡም ለእነርሱ መገዛት እንዳለበት የሚያሳዩ ምንባቦችስ ጉዳይ? እነዚህ ምንባቦች ሽማግሌዎች ሕዝቡ ትክክል ነው ብለው ያሰቡትን ተግባር እንዲፈጽም የማዘዝን መብት አይሰጡአቸውም? እነዚሁ ጥቅሶች ምእመናን ለሽማግሌዎች ውሳኔዎች ሁሉ እሜን ብለው መገዛት እንዳለባቸው አያሳዩምን?

ሽማግሌዎች አዲስ ኪዳን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ስለ መምራት የሚሰጠውን ትምህርት በሚገባ መረዳታቸው ወሳኝ ነው። እስኪ የሽማግሌዎችን ሥልጣንና የሕዝቡን ምላሽ የሚያሳዩትን ጥቅሶች ከአዲስ ኪዳን ውስጥ እንመልከት።

1. መሪዎች የእግዚአብሔርን ሕዝብ «ማስተዳደር» አለባቸው፡- (1ኛ ጢሞ. 5:17)

ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ እንደ ተናገረው፣ ምእመናን በመልካም ሁኔታ የሚያስተዳድሩትን ሰዎች ማክበር አለባቸው። በተለይ ጊዜ ያቸውን ሰውተው የእግዚአብሔርን ሕዝብ በማስተማርና በመስበክ የሚያገለግሉ መሪዎች ክብር እንደሚገባቸው ተመልክቷል። ነገር ግን «መግዛት» የሚለው ቃል ምንን ያመለክታል? በዛሬው ዓለማችን የፖለቲካ ሥልጣን ያላቸው ሰዎች የሚመሩበትን ሁኔታ እንመለከታለን። የፖለቲካ መሪዎች ሕጎችን በማውጣት ሕዝቡ እንዲታዘዝ ይጠይቃሉ። ፈቃደኛ ካልሆነ ደግሞ፣ ቅጣት ይከተለዋል።

በግሪክ ቋንቋ የመሪዎችን ሥልጣንና ኃይል የሚገልጹ ሁለት ቃላት አሉ:: እነዚህ ሁለት ቃላት የፖለቲካ መሪዎች በሕዝቦቻቸው ላይ ያላቸውን ሥልጣን የሚያሳዩ ናቸው:: አንድ ንጉሥ ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት የመናገር መብት ነበረው:: ስምተው የማይታዘዙትን ደግሞ የመቅጣት ሥልጣን ነበረው:: አዲስ ኪዳን እነዚህን ሁለት ቃላት ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች አይጠቀምም:: ነገር ግን ጸሐፊዎቹ የተጠቀሙት አንዳንድ ጊዜ «መግዛት» ተብሎ የተተረጎመውን ሌላ ቃል ነው:: በ1ኛ ጢሞቴዎስ 5:17 የተጠቀሰው ቃል የሚያሳየው ማገልገል ወይም ማስተዳደርን ነው:: አንዳንድ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱሶች የቤተ ክርስቲያንን ጉዳይ መምራት ብለው ተርጉመውታል:: (የ1954ቱ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ «በመልካም የሚያስተዳድሩ» ይላል::) ይኸው ቃል በሮሜ 16:2 ስፌቤን አገልግሎት ላይ ውሎ እናገኘዋለን:: ፌቤን ከጳውሎስ ጋር ብታገለግልም፣ በጳውሎስ ላይ ሥልጣን እንዳልነበራት ግልጽ ነው:: እንዲሁም ደግሞ የተጎዳው ግለሰብ እንክብካቤ እንዲያገኝ ስላደረገው ደጉ ሳምራዊም ይህ ቃል ተጠቅሶ እናገኛለን (ሉቃስ 10:35)::

ስለሆነም፣ ጳውሎስ ስማስት የፈለገው ከኃይልና ከሥልጣን ይልቅ፣ እግዚአብሔርንና ሕዝቡን በሙሉ ልባቸው የሚያገለግሉ ሽማግሌዎች ክብር እንደሚገባቸው ነው:: የሚመሩት ግን ሕዝቡን በኃይል በማዘዝ ወይም በመቅጣት ሳይሆን፣ በማገልገልና ፍላጎታቸውን በማሟላት ነው:: መንፈሳዊ መሪዎች ምን ጊዜም «ሕዝቡ የሚፈልገውን ነገር በመወሰን ተግባራዊ እንዲያደርግ እንነግረዋለን:: ሕዝቡ እኛን መታዘዝ አለበት» የሚል አመለካከት ሊኖራቸው አይገባም:: በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ እንዲህ ዓይነት ሥልጣን ያለው ኢየሱስ ብቻ ነው::

በ1ኛ ተሰሎንቄ 5:12-13 ስለ ሽማግሌዎች «የሚገዙአችሁ» ተብሎ የተተረጎመውም ቃል ይህንኑ አሳብ የያዘ ነው:: ይህ በ1ኛ ጢሞቴዎስ ውስጥ «ማስተዳደር» ተብሎ የተተረጎመው ቃል ነው:: በመሆኑም፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ማገልገል እንጂ በሥልጣን መግዛትን አያመለክትም:: 1ኛ ጢሞቴዎስ 5:14-15



የሽማግሌዎች «የማስተዳደር» ተግባር እንደ ቃሉ የማይኖሩትን መገሠጽን እንደሚጨምር ያመለክታል:: ይህ ጥቅስ ትኩረት የሚያደርገው ሽማግሌዎች ሰዎችን የማዘዝ ሥልጣን እንዳላቸው ማሳየት ሳይሆን፣ የእግዚብሔር ሕዝብ ለቃሉ በማይታዘዝበት ጊዜ ምን ዓይነት ችግሮች እንደሚገጥሙት ማስጠንቀቃቸውን በማመልከቱ ላይ ነው::

ሽማግሌዎች በምእመናን ላይ ብዙ ሥልጣን እንደሌላቸው ግልጽ ነው:: ምእመናን ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡት በገዛ ፈቃዳቸው ስለሆነ፣ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ሊቀይሩ ወይም ወደ ዓለም ሊመለሱ ይችላሉ:: ይህ የራሳቸው ምርጫ ነው:: ስለሆነም፣ የቤተ ክርስቲያን አመራር ሥልጣንና ኃይል የመዋቅሩ አካል ከሆነበት የንግድ ወይም የመንግሥት አመራር የተለየ መሆኑ ግልጽ ነው::

እግዚአብሔር ሽማግሌዎች በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መንገድ እንዲመሩ የሰጣቸው ደንቦች ምንድን ናቸው? ሁለት ደንቦች አሉ::

<u>አንደኛ</u>፣ ሰዎች የሚከተሉትን ምሳሌያዊ ሕይወት በማሳየት መምራት:: ጳውሎስ ሰዎች እንዲታዘዙት አላስገደደም:: ነገር ግን መንፈሳዊ ሕይወቱን ያደንቁ ስለ ነበረ፣ ሰዎች እንዲከተሉት ነበር የጠየቀው:: ምሳሌነቱን እንዲከተሉ አበረታታቸው (1ኛ ቆሮ. 11:1)::

<u>ሁለተኛ</u>፣ የማስተማር፣ የመስበክና የመገሠጽ መሣሪያም ሊጠቀሙ ይችላሉ:: ከላይ ባጠናናቸው ጥቅሶች ውስጥ ጳውሎስ ሽማግሌዎችን እነዚህን ነገሮች እንዲያደርጉ መክሯቸዋል:: ሽማግሌዎች ባስማቋረጥ ሕዝቡን ወደ ክርስቶስና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ወዳለው ቃሉ ማመልከት አለባቸው:: ለሕዝቡ በቃሉ ውስጥ የተገለጸውን የእግዚአብሔርን እውነት መናገር አለብን:: ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲሰሙ ማበረታታት አለብን:: ነገር ግን ስመታዘዝ ወይም ላለመታዘዝ መምረጥ የእያንዳንዱ ሰው የግል ውሳኔ ነው:: ከመሪዎች በላይ ሰዎች «መታዘዝ» ያለባቸው እግዚአብሔርን ነው:: ስለሆነም፣ መሪው ትእዛዛትን ከመስጠት

ይልቅ፣ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን እውነት ካብራራላቸው በኋላ፣ መንፈስ ቅዱስ ትክክለኛውን ምርጫ እንዲያደርጉ እንዲረዳቸው መተው አለበት።

4ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የቤተ ክርስቲያናችሁ ሽማግሌዎች እነዚህን ሁለት የአስተዳደር መሣሪያዎች ምን ያህል በብቃት እየተጠቀሙ ናቸው? እነዚህን መሣሪያዎች በተሻለ መንገድ እንዲጠቀሙ ለማስቻል ምን ቢያደርጉ ይሻላል ትላለህ? ለ) ዕብ. 13፡17ን አንብብ። ይህ ጥቅስ ስለ ሽማግሌዎች ሥልጣንና ሥራ ምን ይላል?

2. መሪዎች የእግዚአብሔርን ሕዝብ ነፍስ የሚንከባከቡ አገልጋዮች ናቸው (ዕብ. 13፡17)።

የዕብራውያን መጽሐፍ ጸሐፊ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሕዝቡን ነፍስ የመጠበቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው ያስረዳል። የሰዎችን አካላዊ ፍላጎቶች ለማሟላት በመጣር ሰዎች ጤናማ እንዲሆኑ፣ ሥራ እንዲያገኙ፣ ቤት እንዲኖራቸው፣ ወዘተ. . . መትጋቱ አንድ ነገር ነው። ነገር ግን ለሰዎች ነፍስ ኃላፊነትን መውሰድ የበለጠ ከባድ ነው። ነፍሳችን ለዘላለም የምትኖር ናት። የዕብራውያን ጸሐፊ መሪዎች የምእመናን ነፍስ የመጠበቅና የእያንዳንዱ አማኝ መንፈሳዊ ሕይወት ጤናማና እያደገ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት እንዳለባቸው ያስረዳል። እግዚአብሔር ሁልጊዜም መሪዎችን ለምእመናን ሕይወት ተጠያቂ ያደርጋቸዋል። ያሁን እንጂ፣ አብዛኞቹ መሪዎች የምእመናንን ሕይወት ከመንከባከብ ይልቅ በአስተዳደራዊ ጉዳዮች ተይዘው ይገኛሉ።

የዕብራውያን ጸሐፊ እነዚህን ሽማግሌዎች «መሪዎች» በማለት ይጠራቸዋል። በግሪክ ይህ መሪ የሚለው ቃል ሰፊ ትርጉም አለው። ይህ እንደ አስተዳዳሪ ወይም ንጉሥ ሥልጣን ወይም ኃይል ያለው ማለት ሊሆን ይችላል። እንዲሁም ደግሞ ከፍተኛ አክብሮት ያገኘንና ሰዎች ለምክር የሚፈልጉትን ሰው ሊያመለክት ይችላል። ጳውሎስ ቃል አቀባይ በመሆኑ፣ ከበርናባስ ጋር የነበረውን ግንኙነት በማስመልከት ይህ ቃል አገልግሎት ሰጥቶ እናገኘዋለን (የሐዋ. 14፡12)። ይሁዳና ሲላስም «መሪዎች» የተባሉት ከሌ



ሎች የበለጠ ሥልጣንና ኃይል ስላላቸው ሳይሆን፣ በአማኞች የተከበሩ በመሆናቸው ነው (የሐዋ. 15፡22)። ስለሆነም፣ ይህ «መሪ» የሚለው ቃል አንድ ሰው የማዘዝ፣ ሌሎች ደግሞ የመታዘዝ ግዴታ እንዳለባቸው ሳይሆን፣ ሰዎች አንድን ሰውና አመለካከቱን በማክበራቸው ምክሩን መስማታቸውን የሚያሳይ ነው።

5ኛ ጥያቄ፡- ዕብ. 13፡7፤ 1ኛ ተሰ. 5፡12-13፤ 1ኛ ጢሞ. 5፡17-20ን አንብብ። እነዚህ ጥቅሶች ከቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት ምን ዓይነት ግዴታዎች እንዳሉባቸው ያሳያሉ?

3. ምእመናን ለሽማግሌዎች የመገዛትና የመታዘዝ ኃላፊነት አለባቸው።

የቤተ ክርስቲያንን አመራር ከአዲስ ኪዳን አስተምህሮ አንጻር መረዳት እንዳለብን ሁሉ፣ የምእመናንንም ኃላፊነት ከአዲስ ኪዳን መረዳት አለብን። በምእመናንና ሽማግሌዎች መካከል የሚኖረውን ግንኙነት የሚያመለክቱ ሦስት አሳቦች አሉ።

ሀ. <u>ማክበር</u>፡- የሚያሳዝነው፣ በዘመናችን ብዙ ክርስቲያኖች ሰውን ማክበር ምን እንደ ሆነ ዘንግተዋል። ልጆች ወላጆቻቸውን ማክበርና ማዳመጥ እንዳለባቸው አያስቡም። ተማሪዎችም አስተማሪዎቻቸውን አያከብሩም። ተማሪዎች ለመምህራቸው አክብሮት ለመስጠት ሲሉ ወደ ክፍል በሚገባበት ጊዜ ብድግ ብለው የሚቀበሉበትን ዘመን አስታውስ። ሰዎች ለፖለቲካ መሪዎቻቸው አክብሮት የላቸውም። ይኸው አመለካከት ወደ ቤተ ክርስቲያንም ስርጎ ገብቷል። ብዙ ምእመናን፣ በተለይ ወጣቶች፣ ሽማግሌዎችን አያከብሯቸውም። ለምሳሌ፣ አንድ ሽማግሌ አንድ የመዘምራን ቡድን አባል የድምጽ ማጉያውን ድምጽ ዝቅ እንዲያደርግ ይነግረዋል። ወይም የፕሮግራሙ መሪ መዘምራኑ አንድ መዝሙር ብቻ እንዲዘምሩ ይነግራቸዋል። ነገር ግን መዘምራኑ የድምጽ ማጉያውን ድምጽ ለመቀነስ አይፈልጉም። ወይም ደግሞ የፈለጉትን ያህል መዝሙሮች ይዘምራሉ። ይህ የአክብሮት ማጣት መንፈስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ዐመፀኝነት በመባል ይታወቃል። ይህ እግዚአብሔር የማይወደው ኃጢአት ነው። የእግዚአብሔር ቃል ሰዎች ለባለ ሥልጣናት እንዲታዘዙ ያዝዛቸዋል። በፖለቲካዊ

ወይም መንፈሳዊ ሥልጣን ላይ ያለን ሰው አለመታዘዝ ያንን ሰው በሥልጣን ላይ ያስቀመጠውን እግዚአብሔርን አለመታዘዝ ነው።

ዛሬ ብዙ ምእመናን የቤተ ክርስቲያን መሪዎቻቸውን ይጠራጠራሉ። ምእመናን ሽማግሌዎችን የሚሰሙት ሲመቻቸው ወይም ሲፈልጉ ነው። አንዳንዶች በቅንዓት መንፈስ በሽማግሌዎች አመራር ላይ ይነሣሣሉ። እነዚህ ነገሮች ግን እግዚአብሔርን ደስ አያሰኙም። ሽማግሌዎች የእግዚአብሔርን ትእዛዛት አለመከተ ላቸውን እስካላረጋገጥን ድረስ፣ ሽማግሌዎችን መታዘዙ የግድ ነው። (ማስታወሻ:- 1ኛ ጢሞቴዎስ 5:19 ማንም ሰው ሽማግሌን ያለ መረጃ መክሰስ እንደሌለበት ያስጠነቅቃል። ግልጽ መረጃ ሳይኖ ረን በአንድ ሽማግሌ ላይ ክስ በምንመሠርትበት ጊዜ (ስናማቸው ወይም አንድን ውሳኔ የሰጠው በራስ-ወዳድነት ፍላጎት ተነሣሥቶ ነው ስንል)፣ ይህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሐሜትን ማስፋፋት ነው የሚሆነው።)

ሰዎች ለሽምግልና የሚመረጡት በሰዎች የተከበሩ በመሆናቸው ነው። ሽማግሌዎች መመረጥ ያለባቸው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መልካም መንፈሳዊ ምሳሌነት ስላላቸው ነው። መንፈሳዊ ጥበብ ያላቸውና ለእግዚአብሔር ባላቸው ፍቅር የታወቁ ናቸው። ባሕርያቸው ምሳሌያዊ ነው። ምእመናን በእምነታቸውና በአገልግሎታቸው እንዲያድጉ ለማገዝ ይጥራሉ። መሥዋዕትነት ከፍለው ምእመናንን በእረኝነት ያገለግላሉ። ስለሆነም፣ ምእመናን በአክብሮት ሊሰሟቸውና ሊከተሏቸው ይገባል።

ነገር ግን ሽማግሌዎች የምንፈልጋቸው ዓይነት መንፈሳዊ ምሳሌዎች ሳይሆኑ ቢቀሩስ? እንዲህ ዓይነት ሁኔታ በሚፈጠርበት ጊዜ እናከብራቸውም ማለት ነው? ሁልጊዜም ልናከብራቸው ይገባል። ሽማግሌዎች እንዲሆኑ የመረጥናቸው ራሳችን ስለሆንን፣ መልካም ምሳሌዎች ካልሆኑ ልንመርጣቸው አይገባም ነበር። ከሁሉም በላይ እግዚአብሔር ነገሮችን ስለሚቆጣጠሩ፣ ሽማግሌ ዎች እንዲሆኑ አድርጓል። ስለዚህ፣ በአክብሮት የማንሰማቸው ከሆነ፣ በመሪነት ላይ ካስቀመጣቸው እግዚአብሔር ጋር እየተዋጋን ነው ማለት ነው።



መሪዎችን ማክበር ማለት ምን ማለት ነው? መሪዎች ቤተ ክርስቲያንን ለመንከባከብ ጥረት በሚያደርጉበት ጊዜ የተስያዩ ችግሮች እንደሚገጥሟቸው በመረዳት እናከብራቸዋለን። የሚናገሩትን ቃል በማዳመጥ፣ ጥያቄዎችን በመጠየቅ፣ አስተያየት በመስጠት፣ ለአገልግሎታቸው በማመስገን፣ በመርዳት፣ ወዘተ. . . አክብሮታችንን እናሳያቸዋለን። ዕብራውያን 13:17 እንደሚያመለክተው አገልግሎታቸውን ከማክበድ ይልቅ ቀላል በማድረግ እናከብራቸዋለን። የመሪዎችን አገልግሎት የበለጠ የምናከብድባቸው ከሆነ፣ ራሳችንን ነው የምንጎዳው። ምክንያቱም ሰነፍሳችን የፍቅር እንክብካቤ የሚያደርጉ መሪዎች አይኖሩንም። በእረኝነት የሚያገለግሉ ሽማግሌዎች ከሌሉ ደግሞ፣ ምእመናን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ሊያድጉ አይችሉም።

| |
|---|
| 6ኛ ጥያቄ:- ሀ) ኅብረተሰባችን በሥልጣን ላይ ላሉት ሰዎች አክብሮት ያጣበትን ሁኔታ ግለጽ። ለ) ይህንን ተመሳሳይ ችግር በቤተ ክርስቲያናት ውስጥ የተመለከትከው እንዴት ነው? ሐ) ምእመናን ለሽማግሌዎቻቸው ያላቸውን አክብሮት እንዴት ሊያሳዩ ይችላሉ? |

ለ. <u>የገንዘብ ሽልማት</u>:- ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ እንደ ተናገረው፣ ከፍተኛ መሥዋዕትነት እየከፈሉ የሚያገለግሉ ሽማግሌዎች እጥፍ ክብር ይገባቸዋል። ጳውሎስ ይህንን ሲል ምእመናን የሽማግሌ ዎችን አገልግሎት በሚያገኙበት ጊዜ ደመወዝ ሊከፍሏቸው ይገባል ማለት ነው። «ሽማግሌዎች በነጻ ሊያስተምሩንና እንድናድግ ሊያደርጉን ይገባል። ለምን እንከፍላቸዋለን? እግዚአብሔር ይከፈላቸው» የሚለው አስተሳሰብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። ቤተ ክርስቲያን እንደ መጋቢ/አስተማሪ/ወንጌላዊ ሙሉ ጊዜ ሰጥተ ው ለሚያገለግሉ ሰዎች በቂ ደመወዝ በመክፈል የመተዳደሪያ ገንዘብ ለማግኘት ሌላ ሥራ መሥራት ሳያስፈልጋቸው ሙሉ ትኩ ረታቸውን ሰጥተው እንዲያገለግሉ ማድረግ ይኖርባታል።

[ማስታወሻ:- እዲስ ኪዳን የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ከሌላው ምእመን ወደ ላቀ የኢኮኖሚ ደረጃ የሚያደርስ ደመወዝ መጠበቅ አለባቸው አይልም። ነገር ግን ከምእመናን የማይተናነስ ሕይወት እንዲመሩ የሚያስችል ገንዘብ ሊከፈላቸው ይገባል። (2ኛ ቆሮ.

8:13-15 ስለ ክርስቲያናዊ የእኩልነት አመለካከት የሚናገረውን አሳብ እንብብ።) መሪዎች የሕዝቡን ገንዘብ ሰብስበው ራሳቸውን ወደ ሀብታምነት ለማሸጋገር መጣር የለባቸውም። ምእመናንም በቂ ደመወዝ ባለመክፈል የአልጋዮቹን ሥራ እንዳሳሰፈሳጊ ማድረግ የለባቸውም። ቤተ ክርስቲያን ለአንድ አገልጋይ አነስተኛ ደመወዝ በመክፈል ከሌሎች እኩል እንዳይኖር ማድረጓ፣ ለግለሰቡ አክብሮትና ፍቅር እንደ ነፈገች የሚያሳይ ነው።]

ከቤተ ክርስቲያናችን የኢኮኖሚ ደረጃ የተነሣ ለብዙ የሙሉ ጊዜ ሠራተኞች ደመወዝ ለመክፈል አንችልም። ነገር ግን ሽማግሌ ዎች ለአገልግሎት በቂ ጊዜ እንዲሰጡ መርዳት የሚቻልባቸው ሌ ሎች መንገዶች አሉ። በገጠር ምእመናን የሽማግሌዎችን መሬት በማረስና እንስሶቻቸውን በመንከባከብ ከዚህ ሥራ ነፃ ሊያደርጓቸው ይችላሉ። ይህም ሽማግሌዎች ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሰፊ ጊዜ እንዲሰጡ ያስችላቸዋል። በከተማ ደግሞ ምእመናን እንጨት በማምጣት፣ እንጨት በመፍለጥ፣ የሽማግሌዎችን ቤትና ግቢ በመንከባከብ እገዛ ሊያደርጉላቸው ይችላሉ። ጊዜያቸውን ሠውተው ለሚያገለግሉ ሽማግሌዎች ቤተ ክርስቲያን በዓመት አንድ ጊዜ ስጦታ ብታበረክት የበለጠ ለማገልገል ይነሣሣሉ። ሽማግሌዎች ስጦታ ካልተሰጠን ማለት የለባቸውም። ነገር ግን ምእመናን ለሽማግሌዎቹ አገልግሎት ያላቸውን ፍቅርና አክብሮት ለመግለጽ በራሳቸው ተነሣሽነት ስጦታ ቢያበረክቱላቸው የተሻለ ነው። የዕ ብራውያን ጸሐፊ እንደ ገለጸው፣ የምእመናንን መንፈሳዊ እድገት መከታተል ከባድ ኃላፊነት ነው። ስለሆነም፣ ምእመናን የሽማግሌ ዎችን የአገልግሎት ጫና ለማቃለል እገዛ ማድረግ አለባቸው።

7ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ቤተ ክርስቲያናችሁ ለሙሉ ጊዜ አገልጋዮች በቂ ደመወዝ ትከፍላቸው ወይም አትከፍላቸው እንደ ሆነ ግለጽ። የበለጠ ፍቅራቸውን ለመግለጽና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ለመሆን ምን ማድረግ አለባቸው ትላለህ? ለ) ምእመናን ገንዘብ ሳይከፍሉ ሽማግሌዎች ላበረከቱላቸው አገልግሎት ምስጋናቸውን የሚገልጹባቸው መንገዶች ምን ምንድን ናቸው? ሐ) እነዚህ ነገሮች ሽማግሌዎች በበለጠ ከራስ-ወዳድነት በጸዳ መንፈስ እንዲያገለግሉ እንዴት ያነሣሷቸዋል ብለህ ታስባለህ?



ሐ. መገዛት፦ አዲስ ኪዳን ምእመናን በሥልጣን ላይ ላሉት እንዲገዙ ያዝዛል። ይህንን ቃል መረዳት ያለብን ከመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከት አንጻር እንጂ፣ ከዓለም አንጻር አይደለም። የፖለቲካ መሪዎችን ወይም የሥራ አለቆችን በተመለከተ፣ «መገዛት» የሚናገሩትን እሺ ብሎ መቀበልን የሚያሳይ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የፖለቲካ ባለ ሥልጣናትን ወይም የሥራ አለቆቻችን ትእዛዝ እንዳናከብር የሚያዝዘን ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር የሚቃ ረን ነገር እንድናደርግ የጠየቁን እንደ ሆነ ብቻ ነው። ስለሆነም፣ ጉቦ እንድንሰጥ ወይም ኢ-ፍትሐዊነት ሳይቀጣ እንዲቀር የምንጠየቅ ከሆነ፣ መታዘዝ የለብንም። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉንም ነገር በእውነተኝነትና በፍትሕ እንድናከናውን ይነግ ረናል።

ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስላሉ ግንኙነቶች ሲናገር፣ መጽሐፍ ቅዱስ መገዛትን የሚመለከተው ለየት ባለ መንገድ ነው። በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ መገዛት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲሆን የምንፈልገውን ነገር ለሌላው ሰው አሳብ በመገዛት መተ ውን የሚያመለክት ነው። በኤፌሶን 5:21 አንዱ አማኝ ለሌላው እንዲገዛ ተጠይቋል። በግልጽ መረዳት እንደሚቻለው፣ ሁሉም አማኞች በሌሎች አማኞች ላይ አስተዳደራዊ ሥልጣን ሊኖራቸው አይችልም። ይልቁንም፣ ይህ አንዱ አማኝ ሌላውን እንዲሰማና ለመርዳትም ፈቃደኛ እንዲሆን የሚጠይቅ ነው። ይህ ሌሎች ባይስማሙበትም፣ የእኛ አመለካከት ተቀባይነት እንዲያገኝ ከመታገል መቆጠብን የሚያሳይ ነው። ጳውሎስ እያንዳንዱ አማኝ (ሽማግሌዎችም ጭምር) የትሕትና ባሕርይ ሊኖራቸውና ሌሎች አማኞችን እንዲያገለግሉ ይጠይቃል።

ይሁን እንጂ፣ አዲስ ኪዳን ምእመናን የትሕትና አመለካከትና ለሽማግሌዎች የመገዛት ፍላጎት ሊኖራቸው እንደሚገባ ያስተ ምራል። በአክብሮት መሪዎችን መስማት ይኖርባቸዋል። ምእመናን ከሽማግሌዎች ጋር አብረው በመሥራት እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የሰጣትን ተግባር ለማከናወን መጣር አለባቸው። ለሽማግሌዎች የሚገዙት ሽማግሌዎቹ የተለየ ኃይልና ሥልጣን

ስላሳቸው ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ሽማግሌዎቹ ነፍሳቸውን እንዲያገለግሉ ኃላፊነት የሰጣቸው መሆኑን በመረዳት ነው:: ምእመናን የሽማግሌዎች ውሳኔና ትምህርት የሚፈልጉት ዓይነት በማይሆንበት ጊዜ ሳይቀር ለመስማት ፈቃደኛ መሆን አለባቸው:: ስለሆነም፣ ምእመናን የድምፅ ማጉያውን ድምጽ ዝቅ እንዲያደርጉ ወይም በሥራ ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመጡ በሚጠየቁበት ጊዜ፣ ባይፈልጉም እንኳን ይህንኑ ማድረግ ይኖርባቸዋል:: ሽማግሌዎች ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚጋጭ ነገር እስካልጠየቁ ድረስ፣ ምእመናን መታዘዝ ይኖርባቸዋል:: ለመገዛት ፈቃደኛ አለመሆን ብዙውን ጊዜ በሽማግሌዎች ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በእግዚአብሔርም ላይ የዐመፀኝነት መንፈስ እንዳለን የሚያሳይ ነው::

በማጠቃለያ፣ የቤተ ክርስቲያንን አመራር በዓለም ዓይን ብንመለከት፣ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሽማግሌዎች በሥልጣን እንዲገዙና ምእመናን ደግሞ ሁልጊዜም እሺ ባዮች ሆነው እንዲገኙ የሚጠይቁ የሚመስሉ ምንባቦች ልናገኝ እንችላለን:: ነገር ግን፣ ኢየሱስ ስለ አመራር ባስተማረው መሠረት እነዚህን ጥቅሶች ብንመለከት፣ ሽማግሌዎች በዚሁ ማዕረጋቸው ምክንያት ምእመናንን ለመግዛት የሚያስችል ልዩ ኃይል እንደሌላቸው እንረዳለን:: ሽማግሌዎች ምእመናን የሚፈልጉትን ሁሉ እንዲያከናውን በማዘዝ ላይ ትኩረት ማድረግ የለባቸውም:: አዲስ ኪዳን እንዲህ ዓይነቱን ሥልጣን አይደግፍም::

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥልጣን የሚመጣው ከአገልጋይነት አመለካከት ነው:: ሽማግሌዎች በተቻላቸው መጠን ምእመናንን ለማገልገል መጣር አለባቸው:: በአዲስ ኪዳን ውስጥ ትኩረት የተ ሰጠው መሪዎች በምሳሌነት፣ በምክር፣ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማር እንዲመሩ ነው:: ሽማግሌዎች መንፈሳዊ ባሕርይ ያላቸው፣ በቤተ ክርስቲያን የተከበሩና በእምነታቸው የበሰሉ መሆን አለባቸው:: በክፉ ዓለም ውስጥ ሰዎች እንዴት ለእግዚአብሔር መኖር እንደሚችሉ በምሳሌነት ያሳያሉ:: ሰዎች ሽማግሌዎችንና መንፈሳዊ ጥበባቸውን ስለሚያከብሩ፣ በፈቃደኝነት ያከተሏቸዋል:: ሽማግሌዎች የእግዚአብሔርን ቃል ስለሚያውቁ፣ እግዚአብሔር የሚፈልግባቸውን ነገር ያስተምሯቸዋል:: ሽማግሌዎች ለሕዝቡ የሚያስቡ መሆናቸውን የሚያሳዩ መንፈሳዊ መሪዎች ከሆኑና ምእመናንም በግል የሚያውቁአቸው ከሆኑ፣ እንዲሁም ሽማግሌ ዎች ሰዎች እንዴት ኢየሱስን እንደሚከተሉ በምሳሌነትና በማስተ ማር ቢያሳዩአቸው፣ ሽማግሌዎች እንደ ዓለም ሥልጣንና ኃይል መጠቀም ሳያስፈልጋቸው ምእመናን በፈቃዳቸው ይከተሏቸዋል::

> 8ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የአዲስ ኪዳንን የመሪነት አስተሳሰብ ከዓለም የመሪነት አስተሳሰብ ጋር አነጻጽር:: ለ) ሽማግሌዎች የዓለምን አመራር ስለሚከተሉ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያላቸውን ሥልጣን በተሳሳተ መንገድ የሚ ረዱበትን ሁኔታ ግለጽ:: ሐ) አዲስ ኪዳን እንደሚያስተምረው ቢመሩ አመራሩ እንዴት ይለወጣል? መ) ምእመናን አዲስ ኪዳን እንደሚያስተም ረው ለሽማግሌዎች ቢገዙ፣ ግንኙነታቸው እንዴት የሚለወጥ ይመስልሃል?

## ሽማግሌዎች እንዴት መመረጥ አለባቸው?

መጽሐፍ ቅዱስ ሽማግሌዎች እንዴት መመረጥ እንዳለባቸው ብዙ መመሪያዎችን አይሰጥም:: በጥቂት አብያተ ክርስቲያናት መሥራቹና ወኪሎቹ ሽማግሌዎችን ያስመርጡ እንደ ነበ ረ እንረዳለን (ለምሳሌ፣ ቲቶ 1):: ጳውሎስ፣ ቲቶ ወይም ጢሞቴዎ ስ ግለሰቦችን መርጠው ለሽማግሌዎች ያቅርቡ ወይም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያትና በወኪሎቻቸው ምሪት ይምረጧቸው የሚታወቅ ነገር የለም:: በሐዋርያት ሥራ 6 ሐዋርያት ለዲያቆናት መስፈርቶችን ካዘጋጁ በኋላ፣ ምእመናን እነዚህን መስፈርቶች ያሟሉትን ሰዎች የመረጡ ይመስላል:: ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት የሚከተሉት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምርጫ መንገድ ይኼ ይመስላል:: ስለዚህ፣ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሰፈሩትን መስፈርቶች በመመልከት ሽማግሌዎችን መምረጥ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት ነበር:: ለሽማግሌዎች ምርጫ መስፈርቶችን ካልተከተልንና በእነዚሁ መስፈርቶች ላይ የራሳችንን ጨምረን እንደ ትምህርት፣ ሀብት ወይም የመንግሥት ሥልጣን መያዛቸውን ለማረጋገጥ የምንፈልግ ከሆነ፣ ቤተ ክርስቲያናትን የምትንቀሳቀሰው እንደ ዓለማዊ ድርጅት ይሆናል:: እግዚአብሔር

ትምህርት ወይም ሀብት የሌላቸውን ወይም ያላቸውን ሰዎች ሊመርጥ ይችላል። እግዚአብሔር ሕዝቡን በእረኝነት ለማገልገል እውነተኛና ክህሎት ያላቸውን ሰዎች ይፈልጋል።

ቤተ ክርስቲያን አንድ ሽማግሌ ጥሩ አገልጋይ ሊሆን እንደሚችል እንዴት ልታውቅ ትችላለች? አንድ ሰው ጥሩ አገልጋይ የሚሆነው ወደ ሥነ-መለኮት ትምህርት ቤት ስለ ገባ አይደለም። ለሽማግሌነት በመመረጡ ደግሞ ጥሩ እረኛ ላይሆን ይችላል። ምእመናን አንድን ሰው ለሽማግሌነት በሚመርጡበት ጊዜ በቀዳሚነት እግዚአብሔር የጠራቸውንና የእረኝነት ስጦታ የሰጣቸውን ሰዎች ከምእመናን መካከል ለይተው ለማውጣት መጣር አለባቸው። ምእመናን የሰዎችን ሕይወት በመመልከት ይህንን ሊያውቁ ይችላሉ። 1) አንድ ሰው መደበኛ በሆነ ወይም ባልሆነ መንገድ ሰዎችን በማስተማር በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ የሚረዳቸው ከሆነ፣ 2) አንድ ሰው ለሕዝቡ የሚራራና መንፈሳዊ ፍላጎታቸውን ለማሟላት የሚሞክር ከሆነ፣ 3) ሰዎች ለመንፈሳዊ ጥበብና ምክር ወደ ግለሰቡ የሚሄዱ ከሆነ። እነዚህ ነገሮች እግዚአብሔር ይህን ሰው እንደ መረጠውና በመደበኛነት ሕዝቡን በእረኝነት ለማገልገል ዝግጁ መሆኑን ያሳያል። በምርጫ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ግለሰቦች ቀደም ሲል ሲያከናውኑ ለነበረው ተግባር እውቅና መስጠት ይጠበቅባታል።

9ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ይህንን የሽማግሌዎች አመራረጥ ብዙውን ጊዜ ሽማግሌዎች ከሚመረጡበት ሁኔታ ጋር አነጻጽር። ለ) ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ሦስት ነገሮች በማገናዘብ ሰዎችን ለሽምግልና ብትመርጥ፣ ምን ዓይነት ሰውጦች እንደሚከሰቱ ግለጽ።

## የሽማግሌዎች ወይም መጋቢዎች ቅባት (ሹመት)

አንዳንድ ቤተ እምነቶች የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን በመቀባት ላይ ከፍተኛ ትኩረት ያደርጋሉ። በመሆኑም፣ ያልተቀባ አገልጋይ ጉባኤውን እንዲመራ፣ እንዲሰብክ፣ የጌታን እራት እንዲመራ፣ ወዘተ. . . አይፈቅዱም። እነዚህ ቤተ እምነቶች በአዲስ ኪዳን መሪዎች እጆቻቸውን በመጫን እንደ ጢሞቴዎስ ያሉትን ሰዎች ለአገልግሎት የለዩበትን መንገድ አጥብቀው ይከተላሉ። ነገር ግን



አዲስ ኪዳንን በጥንቃቄ በምናጠናበት ጊዜ በዚህ ዓይነት መንገድ የተወሰኑ ሰዎችን ከሌሎች ለይቶ ለአገልግሎት መሾሙ ተደጋፊነት ያለው አይመስልም። አዲስ ኪዳን ስለ ቅባት የሚከተለውን የሚያስተምር ይመስላል፡-

1. ሁሉም አማኞች ለማገልገል የሚያስችል መንፈሳዊ ስጦታ ተሰጥቶአቸዋል። ከእነዚህ መካከል አንዳንዶቹ በቅባት ሂደት ቁጥጥር ሊደረግባቸው እንደሚገባ የሚያሳይ ነገር የለም። እያንዳንዱ አማኝ ሌሎችን የሚያገለግልበትን ስጦታ የሚሰጠው መንፈስ ቅዱስ እንጂ ሰው አይደለም። አዲስ ኪዳን አገልግሎትን በተመለከተ ትኩረት የሚያደርገው በመደበኛ የብቃት መመዘኛዎች ላይ ሳይሆን፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና በግለሰቡ ባሕርይ ላይ ነው።

2. አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችን በብሉይና በአዲስ ኪዳን ውስጥ በተጠቀሱት «እጅ የመጫን» ሥርዓቶች ለመለየት ይፈልጋሉ። «እጅን የመጫን» ሂደት የአይሁዶች የባህል አካል ሲሆን፣ ሀ) መንፈሳዊ በረከትን ለሌላ ሰው ማስተላለፍን (ማቴ. 19:13-15፤ የሐዋ. 8:17)፣ እና ለ) ሰዎችን እግዚአብሔር ለሰጣቸው አገልግሎት መለየትን የሚያሳይ ነው (የሐዋ. 6:5-6፤ 13:3)።

በብሉይ ኪዳን፣ ካህናት ለመሪነት የሚለዩት እጅ በመጫን ነበር። ሙሴም ኢያሱን በዚሁ መንገድ ለመሪነት አብቅቶታል (ዘኁ. 8:10፤ 27:18-23)። በአዲስ ኪዳን፣ የመጀመሪያዎቹ ዲያቆናት የተመረጡት እጅ በመጫን ነበር፤ ጳውሎስና በርናባስም ለወንጌል መልእክተኛነት አገልግሎት የተለዩት እጅ በመጫን ነበር።

በአዲስ ኪዳን እጅን መጫን ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ምሪት እግዚአብሔር አንድን ሰው ለአንድ አገልግሎት መጥራቱን መገንዘቧን ይፋ የምታደርግበት ሂደት ነበር። እጆቻቸውን በመጫን እግዚአብሔር ግለሰቡን ለአገልግሎት መጥራቱንና ማስታጠቁን መረዳታቸውን ያሳያሉ።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ አንድ ሰው እንደ «ሙያተኛ» ልዩ ሥልጣን ይዞ ሌሎችን የሚቆጣጠርበት ሁኔታ መኖሩ አልተ መለከተም:: ይህ አንድ ሰው ብቃቱን ለሽማግሌዎች የሚያሳይበት ሂደት አይደለም:: ነገር ግን ይህ የመደበኛ አገልግሎትን ጅማሬ የሚያሳይ ነው::

3. መጋቢዎችና ካህናት በመደበኛ ሁኔታ የሚቀቡት ዋናው የቤተ ክርስቲያን መሪ («አስተማሪ ሽማግሌ») የመሪነትን መመዘኛ ዎች ማሟላቱን ለማሳየት ነበር:: ቤተ ክርስቲያን መደበኛ የቅባት ሥነ-ሥርዓት የምታካሂደው እነዚህ መሪዎች (በኋላ ካህናት የተ ባሉት) ሕዝቡን ለማስተማር የሚያስችል ሰፊ የእግዚአብሔር ቃል እውቀት፣ ለሙሉ ጊዜ አገልግሎት የእግዚአብሔር ጥሪ፣ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ሕዝብ በእረኝነት ለማገልገል የሚያስችል መንፈሳዊ አገልግሎት እንዳላቸው ለማረጋገጥ ነበር::

እግዚአብሔር ለአገልግሎት ጠርቶናል የሚሉትን ሰዎች ጥሪና የብቃት መመዘኛዎች እውነተኛነት ማረጋገጡ ጥሩ ነገር ነው:: የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ ሳያውቁ «መጋቢ» ወይም «ወንጌላዊ» ነኝ ለማለት የሚፈልጉ ሰዎች አሉ:: አንዳንድ ሰዎች ደግሞ እግዚአብሔርን ከማገልገል ይልቅ ሥራ በማግኘቱ ላይ ትኩ ረት ያደርጋሉ:: አንዳንዶቹ ደግሞ ገና ከሥነ-መለኮት ትምህርት ቤቶች የወጡና መንፈሳዊ ብስለት የሌላቸው ወጣቶች ይሆናሉ:: ስለሆነም፣ ቤተ ክርስቲያን በቅባት ሥነ-ሥርዓት አማካኝነት የሙሉ ጊዜ አገልግሎት ከበድ ያለ ጉዳይ መሆኑንና ለሙሉ ጊዜ አገልግሎት የተጠሩት ክርስቲያኖች ለዚሁ አገልግሎት የሚያስፈልግ የእግዚአብሔር ጥሪ እንዳላቸው ማረጋገጡ አስፈላጊ ነው:: አብያተ ክርስቲያናት በፍጥነት በሰዎች ላይ እጆቻቸውን እንዳይጭኑ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአቸዋል:: (1ኛ ጢሞ. 5:22 አንብብ::) በመጀመሪያ ደረጃ የሚመረጡት ሰዎች በእግዚአብሔር መጠራታቸውንና አገልግሎቱ የሚጠይቃቸውን መመዘኛዎች ማሟላታቸውን ማረጋገጥ አለብን:: ብቃት በሌለው አገልጋይ ላይ እጃችንን የምንጭን ከሆነ፣ ግለሰቡ እግዚአብሔርን በመንፈሳዊ መንገድ የማያገለግል ከሆነ፣ ተጠያቂዎች እንሆናለን ማለት ነው::



ቤተ ክርስቲያን የቅብአት ሂደት የምታካሂድ ከሆነ፣ የሚከተ ሉት ችግሮች እንዳይፈጠሩ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባታል:-

ሀ. ሰይጣን በቀላሉ ግለሰቡን ወደ ትዕቢት ሊመራው ይችላል:: «እኔ የተቀባሁ ነኝ:: እኔ መጋቢ ነኝ:: እኔ ከእናንተ የተሻልኩ ነኝ::» የሚል አስተሳሰብ ሊኖረው ይችላል:: በመሆኑም፣ ከሌሎች የሚለየን የሚመስለውን የተለየ ልብስ መልበስ እንጀምራለን:: ይህ የተሳሳተ ግንዛቤ ነው:: እግዚአብሔር አጥብቆ የሚጠላው የትዕ ቢት ኃጢአት ይህ ይፋዊ እውቅና የሚሰጣቸውን ያልበሰሉ አገልጋዮች በቀላሉ ሊያሸንፋቸው ይችላል::

ለ. ይህ በምእመናንና በተቀቡት ሰዎች መካከል ልዩነትን ሊፈጥር ይችላል:: የተቀቡት ሰዎች ብቻ የተወሰኑ ነገሮችን እንደሚያደርጉና ያልተቀቡት ደግሞ ምንም ነገር ሊያደርጉ እንደማይችሉ ሊታሰብ ይችላል:: ቅዱስ ቁርባን፣ ጥምቀት፣ ስብከት፣ ማስተማርና ሌሎችም አገልግሎቶች መካሄድ ያለባቸው በተቀቡ አገልጋዮች ብቻ ነው የሚለው አመለካከት ለቤተ ክርስቲያን አደገኛ ነው:: ምእመናን ባለሙያዎች ሊያገለግሉ ቁጭ ብለው የሚመለከቱ ሰዎች ይሆናሉ:: በአዲስ ኪዳን እንዲህ ዓይነት ክፍፍል አይታይም:: ሁሉም አማኞች ካህናት በመሆናቸው፣ መንፈሳዊ ብቃትና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ያላቸው ሰዎች ሁሉንም አገልግሎት ማከናወን ይችላሉ::

ሐ. የተሳሳቱ ነገሮችን መገምገም ቀላል ነው:: በመጀመሪያ፣ ይህ ብዙውን ጊዜ በወረቀት ብቃቶች፣ ወይም ሰዎች የሥነ-መለኮ ት ወይም ሌላ ትምህርት በማጠናቀቃቸው ላይ ትኩረት እንድናደርግ ሊገፋፋን ይችላል:: ሁለተኛ፣ ቅብአት ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል ሥነ-መለኮታዊ እውቀት ይገመግማል:: የሚነሡት ጥያቄዎች አነስተኛ አስተምህሯዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ናቸው:: ከዚህም የተነሣ፣ ብዙውን ጊዜ የሚቀቡት ትምህርታቸውን ያጠናቀቁና መጋቢ ለመሆን የሚፈልጉ ወጣቶች ናቸው:: እነዚህ ወጣቶች የጥያቄዎቹን መልሶች ያውቃሉ:: ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሚጠይቀውን የሽማግሌ ወይም የአገልጋይ ክህሎቶች አያሟሉም:: መጽሐፍ ቅዱስ ትኩረት የሚሰጥባቸው

የአገልግሎት መስፈርቶች መንፈሳዊ ብስለት፣ በትሕትና ከሰዎች ጋር አብሮ መሥራት (እረኝነት)፣ የእግዚአብሔር ጥሪ የመሳሰሉት ናቸው።

መ. ይህ ቤተ ክርስቲያን በአንድ ግለሰብ ላይ ትኩረት በማድረግ ልዩ ሥልጣን እንድትሰጠው ያደርጋል። ነገር ግን አዲስ ኪዳን ሁልጊዜም ትኩረት የሚሰጠው በቡድን ቤተ ክርስቲያንን በሚመሩ ሽማግሌዎች ላይ ነው። እንዲህ ዓይነቱ የቅባት ሥርዓት ብዙዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመሪነት ስጦታቸውን እንዳያሳድጉ ያደርጋል።

ሠ. ቤተ ክርስቲያን ግለሰቡ እንደ ሽማግሌ/መጋቢ መጠራቱን ለማረጋገጥ እንድትቸገር ያደርጋል። ሽማግሌዎችን/መጋቢዎችን የሚጠራው እግዚአብሔር ከሆነ፣ ይህንኑ እውነታ ለማረጋገጥ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምርጥ ስፍራ ነች። ግለሰቡ ሌሎችን ማገልገሉንና ሰዎችም ወደ እርሱ ለመገልገል መምጣታቸውን በመመልከት የእረኝነት ልብ እንዳለው ወይም እንደሌለው ያ ረጋግጣሉ። ትምህርት ቤቱ ወይም በሩቅ ያሉት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች (የአውራጃ ወይም የዋናው ጽ/ቤት) ግለሰቡን ለመቀባት ስለሚያስችል የግል ባሕርዩ የሚያውቁት ነገር የለም።

> 10ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ሽማግሌዎች፣ መጋቢዎችና ወንጌላውያን ጠቃሚ አገልግሎቶችን ከመያዛቸው በፊት እውቀታቸውን፣ ባሕርያቸውንና ክህሎታቸው ለመመዘን (ከቅብአት ሥነ-ሥርዓት ጋር በሚመሳሰል መንገድ) ምን ምን ዓይነት ነጥቦች ቢሰፍሩ መልካም ነው ትላለህ? ለ) ለእነዚህ ለሦስቱም ዓይነት መሪዎች ምን ዓይነት መመዘኛዎች ቢመሠረቱ መልካም ነው ትላለህ? ሐ) የተሳሳቱ መመዘኛዎችን መመሥረት ምን ዓይነት ችግሮችን ያስከትላል ብለህ ታስባለህ?

## አመራር በቤተ እምነታዊ መዋቅር ውስጥ

ቀደም ሲል ከታሪክ አስሳችን እንደ ተመለከትነው፣ ቤተ እምነቶች የተለያዩ ዓይነት የአመራርና የአስተዳደር መዋቅሮችን ይከተላሉ። ከእነዚህ መካከል አንዳንዶቹ በብሔራዊ ደረጃ በሚገኙ ማዕከላዊ የአስተዳደር አካሎች በጥብቅ ቁጥጥር የሚንቀሳቀሱ ናቸው። ሌሎች ደግሞ ሥልጣን በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት



ወይም በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን እንዲያዝ የሚያደርጉ ናቸው። ከሁሉም በላይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው የትኛው አሠራር ነው? በማለው ጥያቄ ላይ ክርክር መካሄዱ የሚቀጥል ቢሆንም፣ የሚከተሉትን አሳቦች መመልከቱ ጠቃሚ ይሆናል ብዬ አስባለሁ፡-

1. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም ሆነ ሐዋርያት ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውጭ የአስተዳደር መዋቅር አስፈላጊ መሆኑን የሚያሳይ ቃል አልተናገሩም። የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሮም ግዛት ውስጥ የሚገኙ ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ለእነርሱ እንዲገዙ አልጠየቁም። ሐዋርያት የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ምን መሆን እንዳለበት በመወሰኑ ረገድ የመጨረሻውን ውሳኔ ቢሰጡም (ለምሳሌ፣ የሐዋ. 15)፣ በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ላይ ባለ ሥልጣናትና አስተዳዳሪዎች ለመሆን አልፈለጉም። ሐዋርያው ጳውሎስ በመሠረታቸው አብያተ ክርስቲያናት ላይ ጠንካራ የአማካሪነት ሚና ቢጫወትም፣ በአሕዛብ ግዛቶች ውስጥ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ መሪ ለመሆን ወይም ሁሉም በእርሱ የበላይነት ሥር የሚተዳደሩበትን መዋቅር ለመዘርጋት አልሞከረም። የቤተ ክርስቲያን ትኩረትና ሥልጣን ሁልጊዜም በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ደረጃ ነው። ይህ አብዛኛውን ሥልጣን ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች በመውሰድ በከፍተኛ የቤተ እምነት አስተዳደራዊ አካላት እጅ ከማስቀመጥ እንድንቆጠብ ሊያስጠነቅቀን አይገባምን?

2. አዲስ ኪዳን ተፎካካሪ ቤተ እምነቶች ወይም አጠቃላይ አስተዳደራዊ መዋቅር መኖሩን አያሳይም። ሁሉም ምእመናን በእግዚአብሔር ትልቅ ቤተሰብ ውስጥ እንዳሉ የቤተሰብ አባላት ነበር የሚተያዩት። ሐዋርያው ጳውሎስና ጴጥሮስ በጽሑፎቻቸው አማኞችን «ወንድሞችና እኅቶች» እያሉ ይጠሯቸው ነበር። በአብያተ ክርስቲያናት መካከል የነበረው ግንኙነት የመነጨው ከቤተሰባዊ ግንኙነት እንጂ፣ ከመዋቅር አልነበረም። የግሪክ ቤተ ክርስቲያን የኢየሩሳሌም አማኞችን እንደ ወንድሞችና እኅቶች በመመልከቷ ነበር ለችግራቸው ርዳታ ያደረገችው። ይህ የሥልጣን

ጉዳይ አልነበረም (2ኛ ቆሮ. 8)። የየትኛውም ቤተ እምነታዊ መዋቅር መንፈስ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ቤተሰባዊ-ዓይነት ግንኙነቶችን መመሥረት ሊሆን ይገባል። ቤተ እምነት የሌላቸው ወይም ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት በቀዳሚነት እርስ በርሳቸው በክርስቶስ ፍቅር ሊዛመዱና ሊተሳሰቡ ይገባል። አብያተ ክርስቲያናት ግንኙነት መፍጠር ያለባቸው ለእግዚአብሔር መንግሥት የበለጠ ታላቅ ተግባር ለማከናወን በማሰብ ሊሆን ይገባል።

3. እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰዎችን የሚቆጣጠር አስተዳደራዊ መዋቅር ለመዘርጋት አልመረጠም። በአዲስ ኪዳን ውስጥ አመራር የተገለጸው እንደ ማገልገል እንጂ፣ እንደ ቁጥጥር ወይም አስተዳደር አይደለም። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትልቁ ሥልጣን የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ነው። ሁሉም ምእመናን እኩል ናቸው። እነዚህ እውነቶች በቤተ ክርስቲያን መዋቅሮች ላይ ያሉንን አመለካከቶች፣ አደረጃጀቶችና አስተዳደራዊ ተግባራት ሊመሩ ይገባል። <u>የዚህ ጥናት መምሪያ ጸሐፊ በሚከተሉት ነጥቦች ያምናል፡-</u>

ሀ. ቤተ እምነቶችን ለብቻቸው የማያከናውኗቸውን ነገሮች ተግባራዊ ለማድረግ እንደ ተሰባሰቡት የአብያተ ክርስቲያናት ኅብረት መመልከቱ ጠቃሚ ነው። የቤተ እምነት ዓላማ አንዲት ቤተ ክርስቲያን ለብቻዋ ልታደርግ የማትችላቸውን ነገሮች በጋራ ማከናወን መሆን አለበት። ሀብታቸውን አንድ ላይ በማድረግ አብያተ ክርስቲያናት ለብቻቸው ለማከናወን የሚያስቸግሯቸውን ተግባራት ያከናውናሉ። ስለሆነም፣ አብያተ ክርስቲያናት እንደ የመሪነት ሥልጠና፣ ብሔራዊ ወንጌላውያንንና ሚሲዮናውያንን ለመላክ፣ ለመንፈሳዊ እድገት ሥነ-ጽሑፎችን ለማዘጋጀት፣ ወዘተ. . . በፈቃደኝነት አብረው ሊሠሩ ይችላሉ። አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አብያተ ክርስቲያናት አገልግሎቶችን ለማቀናጀት በሚያደርጉት ጥረት ተካፋይ ለመሆን ብትፈልግ፣ እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን የራሷን ድርሻ መወጣት አለባት። ልክ እንደ «ዕቁብ»[1] እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን ሌሎችን ለመርዳት መተባበር አለባት።



አብያተ ክርስቲያናት እንደ ትልቅነታቸውና እንዳላቸው የገንዘብ አቅም ብዙም ትንሽም ሊሰጡ ይችላሉ። ነገር ግን አንዲት ቤተ ክርስቲያን ሁሉንም አብያተ ክርስቲያናት ለሚጠቅሙ ተግባራት ምንም ዓይነት አስተዋጽኦ ሳታደርግም ልትል አይገባም። ይህ አብያተ ክርስቲያናት አብረው እንዳይሠሩ የሚያደርግ ችግር ነው።

ሐ. እግዚአብሔር ለአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ምእመናንን የመንከባከብ ኃላፊነት ሰጥቶአቸዋል። ሽማግሌዎች ይህንን ኃላፊነታቸውንና ሥልጣናቸውን ለሌሎች መስጠት የለባቸውም። እግዚአብሔር ለምእመናን ሕይወት በቀዳሚነት ተጠያቂ የሚያደርገው ሽማግሌዎችን እንጂ የአውራጃ፣ የቀጣና ወይም የዋናው ጽ/ቤት ኃላፊዎችን አይደለም። የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለቤተ ክርስቲያን አመራር ከእነርሱ በላይ ያሉትን ኃላፊዎች መጠበቅ የለባቸውም። ሌሎች አብያተ ክርስቲያናትም ሥራቸውን እንዲያከናውኑላቸው መጠበቅ የለባቸውም። ለድንገተኛ ነገሮች ካልሆነ በስተቀር፣ እያንዳንዷ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለአገልግሎት መክፈል ያለባት ከራሷ ሀብት ነው። አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ አገልግሎቶች ነፃ ርዳታ መጠበቃቸው ጤናማ ነገር አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኘው መርሕ ምእመናን መንፈሳዊ እድገት እንዲያዳብሩ ለሚያገለግሏቸው ወገኖች የገንዘብ ድጋፍ ማድረጋቸውን የሚያመለክት ነው።

መ. በከፍተኛ የቤተ እምነት አስተዳደር ላይ የሚገኙ ሰዎች ራሳቸውን መመልከት ያለባቸው ለአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት አስተያየቶችን እንደሚሰጡ አድርገው ሊሆን ይገባል። እነዚህ መሪዎች ለተለያዩ ዓይነት ፕሮግራሞች «አስተያየቶችን» በመስጠት የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ሽማግሌዎች ጥቅሙንና ጉዳቱን እንዲያመዛዝኑ ያደርጋሉ። ነገር ግን የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ለቤተ ክርስቲያናቸው ምርጫዎችን እንዲያደርጉ መተው አለባቸው። ምክንያቱም በእግዚአብሔር ፊት የሚጠየቁት እነርሱው ናቸውና። በከፍተኛ የቤተ እምነት አስተዳደር ላይ የሚገኙ መሪዎች የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት

አገልጋዮች መሆናቸውን መዘንጋት የለባቸውም። ቀዳሚ ውትክ ረታቸው ምክርና ሥልጠና በመስጠት አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በጥሩ ሁኔታ እንዲሠሩ ማድረግ ነው። ዋናው ጽ/ቤት አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የእነርሱን ውሳኔዎች ተግባራዊ እንዲያደርጉ ማስገደድ የለባቸውም።

ሠ. በቤተ እምነቶች ውስጥ አንድ ዓይነትነት እንዲኖር ማስገደድ የለብንም። የትኛውንም አገልግሎት በተለያዩ መንገዶች ማከናወን እንደሚቻል ሁሉ፣ እያንዳንዷ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ግቧን ለመምታት ትክክለኛ የሆኑትን ነገሮች የመምረጥ ነጻነት ሊኖራት ይገባል። ይህ መንፈስ ቅዱስ የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችን ከሚመራበት ሁኔታ አንጻር ከቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን ወይም ከቀጣና ቀጣና ሊለያይ ይችላል። የቤተ እምነት ዓላማ የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን ፍላጎቶች ለማሟላት እንዲቻል ሀብትን ማሰባሰብ ነው። ነገር ግን የቤተ እምነት መሪዎች ልክ እንደ ማዕከላዊ ባለ ሥልጣን አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትን ለማዘዝ መጣር የለባቸውም።

ረ. ቤተ እምነቶች ይበልጥ እየገዘፉና ቢሮክራሲያዊ እየሆኑ የመሄዱን ተፈጥሮአዊ ፈተና ለመቋቋም ጥረት ማድረግ አለባቸው። አንድ ድርጅት ይበልጥ መዋቅራዊ ጥንካሬውን እያጎለበተ በሚሄድበት ጊዜ፣ አብዛኛው ገንዘብ ለአስተዳደራዊ ጉዳዮች ስለሚውል፣ አገልግሎቶች ሊዳከሙ ይችላሉ። ይህ አይሁዶች ንጉሥን በፈለጉ ጊዜ ሳሙኤል ከሰጣቸው ማስጠንቀቂያ ጋር ተመሳሳይ ነው (1ኛ ሳሙ. 8:10-18)። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ለእያንዳንዱ የመዋቅር ደረጃ የቤተ እምነቱ ወጪ ይጨምራል። ይህ ደግሞ የቤተ እምነት መሪዎች ምእመናን ገንዘብ እንዲሰጡ ለማሳመን እንዲገደዱ ያደርጋል። ይህም ምእመናን መሪዎቹ ገንዘብ ብቻ እንደሚፈልጉ በማሰብ እንዲጠራጠሯቸው ያደርጋል። የቤተ እምነት መሪዎች ገንዘቡ እንዴት ከጥቅም ላይ እየዋለ እንደ ሆነ ሪፖርት ማድረጋቸውን ያቆማሉ። ማን ገንዘብ እንደ ሰጠ፣ ምን ያህል ገንዘብ ለደመወዝ፣ ለበዓል አክባበር፣ ለትራንስፖርት፣ ወዘተ. . . እንዳገለገለ ለምእመናን ከማሳወቅ ይቆጠባሉ። በዚህ ጊዜ ምእመናን ጥርጣሬ ያድርባቸውና የሚሰጡትን ገንዘብ ይቀንሳሉ። በዚህ ጊዜ መሪዎቹ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ፕሮግራሞችን መጠቀምና እውነተኞቹን ፍላጎቶች መደበቅ ይጀምራሉ። «ማኅበረሰባችንንና አገራችንን በወንጌል እንድንደርስ ገንዘብ ስጡን፣» ሲሉ ይሰብካሉ። ነገር ግን አብዛኛው ገንዘብ የሚውለው ለአስተዳደራዊ ወጪዎች እንጂ፣ ለወንጌል አይሆንም።



11ኛ ጥያቄ:- ስለ ቤተ ክርስቲያናችሁ አስተዳደራዊ መዋቅር አስብ። ሀ) ከሦስቱ መዋቅሮች የትኛውን ነው የሚከተለው? ለ) ዘቤተ እምነታችሁ ሥልጣንን ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች አውጥቶ በተዋረድ ለተ ዋቀሩ መሪዎች ለመስጠት ጥረት የሚደረገው እንዴት ነው? ሐ) የዚህ ዓይነቱ አሠራር ጠቃሚና ጎጂ ገጽታዎች ምን ምንድን ናቸው? መ) ለቤተ እምነት መሪዎች ስለዚህ ጉዳይ ምን ምክር ትሰጣቸዋለህ?

## ሁለተኛ ቀን

### መሪዎችን በማሳደግ ላይ የሚታዩ የተለያዩ አመለካከቶች

12ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ያሉትን መሪዎችና አገልጋዮች ዘርዝር። ለ) እያንዳንዳቸው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲያገለግሉ ያስቻሏቸው ምን ዓይነት ሥልጠናዎች ናቸው? ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች በአግባቡ አለመሠልጠናቸው ምን ዓይነት ችግሮችን ያስከትላል? መ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ወይም አገልጋዮች ስለ ትምህርትና ዓላማው የተሳሳተ ግንዛቤ መያዛቸው ምን ዓይነት ችግሮችን ያስከትላል?

ለቤተ ክርስቲያናችን መሪዎችን ልናሳድግ የምንችለው እንዴት ነው? ይህ ቤተ ክርስቲያን መጠየቅ ያለባት አስፈላጊ ጥያቄ ነው። ዛሬ የመሪነት ችግር በብዙ አብያተ ክርስቲያን ውስጥ ስለሚታይ፣ ችግሩ የሚፈታባቸውን መንገዶች መፈለጉ ተገቢ ነው። ነገር ግን መሪዎችን ማሳደግ ያለብን እንደ እግዚአብሔር ቃል ነው። የዓለምን መንገድ ብንከተል፣ እንደ ዓለም አሠራር የሚመሩትን ሰ ዎች ይዘን ልናገኘው። ዛሬ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ማሳደግና ማሠልጠን የሚቻልባቸውን መንገዶች እንመለከታለን።

13ኛ ጥያቄ፡- ሀ) እግዚአብሔር ሙሴን ለመሪነት ያዘጋጀው እንዴት ነበር? ለ) ኢየሱስ ሐዋርያትን ለአገልግሎት ያዘጋጀው እንዴት ነበር? ሐ) እነዚህን መሪዎች መንፈሳዊ መሪዎች በማድረጉ በኩል የእግዚአብሔር ድርሻ ምን ነበር? መ) እግዚአብሔር ያዘጋጃቸው ሁኔታዎችስ ምን ዓይነት ሚናዎችን ተጫወቱ? ሠ) ሥልጠና የተሻሉ መሪዎች እንዲሆኑ የረዳቸው እንዴት ነበር? ሸ) የብሉይና የአዲስ ኪዳን የመሪዎች ዝግጅት ከዛሬው ዘመን የመሪዎች ዝግጅት ጋር የሚመሳሰለው ወይም የሚለየው እንዴት ነው?

1. መሪዎችን ማዘጋጀት የእግዚአብሔር፣ የግለሰቡና የሌሎችም የጋራ ጥረት ነው።

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን በመምረጡና ለአገልግሎት በማዘጋጀቱ በኩል እግዚአብሔር ቀዳሚውን ሚና እንደሚጫወት ያስረዳል። የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪ ለመሆን የሚመርጠው ግለሰቡ አይደለም። ቤተ ክርስቲያን ወይም ሽማግሌዎችም አይደሉም የሚመርጡት። እንዲያገለግለው የሚመርጠው እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ለአንድ ሰው ተፈጥሮአዊ የመሪነትን ችሎታ ይሰጠዋል። መንፈስ ቅዱስም ግለሰቡ ብቃት ያለው መሪ እንዲሆን የተፈጥሮ ስጦታውን የሚያሳድግለትን መንፈሳዊ ስጦታ ይሰጠዋል። እግዚአብሔር መሪውን ለማሳደግ ሰዎችንና ሁኔታዎችን ይጠቀማል። ከሰዎች ጋር እንዴት እንደሚዛመዱና ከሁሉም በላይ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በሳሎች እንዲሆኑ ለማስቻል ጊዜን ይጠቀማል። ሰዎችን ወደ ትምህርት ቤት መላካችን እግዚአብሔር በቀዳሚነት የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ለማዘጋጀት የሚጠቀምበት መንገድ ነው ብለን እንዳናስብ መጠንቀቅ አለብን።

ለ. የግለሰቡ ምርጫዎች ውጤታማ መሪ ሊሆን መቻል አለመቻሉን ይወስናሉ። አንድ ሰው ለመሪነት ብቁ መሆን አለመሆኑ እግዚአብሔር በሕይወቱ ውስጥ ለማድረግ የሚፈልጋቸው ነገሮችና የግለሰቡ የጋራ ሥራ ነው። እግዚአብሔር ለግለሰቡ መንፈሳዊ የማስተማር ስጦታን ይሰጠዋል። ነገር ግን ሰውዬው ስጦታውን በመጠቀም ሰዎችን ለማገልገል ላይፈልግ ይችላል። ወይም ደግሞ እግዚአብሔር አንድ ሰው በመንፈሳዊ



ሕይወቱ ከበሳልነት ደረጃ ላይ እንዲደርስ የሚያግዝ ሁኔታ ወደ ሕይወቱ ሊያመጣ ይችላል። ነገር ግን ሰውዬው እግዚአብሔር በዚህ ሁኔታ ውስጥ እንዲማር የሚፈልጋቸውን ትምህርቶች ሳይማር ሊመርጥ ይችላል። እግዚአብሔር አንድን ሰው ለመጋቢነት ሊመርጥና ግለሰቡ ግን ዓለማዊ ሥራ ላይ ለመስማራት ሊፈልግ ይችላል። ስለሆነም፣ መሪዎችን በማሳደጉ ተግባር ውስጥ ሁለተኛው ወሳኝ ነገር ግለሰቡ ራሱን ዝግ አድርጎ ከእግዚአብሔር ጋር መተባበሩ ነው።

ሐ. እግዚአብሔር መሪዎችን በሚያሳድግበት ጊዜ ሌሎች ሰዎችን ለዚህ ተግባር ይጠቀማል። ይህ አንድ ሰው የመንፈሳዊ መሪን ሕይወት አይቶ እርሱን ለመምሰል በሚያደርገው ጥረት መደበኛ ባልሆነ መንገድ የሚከናወን ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ ልምድ ያለው መሪ የመሪነት ስጦታ ያለውን ወጣት የሚያሠለጥንበት ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ በትምህርት ቤት ውስጥ የሚሰጥ መደበኛ ሥልጠና ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር እነዚህን ሁሉ በመጠቀም የአንድን ሰው የመሪነት ችሎታ ሊያሳድግ ይችላል። ከእነዚህ መካከል ምናልባትም ከሁሉም ያነሰ ውጤታማ የሚሆነው የትምህርት ቤት ሥልጠና ሊሆን ይችላል።

14ኛ ጥያቄ፡- ስለ ራስህ ሕይወት አስብ። ሀ) እግዚአብሔር በመሪነት እድገትህ ውስጥ ምን ድርሻ ነበረው? ለ) የአንተስ ድርሻ ምን ነበር? ሐ) ሌሎችስ አንተ መሪ እንድትሆን ምን ሚና ተጫወቱ?

2. ጤናማ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ለማከናወን የሚያስችሉ የተለያዩ ዓይነት መሪዎች ይኖሯታል።

ብዙውን ጊዜ ስለ መሪነት ሥልጠና በምናስብበት ጊዜ፣ የምናስበው ስለ መጋቢ ወይም ወንጌላዊ ሥልጠና ነው። ነገር ግን በሚገባ የሠለጠነ መጋቢ ወይም ወንጌላዊ እያለን፣ በሳል ቤተ ክርስቲያን ላትኖረን ትችላለች። በቤተ ክርስቲያን ብዙ የተለያዩ አገልጋዮች መኖራቸውን መረዳት አለብን። የሰንበት ትምህርት ቤት መምህራን፣ የጸሎት ቡድን መሪዎች፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መምህራንና የታመሙትን ወይም ድሆችን የሚረዱ

ሰዎች አሉ። መሪነት ሽማግሌዎችን ወይም መጋቢዎችን ብቻ የሚያካትት ነገር አይደለም። ውጤታማ ቤተ ክርስቲያን ሁሉም ዓይነት መሪዎች እግዚአብሔርን በውጤታማነት እንዲያገለግሉ ማሠልጠን አለባት።

አንድ ምሁር እንደሚለው፣ ጤናማ ቤተ ክርስቲያን (ቤተ እምነትን ጨምሮ) አምስት ዓይነት አገልጋዮች ያሉባት ናት፦

ሀ. የመጀመሪያዎቹ ዓይነት መሪዎች፦ እነዚህ በአነስተኛና ዳሩ ግን በጣም አስፈላጊ በሆኑ አገልግሎቶች ላይ የተሰማሩ በጎ ፈቃደኞች ናቸው። እነዚህ ሰዎች ብዙውን ጊዜ ለአገልግሎታቸው ሥልጠና የተሰጣቸው አይደሉም። ይሁን እንጂ፣ ቤተ ክርስቲያን ጠንካራ መሆን አለመሆኗ የሚወሰነው በእነዚህ አገልግሎቶች ነው። እነዚህ አገልጋዮች የመዘምራን አባላት፣ የአነስተኛ ቡድን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መሪዎች፣ የአምልኮ መሪዎች፣ የጸሎት ቡድን መሪዎች፣ የሰንበት ትምህርት ቤት መምህራን፣ የጽዳት አገልጋዮች፣ ወዘተ. . . ናቸው።

> 15ኛ ጥያቄ፦ ሀ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ያሉ የአንደኛ ደረጃ መሪዎችን የእሥሩን ስም ጻፍ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየሰጡ ያሉት አገልግሎት ምንድን ነው? ለ) እነዚህ አገልጋዮች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የማያገለግሉ ከሆነ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊተጓጎሉ የሚችሉ አገልግሎቶችን ግለጽ። ሐ) እነርሱ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እጅግ አስፈላጊ የሆኑ አገልጋዮች የሆኑት ለምን እንደ ሆነ አብራራ። መ) የበለጠ ውጤታማ በሆነ መልኩ በማገልገል ረገድ እነዚህ አገልጋዮች ከተጨማሪ ሥልጠናዎች በምን መንገድ ሊጠቀሙ ይችላሉ?

በእነዚህ መንገዶች በቤተ ክርስቲያናችን የሚሠሩ ሰዎችን ሁሉ የምንመዘግብ ከሆነ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ አብዛኞቹ አገልግሎቶች በእነዚህ የበጐ ፈቃድ አገልጋዮች ላይ ተደግፈው የሚገኙ እንደ ሆነ እንገነዘባለን። ካለ እነርሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች፣ ጸሎት፣ የአገልግሎት ቡድኖች፣ የእሑድ ትምህርት ቤት፣ ወዘተ. . . አይኖርም። ጠንካራ ቤተ ክርስቲያን የአንደኛ ደረጃ መሪዎችን ቁጥር ለመጨመር ሁልጊዜ ትሻለች። ልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች በተቻለ መጠን ውጤታማ በሆነ መልኩ



እንዲከናወኑ ይህን የመሪዎች ደረጃ በሥልጠና ለመደገፍ አመቺ መንገዶችን ጭምር ትፈልጋለች።

ለ. ሁለተኛ ደረጃ መሪዎች፦ እነዚህም መሪዎች እንደዚሁ የበጎ ፈቃድ አገልጋዮች ናቸው፣ ነገር ግን አገልግሎቶቻቸው በአብዛኛው በመላው ቤተ ክርስቲያን ተጽዕኖን የሚያሳድር ነው። መደበኛ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አይኖራቸው ይሆናል፣ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ ወይም ወንጌላዊ አይደሉም ይሆናል። ነገር ግን በብስለታቸው እና መንፈሳዊ ሕይወታቸው ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚያሳድሩት ተጽዕኖ ምክንያት፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመሪነት ኃላፊነት ተሰጥቷቸዋል። እነዚህ መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንዳንድ የአገልግሎት ክፍሎች መሪ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ ያህል፣ የጸሎት አገልግሎትን፣ ወይም የእሑድ ትምህርት ቤቶች፣ ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መርሐ ግብሮችን የሚያስተባብሩ ሊሆኑ ይችላሉ። አሊያም እንደ ዲያቆናት፣ ሽማግሌዎች፣ የወጣቶች ቡድን መሪ ወይም የሴቶች ቡድን መሪ ሆነው ተመርጠው መደበኛ ወደ ሆነው የቤተ ክርስቲያን አመራር ስፍራዎች የመጡ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ። በአብዛኛው የቤተ ክርስቲያንን አመራር በተመለከተ መደበኛ የሆነ ሥልጠና ያላገኙ ናቸው። በዓለም ውስጥ ሥልጠና አግኝተዋል። ይሁን እንጂ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሰዎች ላይ ተጽዕኖን የሚሰድሩ ስለሆኑ፣ ለአመራር ስፍራዎች የተመረጡ ናቸው።

> 16ኛ ጥያቄ፦ ሀ) በመላው ቤተ ክርስቲያናችሁ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ የሁለተኛ ደረጃ መሪዎችን ስም ዘርዝር። ለ) እነዚህ ሰዎች ለቤተ ክርስቲያናችሁ በጣም ጠቃሚ የሆኑት እንዴት እንደ ሆነ አብራራ። ሐ) ተጨማሪ ሥልጠና ካገኙ፣ እነርሱም ሆነ ቤተ ክርስቲያን ተጠቃሚ የሚሆኑት በምን መንገድ ነው?

ሽማግሌዎች፣ ዲያቆናት፣ የእሑድ ትምህርት ቤት መርሐ ግብሮች አስተባባሪዎች፣ ወዘተ. . . የሌላትን ቤተ ክርስቲያን አስቡ! በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለእግዚአብሔር የሚደረግ አገልግሎት በጣም ትንሽ ነው የሚሆነው። እግዚአብሔርን በበለጠ ውጤታማነት ማገልገል ይችሉ ዘንድ እነዚህ የበጐ ፈቃድ

አገልጋዮች ሥልጠና ካገኙ፣ አንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ምን ያህል የበለጠ ውጤታማ እንደምትሆን አስብ! ልክ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥራውን እንደሚያከናውኑ የበጐ ፈቃድ አገልጋዮች፣ ሁለተኛ ደረጃ መሪዎች የጠንካራ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ናቸው። በዙሪያቸው ያለው ማኅበረሰብን ለመለወጥ እግዚአብሔር የሚጠቀምባት ቤተ ክርስቲያን እንድትኖር የመጨረሻው ወሳኝ ነገር የእነርሱ አገልግሎት ነው።

ሐ. ሦስተኛ ደረጃ መሪዎች፡- እነዚህ በአብዛኛው ልክ እንደ መጋቢ፣ ወንጌላዊ ያሉ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች፣ ወይም እንዳንድ ጊዜ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሽማግሌዎች ሰብሳቢ የሆኑ ሰዎች ናቸው። በገጠር አብያተ ክርስቲያናት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ደመወዝ የሚከፈላቸው የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ላይሆኑ ይችላሉ፣ ነገር ግን ዋነኛውን የቤተ ክርስቲያንን አመራር የማስተማር አገልግሎቶች ያከናውናሉ። በከተሞች ባሉ አብያተ ክርስቲያናት እነርሱ የሽማግሌዎች ሰብሳቢ፣ መጋቢ እንዲሁም የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ተቀጣሪ አገልጋዮች ናቸው።

17ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ያሉ ደረጃ ሦስት መሪ ዎችን ስም ዘርዝር። ለ) እነዚህ መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለመሥራት በበቂ ሁኔታ መሠልጠናቸው ጠቃሚ የሚሆነው ለምንድን ነው ብለህ ታስባለህ?

አንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ ቤተ እምነት ጠንካራ ሊሆን የሚችለው ደረጃ ሦስት መሪዎች ውጤታማ በሆኑ መጠን ብቻ ነው። ጠንካራ ቤተ እምነት የሚመሠረተው አባላቶቻቸው የእግዚአብሔርን ቃል የሚያውቁና ለእግዚአብሔር በመታዘዝ በሚኖሩ ብዙ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ነው። አብያተ ክርስቲያናት ወደ መንፈሳዊ ብስለት ያድጋሉ ወይስ አያድጉም የሚለውን በመወሰን ረገድ ደረጃ ሦስት መሪዎች በጣም አስፈላጊ ናቸው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ አገልግሎቶችን በተመለከተ አብዛኞቹን ዋና ዋና ውሳኔዎች የሚያስተላልፉት የደረጃ ሦስት መሪዎች ናቸው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን አብዛኛውን የስብከትና የትምህርት አገልግሎት የሚሸፍኑት እነርሱ ናቸው።



በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥም እንዲሁ የደረጃ አንድና የደረጃ ሁለት አገልጋዮችን የሚያሠለጥኑት እነርሱ ናቸው። ስለዚህ፣ እግዚአብሔርን የሚያደምጥ ቤተ እምነት፣ የአመራር (መሪነት) ሥልጠናውን በእነዚህ ዋጋ ባላቸው መሪዎች ላይ በማነጣጠር ማካሄድ ይኖርበታል።

እነዚህ መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስፈላጊ አመራርና የማስተማር ሚናዎች ያሏቸው በመሆኑ፣ ተገቢ በሆነ መንገድ መሠልጠናቸው አስፈላጊ ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአብዛኛ ው መጋቢው እና ወንጌላዊው አብዛኛውን የማስተማርና የወንጌል ማዳረስ ተግባር፣ ደግሞም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉ መሪዎችን ማሠልጠን በቀጥታ ያከናውናሉ። ስለዚህ፣ መደበኛ የሆነ የሥነ መለኮት ትምህርት ሥልጠና ሊኖራቸው ይገባል። በሌሎች ዓይን ተቀባይነት እንዲኖራቸው፣ በዚህም አባላቱ እንዲያደምጡዋቸው፣ እነዚህ አገልጋዮች በማኅበረ ምእመኑ ካሉት ከአብዛኛዎቹ ሰዎች በትምህርት አንድ ደረጃ ከፍ ያሉ መሆን ይኖርባቸዋል። የሽማግሌዎች ሰብሳቢ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ተጽዕኖ የሚያሳርፉ ብዙ ውሳኔዎችን የሚያስተላልፍ ስለሆነ፣ እርሱም ጭምር የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ሥልጠና ያስፈልገዋል። ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ለመሄድ የማይቻለው ከሆነ፣ እንደ ት.መ.ማ ወይም ቢ.ቲ.ሊ.ፒ. (የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጠና - ለመጋቢዎችና ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች) ያሉ መደበኛ ባልሆኑ የሥልጠና መርሐ ግብሮችን መጠቀም ይኖርበታል። አመራራቸውን በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች መሠ ረት ላይ ማድረግን ለመፍቀድ በእግዚአብሔር ቃል ላይ በቂ የሆነ ትምህርት ከሌላቸው፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመምራት ለሽማግሌዎች፣ በተለይም ለሽማግሌዎች ሰብሳቢ ይህ አደገኛ ነገር ነው። እንዲሁም እግዚአብሔር ሽማግሌ ለመሆን ከአንድ ሰው የሚጠብቀው «ለማስተማር የሚበቃ» የሚል ሲሆን፣ ይህም አገልጋዮቹ በእግዚአብሔር ቃል መሠልጠን ይገባቸዋል ማለት ነው።

መ. ደረጃ አራት መሪዎች፦ ደረጃ አራት መሪ፣ ምናልባት ትልቅ የሆነ በከተማ ውስጥ ያለ ቤተ ክርስቲያን መሪ (መጋቢ) ሊሆን ይችላል። ወይም የብዙ ቤተ ክርስቲያኖች ኃላፊነት የወደቀባቸው ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አስተ ማሪዎች አስተባባሪ፣ የወንጌል ስርጭት ሥራ አስተባባሪዎች፣ ወዘተ. . . ያሉ የክልል አገልግሎት አስተባባሪዎች ያሉትም እንደዚሁ ከደረጃ አራት መሪዎች ሊመደቡ ይችላሉ። አሊያም የክልል ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ።

ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ያሉት መሪዎች ከቤተ ክርስቲያናቸው ሰዎች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ሲኖራቸው፣ ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር በመሥራት በሰዎች ላይ ቀጥተኛ ያልሆኑ ተጽዕኖዎችን ያሳድራሉ። አገልግሎቶችን (ለምሳሌ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መምህራን፣ የወንጌል ስርጭት አስተባባሪዎች) በማስተባበር ላይ ከተሳተፉ፣ በሚገባ መሠልጠን አለባቸው። የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪነት ሥልጠና ያገኘን ሰው የወንጌል ስርጭት ኃላፊ ማድረጉ ጥቅም የለውም። ይህ የእርሱ ችሎታ አይደለም። ወይም ደግሞ የተወሰነ የሥነ-መለኮት ሥልጠና በማግኘቱ ምክንያት የአገልግሎት አስተባባሪነትን ሥራ መስጠቱ ተገቢ አይሆንም። ነገር ግን እነዚህ የአገልግሎት አስተ ባባሪዎች በሚያስተባብሩት የአገልግሎት ዘርፍ በቂ ሥልጠና ሊኖራቸው ይገባል። ይህ ካልሆነ፣ በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ከፍተኛ ሊሆን አይችልም።

የደረጃ አራት መሪዎች እንደ ቀጣና መሪዎች አስተዳደራዊ መሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት መምራት የሚችሉ ሊሆኑ ይገባል። ይህ ካልሆነ፣ ሰዎቹ የቀጣና መሪነትን ቦታ ቢይዙም፣ በአብያተ ክርስቲያናት ላይ ለውጥ ለማምጣት አይችሉም። በዚህ ደረጃ ላይ ያሉት መሪዎች ግብ በቀዳሚነት በአብያተ ክርስቲያናቱ ውስጥ የሚከሰቱትን ነገሮች መቆጣጠር ወይም ማስተዳደር አይደለም። ከዚህ ይልቅ፣ ትኩረት የሚሰጠው የእነዚህን መሪዎች ችሎታዎችን በማሳደግ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች፣ ወንጌላውያንና ሽማግሌዎች የተሻለ አገልግሎት እንዲሰጡ ማስቻል ነው።



18ኛ ጥያቄ፦ ሀ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ያሉትን አራተኛ ዓይነት መሪዎች ዘርዝር። ለ) የእነዚህ መሪዎች ሥልጠናና ችሎታ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካሉት መሪዎች ልቆ መገኘት ያለበት ለምንድን ነው? ሐ) በዚህ ደረጃ ላይ ያሉት መሪዎች አብያተ ክርስቲያናት በመንፈሳዊ ብስለታቸው እንዲያድጉ ለማገዝ የሚጫወቱት ሚና ምንድን ነው?

ሠ. አምስተኛ ዓይነት መሪዎች፦ እነዚህ በአገሪቱ ወይም በቤተ እምነቱ ከፍተኛ የሥነ-መለኮት ትምህርት የሚሰጡ ሰዎች ናቸው። በእያንዳንዱ ቤተ እምነት በአገልግሎት ዘርፋቸው ምሑር የሆኑ ሰ ዎች ያስፈልጋሉ። ስለሆነም፣ የልማት፣ የወንጌል ስርጭት፣ የሥነ-መለኮት ወይም የአመራር ምሑራን አስፈላጊዎች ናቸው። እነዚህ ምሑራን ሦስት አስፈላጊ ሚናዎችን ይጫወታሉ።

በመጀመሪያ፣ በአገሪቱ ውስጥ ያሉትን አሳሳቢ ችግሮች በማጥናት አብያተ ክርስቲያናት እነዚህን ችግሮች እንዲፈቱ ጥረት ያደርጋሉ። እንደ ውርጃ፣ የወሊድ ቁጥጥር፣ የሴቶች ግርዛት፣ የሐሰት ትምህርት መስፋፋት፣ ምእመናንን እንዴት ወደ ብስለት ማድረስ እንደሚቻል፣ ወዘተ. . . የተለያዩ መፍትሔዎችን ያቀርባሉ።

ሁለተኛ፣ ለደረጃ ሦስትና አራት መሪዎች አሠልጣኞች ሆነው ያገለግላሉ።

ሦስተኛ፣ በቤተ ክርስቲያን አመራር ላይ በቂ ችሎታ ያላቸው የቤተ እምነት መሪዎችም ናቸው።

እነዚህ ወገኖች በተሰጣቸው የአገልግሎት ዘርፍ ከፍተኛ ችሎታ እንዳላቸው ያረጋገጡ በመሆናቸው፣ በመሪነት ቦታቸው መመረጥ አለባቸው። ስለሆነም፣ የቤተ እምነቱ የወንጌል ጉዳይ ኃላፊዎች ከሆኑ፣ ክህሎት ያላቸው ወንጌላውያን መሆናቸው መ ረጋገጥ አለበት። ሰዎች እነዚህን መሪዎች የሚከተሉት ዲግሪ ስላላቸው ሳይሆን፣ እግዚአብሔር በአገልግሎት ዘርፋቸው ታላላቅ ነገሮችን ስላደረገ ሊሆን ይችላል። በአገልግሎት ዘርፋቸው በቂ ሥልጠና ያገኙ መሆን አለባቸው። የቤተ እምነት መሪዎች እንዲሆኑ ከተመረጡ፣ ውጤታማ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መሆናቸውን ያሳዩ መሆን አለባቸው። ጥሩ የሥራ መሪ መሆኑ

ብቻ በቂ አይደለም:: ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች የንግድና የሥራ ድርጅቶች የተለየች ነች:: የንግድ ሙያ ያላቸው ከሆነ፣ ውጤታማ የወንጌል ስርጭት መሪ ስመሆን እችላለሁ ብለው ማሰብ የለባቸውም:: የቤተ ክርስቲያን አመራር ክህሎት የሌለውን ሰው የዩኒቨርስቲ ዲግሪ ስላለው ብቻ በአመራር ላይ ማስቀመጥ ጥሩ ውጤት ሊያስገኝ አይችልም::

> 19ኛ ጥያቄ:- ሀ) በቤተ እምነታችሁ ውስጥ እንደ ምሑራን (ልሁቃን) የምትቆጥራቸውን ሰዎች ዘርዝር:: ልሁቃን ናቸው ብለህ የምታስበው ለምንድን ነው? በቤተ እምነት ደረጃ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የተለያዩ ዘርፎች ላይ ልሁቃን መኖራቸው አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው? ለ) የቤተ እምነታችሁን መሪዎች ዘርዝር:: እንደ ቤተ እምነት መሪ ዎች ውጤታማ መሪነት እንዲሰጡ ያስቻሏቸው ሥልጠናዎች ምን ምንድን ናቸው?

3. እግዚአብሔር በእያንዳንዱ ዓይነት አመራር ላይ ያሉት ሰዎች በአመራራቸው እንዲያድጉ የደነገገው የተሰጣቸውን ኃላፊነት በብቃት ከተወጡ በኋላ ተጨማሪ ኃላፊነት እንዲሰጣቸው ነው::

ስለሆነም፣ አንድ ሰው በአንደኛው ዓይነት አመራር ላይ ተ ሳትፎ ውጤታማ የመጽሐፍ ቅዱስ የማስተማር አገልግሎት ከሰጠ፣ ወደ ሁለተኛው ዓይነት መሪነት ማደግና በቤተ ክርስቲያን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መሪዎችን የማሠልጠን ኃላፊነት ሊሰጠው ይገባል:: በዚህ በኩል ውጤታማ ከሆነ ደግሞ፣ የበለጠ ሥልጠና ተሰጥቶት ደመወዝ እየተከፈለው በሙጋቢነት ወደሚያገለግልበት የሦስተኛው ዓይነት መሪነት ማደግ አለበት:: በዚህ ደረጃ ውጤታማ ከሆነ ደግሞ፣ ተጨማሪ ሥልጠና ተ ሰጥቶት በአካባቢው ለብዙ አብያተ ክርስቲያናት የሚሰጠውን ሥልጠና ወደሚከታተልበት ደረጃ ማደግ አለበት:: በዚህም በኩል ውጤታማ ከሆነ፣ ሥልጠና ተሰጥቶት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሌ ሎችን የሚያሠለጥን ምሑር ወደሚሆንበት ደረጃ መሸጋገር አለበት::

በመሪነት ደረጃ ወደ ላይ ለማደግ ዋናው መስፈርት ተጨማሪ ሥልጠና ማግኘቱ ሳይሆን፣ ተጨማሪ የመሪነት ክህሎቶችን



ማሳየት ነው:: ለደረጃው የሚመጥን ባሕርይና ክህሎት ያላሳየን ሰው ማሳደጉ አደገኛ ነው:: አንድን ሰው ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪነት ወደ ቤተ እምነት መሪነት በቀጥታ ማሸጋገሩ አስተዋይነት አይደለም::

> 20ኛ ጥያቄ:- ሀ) አንድ አገልጋይ ለተጨማሪ አገልግሎት የሚያበቃ ባሕርይና ክህሎት ያለው ሆኖ በመገኘቱ ከአነስተኛ የመሪነት ደረጃ ወደ ከፍተኛ የመሪነት ደረጃ ሲሸጋገር የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ:: ግለሰቡ በከፍተኛ የመሪነት ደረጃው ውጤታማ ሊሆን ቻለ? ለ) ለአገልግሎቱ የሚያስፈልገውን ባሕርይና ክህሎት ሳያሟላ የተወሰነ ሥልጠና በማግኘቱ ብቻ የመሪነት እድገት በማግኘቱ ውጤታማ ሊሆን ያልቻለ ሰው ታውቃለህ?

4. አንዳንድ ምሑራን ጤናማ ቤተ እምነት የሚከተለውን የመሪ ዎች ዓይነት ስብጥር ማካተት አለባት ይላሉ:-

ሀ. <u>አንደኛ ዓይነት</u> መሪዎች:- ለየአሥሮቹ ምእመናን አንድ በጎ ፈቃደኛ መሪ መኖር አለበት:: ስለዚህ፣ 400 ምእመናን ሳሉባት ቤተ ክርስቲያን በአነስተኛ ቡድኖች ውስጥ በንቃት የሚሳተፉ ቢያንስ 40 ሰዎች መኖር አለባቸው ማለት ነው:: ብዙውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁሉንም ተግባር የሚያከናውኑት ጥቂት ሰዎች ናቸው:: በመዘምራን ቡድን ውስጥ የሚዘምሩ ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶችንና የሰፈር የጸሎት ስብሰባዎችን ያስተ ባብራሉ:: እነዚህ ሰዎች ብዙ ከመሥራታቸው የተነሣ ይደክማሉ:: በቂ ጊዜ ስለማያገኙም፣ ጥራት ያለው አገልግሎት ለመስጠት ይቸገራሉ:: ሌሎች መንፈሳዊ ስጦታ ያላቸው ሰዎች ግን ምንም ነገር ሳይሠሩ ቁጭ ይላሉ:: ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ጠንካራ ልትሆን የምትችለው፣ ሁሉም ምእመናን መንፈሳዊ ስጦታዎቻ ቸውን ተጠቅመው የሚያገለግሉ ሲሆን ነው:: ስለሆነም፣ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአገልግሎት ላይ የሚሳተፉ ሰዎችን ቁጥር ለመጨመር ጥረት ማድረግ አለባቸው::

ለ. ሁለተኛ <u>ዓይነት</u> መሪዎች:-- ለየኀምሳዎቹ ምእመናን ቢያንስ ሁለት በጎ ፈቃደኛ መሪ ያስፈልጋቸዋል:: ይህ ማለት 400

ምእመናን ባሉባት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ 8 ሁለተኛ ዓይነት መሪ ዎች ያስፈልጋሉ ማለት ነው፡፡

ሐ. ሦስተኛ ዓይነት መሪዎች፡- ለ200 ምእመናን ወይም ለየ20 ዎቹ የሁለተኛ ደረጃ መሪዎች በሚገባ የሠለጠነ የሙሉ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ስለዚህ፣ 400 ምእመናን ያሉባት ቤተ ክርስቲያን ሁለት በሚገባ የሠለጠኑ ሦስተኛ ዓይነት መሪ ዎችን መቅጠር ይኖርባታል፡፡

መ. አራተኛ ዓይነት መሪዎች፡- ለየአንድ ሺህ ምእመናን ወይም ለየ20ዎቹ ሦስተኛ ዓይነት መሪዎች አንድ አራተኛ ዓይነት መሪ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ፣ 400 ምእመናን ያሏት ቤተ ክርስቲያን አራተኛ ዓይነት መሪ አያስፈልጋትም ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ከ1000 በላይ ምእመናን ወይም የየራሳቸው መጋቢዎች ላሉባቸው 20 አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የዚህ ዓይነቱን መሪ መቅጠሩ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ትልቁ ነገር የቀጣና ኃላፊ የሆነ ሰው መኖሩ ሳይሆን፣ የተፈለገውን አገልግሎት ለመፈጸም የሚያስችሉ ክህሎቶችና ሥልጠናዎች ያሉት መሪ መኖሩ ነው፡፡ ሥልጠናውና ክህሎቱ የሌለው ሰው አራተኛ ዓይነት መሪነት መያዙ ምንም ጥቅም የለውም፡፡ አብያተ ክርስቲያናት በመንፈሳዊ ሕይወትና አገልግሎት እድገት እንዲያሳዩ የሚያስችል ሥልጠና ለአንድ ሰው መስጠቱም ዋጋ የለውም፡፡ በዚህ ደረጃ የሚሠራ መሪ 1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ዓይነት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችን አገልግሎት ለማሳደግ የሚጥር ነው፡፡ ስለሆነም፣ በአስተዳዳሪነት ወጥመድ መያዝ የለበትም፡፡

ሠ. አምስተኛ ዓይነት መሪዎች፡- ለየአሥር ሺህ ምእመናን ወይም ለየ20ዎቹ አራተኛ ዓይነት መሪዎች አንድ አምስተኛ ዓይነት መሪ ሊኖር ይገባል፡፡

21ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችሁ ወይም በቤተ እምነታችሁ በእያንዳንዱ ዓይነት አመራር ላይ ያሉትን ሰዎች ስሞች ዘርዝር፡፡ ለ) ከዚህ በላይ በየደረጃው የተጠቀሱት መሪዎች ለስንት ምእመናን እንደሚያስፈልጉ የተገለጸውን አስብ፡፡ ቤተ ክርስቲያናችሁ ከላይ የተ መለከተውን የአገልጋዮች ቁጥር ለመጠበቅ ምን ያህል ጥረት አያደረገች ነው? የቤተ ክርስቲያናችሁ ደካማና ጠንካራ ጎኖች ምን ምንድን ናቸው? ሐ) እነዚህ አምስት ዓይነት መሪዎች በጥሩ ሁኔታ አገልግሎት እንዲያበ ረክቱ ቤተ ክርስቲያናችሁ ልታደርግ የምትችላቸው ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?



5. 1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ዓይነት መሪዎች ለእያንዳንዷ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጤንነት እጅግ ወሳኞች ናቸው፡፡ የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት የሚያከናውኑት እነርሱ ናቸው፡፡

አነስተኛ ቁጥር ያላቸው 4ኛ እና 5ኛ ዓይነት መሪዎች መኖራቸውና ምእመናን ስለ እግዚአብሔር ቃል ጥልቅ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ቢያደርጉ፣ እንዲሁም 3ኛ ዓይነት መሪዎችን ቢያሠለጥኑና ለተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ስልታዊ ሥልጠናዎችን ቢያዘጋጁ መልካም ነው፡፡ ነገር ግን እነዚህ መሪ ዎች በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ላይ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉት በ1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ዓይነት መሪዎች ላይ ለውጥ ለማምጣት ሲችሉ ብቻ ነው፡፡ የየትኛውም ሥልጠና ፕሮግራም ስኬታማነት 1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ዓይነት መሪዎችን በሚገባ በማዘጋጀት ላይ የተ መሠረተ ነው፡፡ የሥልጠና ፕሮግራሙ በ4ኛ እና 5ኛ ዓይነት መሪ ዎች ላይ ካተኮረና ከ1-3 ባሉት መሪዎች ላይ ለውጥ ለማምጣት ካልተቻለ፣ የሥልጠና ፕሮግራሙ ዋጋ የለውም፡፡ ሁልጊዜም የሥልጠናዎች ግብ መሆን ያለበት ብዙ የተማሩ ሰዎችን ማፍራት ሳይሆን፣ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለውጥ ማምጣት መሆን አለበት፡፡

22ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በቤተ እምነታችሁ ወስጥ መደበኛ ሥልጠና ስለሚሰጣቸው ሰዎች አስብ፡፡ እነዚህ ሰዎች በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በ1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ዓይነት መሪዎች ላይ ምን ዓይነት ለውጦችን በማምጣት ላይ ናቸው? ለ) የሥነ-መለኮት የሥልጠና ፕሮግራም መገምገም ያለበት በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ላይ በሚያመጣው ለውጥ መሆን ያለበት ለምንድን ነው?

6. አብያተ ክርስቲያናት አገልጋዮችን ከ1ኛ እና 2ኛ መሪነት ወደ 3ኛ፣ 4ኛ እና 5ኛ መሪነት በሚያሸጋግሩበት ጊዜ ጥንቃቄ ማድ

ረግ ይኖርባቸዋል። ብዙ የ3ኛ፣ 4ኛ እና 5ኛ ዓይነት መሪዎች ካሉ፣ የሚከተሉት ችግሮች ሊፈጠሩ ይችላሉ፡-

ሀ. ብዙ ደመወዝ የሚከፈላቸው ሰዎች ይኖራሉ። ይህም የቤተ ክርስቲያኒቱን የገንዘብ አቅም ያዳክማል። አንድ ሰው በአመራር ደ ረጃ ከፍ እያለ በሚሄድበት ጊዜ፣ በአብዛኛው ብዙ ደመወዝ ስለሚከፈለው፣ በከፍተኛ ደረጃ ላይ ያሉት መሪዎች ለቤተ ክርስቲያን በጣም ውድ ይሆናሉ። ስለሆነም፣ እያንዳንዱ ቤተ እምነት ከ4ኛ እስከ 5ኛ ደረጃ ላይ ያሉትን መሪዎች ለመቀነስና ውጤታማነታቸውን ለመጨመር መጣር አለበት።

ለ. ቤተ ክርስቲያኒቱ ብዙ «አለቆች» እና ጥቂት ሠራተኞች ይኖሯታል። ብዙ ሰዎች ውሳኔ ሰጭዎች ይሆኑና ሥራውን ተ ግባራዊ የሚያደርጉ ሰዎች አይኖሩም። አገልግሎቶችን ተግባራዊ የማያደርጉ ብዙ ሊቆች መኖራቸው የእግዚአብሔርን መንግሥት እምብዛም አያሳድግም።

ሐ. ብዙ የ3ኛ፣ 4ኛ እና 5ኛ ዓይነት መሪዎች በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለውጥ እንዳይመጣ ይገድባሉ። ምክንያቱም ብዙውን ጊዜ ለውጥ የሚያመጡ ሰዎች በቀጥታ በአገልግሎት ውስጥ የተ ሳተፉ ናቸው። ውጤታማ የመሪዎች ሥልጠና የ1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ደረጃ መሪዎችን በመለወጥ የምእመናንን መንፈሳዊ ሕይወት እንዲያሳድጉ ይረዳቸዋል።

መ. ብዙ የ3ኛ፣ 4ኛ እና 5ኛ ዓይነት መሪዎች በሚኖሩበት ጊዜ ምእመናን ተግተው አያገለግሉም። በአዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ብዙ ሰዎች አገልግሎት ላይ እንደሚሰማሩ ይታወቃል። ነገር ግን ደመወዝ የሚከፈላቸው መጋቢዎች፣ ወንጌላውያንና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት አስተማሪዎች በሚበዙበት ጊዜ ምእመናን እነዚሁ ሰዎች ሥራውን እንዲያከናውኑ ስለሚጠብቁ፣ ራሳቸውን ከአገልግሎት ያገልላሉ።

ሠ. ቤተ ክርስቲያን አብዛኛውን ገንዘብ ለምእመናን መንፈሳዊ ብስለት ብዙም እገዛ ለማያደርጉ ሰዎች ታውላለች። ቤተ ክርስቲያን ጠንካራ ልትሆን የምትችለው የ1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ደረጃ



መሪዎች ውጤታማ አገልግሎት ሲሰጡ ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አብዛኛውን ሥራ የሚሠሩትና ምእመናን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ የሚረዱት እነርሱ ናቸው። ስለሆነም፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሥልጠና የሚወጣው ገንዘብ እነርሱን በማጠናከሩ ላይ ሊውል ይገባል። ነገር ግን 3ኛ፣ 4ኛ እና 5ኛ ዓይነት መሪዎችን ማሠልጠኑ ውድ ዋጋ ስለሚጠይቅ፣ አብዛኛው ገንዘብ የሚወጣው በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ደረጃ ለማይሠሩ ሰ ዎች ነው። ይህ ውድ የሆነውን የቤተ ክርስቲያን ገንዘብ አላግባቡ መጠቀማችንን የሚያሳይ ነው። አስተዋይ ቤተ ክርስቲያን ሁልጊዜ ም አገልጋዮችን በማዘጋጀቱ ረገድ ከፍተኛ ትኩረት የምትሰጠው ሥራውን በሚያከናውኑት ሰዎች ላይ እንጂ ደመወዝ ተከፋይ በሚሆኑት ላይ ብቻ አይደለም።

| |
|---|
| 23ኛ ጥያቄ፡- ሀ) እነዚህ ማስጠንቀቂያዎች በቤተ ክርስቲያናችሁ እውን ሲሆኑ የተመለከትከው እንዴት ነው? ለ) ቤተ ክርስቲያናችሁ ከ3ኛ፣ 4ኛ እና 5ኛ መሪዎች ይልቅ 1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ዓይነት መሪዎችን በማ-ሠልጠኑ ተግባር ላይ ገንዘቧን ብታውል ምን የሚከሰት ይመስልሃል? |

7. አንዳንድ ምሁራን ለአንድ አገልጋይ የሚሰጠው ሥልጠና ከአብዛኞቹ ምእመናን አንድ ደረጃ ብቻ ሊያስበልጠው እንደሚገባ ያምናሉ።

ይህም ማለት አብዛኞቹ ምእመናን መሐይማን ከሆኑ፣ በጣም ውጤታማ የሚሆነው መሪ የምስክር ወቀረት ያለው ይሆናል ማለት ነው። ነገር ግን በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ያሉት አብዛኞቹ ምእመናን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ከሆኑ፣ ከፍተኛ ውጤታማ የሚሆነው አገልጋይ ዲፕሎማ ያለው ይሆናል ማለት ነው። ብዙ ምእመናን ዲፕሎማ በያዙባቸው ስፋፊ የከተማ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት አገልጋዩ የዲግሪ ምሩቅ መሆን አለበት ማለት ነው።

ብዙውን ጊዜ አገልጋዩ በርካታ ሥልጠናዎችን ካገኘ፣ ከሚያገለግላቸው ሕዝብ ጋር ለመግባባት የሚቸገርበት ክፍተት ይፈጠራል። ይህም ክፍተት አገልጋዩ በሥልጠናው ምክንያት የተ ሻለ ደመወዝ በማግኘቱ ምክንያት የተፈጠረ የገንዘብ ልዩነት ሊሆን

ይችላል። ይህ የማንኙነት ክፍተቶችንም ይፈጥራል። ከፍተኛ ትምህርት ያላቸው መሪዎች ካልተማሩ ምእመናን ጋር የአሳብ ልውውጥ ለማድረግ ይቸገራሉ። ምክንያቱም የተማሩ ሰዎች ነገሮችን የሚገልጹበት መንገድ ያልተማሩ ሰዎች ከሚረዱበት በላይ ሊሆን ይችላል። ብዙዎቻችን ይህ ችግር ገጥሞናል። በእመዛኙ ሁለት ዲግሪዎች ያሏቸው ሰዎች ማንበብና መጻፍ የማይችሉትን የገጠር ሰዎች ለማስተማር ይቸገራሉ። የሥነ-መለኮት ትምህርት ግለሰቡ ቀደም ሲል የነበረውን ያህል በገጠር የትውልድ አካባቢው ከሰዎች ጋር እንዳይግባባ ያደርገዋል።

እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ብዙ ሰዎች በትምህርትም ሆነ በኢኮኖሚ ከእነርሱ ከአንድ እርከን በላይ ያነሱትን ሰዎች ለማገልገል አይፈልጉም። ስለዚህ፣ አንድ ሰው የዲፕሎማ ምሩቅ ከሆነ፣ አብዛኞቹ ሰዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ወዳላጠናቀቁባቸው ወይም ለዲፕሎማ ምሩቅ የሚገባውን ደመወዝ ወደማይከፍሉበት የገጠር አካባቢዎች ሄዶ አያገለግልም።

ይህ ማለት በስልታዊ የመሪዎች የልማት/የሥልጠና ዕቅዳችን ለአብያተ ክርስቲያኖቻችን የሚያስፈልገን የሥልጠና ደረጃ መወሰን አለብን ማለት ነው። የሥልጠናውን ደረጃ የሚወስነው የአብዛኞቹ ምእመናን የትምህርትና የኢኮኖሚ ደረጃ ነው። በአንዲት የገጠር ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዲፕሎማ ያላቸው ጥቂት የመንግሥት ሠራተኞች ቢኖሩና አብዛኞቹ ምእመናን ግን ከስድስተኛ ክፍል ያልዘለሉ ከሆነ፣ መጋቢው ዲፕሎማ መያዝ አለበት ማለቱ አስፈላጊ ላይሆን ይችላል። እንደዚያ ካደረግን ግን፣ ከአብዛኞቹ ይልቅ ሁለቱን ሰዎች ብቻ ማገልገላችን ነው። ለመጋቢዎች ከፍተ ኛ ትምህርት ከመስጠታችን በፊት በሚገባ ማሰብ ይኖርብናል። ትልቁ ጥያቄ፣ «እግዚአብሔር በእረኝነት እንድናገለግል የሰጠንን ሰ ዎች በአግባቡ እየተንከባከብን ነው ወይ?» የሚለው ነው። አብዛኞቹ ምእመናን ከ10ኛ ክፍል በታች ስሆኑባቸው የገጠር አብያተ ክርስቲያናት የምስክር ወረቀት ያለው መጋቢ የተሻለ አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል። አብዛኞቹ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ሳጠናቀቁባቸውና ጥቂቶች ደግሞ የዲፕሎማ



ምሩቃን በሆኑባቸው አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ዲፕሎማ ያላቸው መጋቢዎች ቢያገለግሉ መልካም ነው። አብዛኞቹ ሰዎች ከፍተኛ ትምህርት ባገኙባቸው የከተማ አብያተ ክርስቲያናት የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው፣ ኮሌጆች ባሉባቸው ወይም ምእመናን ዲግሪ በያዙባቸው አካባቢዎች ደግሞ ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው መጋቢዎች ቢያገለግሉ የተሻለ ነው።

24ኛ ጥያቄ:- ሀ) አገልጋይ ከምእመናኑ ከአንድ ደረጃ በላይ መብለጥ የለበትም የሚለውን አሳብ ትደግፋለህ? ለምን? ለ) ብዙ ትምህርት በመጋቢውና በምእመናን መካከል ክፍተት ሲፈጥር የተመለከትከበትን ሁኔታ ግለጽ። ሐ) አገልጋዩ በትምህርት ደረጃው ከእነርሱ በታች በመሆኑ ምክንያት ምእመናን እርሱን የናቁበትንና የሚናገራቸውን ነገሮች ከመስማት የተቆጠቡበትን ሁኔታ ግለጽ።

8. የመሪዎች ሥልጠና የአገልግሎት ሽልማት ሳይሆን፣ አገልግሎትን ለማሳደግ የሚያግዝ መሣሪያ ነው።

አንዳንድ ጊዜ ለተወሰነ ጊዜ በማገልገላቸው ምክንያት ሰዎችን ለተጨማሪ ትምህርት ለመላክ የምንፈተንባቸው ጊዜያት አሉ። ተ ጨማሪ ሥልጠና ለቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች እንደሚሰጥ ጥቅም ወይም ሽልማት የሚታይበት ጊዜ አለ። ነገር ግን ተጨማሪ ትምህርት የሠራተኛው መብት መሆን የለበትም። ተጨማሪ ትምህርትን መመልከት ያለብን የአገልግሎት ክህሎትን ለመጨመር እንደሚያግዝ መሣሪያ ወይም ለተጨማሪ ኃላፊነት እንደሚያዘጋጅ ነገር ነው። አንዲት ቤተ ክርስቲያን ተጨማሪ ሥልጠና መስጠት አስፈላጊ መሆኑንና አንድ አገልጋይ ደግሞ ተጨማሪ ሥልጠና ቢሰጠው የተፈለገውን አገልግሎት ሊፈጽም እንደሚችል የሚያ ረጋግጥ ባሕርይና ክህሎት ካለው፣ ትምህርቱ ሊሰጠው ይገባል። የሥልጠናው ዓይነትና ደረጃ (የምስክር ወረቀት፣ ዲፕሎማ ወይም ዲግሪ) መወሰን ያለበት በግለሰቡ ፍላጎት ሳይሆን፣ በቤተ ክርስቲያኒቱ ፍላጎት ነው። ቤተ ክርስቲያን ግለሳቡን በመሪነት አንድ ደረጃ ከፍ የማድረግ ፍላጎት ከሌላት፣ ለግለሰቡ ተጨማሪ ትምህርት የመስጠት ግዴታ አለብኝ ብላ ማሰብ የለባትም። በቀዳሚነት የመሪነት ሥልጠና ቤተ ክርስቲያን ከ2ኛ ዓይነት

መሪነት ወደ 3ኛ ዓይነት መሪነት ለመውሰድና ብቃት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ ስምታቀዳቸው አገልጋዮች የሚሰጥ ነው:: (ተጨማሪ ትምህርት 3ኛ ዓይነት መሪዎችን ወደ አራተኛ፣ አራተኛ ዓይነቶቹን ወደ አምስተኛ ለማሸጋገርም ሊሰጥ ይችላል::)

አንድ ሰው ተጨማሪ ትምህርት የማግኘት ራእይ ቢኖረውና ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ስልታዊ ግቦቿን ስመምታት የማላስቡ በዚያ ደረጃ መማር አስፈላጊ አይደለም የሚል እምነት ካላት፣ ግለሰቡ ለትምህርቱ በግሉ ለመክፈል ዕቅድ ማውጣት አለበት:: ቤተ ክርስቲያን ለትምህርቱ እንድትከፍልለት መጠበቅ የለበትም::

| |
|---|
| 25ኛ ጥያቄ:- ሀ) አንዳንድ ሰዎች ትምህርት ቤተ ክርስቲያን ስልታዊ ዕቅዷን የምትፈጽምበት ሳይሆን፣ ለእነርሱ መስጠት ያለበት መብት ነው የሚያስቡት ለምንድን ነው? የእነዚህን ሰዎች አስተሳሰብ ብለው የሚያስቡት ለምንድን ነው? ትደግፋለህ? መልስህን አብራራ:: ለ) ቤተ ክርስቲያን የአንድን ሰው የመማር ፍላጎት ከማርካት ይልቅ፣ ስልታዊ ፍላጎትዋን ለማሟላት ስትል ሰዎችን ብታሠለጥን የሚሻል ይመስልሃል? |

9. የመሪዎች የሥልጠና ዘዴ ክምናሠለጥነው መሪ ጋር የሚስማማ መሆን አለበት::

የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ሁሉ የግድ ዲግሪ አያስፈልጋቸውም:: ክዚህ ይልቅ፣ እያንዳንዱ አገልጋይ እግዚአብሔርና ቤተ ክርስቲያን ባስቀመጡት ደረጃ ላይ በብቃት እንዲያገለግል የሚያስችል ሥልጠና መስጠቱ ጠቃሚ ይሆናል:: እንዲያገለግል የሚያስችል ሥልጠና መስጠቱ ጠቃሚ ይሆናል:: ከዚህ በታች በተለያዩ ደረጃዎች ላይ ለሚገኙ ሰዎች የመሪነትን ሥልጠና ስለ መስጠት የተለያዩ አሳቦች ተመልክተዋል:-

ሀ. 1ኛ ዓይነት መሪዎች:- እነዚህ መሪዎች በእነስተኛ ቡድኖች ውስጥ የሚያገለግሉ ናቸው:: ለዚህ ደረጃ ሰዎችን በምናሠለጥንበት ጊዜ፣ ዓላማቸውን የተወሰኑ ኃላፊነቶችን ለመፈጸም የሚያስችል ክህሎትና እውቀት ማስጨበጥ ይሆናል:: ስለዚህ፣ ግለሰቡ የሰንበት ትምህርት ቤት አስተማሪ ከሆነ፣ በተሻለ ሁኔታ እንዲያስተምር የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀቱን ለማሳደግ የሚያስችል ሥልጠና መስጠት ያስፈልገዋል:: እንዲሁም ደግሞ ክትልልቅ ሰዎች ይልቅ ልጆችን የሚያስተምር ከሆነ፣ እንዴት በጥሩ ሁኔታ እንደሚያስተ



ምሩቸው የሚያስገነዝብ ክህሎት የሚያስጨብጥ ሥልጠና መስጠት ይቻላል:: ትኩረት መስጠት ያለበት የምስክር ወረቀት በማግኘቱ ላይ ሳይሆን፣ ለአገልግሎቱ የሚያስፈልግ ክህሎት በማሳደጉ ላይ ነው::

ብዙውን ጊዜ ሥልጠናውን የሚሰጠው መጋቢው ወይም ልምድ ያላቸው ሁለተኛ ዓይነት መሪዎች ናቸው:: አሠልጣኙ ለ2ኛ ዓይነት መሪዎች በሚያመች መንገድ የአጭር ጊዜ ሥልጠናዎችን ያዘጋጃል:: በዚህ ደረጃ እጅግ ውጤታማ የሚሆነው ሥልጠና መደበኛ ያልሆነ (ለምሳሌ፣ ልምድ ያለው የቡድን መሪ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኑን በመንብኘት መሻሻል የሚቻልባቸውን መንገዶች ይጠቁመዋል)፣ ሥራው እንዴት እንደሚሠራ በምሳሌነት ማሳየት (ለምሳሌ፣ ግለሰቡ እየተመለከተ ልምድ ያለው መሪ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኑን መምራት)፣ ወይም ሰዎች ልምድ እንዲያገኙ መርዳት ነው:: (ለምሳሌ፣ ልምድ ያለው የቡድን መሪ ከግለሰቡ ጋር በቡድኑ ውስጥ አብሮ በመሥራት ጥሩ የእነስተኛ ቡድን መሪ እንዲሆን ያግዘዋል:: ከዚያም አሠልጣኙ ወደ ሌላ ቡድን በማለፍ ማሠልጠኑን ይቀጥላል::)

የቤተ ክርስቲያን ጥንካሬ የሚወሰነው በጸሎት ቡድኖች፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች ወይም በእነስተኛ ቡድኖች አገልግሎት ስለሆነ፣ ይህ በጣም አስፈላጊ የሆነ የሥልጠና ክፍል ነው:: ብዙውን ጊዜ የዚህ ዓይነቱ አገልግሎት በጣም ርካሽ ነው:: የሚጠይቀው የሠልጣኙንና የአሠልጣኙን ጊዜና ጥቂት ቁሳቁሶችን ብቻ ነው:: የዚህ ዓይነቱ ሥልጠና ሁሉም ምእመናን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ያደርጋል::

| |
|---|
| 26ኛ ጥያቄ:- የቤተ ክርስቲያናችሁ የሰንበት ትምህርት ዳይሬክተር ነህ እንበል:: ከላይ የተጠቀሱትን ሦስት የሥልጠና ዓይነቶች በመጠቀም የተለያዩ የሰንበት ትምህርት ቤት አስተማሪዎችን እንዴት እንደምታሠለጥን ግለጽ:: |

ለ. 2ኛ ዓይነት መሪዎች:- እነዚህም በጎ ፈቃደኛ መሪዎች ናቸው:: ነገር ግን በልምዳቸውና በችሎታቸው ምክንያት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልግሎቶችን እንዲከታተሉ ይጠየቃሉ:: ልክ

እንደ 1ኛ ዓይነት መሪዎች፣ ለእነዚህም መሪዎች ቀጣይነት ያለው ሥልጠና መስጠቱ አስፈላጊ ነው። 1ኛ ዓይነት መሪዎች ብቃታቸውን የሚያጎለብቱት በእነዚህኞቹ አማካኝነት ነው። ሥልጠናቸው በአገልግሎት ክፍላቸው የአጭር ጊዜ ሥልጠና መስጠትን የሚያካትት ነው። (ማስታወሻ፡- ያገለግላሉ ተብሎ በማይጠበቅ አካባቢ ሥልጠና መስጠቱ እምብዛም ውጤታማ አይሆንም። አምልኮ በመምራት ያገለግላል ተብሎ ለማይጠበቅ ሰው በዚህ አካባቢ ሥልጠና መስጠቱ ጠቃሚ አይሆንም። አዋቂ ሰዎች ስለማይመለከቱአቸው ነገሮች ንድፈ-አሳቦችን ከመማር ይልቅ፣ ከሥራቸው ጋር የሚዛመዱትን ነገሮች መማርን ይመርጣሉ። ይህንን ሥልጠና መስጠት ያለባቸው መጋቢውና በዚህ በኩል ብዙ ልምድ ያላቸው 4ኛ ዓይነት መሪዎች ናቸው። ንድፈ-አሳባዊ እውነቶችን መማሩ ጠቃሚ ቢሆንም፣ እነዚህ መሪዎች ልምድ ያላቸው ሰዎች ሲያገለግሉ በመመልከት፣ እንዲሁም ልምድ ያላቸው አገልጋዮች የአነርሱን አገልግሎት አይተው አስተያየት ሲሰጡ በመቀበል ከፍተኛ ጥቅም ሊያገኙ ይችላሉ፡

> 27ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ቤተ ክርስቲያናችሁ አብዛኛውን ጊዜና ገንዘብ የምታጠፋው 1ኛ እና 2ኛ ዓይነት መሪዎችን በማሠልጠን ነው ወይስ 3ኛ እና 4ኛ መሪዎችን በማሠልጠን? ለ) 1ኛ እና 2ኛ ዓይነት መሪዎች ለአገልግሎታቸው በሚገባ መሠልጠናቸው ጠቃሚ የሚሆነው ለምንድን ነው? ሐ) አብዛኞቹ አብያተ ክርስቲያናት 1ኛ እና 2ኛ ዓይነት መሪዎችን በማሠልጠኑ ላይ ቢያተኩሩ፣ የመሪነት ሥልጠና ግንዛቤያችን እንዴት እንደሚለወጥ ግለጽ።

ሐ. <u>3ኛ ዓይነት መሪዎች</u>፡- እነዚህ የአነስተኛ ወይም የመለስተኛ ማኅበረ ምእመናን መሪዎች ናቸው። እነዚህን ሰዎች በመሪነት ማሠልጠኑ ውድ ነው። የቤተ ክርስቲያናቸው የሙሉ ጊዜ መሪዎች ስለሚሆኑ፣ ወደ መደበኛ ትምህርት ቤት ገብተው መማር ያስፈልጋቸዋል። 2ኛ ዓይነት መሪዎች ሆነው ያገለገሉ ሰዎች ብቻ ለዚህ ሥልጠና መታጨት አለባቸው።

በዚህ ደረጃ ያለው አመራር ምን ምን እንደሚፈልግ መረዳቱ አስፈላጊ ነው።



<u>በመጀመሪያ</u>፣ የ3ኛ ዓይነት መሪዎች ሥልጠና በአገልግሎት ዘርፍ ላይ ማተኮር አለበት። አገልጋዩ በመጋቢነት እንዲያገለግ ከሆነ የታሰበው፣ ሥልጠናው ይህንኑ አገልግሎት የሚያዳብርለ መሆን አለበት። ወንጌላዊ እንዲሆን ከተፈለገም፣ እንዲሁ ለብ ወንጌላዊነት የሚያግዝ ሥልጠና ሊሰጠው ይገባል። አጠቃላ ሥልጠና መስጠቱ ግለሰቡ ውጤታማ አገልግሎት የሚሰጥበት እውቀትና ክህሎት አያስጨብጠውም።

<u>ሁለተኛ</u>፣ ሥልጠናው ለሚፈለገው አገልግሎ የሚያስፈልጉትን ክህሎቶች ማስጨበጥ አለበት። ብዙውን ጊ መደበኛ የሥልጠና ፕሮግራሞች መሪው ከሚያከናውናቸው ግባራት ጋር ግንኙነት በማይኖራቸው «ንድፈ-አሳቦች» እ እውቀት ላይ ያተኩራል። በዚህ ደረጃ የሚገኝ መሪ ለአገልግሎ ውጤታማነት እገዛ የሚያደርጉትን ክህሎቶች መማሩ ወሳኝ ነው ስለሆነም፣ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ለሚሆን አገልጋ የእግዚአብሔርን ቃል የማጥናትና የመተርጎም፣ የማስተማር የመስበክ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የመምራት ወይም በሰንበ ትምህርት ቤት የማስተማር፣ ሳልዳኑት የመመስከር፣ የደ መዘመርነት ትምህርት የመስጠት፣ ቤተ ክርስቲያንን የማስ ዳደር፣ የማማከር፣ ወዘተ. . . ክህሎቶች ያስፈልጉታል። ማወ ባለብህ ነገር ክህሎትን ለማዳበር የአገልግሎቱን ንድፈ-አሳብ ማወ ያስፈልግሃል። ነገር ግን ያንን አገልግሎት በሚገባ አስክትወጣ ድረስ መለማመድም አለብህ።

ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶቻችን የደረጃ ሦስ አገልጋዮችን የምናሠለጥንበት መንገድ መቀየር አለበት ማለ ነው። አብዛኞቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች በንድፈ-አሳባ እውነቶች ላይ ያተኩራሉ። ነገር ግን ተማሪዎቻቸው ተግባራ የአገልግሎት ልምድ እንዲያገኙ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ብ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች ምሩቃን በቂ የአገልግሎ ክህሎት ሳያገኙ የአእምሮ እውቀት ብቻ ይዘው ይወጣሉ። እነዚ ምሩቃን ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው በሚመለሱበት ጊዜ ለምእመና

የሚሰጡት የአእምሮ እውቀትን እንጂ ክህሎትን አይደለም:: ይህ በብቃት እንዳያገለግሉ ያደርጋቸዋል::

28ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ቤተ ክርስቲያናችሁ አንድን ሰው የቦላይ መጋቢ እንዲሆን ትሻው ከነበረ፣ ይህ ሰው ሊያጠናቸው ይገባቸዋል ብለህ የምታስባቸው የትኞቹን የተለያዩ የትምህርት ይነቶችን (ኮርሶችን) ነው? ለ) መጋቢ ለመሆን የሚያበቃውን አስፈላጊ ክህሎት እንዴት ሊያገኘው ይችላል ብለህ ታስባለህ?

መ. <u>ደረጃ 4 እና 5 መሪዎች</u>:- ደረጃ 4 መሪዎች፣ የትልቅ ማኅበረ ምእመናን ወይም የቤተ እምነት የክልል መሪዎች ናቸው:: ደረጃ 5 መሪዎች ብሔራዊ መሪዎች፣ ምሑራን፣ የሥነ መለኮት ተቋማት አስተማሪዎች፣ ወዘተ. . . ናቸው:: እንዲህ ላለው መሪ ለማሰሰቡ ምርጥ የሆነው መንገድ መደበኛ የሆነ ትምህርትን በከፍተኛ ደረጃ መማር እንደ ሆነ ማሰቡ ፈታኝ ነው:: ለአንዳንዶች ይህ እውነት ነው:: ምሑራን ወይም አስተማሪ ጥልቀት ካለው ሥልጠና ብዙ ነገሮችን ያገኛሉ፤ ስለዚህም፣ በሕዝባችን ውስጥ ያሉ አሠራሮችን ማጥናት ይችላሉ፣ በዚህም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልሶችን ያመጣሉ፣ ወይም የቤተ ክርስቲያኖቻቸውን ደረጃ 3 መሪዎች በበቂ ሁኔታ ማሠልጠን ይችላሉ:: ነገር ግን አንድ ሰው መደበኛ በሆነ ትምህርት በከፍተኛ ደረጃ በተማረ መጠን፣ በአብዛኛው የሚያተኩረው በሚያጠናው የትምህርት ዘርፍ ላይ ነው:: ስለዚህ፣ የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ሰዎች ልክ እንደ ግሪክ ቋንቋ ወይም በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያሉ የጳውሎስ መልእክቶች ባሉ በጣም ልዩ በሆኑ ርእሶች ላይ በአብዛኛው ያተኩራሉ:: ይህ ጠበብ ያለ ትኩረት ሰውየውን ለቤተ ክርስቲያን ያነሰ ጠቀሜታ እንዲኖረው ሊያደርገው ይችላል:: በከፍተኛ ደረጃ ካሉ የሥነ መለኮት ትምህርት ቤቶች በስተቀር፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የደረጃ 4 እና 5 መሪዎች አስፈላጊነት ሰፋ ያለ እውቀት እንዲኖራቸውና በዚህም ቤተ ክርስቲያን በጣም ልዩ በሆኑ ርእሶች ላይ ጥናት ያደረጉ ብዙ ሰዎችን ለመቅጠር ገንዘቡ አይኖራትም:: በክልል የሚሠሩ ወይም አስተማሪ መጋቢዎች እና ወንጌላውያን በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ መሪዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንዴት እንተርጉም በሚለው ረገድ ማሠልጠን እንዲችሉ



በእግዚአብሔር ቃል ላይ በቂ የሆነ እውቀት ሊኖራቸው ያስፈልጋል:: ነገር ግን የተለያዩ ሃይማኖታዊ ቡድኖች የሚያከናውኑትን የወንጌል ስርጭት ማወቅም ጭምር ያስፈልጋቸዋል፤ ባዚህም ደረጃ 2 እና 3 መሪዎችን ማኅበረሰባቸውን በወንጌል በመድረስ ረገድ እንዴት የበለጠ ውጤታማ እንደሚሆኑ ማሠልጠን አስፈላጊ እንደ ሆነ ማወቅ ያስፈልጋቸዋል:: ስለዚህ፣ አንድ ሰው አንድ ጊዜ በዚህ የአመራር ደረጃ ላይ ካለ፣ ግለሰቡ ንድፈ እሳቡንና እርሱን ተግባራዊ የሚያደርግበትን መመሪያዎች የሚሰጥበትን አጫጭር ሥልጠና መውሰድ በእብዛኛው የበለጠ ውጤታማ የሚያደርግ ነው:: ስለዚህ፣ አንድ ሰው እንዴት የቤተ ክርስቲያን መጋቢ ይክናል በሚለው ላይ መሠረታዊ ሥልጠና ከወሰደ፣ መደበኛ ትምህርት ቤት በመግባት ልዩ በሆነ የትምህርት ዘርፍ ዲግሪ ከመውሰድ ይልቅ፣ በዚህ አካባቢ ላሉ ልዩ ወገኖች ወንጌል እንዴት እናዳርስ፣ ወይም መሃይም የሆኑ ሰዎችን በእምነታቸው እንዲያድጉ እንዴት ልንረዳቸው እንችላለን በሚሉ አጫጭር ሥልጠናዎች በኩል ልዩ የሆኑ ሥልጠናዎችን መውሰድ የበለጠ ውጤታማ ያደርገዋል::

ይህ ዓይነት ጸሎት ዘወትር መደረግ ያለበት በመሪው ጥያቄ ነው:: እያገለገለ ሳለ፣ በአብዛኛው በእውቀትና በክህሎት ደክሞ የተገኘበትን ስፍራ ልብ ይለዋል:: ከዚያም የአገልግሎቱን አድማስ ለማስፋት ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር መሥራት ያስፈልገዋል:: ተጨማሪ የሆነ ሥልጠና የአገልግሎት አድማሱን ያሰፋዋል የሚል ግልጽ የሆነ አመልካች ነገር ከሌለ፣ በዚያን ጊዜ እንዲሰጥ ለሚሻው ሥልጠና የገዛ ራሱን ጊዜና የገንዘብ ምንጭ መጠቀም እንዳለበት ሊቆጥር ይገባል::

29ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ይህ ደረጃ 3፣ 4፣ እና 5 መሪዎችን ከማሠልጠኑ ሚና ጋር እንዴት የተለያየ እንደ ሆነ አብራራ:: ለ) ከዚህ የአመራር ሥልጠና መረዳት ጋር ትስማማለህ? ለምንድን ነው የምትስማማው ወይም ለምን አትስማማም? ሐ) እኛ ክህሎትን ለማጉልበት ለመሪዎች የሚሰጥ ሥልጠናን፣ የተወሰነ ደረጃ ተምረው የምስክር ወረቀት ከሚያገኙበት የመሪዎች ሥልጠና በተቃረነ መልኩ የምንወስደውና በዚህ ላይ የምናተኩር ከሆነ፣ የእኛ የአመራር ሥልጠና ግንዛቤያችን እንዴት ሊሰጥ ይችላል?

10. እግዚአብሔርን ለማገልገል መሠልጠን ያስፈልጋል የሚል የተ ሳሳተ አስተሳሰብ፡-

ሀ. «በእግዚአብሔር ቃል እውቀት ማደግ የምችልበት እንዲሁም የእግዚአብሔርን ሰዎች እንዴት የበለጠ ለማገልገል ልማር የምችልበት ብቸኛው መንገድ ትምህርት ቤት በመሄድ ነው።» ብዙ ሰዎች ትምህርት የሚከናወነው በመማሪያ ክፍል ውስጥ ብቻ እንደ ሆነ ያስባሉ። ይህ ዛሬ ስይጣን ከሚያስማቸው ከዋናዎቹ ሐስቶች አንዱ ነው። በክፍል ውስጥ አስተማሪዎች መ ረጃን እየሰጡ የሚደረገው ትምህርት አዲስ የማስተማሪያ መንገድ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶችና ሴሚናሪዎች (ኮሌጆች) ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት የተጀመሩ ናቸው። በታሪክ ውስጥ እንደ ሙሴ፣ ዳዊት፣ ኢሳይያስ፣ እንዲሁም ሐዋርያት ያሉ መሪ ዎች ክቶ በትምህርት ክፍል ውስጥ ሳይቀመጡም ሆነ «ዲግሪን» ሳያገኙ ውጤታማ በሆነ መልኩ ሠልጥነዋል። በእርግጥ፣ በአሜሪካ ያሉ የቅርብ ጊዜ የሴሚናሪ ተመራቂዎች አስሳ፣ አብዛኞቹ ተ መራቂዎች ከተማሩዋቸው ትምህርቶች ውስጥ የሚበዛው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላለ አገልግሎታቸው በጣም ጠቃሚ እንዳልነበሩ እንደሚያምኑ ያመለክታል። በታሪክ ሁሉ ውስጥ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ለማሠልጠን ሁለት ዋነኛ መሣሪያዎች ነበሩ፡

1) ልምድ ያካበቱ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አዳዲስ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን በአገልግሎት ክህሎት ረገድ ያሠለጥኑዋቸዋል። ምናልባትም አንድን ሰው እጅግ ውጤታማ በሆነ መልኩ ማሠልጠኛ መንገድ «በሥራ ላይ የሚደረግ ሥልጠና» ይሆናል። በዚህም፣ ውጤታማ የቤተ ክርስቲያን መሪነቱን ያስመስከረ አንድ ሰው በዙሪያው አዳዲስ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ይሰበስባል፣ ከዚያም የእግዚአብሔርን ሰዎች ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዴት ማገልገል እንደሚቻል ያሳያቸዋል ማለታችን ነው። ኢየሱስ አሥራ ሁለት ደቀ መዛሙርትን አሠልጥኦቸዋል፤ በርናባስ እና ጳውሎስ ጢሞቴዎስን አሠልጥነዋል፣ ወዘተ. . . ። የሚያሳዝነው፣ ይህ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዘወትር የሚከሰት አይደለም። ወጣት ምሩቃን



ውጤታማ በሆነ መልኩ ማገልገል እንዴት እንደሚቻል እንዳወቁ እያሰቡ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይመጣሉ። በውጤቱም በእነርሱና ልምድ ባካበቱ የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች ወይም በእነርሱና በቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል ውጥረቶች እየጐለበቱ ይሄዳሉ። ለአንድ ዓመት ወይም ለሁለት ዓመታት፣ አዳዲስ ምሩቃን ውጤታማ ከሆኑ ወንጌላውያን (እነርሱ ወንጌላውያን የሚሆኑ ከሆነ) ወይም ባለ ተሰጥኦ ከሆኑ መጋቢዎች ጋር (እነርሱ መጋቢያን የሚሆኑ ከሆነ) አብረው እንዲሠሩ ቢደረግ ምን ይከሰታል? አንድ ትምህርታዊ መመሪያ እንደሚለው፣ ነገሮችን «ከመማር» ይልቅ «መያዝ» ይቀልላል። ይህም ከአንድ ሰው ጋር አብረን በምንሠራበት ጊዜ እንዲሁም አንድ ነገር እንዴት ሊሠራ እንደሚገባ ከሚነገረኝ ይልቅ ነገሮችን እንዴት እንደሚሠሩ ማየቱ ቀላል ነው ማለት ነው።

2) በእግዚአብሔር ቃል መረዳታችን እንዲሁም እርሱን እንዴት ማገልገል እንዳለብን በዚህ እንድናድግ የሚረዱንን መጻሕፍት ማንበብ። ታላላቆቹ መሪዎች «እራሳቸውን ያስተማሩ» ናቸው። ይህም እቤታቸው በሚሆኑበትና አገልግሎት በሚሰጡበት ጊዜ፣ እነዚህ መሪዎች መጻሕፍት በማንበብ ሁልጊዜ እውቀታቸውን ለማዳበር ይጥራሉ። እያንዳንዱ መጽሐፍ «አስተ ማሪ» መሆን ይችላል። ታላላቆቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እራሳቸውን ሥርዓት እንዲያስይዙ፣ በዚህም ሁልጊዜ የሚያነብቡ እንደ እግዚአብሔርም አገልጋይ መረዳታቸውንና ውጤ ታማነታቸውን ለመጨመር መንገዶችን ሊፈልጉ እንደሚገባ ተም ረዋል። በየዓመቱ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ሊረዱ የሚችሉ ብዙ የሥነ ጽሑፍ ውጤቶች የበለጠ እየጐለበቱ ይሄዳሉ። ከዚህ ጋር የሚዛመዱ የት.መ.ማ. መጻሕፍት፣ እንደ ጋብቻ ወይም ልጆችን ማሳደግ ያሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ጋር የተዛመዱ፣ ወዘተ. . . መጻሕፍት አሉ። በዚህ መልኩ፣ «መማር» የሚፈልግ የቤተ ክርስቲያን መሪ እነዚህን መጻሕፍት ሊገዛ ይገባዋል፣ ደግሞም በእውቀቱ እያደገ ሊሄድ ይገባል።

ለ. ትምህርት ወደ ትምህርት ቤት መሄድ፣ ትምህርት ሲሰጥ ማዳመጥ፣ እንዲሁም መጻሕፍትን ማንበብና ዲፕሎማ ወይም ዲግሪ መቀበልን ይጠይቃል። ባለሙያ በሆነ መልኩ እንዴት ማገልገል ይቻላል የሚለውን በተመለከተ ሊኖር የሚገባን የክህሎት ትምህርትን አያካትትም። ከትምህርት ቤት በምንመረቅበት ጊዜ፣ ዘወትር ሦስት ነገሮችን እንገነዘባለን:-

1) አብዛኞቹ የተማርናቸው ነገሮች እኛ ለምንሳተፍበት አገልግሎት ዓይነት (መልክ) የሚስማሙ እንዳይደሉ እንገነዘባለን። ከወሰድናቸው የትምህርት ዓይነቶች አብዛኞቹ የበሰጠ ለማገልገል የሚያዘጋጁን አይደሉም።

2) በትምህርቱ እስጣጥ ልምምድ ወቅት በበለጠ በተማርናቸው ነገሮች በኩል ማደጋችንን እንገነዘባለን። በመጀመሪያ፣ ከሌሎች ተማሪዎችና ከአስተማሪዎች ጋር የነበረን ጊዜ፣ ሕይወታቸውን የተመለከትንበትና ተሞክሮዎቻቸውን የምናዳምጥበት ሁኔታ በክፍል ውስጥ ከሚሰጠው ትምህርት በላይ ዘወትር ተጽዕኖን ያሳድርብናል። ሁለተኛ፣ የተለያዩ አሳቦችን የመመልከት እንዲሁም የትኛው ምርጥና የበለጠ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንደ ሆነ ለማየት የመሞከር ሂደት፣ ነገሮችን ለመገምገምና ለመማር፣ እንዲሁም በቤታችን ለብቻችን ከመቆየት ይልቅ ፈጠራ ባለበት መልኩ የበለጠ ለማሰብ ይረዳናል።

3) የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመምራት አስፈላጊ ከሆኑት ክህሎቶች ጥቂቶቹ አሉን። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለ አገልግሎት ከሰዎች ጋር መጐዳኘት፣ በሕይወታቸው ውስጥ ካሉ ጉዳዮች ጋር በሚታገሉበት ጊዜ ሰዎችን ማማከር፣ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ባላቸው ግንኙነት እንዲያድጉ ሰዎችን መርዳት፣ በማኅበረሰባችን ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች ወንጌልን መመስከር፣ ማኅበረሰባችንን እንደ አርአያ የሚሆን ዜጋ ማገልገል፣ ወዘተ. . . ያለ ነገር ነው። ነገር ግን፣ ትምህርት ቤት በአብዛኛው እነዚህን ነገሮች በተሻለ መልኩ በማድረግ ረገድ አይረዳንም።



ሐ. «እኔ የሠሰጠንኩት ነገር ምንም የሚፈይደው ነገር የለም። እንደ ተማረ ሰው ተደርጌ እንድታይ የበለጠ ትምህርት እፈልጋለሁ። የምስክር ወረቀቱን ማግኘት ነው የበለጠ አስፈላጊው ነገር፤ ለአመራር የሚያዘጋጁኝ ጠቃሚ መረጃዎችን ማግኘት አለማግኘቴ አይደለም።» በአብዛኛው እንዲህ ዓይነት ዝንባሌ ለትምህርት በሚኖረን ጊዜ፣ የሥነ መለኮት ትምህርትን ዓላማ በተሳሳተ መንገድ እንረዳዋለን። ብዙ ሰዎች ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት የሚሄዱት ሥራ ስለሌላቸው ወይም ለትምህርት የሚሆን ሌላ አማራጭ ስለሌላቸው ነው። «ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት የመሄድንና የምስክር ወረቀት የማግኘትን» ክብር በደስታ ያጣጥሙታል። ነገር ግን ሁለት ነገሮችን ረስተዋል:-

1) የሥነ መለኮት ትምህርት በቀዳሚነት በጠባያችንና በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ለማገልገል ችሎታን በማጐልበት ረገድ ለማደግ የሚረዳን አንድ መሣሪያ ነው። ሥራ እንድናገኝ ወይም የተሻለ ክፍያ እንድናገኝ እንዲረዳን ለማድረግ የታሰበ መሣሪያ አይደለም።

2) እግዚአብሔር በሕዝቡ በኩል (በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በለጋሾች) በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ ላለ አገልግሎት የበለጠ የምንሠለጥንበትን ዕድል ሰጥቶናል። ከሥልጠናው ጋር የተማርነውን ነገር ለእግዚአብሔር ክብር ለመጠቀም የሚሆን ትልቅ ኀላፊነት ይመጣል። ሥልጠናችንን በመጠቀም ረገድ በእግዚአብሔር ተጠያቂ ተደርገናል። «ብዙ ከተሰጣቸው ብዙ ይጠበቃል» (ሉቃስ 12:48)።

ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ በየዓመቱ በሺህዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎችን የሚያስመርቁ በመቶዎች የማቆጠሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች አሉ። ዳሩ ግን፣ እያንዳንዱ ቤተ እምነት የሠለጠኑ አገልጋዮችን ለማግኘት በመጮኽ ላይ ነው። ግልጽ በሆነ መልኩ፣ አንድ ነገር ተሳስቷል። ሰዎች የተማሩ እንዲሆኑ እጅግ ትኩረት እያደረግን፣ ሆኖም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚያገለግሉበት ጠቃሚ መሣሪያዎችን ሳናቀርብላቸው የቀረንበት ሁኔታ ሊሆን አይችልምን? የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ግብ

«አጠቃሳይ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እውቀትን» መስጠት አይደለም፡፡ ይልቁንም፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ግቡ ሰዎችን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚደረግ አገልግሎት ማዘጋጀት ሊሆን ይገባል፡፡ ይህ የማይከሰት ከሆነ፣ ሰዎችን ለምን እያሠለጠንን ነው፣ እንዲሁም ሰዎችን እንዴት እያሠለጠንን ነው በሚለው ዙሪያ አንድ የተሳሳተ ነገር ለመኖሩ ይህ በአብዛኛው አመልካች የሆነ ምልክት ነው፡፡

መ. «በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለብዙ ዓመታት የሠራሁ በመሆኔ፣ ተጨማሪ ሥልጠና ያስፈልገኛል፡፡» ሥነ መለኮታዊ ትምህርትን የምንመለከትባቸው ሁለት መንገዶች አሉ፡፡ እንደኛው፣ ለግለሰቡ የማሻሻያ መሣሪያ አድርጎ መመልከት ነው፡፡ አንድ ሰው ቡተሻለ ደመወዝ የተሻለ ሥራ እንዲያገኝ የሚረዳ አንድ መንገድ ነው፡፡ ሁለተኛ፣ አንድ ሰው ቤተ ክርስቲያን በምትፈልገው ስፍራ ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲያገለግል የሚረዳ አንድ መሣሪያ ነው፡፡ እንግዲህ መሪዎችን ለቤተ ክርስቲያናቸው ለማጕልበት በሚኖራቸው ዕቅድ ረገድ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች የትኛው አመለካከት መሠረት ሊሆናቸው ይገባል? ምንም እንኳ ሰዎች በትምህርታቸው እንዲያድጉ ልንረዳቸው የምንፈልግ ቢሆንም፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መሠረታዊ ሚና የቤተ ክርስቲያን አባላትን (ግለሰቡን ብቻ ሳይሆን) በእምነታቸው እንዲያድጉ መርዳት ነው፡፡ ስለዚህም፣ ሰዎችን ለሥልጠና መምረጥ ስልታዊ በሆነ መሠረት እንጂ በሽልማት መልኩ ሊደረግ አይገባም፡፡ ቤተ ክርስቲያን የሥራ ቅጥር መፈጸሚያ ቦታ አይደለችም፡፡ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች የተቻላቸውን ያህል ብዙ ገንዘብ ይዘው በመሄድ ሥራ እንደሚያገኙበት እንደ ንግዱ ዓለም አይደለችም፡፡ ይልቁንም፣ ቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ስፍራ ናት፡፡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት፣ እንዲሁም በእምነታቸው የበለሉ እንዲሆኑ ለመርዳት በእግዚአብሔር ተ መርጠዋል፡፡ ስለዚህ፣ ሥልጠናን የምትሰጥ ቤተ ክርስቲያን ሚና እግዚአብሔር የጠራቸውን እንዲሁም እነዚያን ፍላጎቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲፈጽሙ ለአገልግሎት ስጦታ የተሰጣቸውን ሰዎች ማስታጠቅ ነው፡፡ በማቴዎስ 25:14-30 ባለው ምሳሌ ውስጥ



ለውየውን የሚመርጠው፣ በሥራውም በተለያዩ ደረጃዎች ላይ ኀላፊነትን በመስጠት በመጋቢነት የሚለይመው ጌታው ነበር፡፡ ወደ ጌታቸው መጥቶ፣ (5፣ ወይም 2፣ አሊያም 1 መክሊት) ስጠኝ የሚለው መጋቢው አይደለም፡፡ በተመሳሳይ መንገድ፣ እነዚያን ለአገልግሎት የሚፈለጉ ሰዎችን መምረጥ እና ከዚያም ለዚያ አገልግሎት እነርሱን ማሠልጠን የቤተ ክርስቲያን ሚና ይመስላል፡፡ አንድ ቤተ ክርስቲያን በአካባቢው ያሉ ሌሎች ሃይማኖቶችን በወንጌል እንዲደርስ አንድ ወንጌላዊ የሚያስፈልጋት ከሆነ፣ ግለሰቡ ሊሆን የሚችለውን ምርጥ ወንጌላዊ እንዲሆን ማሠልጠን ይገባታል፡፡ ወይም አንድ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚመራ አንድ መጋቢ የምትፈልግ ከሆነ፣ እንግዲያውስ ሰውየው ውጤታማ የሆነ መጋቢ እንዲሆን ልታሠለጥነው ይገባል፡፡ ውጤታማ ለሆነ አገልግሎት በምን ያህል ደረጃ የሚሰጥ ሥልጠና እንደሚያስፈልግ መወሰን የሚገባት ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ ለገጠር ቤተ ክርስቲያን በሰርተፊኬት (የምስክር ወረቀት) ደረጃ የሠለጠን ሰው ብቻ የሚያስፈልግ ከሆነ፣ አንድ ሰው ዲግሪ እንዲያገኝ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ክፍያውን ሊከፍሉለት እንደሚገባ ሊሰማቸው አይገባም፡፡ በትንሽ ከተማ ላለ አገልግሎት የሚያስፈልገው በዲፕሎማ ደረጃ የሠለጠነ ሰው ከሆነ፣ አንድ ግለሰብ በዲግሪ ደረጃ የሚያደርገው ሥነ መለኮታዊ ሥልጠና የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ክፍያውን ለመፈጸም ግዴታ እንዳለባቸው የሚያደርግ ምንም ምክንያት የለም፡፡ እግዚአብሔር የሰጠንን ገንዘብ ለሰዎች የበለጠ ትምህርትና የተሻለ ክፍያ ለመስጠት ሳይሆን፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላለ ስልታዊ ፍላጎቶች ልንጠቀምበት ይገባል፡፡

ሠ. «ሥልጠናዬ ምንም ክፍያ ሊያስከፍለኝ አይገባም፡፡ ቤተ ክርስቲያኔ ወይም ሌሎች ለጋሾች የትምህርት ወጪዬን ሊከፍሉ ይገባል፡፡» ትልቅ ቤት ለመገንባት ወይም የተሻለች ላም ለመግዛት ቤተ ክርስቲያንን አንጠባበቅም፡፡ ስለዚህ፣ ቤተ ክርስቲያን ለግል እድገታችን ልትከፍልልን ይገባል ብለን ለምን እንጠባበቃለን? ቤተ ክርስቲያን የተለየ ፍላጎት ኖሯት ቀጣይ ሥልጠና እንድናገኝ ለዚሁ ካልጠየቀችን በቀር፣ የተሻሉ ሰዎች ለመሆን፣ እንዲሁም

ለእግዚአብሔር ክብር ውጤታማ ሠራተኞች ለመሆን እራሳችንን ማሳደግ የእኛው ኃላፊነት እንደ ሆነ ማሰብ ይገባል:: ሌሎች ለእኛው እድገት ክፍያ እንዲፈጽሙ ዘወትር መጠባበቅ ለእኛ ጤናማ ነገር አይደለም:: ሴሚናር መካፈልም ሆነ ትምህርት ቤት መግባት፣ በእውቀቴም ሆነ በክህሎቴ እንዳድግ ሊከፈለኝ ይገባል ብሎ ማሰብ ትክክል ነው:: ይልቁንም፣ እንደ ሰው ለእግዚአብሔር አገልግሎት የበለጠ ውጤታማ ለመሆን ማደግን ልፈልግ ይገባኛል:: ስለዚህ፣ እንዳድግ እግዚአብሔር የሰጠኝን ገንዘብ እጠቀማለሁ ብዬ ላስብ ይገባኛል፣ ደግሞም እንዳድግ አንድ ሰው ይከፍልልኛል ብዬ ልጠባበቅ አይገባም:: አንድ ግለሰብ ትልቅ ምንዳ ያገኝ ዘንድ፣ ቤተ ክርስቲያን ለምን የትምህርት ቤት ክፍያ ልትከፍል ይገባታል? የበለጠ ክፍያ ለማግኘት በትምህርት ማደግ የምፈልግ ከሆነ፣ እንግዲያስ የትምህርት ቤት ክፍያን ለመክፈል ገንዘቤን መጠቀም ይገባኛል::

ረ. «ብዙ ተምሬአለሁ፣ የትምህርት ዓይነቶቹንም ጨርሼአለሁ:: ስለዚህ የበለጠ ክፍያ ማግኘት ይኖርብኛል:: ደግሞም ታላቅ ደረጃ ያለው የአገልግሎት ኀላፊነት ሊኖረኝ ይገባል::» እግዚአብሔር ለሥልጠና የሚሆን ዕድልን ከሰጠኝ፣ አንድ ጊዜም ያንን ሥልጠና ከጨረስሁ፣ የበለጠ ክፍያ ማግኘት ይኖርብኛል የሚለውን አሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የትም አናገኘውም:: ይህ በዘመናችን ወንጌልን የምንሸቅጥበት አንዱ መንገድ ሊሆን አይችልምን? (2ኛ ቆሮ. 2:17) ይህ «የክርስቶስ ከሆነው ጥበብ ይልቅ የዓለም ጥበብ ሊሆን አይችልምን?» ቤተ ክርስቲያን ለሙሉ ጊዜ አገልጋዮችዋ ልትከፍል የሚገባትን እንዴት መረዳት እንዳለበት የሚያሳይ አንድ እመለካከትን አጥንተናል:: ነገር ግን ከዓለም አይታ አንጻር እንኳ፣ ክፍያ ከትምህርት ጋር በቀጥታ የተያያዘ አይደለም:: አንድ የጥበቃ ሠራተኛ ዲግሪ ሊኖረው ይችላል፤ በትምህርቱ መሠረት ሳይሆን፣ ነገር ግን ለጥበቃ ሠራተኛ የሚሆን ገንዘብ ይከፈለዋል:: ወይም አንድ ሰው መጠነኛ ትምህርት ካለው፣ ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ አስተዳደራዊ ተግባራትን ማከናወን የሚችል ከሆነ፣ እርሱ ባለው መጠነኛ ትምህርት መሠረት ሳይሆን፣ ከሚያከናውነው ክህሎት የተመለሰው ሥራ አኳያ



ለዚያ ሰው ክፍያን ልንፈጽም ይጠበቅብናል:: ስለዚህ፣ ለሰዎች በትምህርት ደረጃቸው መሠረት ብቻ ሳይሆን፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚያከናውኑት ሥራ መሠረት መክፈል ለአብያተ ክርስቲያናት የበለጠ እውነታን የያዘ ይሆናል:: እንግዲህ ይህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሠርተፊኬት ደረጃ የሚከናወን ዝግጁ የሆነ የአገልግሎት መስክ አለን ማለት ከሆነ፣ ዲፕሎማ ስላለው ብቻ ለአንድ የዲፕሎማ ምሩቅ ተጨማሪ ክፍያ ለመክፈል ግዴታ እንዳለብን ሊሰማን አይገባም:: ወይም በሠርተፊኬት ደረጃ ያለ ስጦታ ያለው ወንጌላዊ ካለን፣ እርሱ ስላከናወነው ክህሎት ያለበት ሥራ ልከፍለው ይገባኛል እንጂ ሠርተፊኬት ብቻ ስላለው አልቀጣውም::

በተመሳሳይ መንገድ፣ ትምህርት ከሥልጣን ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካሉ የአገልግሎት ደረጃዎች ጋር ትንሽ ቍርኝት አለው:: ተሞክሮ (ልምድ) እና ውጤታማ አገልግሎት የሥራ እድገትንና ደመወዝን መወሰን ይገባቸዋል:: ዲግሪ ኖሯቸው ግን ምንም ልምድ የሌላቸው ሰዎች በአገልግሎት ውስጥ ለብዙ ዓመታት ከሠሩት ሰዎች ያነሰ ውጤታማነት በአብዛኛው ይኖራቸዋል:: የትምህርት ደረጃቸው ሳይሆን፣ የሚከናወነው ሥራ ምን ያህል ሥልጣንና ክፍያ ለአንድ ሰው ሊሰጠው ይገባዋል ለሚለው አመልካቾች ናቸው:: ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የእግዚአብሔር የሆነ መንገድ በትናንሽ ደረጃዎች ያሉ ኀላፊነቶችን መስጠት ነው:: አንድ ሰው በአገልግሎት የላቀ ደረጃን ሊሰጠው የሚገባው ያንን ኀላፊነት በታማኝነትና በክህሎት በማከናወኑ ብቻ ነው:: ዲግሪያቸውን የተቀበሉ ሰዎች እንኳ የበለጠ ኃላፊነት ከመቀበላቸው በፊት ታማኝነታቸውንና ክህሎታቸውን በዝቅተኛ የአገልግሎት ደረጃዎች ማሳየት እንደሚገባቸው መጠበቅ ይኖርባቸዋል::

የታማኝነት ጠባይን ወይም በአገልግሎት ውስጥ ክህሎትን ላላሳዩ ሰዎች ኀላፊነትን ጨምረን በምንሰጥበት ጊዜ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት በሚገባ እያገለገልን አይደለንም:: ለሥራው ታማኝ እንደ ሆኑ፣ እንዲሁም በአገልግሎት ውስጥ ክህሎት ያላቸው እንደ

ሆኑ ላላሳዩ ሰዎች ጥሩ የድጋፍ ደብዳቤ፣ የበለጠ የአገልግሎት ኀ ላፊነት ወይም የክፍያ ጭማሪ ለማሰጥ መጋቢ ይህ ምግባራዊ የሆነ ስሕተት ነው:: ይህም ለእርሻ ሥራ በሬን ለሚፈልግ ሰው ዕ ውር የሆነ በሬ እንደ መሸጥ ያለ መጥፎ ነገር ነው:: እርሱን በማታለል ተጠቃሚ ሆነናል ማለት ነው::

ሰ. «መጠነኛ ትምህርት ኖሯቸው አሁን በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ካሉ ሰዎች ይልቅ የተማሩ ወጣቶችን ለወደፊት የመሪነት አገልግሎት በማሠልጠን ተግባር ላይ ገንዘብን ማዋል ይሻላል::» የትውልዳችን እምነት የቤተ ክርስቲያንና ለጋሾችን አንጡራ ሀብት ባልተፈተሹ የተማሩ «ወጣቶች» ላይ ማፍሰስ ይመስላል:: ዛሬ ብዙ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቀድሞውንም እያገለገሉ ያሉ ሰዎችን ማሠልጠን ጥሪትን ማባከን ነው ብለው ያስባሉ::

ነገር ግን፣ ትኩረታቸውን በወጣቶች ላይ በሚያደርጉበት ጊዜ፣ አብያተ ክርስቲያናት የሚቀበሉዋቸውን አደጋዎች አስብ::

1) ብዙዎቹ የተማሩ ወጣቶች ጥሪያቸውን ከእግዚአብሔር ዘንድ ለመለየት ጊዜ የሌላቸው ናቸው:: «ወንጌልን ባልሰብክ ወዮልኝ» (1ኛ ቆሮ. 9:16) ባለ ጊዜ ጳውሎስ የነበረውን ዝንባሌ አልተቀበሉም:: ስለዚህ፣ በአንድ ሰው ላይ ብዙ ገንዘብ ከፈሰሰ በኋ ላ፣ ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል ጥልቀት ያለው ጥሪ የሌላቸው ሰ ዎች በአብዛኛው የተሻለ ክፍያ የሚያገኙበት ሥራን ለማግኘት ወደ መንግሥት ድርጅት፣ እርዳታ ድርጅት ወይም ወደ ሌላ ኩባንያ ይሄዳሉ:: ብዙዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ምሩቃን መጨረሻቸው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማገልገል እንዳይደለ፣ ነገር ግን የተሻለ ሥራ ወዳገኙበት ወደ የትም እንደሚሄዱ በዘመናችን ተመልክተናል:: በአንጻሩም፣ በሕይወታቸው ውስጥ የእግዚአብሔር ጥሪ ከቍሳዊ ነገሮች የበለጠ አስፈላጊ እንደ ሆነ ያ ረጋገጡ ሰዎችን ማሠልጠን ላይ በምናተኩርበት ጊዜ፣ ለሌላ ሥራ ሲሉ አገልግሎትን የተዉ ሰዎች ጥቂት ሆነው እናገኛለን::

2) ለቤተ ክርስቲያን አመራር መንፈሳዊ የሆነ ጠባይ መሆኑ የተረጋገጠውን ዋና መመዘኛ ማጕልበት የሚችሉ ጥቂት ወጣቶች



ናቸው:: መንፈሳዊ ለሆነ አመራር የሚሆን ጠባይን ለማጕልበት ጊዜ ይወስዳል:: ደግሞም የአንድን ሰው ባሕርያት ለመፈተን ችግሮች ይኖራሉ:: ብዙዎቹ ወጣቶች ባሕርያቸውን በሚገልጥ መንገድ በጥልቀት አልተፈተኑም:: ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባለ የብዙ ዓመታት አገልግሎት ባሕርያቸውን ያሳዩትን ሰ ዎች ብናሠለጥን፣ ጳውሎስ በ1ኛ ጢሞቴዎስ 3 ላይ ያሰፈረውን መመዘኛዎች የሚያሟላ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ለማግኘት ትልቅ ዕድል አለን::

3) ብዙውን ጊዜ የወጣት ሰው መንፈሳዊ ስጦታዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አይታዩም:: ብዙውን ጊዜ ጥሩ ስብዕና ያለውን ሰው ወይም በመዘምራን ቡድን ውስጥ ያለ መልካም የተባለ ሰውን እንመርጥና ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት እንልካለን:: ነገር ግን፣ የዚያን ሰው መንፈሳዊ ስጦታዎች ማን ያውቃል? ወንጌል ማዳረስ ነውን? ማስተማር ነውን? ለቤተ ክርስቲያናችን ወንጌላዊ የምንፈልግ ከሆነ፣ ደግሞም እንደ ወንጌላዊነቱ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ስጦታዎቹን ያሳየ ሰው ካለ፥ ቤተ ክርስቲያንን በወንጌላዊነት ለማገልገል ተጨማሪ ትምህርት፣ ችሎታውን እንደሚያጠናክርለት እምነት ሊኖረን ይችላል::

በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ እንዲጐለብት በምንፈልገው አካባቢ ላይ መንፈሳዊ ስጦታዎችን ግልጽ በሆነ መልኩ ባሳዩ ወጣቶች ላይ እንሥራ:: ነገር ግን አብዛኞቹ ጥሪቶቻችን በእነዚያ ጥሪ ያቸውን፣ ባሕርያቸውን እንዲሁም ስጦታቸውን ባረጋገጡና ባሳዩ ሰዎች ላይ ሊውል የሚገባ ይመስላል:: እነዚህ ሰዎች ቤተሰብ እና ኀላፊነት ያለባቸው በመሆኑ በወትር ለሥልጠና አዳሪ ትምህርት ቤ ት ለመግባት አስቸጋሪ ቢሆንባቸውም፣ እነርሱን ለማሠልጠን ፈጠራ የታከለባቸውን መንገዶች መፈለግ ይኖርብናል:: እግዚአብሔር በአገልግሎት እንዲያድጉ በአብያተ ክርስቲያናችን ያሉ ወጣቶችን ለማጕልበት ጊዜንና አጋጣሚዎችን በሚጠቀምበት ጊዜ፣ ለአገልግሎት የሚሆን ወቅታዊ (ድንገተኛ) ፍላጎቶችን ያሟላሉ::

30ኛ ጥያቄ:- ሀ) ከእነዚህ ከተሳሳቱ የትምህርት ግንዛቤዎች በቤተ ክርስቲያናችሁ የትኛውን ተመልክተሃል? ለ) ከደራሲው እይታዎች ከየትኞቹ ጋር ትስማማለህ፣ ደግሞስ ከየትኞቹ ጋር አትስማማም? ለምን? ሐ) ተገቢ በሆነ መንገድ አገልጋዮችን ለማሠልጠን ቤተ ክርስቲያናችሁ ስልታዊ በሆነ መልኩ ገንዘብዋን የምትጠቀምባቸው መንገዶች ምንድን ናቸው?

## ሦስተኛ ቀን

## ሴቶች እና የቤተ ክርስቲያን አመራር

31ኛ ጥያቄ:- ሀ) ሴቶች አስተማሪ ወይም መጋቢ መሆናቸውን አስመልክቶ ቤተ ክርስቲያናችሁ የምታስተምረው ምንድን ነው? ለ) የግል አመለካከትህ ምንድን ነው? ሐ) ሴት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪ ልትሆን ትችላለች ወይም አትችልም በሚለው ላይ በምን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ላይ አመለካከትህን ታሳርፋለህ?

በዘመናችን ካሉት እጅግ አከራካሪ ከሆኑት ጉዳዮች መካከል አንዱ ሴቶች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መሆን ተፈቅዶላቸዋል ወይስ አልተፈቀደላቸውም የሚለው ጥያቄ ነው። ይህን ጥያቄ በጥልቀት መመርመር ከዚህ መጽሐፍ ዓላማ በላይ ነው። ይሁን እንጂ፣ በጉዳዩ ላይ እግዚአብሔር የተናገረውን ለመመልከት እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ከመጽሐፍ ቅዱስ እይታ አንጻር ይህን ጥያቄ በጥንቃቄ መመርመር አለበት። የምናምነውን ነገር የዘመናችን ፖለቲካዊ አጀንዳዎች እንዲወስኑ መፍቀድ የለብንም። ይልቁንም፣ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች፣ የእግዚአብሔርን ቃል ካነበብን በኋላ፣ ውሳኔዎችን ማድረግ ይኖርብናል።

መጽሐፍ ቅዱስ በሚተረጐምበት ጊዜ አንድ ግለሰብ መጽሐፍ ቅዱስን ከማንበቡ በፊት የያዘው አመለካከት ብዙውን ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን የሚተረጒምበትን ሁኔታ ይወስናል። ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩል ናቸው፣ ወንዶች ሊያደርጉት የሚችሉትን ማንኛውንም ነገር ማድረግ ይችላሉ ብለን «የምናስብ» ከሆነ፣ እንግዲያው በቅድሚያ የእኛን አቋም የሚደግፉ ክፍሎች ላይ በማተኮር ሴቶች በአመራር ስፍራ ሊሆኑ አይገባቸውም የሚሉ ለሚመስሉት ለእነዚያ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የማብራሪያ



መንገድን እንፈልጋለን። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ እኩል መሆን ሲባል ሴቶች የግድ በአመራር ስፍራ ሊሆኑ ይችላሉ ማለት አይደለም ብለን «የምናስብ» ከሆነ፣ ሴቶች በአመራር ስፍራ ላይ ሊሆኑ እንደማይገባ የሚያሳዩ ክፍሎችን እናገኛለን፣ እንዲሁም ሴቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያላቸውን ሙሉ እኩልነት የሚያሳዩ የሚመስሉ ክፍሎችን በተመለከተ መልስ ለመስጠት መንገዶችን እናገኛለን። ባህላችንና ያደግንባቸው አብያተ ክርስቲያናት ዘወትር አንዱን አሳብ ወይም ሌላውን እንድንቀበል ተጽዕኖ ያደርጉብናል። ቀድሞውኑ የያዝናቸውን አመለካከቶች ሁሉ ማስወገድና የእግዚአብሔርን ቃል በሙላት መመርመር በጣም አስቸጋሪ ነው። ነገር ግን እያንዳንዳችንም ሆነ እያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን የመጨረሻው ችሎታችንን ተጠቅመን እንድናደርገው የምንጠየቀው ይህንኑ ነው። ይሁንና፣ የቱ ትክክል ወይም ስሕተት እንደ ሆነ እግዚአብሔር እንዲነግረን እንፈቅድለትም። ነገር ግን ቀድሞውኑ አእምሮአችንን እናዘጋጃለን፣ ደግሞም መጽሐፍ ቅዱስ ከእኛ ጋር እንዲስማማ መንገዶችን እንፈልጋለን። ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ጌታ ከሆነ፣ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ጳውሎስ ያለን ሰው አስተሳሰብ ከማንጸባረቅ ይልቅ በትክክል የእርሱን ፈቃድ የሚያንጸባርቅ ከሆነ፣ እንግዲያውስ በጉዳዩ ላይ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመረዳት በመሻት መጽሐፍ ቅዱስን ልንቀርብ ያስፈልገናል። በመቀጠልም፣ በሴቶችና በአመራር ላይ የሁለቱን ዋና ዋና አመለካከቶች አቋሞችን ለማብራራት እሞክራለሁ። መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረዋል ብላችሁ የምታምኑትን ለመመልከት መጽሐፍ ቅዱሳችሁን በጥንቃቄ ማጥናት ያስፈልጋችኋል።

### ሁሉም ወንጌላውያን አማኞች የሚስማሙበት ስለ ሴቶች የተሰጠ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት።

1. ወንዶችም ሆኑ ሴቶች፣ ሁለቱም በእግዚአብሔር ፊት እኩል ዋጋ አላቸው። ዘፍጥረት 1:27-28 ወንዶች እና ሴቶች፣ ሁለቱም በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥረዋል ሲል ያስተምረናል። በተፈጠረችው ዓለም ላይ እንዲገዙ ለሁለቱም ተነግሮዋቸዋል። ስለዚህ፣ ሴቶች ተፈጥሮአዊ በሆነ መልኩ ከወንዶች ያነሱ ናቸው

የሚል፤ እንዲሁም ከእንስሳት በጥቂት እንዲሚያንስ አድርጎ የሚቆጥራቸው የትኛውም ባህላዊ አመለካከት፣ ወንዶች እንደ ሆኑት ሁሉ እንዲሁ ሴቶችም በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩ ናቸው የሚለውን የእግዚአብሔርን ትምህርት ይቃወማል።

2. ወንዶችና ሴቶች ሁለቱም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እኩል ናቸው ይባላል። በገላትያ 3:28 በቤተ ክርስቲያን ወንድ ወይም ሴት የለም፣ ነገር ግን ሁሉም አንድ ናቸው ተብሎ ተነግሮናል። እንዲሁም 1ኛ ጴጥሮስ 3:7 ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩልነት ወራሾች ናቸው ይላል። ስለዚህ፣ አንድ ሰው ሴቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለሚኖራቸው ስፍራ የቱንም አቋም ይያዝ፣ በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩል ዋጋ እና ጥቅም እንዳላቸው ማመን ይኖርብናል። ሴቶች ጉልህ ድርሻ የላቸውም፣ በእግዚአብሔር መንግሥትም ድምፃቸውን እንዲያሰሙ አይፈቀድላቸውም የሚል የቱም ባህላዊ ግንዛቤ መጽሐፍ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለ ሴቶች ሚና የሚናገረውን የሚቃወም ነው።

3. መንፈሳዊ ስጦታዎች ለወንዶችም ለሴቶችም፣ ለሁለቱም ተሰጥተዋል። በ1ኛ ቆሮንቶስ 12:11 መንፈስ ቅዱስ እርሱ ለሚሻቸው ሁሉ መንፈሳዊ ስጦታዎችን ይሰጣል ሲል ጳውሎስ ተናግሯል። በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ ከተዘረዘሩት መንፈሳዊ ስጦታዎች የቱም ስጦታ በአንድ ሰው ፆታ ላይ ተመሥርቶ የተሰጠ አይደለም። ለምሳሌ ያህል፣ «የማገልገል ስጦታ» ለሴቶች ነው፣ እንዲሁም «ወንጌልን የማዳረስ» ስጦታ የወንዶች ነው ሲል ጳውሎስ አልተናገረም።

4. ሴቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲያገለግሉ ተፈቅዶላቸዋል። ሴቶች ነቢያትና ወንጌላውያን ነበሩ (የሐዋርያት ሥራ 21:9)። 1ኛ ቆሮንቶስ 11:5 ሴቶች ሊጸልዩና ትንቢት ሲናገሩ እንደሚችሉ ይጠቁማል። ስለዚህ፣ ሴቶች በቤተ ክርስቲያን ጠቃሚ የሆነ አገልግሎት ሊኖራቸው ይችላል። ወንጌላውያኑ የማይስማሙበት ጥያቄ፣ «ሴቶች እንዲያገለግሉ መጽሐፍ ቅዱስ



የፈቀደበት ስፍራ የት ነው፣ እንዲሁም ሴቶች በቤተ ክርስቲያን ምን ያህል ሥልጣን ሊኖራቸው ይገባል?» የሚለው ነው።

5. መጽሐፍ ቅዱስ የተለመደውን ባህላዊ አመለካከት ስለ ሴቶች ያቀርባል። ኢየሱስ እርሱን እንዲያገለግሉት ለሴቶች ፈቅዶላቸዋል (ሉቃስ 8:1-3)፣ ደግሞም የትንሣኤው የመጀመሪያ ምስክሮች የሚሆኑበትን ዕድል ሰጥቷቸዋል (ሉቃስ 24:1-10)። በወንጌል ስርጭት ላይ ጉልህ ሚና የነበራቸውን ሰዎች ጳውሎስ አክብሯቸዋል (ሮሜ 16:1-7፣ 12)። ሴቶች፣ እንደ ወንዶች ሁሉ፣ በእኩልነት መንፈስ ቅዱስን ተቀብለዋል (ሐዋ. 1:14-2:4)። ሴቶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን በተመለከተ አላዋቂ ከሚሆኑ ይልቅ እንዲማሩ ተበረታትተዋል (1ኛ ጢሞ. 2:11)። ከእንዳንድ መንፈሳዊ ስጦታዎች እንደሚገለሉ የሚያሳይ አመልካች ነገር የለም። ከአይሁድ ምኩራብ ጋር በማይመሳሰል መልኩ፣ ወንዶች አስፈላጊነታቸውን ለማሳየት ከፊት የሚቀመጡበት፣ እንዲሁም ሴቶች ጸጥ ብለው ከበስተጀርባ የሚሆኑበት በአምልኮ ላይ የሚሆን መለያየት አልነበረም። ስለ ሴቶች የሆኑ እነዚህ ግንዛቤዎች በዚያን ጊዜ አይሁዶችና ግሪኮች የሴቶችን ሚና በተመለከተ ከሚረዱት በጣም የተለዩ ነበሩ።

> 32ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩል ናቸው፣ በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠሩ ቤተ ክርስቲያን ተብላ በምትታወቅ አንድ አካል የተዋሐዱ ናቸው የሚለውን አንዳንድ ክርስቲያኖች የሚያንጸባርቁበትን ባህላዊ መረዳቶች አብራራ። ለ) አማኞች ሚስቶቻቸውንና ሴቶች ልጆቻቸውን እንዴት ሊይዙ ይገባል የሚለውን በተመለከተ ሴቶች በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት የሚኖራቸውን ዋጋ እና ጥቅም ግንዛቤ ተግባራዊ ለማድረግ ቤተ ክርስቲያን ልታደርጋቸው የሚገቡ አንዳንድ ነገሮች ምንድን ናቸው?

## ሴቶች በቤተ ክርስቲያን አመራር ላይ ስለሚኖራቸው ስፍራ ወንጌላውያን አማኞች የያዟቸው ሁለት ዋና አመለካከቶች።

ምንም እንኳ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ከላይ ያሉትን ነጥቦች የሚያምኑ ቢሆንም፣ ሴቶች በቤተ ክርስቲያን ምን ዓይነት አገልግሎቶች ሊኖራቸው ይችላል፣ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን

ውስጥ ምን ያህል ሥልጣን እግዚአብሔር ለሴቶች ፈቅዶላቸዋል በሚሉት ላይ የሰሉ ክርክሮች አሉ። ይሁን እንጂ፣ በታሪክ ሁሉ ውስጥ ያለው አጠቃላዩ ግንዛቤ መደበኛ በሆነ አመራር ውስጥ ሴቶች በሥልጣን ስፍራ መቀመጥ የለባቸውም የሚል ነው። ይሁን እንጂ፣ በቅርቡ በመሰው ዓለም በማኅበረሰቡ ውስጥ የሴቶችን ሚና በተመለከተ ሴቶች በምን ዓይነት አገልግሎቶች መሳተፍ እንደሚገባቸው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲይዙትም የሚፈቀድላቸው ሥልጣን ምን ያህል ነው የሚለውን በተመለከተ ልማዳዊው መረዳት መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረዋል ብሎ የሚናገረውን ቤተ ክርስቲያን እንደ ገና እንድትመረምር ተገደደች። ዛሬ ከዚህ ጋር የሚዛመዱ ሁለት ጥያቄዎች መከራከሪያ ሆነዋል።

የመጀመሪያው፣ ሴቶች በሁሉም የቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች ውስጥ ማገልገል ይችላሉን? በወንዶች በተሞላው የእሑድ ትምህርት ቤት ውስጥ አስተማሪ መሆን ትችላለችን? መጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ መንፈሳዊ ስጦታዎች ለወንዶች ብቻ የተ ወሰኑ ናቸው በማለቱ ብቻ ምክንያት ሴቶች መንፈሳዊ ስጦታዎቻ ቸውን ያለ ምንም ቅድመ - ሁኔታ እንዲጠቀሙበት ተ ፈቅዶላቸዋል ማለት አይደለም። ስለዚህ፣ ለአንዲት ሴት የወንጌል ማዳረስ ስጦታ በብቃት ደረጃ ሊሰጣት ይችላል፣ ነገር ግን ያን ስጦታ በመጠቀም ረገድ በሴቶች መካከል በማገልገል የተወሰነች ናት። ወይም የማስተማር መንፈሳዊ ስጦታ ሊኖራት ይችላል፣ ነገር ግን ልታስተምር የሚፈቀድላት ልጆችንና ሴቶችን ብቻ ነው። እግዚአብሔር መንፈሳዊ ስጦታን ለሴቶች የሚሰጥ ከሆነ፣ መንፈሳዊ ስጦታውን እንዴት ልትጠቀምበት ይገባል በሚለው ላይ ምንም ቅድመ - ሁኔታ ሊኖር አይገባም የሚለውን አሳብ ሌሎች በጥብቅ ይለንዝሩታል። ሁሉም አገልግሎቶች ለሴቶች ክፍት ናቸው። ስለዚህ፣ ሴቶች መንፈሳዊ ስጦታዎቻቸውን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመጠቀማቸው ረገድ እገዳዎች አሉ ወይስ የሉም በሚለው ላይ ምሁራን ይከራከሩበታል።

ሁለተኛ፣ አንዲት ሴት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊፈቀድላት የሚገባው ሥልጣን ምን ያህል ነው? ሴቶች ከወንዶች እኩል



ክፍት የሆነላቸው ወንዶች በያዙት መጠን ሊኖራቸው የሚችል ሥልጣን ተፈቅዶላቸዋልን? ለሊያም ሴቶች በአመራር ስፍራ ሊቀመጡ ወይም በወንዶች ላይ ሊሠለጥኑ ከቶ አልተ ፈቀደላቸውምን? አንዳንድ ክርስቲያኖች በሽማግሌዎች ሥልጣን ሥር እስከ ሆነች ድረስ፣ ሴት የወንዶች የእሑድ ትምህርት ቤት ማስተማር ትችላለች ብለው ያምናሉ። ወንዶችን ማስተማሩን ብቻ ሳይሆን፣ የምታስተምረውንም ትምህርት ተቀባይነት እንዳለው አድርገው ይቀበላሉ። ሴት በሥልጣን ላይ ላሉ ሰዎች እስከ ታዘዘች ድረስ (ባልዋም ይሁን ወይም ሽማግሌዎች)፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ አገልግሎቶች ለእርስዋ ክፍት ናቸው ብለው ይናገራሉ። ይህን አመለካከት የያዙ ሰዎች በአብዛኛው አመራርን ለወንዶች ብቻ የሚገድቡ ናቸው፣ ነገር ግን ሴቶች በየትኛውም የአገልግሎት ዓይነቶች ውስጥ መሳተፍ ይችላሉ። ሌሎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ «የወንድና የሴት ልዩነት» ከሌለ (ገላ. 3:28)፣ እንግዲያውስ በሴቶች ላይ ምንም የአመራር ገደብ ሊኖር አይገባም በሚለው ይጸናሉ።

በመቀጠልም ከእነዚህ ሁለት ጥያቄዎች ጋር የሚዛመዱ ዋነኞቹን ክፍሎች እንመረምራለን። ሁለቱም ቡድኖች በሙላት ወደ እግዚአብሔር ቃል ሊመጡ፣ እንዲሁም ለእነዚህ ለሁለቱ ጥያቄ ዎች የእግዚአብሔርን ምላሽ ሊፈልጉ ይገባል። ሁላችንም ጠንቃቆች ልንሆንና አመለካከቶቻችንን በማስረጃ ለመደገፍ፣ የእግዚአብሔርን ቃል አተረጓጐም ለመጠምዘዝ ባህላዊ መረዳታችን እንደሚዳርገን መገንዘብ ያስፈልገናል።

እንደ አለመታደል ሆ፣ እነዚህን ክፍሎች ለመተርጐም የበለጠ አስቸጋሪ የሚያደርገው ጳውሎስ ይህን ትእዛዝ እንዲሰጥ የገፋፋውን የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ ያለን በጣም ትንሽ መረዳት ነው። ወደ ቤታቸው እየገባህ ባለበት ጊዜ፣ አባት ልጁን «ልትናገር አልተፈቀደልህም» ሲለው ትሰማለህ። አባትየው ለልጁ ይህን ልትናገር አልተፈቀደልህም ያለበትን ሁኔታ የማታውቀው ከሆነ፣ አባትየው ልጁ በቤት ውስጥ እንዲናገር አይፈቅድለትም ብለህ ልታስብ ትችላለህ። ነገር ግን፣ አባትየው ከልጁ ጋር በአንድ ነገር

ላይ ሲከራከር ከቆየ በኋላ፣ «በዚህ ጉዳይ ላይ ሌላ ቃል አትናገር» ብሎትስ ቢሆን? ልክ ከመድረሱ በፊት በቤቱ ውስጥ የተከሰተውን ነገር ለማወቅ አንድን ሰው የተሳሳተ ግንዛቤ እንደሚያስጨብጠው ሁሉ፣ እንዲሁ በቆሮንቶስ እና በኤፌሶን ባሉ አብያተ ክርስቲያናት የተከሰተውን ነገር ለማወቅ ጳውሎስ ትእዛዙን የሰጠበትን መነሻ ታሪክ ለማወቅ አስቸጋሪ ሆኖብናል። «አታመንዝር» ከሚለው ጋር ተመሳሳይ የሆነ በሁሉም አገሮች ላሉት ለመላዋ ቤተ ክርስቲያን የሚሆን ሁሉን ዓቀፍ ትእዛዝ ለመስጠት ጳውሎስ እየፈለገ ነበርን? ወይስ ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለ የተለየ ሁኔታን አስመልክቶ እየተናገረ፣ እንዲሁም ችግሩን ለመፍታት ጊዜያዊ ክልከላዎችን እያደረገ ነበር? ከታች የሰፈረው ጥናታችን የመጀመሪያው አመለካከት የጳውሎስ ትእዛዛት በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ላይ ተፈጻሚነት የሚኖረው ሁሉን ዓቀፍ ትእዛዛት እንደ ሆነ ይረዳል። ሁለተኛው አመለካከት የጳውሎስ ትእዛዝ በቆሮንቶስ እና በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ያለን ችግር የሚዳስስ ጊዜያዊ ትእዛዝ እንደ ሆነ ይመለከታል። ይህን አመለካከት የሚደግፉ ሰዎች እነዚያ ትእዛዛት በእኛ ላይ በቀጥታ ተግባራዊ አይሆኑም በሚለው ይጸናሉ።

| |
|---|
| 33ኛ ጥያቄ፡- የሚከተሉትን ክፍሎች አንብብ፡- ገላ. 3:28፤ 1ኛ ቆሮ. 11:3-16፤ 1ኛ ቆሮ. 14:33-35፤ 1ኛ ጢሞ. 2:11-15። እነዚህ ክፍሎች ሴቶች በአመራር ላይ ስለሚኖራቸው ሚና የሚያስተምሩዋቸው መርኖዎች ምንድን ናቸው ብለህ ታምናለህ? |

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሴቶችን መሪ ከመሆን እና ከማስተማር የሚከለክሉ የሚመስሉ ክፍሎችን ለመተርጐም ብዙ መንገዶች አሉ። በመሠረቱ ሴቶች በቤተ ክርስቲያን ለማገልገል፣ እንዲሁም የሽማግሌዎችንና የመጋቢያንን ስፍራ ለመያዝ የሚፈቀድላቸው መሆኑን የሚያመለክቱትን እነዚያን ክፍሎች በተመለከተ ሁለት መሠረታውያን አመለካከቶች አሉ። በእያንዳንዱ ዋና አቋም ውስጥ እያንዳንዱ ቡድን አመለካከቱን እንዴት ተግባራዊ ያደርጋል በሚለው ላይ ብዙ ልዩነቶች አሉ። ስለዚህ፣ አንዳንድ ወንጌላውያን ሴቶች በየትኛውም የማስተማር አገልግሎቶች ውስጥ መሳተፋቸውን ይቃወማሉ፣ እንዲሁም ሌሎች ደግሞ ከሽማግሌዎች ፈቃድ እስካገኙ ድረስ፣ ማንንም እንዲያስተምሩ ይፈቅዳሉ። በዚህ ጉዳይ ላይ ሁሉም የተለያዩ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ያሏቸውን ልዩ ልዩ አቋሞች አንመረምርም። ይልቁንም፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሴቶች ስለሚኖራቸው ሚና ወንጌላውያን የያዙዋቸውን ሁለቱን ዋና ዋና መረዳቶች ከዚህ በታች እንመለከታለን።

1. ምንም እንኳ ባላቸው ዋጋና ጠቃሚነት እኩል ቢሆኑም፣ መጽሐፍ ቅዱስ ሴቶችን ከወንዶች ራስነት በታች አስቀምጦአቸዋል።

ሀ. በደረጃ አንድ ናቸው ማለት የግድ አንድ ሰው እኩል ሥልጣን አለው ማለት አይደለም። የሥላሴ አካላት ሁሉ እኩል ናቸው። እያንዳንዳቸው ሁሉን ቻይ፣ አፍቃሪ፣ ሁሉን አዋቂ፣ ጻድቅ፣ ፈጣሪ፣ ወዘተ. . . ሆነው፣ በባሕርያቸው እኩል ናቸው። ነገር ግን ኢየሱስ ለአባቱ በመታዘዝ ኖሯል። አብ እርሱን ላከው፣ ኢየሱስ አብን አልላከውም። እንዲሁም ኢየሱስ እርሱ የደረጋቸው ሥራዎች ሁሉ እና የተናገራቸው ቃሎች ሁሉ ከእግዚአብሔር አብ እንደ መጡ ተናገረ (ዮሐ. 7:16-18፤ 12:49)። ጳውሎስ ታሪክ በሚደመድምበት ጊዜ፣ ኢየሱስ መንግሥትን ለአብ ይመልሳል፣ እርሱም ራሱ ለአባቱ ይገዛል (1ኛ ቆሮ. 15:28) ብሎ ተናግሮአል። በተመሳሳይ መንገድ፣ አብና ወልድ መንፈስ ቅዱስን ልከዋል ተብሎአል (ዮሐ. 14:26፤ 15:26)። ይህ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ሥልጣን እንዳላቸው ያመለክታል። ይህ የሥላሴ ምሳሌነት፣ ሁሉም እኩል ባሕርይ ኖሯቸው ሳለ፣ የተለያዩ የሥልጣን ደረጃዎች ያላቸው መሆኑ ወንዶችና ሴቶች እኩል እንዲሆኑ፣ ሆኖም ግን፣ ወንዶች በሴቶች ላይ ሥልጣን እንዲኖራቸው ያስችላቸዋል።

ለ. በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ፣ የብሉይ ኪዳን ሕዝቦች መሪዎችም ሆነ አይሁድ፣ አሊያም የአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝቦች፣ ቤተ ክርስቲያን፣ ሴቶች መሪዎች አልነበሩዋቸውም። የአሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች መሥራቾችም ሆኑ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት፣ ሁለቱም ቡድኖች የተዋቀሩት በወንዶች ነበር።

አመራር ከወንዶች ጋር የተያያዘ ስለ መሆኑ መዋቅራዊ አሠራሩን እግዚአብሔር በግልጽ አበጅቶታል።

ሐ. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሴቶች በመሪነት ሚና ሳይ የነበሩባቸው ጊዜያት እንደ እንግዳ (ያልተለመዱ) ተደርገው የታዩበት ሁኔታ ነው ያለው። ነቢይት ዲቦራ እስራኤልን መርታለች። ነገር ግን የነፃ አውጪነትን ሚና ባርቅ ለመውሰድ እንቢ ባለ ጊዜ ዲቦራ ባርቅን ገሥጻችው፤ ደግሞም ላላመኑ በሆነው ቅጣት ውስጥ ነፃ የማውጣቱ ሚና ወደ ሴቶች የሚሄድ ሆኗል። ስለዚህም፤ የጠላትን ጦር ሠራዊት መሪ (አዛዥ) የገደለችው ሴት ነበረች (መሳ. 4:4-24)። ዲቦራ እና ባርቅ የዘመሩት ዝማሬ ባርቅ ከዲቦራ የሚያንስ መሆኑን አያመለክትም። ደግሞም የዕብራውያን ጸሐፊ እንደ እምነት ምሳሌ አድርጎ የዘገበው ስለ ዲቦራ ሳይሆን ስለ ባርቅ ነው (ዕብ. 11:32)። በይሁዳ ላይ ገዢ የነበረችው ብቸኛዋ ንግሥት የዳዊትን የዘር ሐረግ ለማጥፋት ሞክረች (2ኛ ዜና 22:10 -12)። ስለዚህ፤ ሴት በሕዝቡ ላይ እንድትገዛ እግዚአብሔር የመደበት ልዩ የሆኑ ምሳሌዎች የሉም።

መ. እጅግ ተፈጥሮአዊ የሆነው የክፍሎቹ ንባብ እንዲሁም በጳውሎስ የተሰጡትን ትእዛዛት ቤተ ክርስቲያን በታሪክ ውስጥ እንዴት ተረዳችው የሚለው የሚያመለክተው ሴቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪዎች አይሆኑም ነበር የሚለው ነው።

1) 1ኛ ቆሮንቶስ 11:1-16:- በዚህ ክፍል ጳውሎስ ሁለት እውነቶችን ሚዛናዊ ለማድረግ ይፈልጋል። በአንድ በኩል፤ በእግዚአብሔር አሠራር፤ ሴት ለባልዋ በመታዘዝ ውስጥ ናት። ልክ እግዚአብሔር የክርስቶስ ራስ ወይም በክርስቶስ ላይ ሥልጣን እንዳለው ሁሉ፤ በተመሳሳይ መንገድ ባል በሚስቱ ላይ ራስ ነው። ራስነት፤ ራስ የሆነው ከእርሱ በታች ያለውን ሰውየው የእርሱ ባሪያ የሆነ ይመስል የሚያዝዝበት ከቶ እንዳይደለ ዐውደ ንባቡ በግልጽ ያስተምረናል። የእግዚአብሔር አብ ራስነት ወልድን በተለየ ሁኔታ እንዲይዘው አላደረገውም። ይልቁንም፤ ከሌሎች ስሞች ሁሉ በላይ የሆነውን ስም በመስጠት በፍቅር አብ ኢየሱስን ሊያከብረው ፈለገ። በተመሳሳይ መንገድ፤ ራስ ተብሎ መጠራቱ፤ ባል



ሚስቱን ምንም ነገር የመናገር መብት እንደሌላት ሲቆጥራት ወይም እንደ ገዛ ንብረቱ ሲይዛት ይችላል ማለት አይደለም። ይልቁንም፤ ፡ ከ ኤፌሶን 5:25-33 እንደሚያመለክተው፤ ባል ለሚስቱ ያለው ፍቅር ሕይወቱን በፈቃዱ ስለ እርሷ የሚያስጥ ነው። ተቀዳሚ ትኩረቱ ስለ ፍላጎቶችዋ መሟላት እንክብካቤ ማድ ረግ ነው።

ይሁን እንጂ፤ ራስ መሆን በሌላው ላይ ሥልጣን መያዝንና የመምራት ኃላፊነት መቀበልን ያሳያል። ኢየሱስ የእግዚአብሔር አብ «ራስ» እንዳልተባለ ሁሉ፤ ሚስትም የባል ራስ ተብላ የተ ጠራችበት ስፍራ የለም። የሥልጣን ተዋረዱ ከአብ ወደ ወልድ እንጂ ከወልድ ወደ አብ አይሄድም። ከባል ወደ ሚስት እንጂ ከሚስት ወደ ባል አይሄድም። በቆሮንቶስ ባህል፤ ራስን መሸፋፈን ባል በሚስቱ ላይ ሥልጣን እንዳለው የሚያሳይ ምልክት ነበር። ይህንን አለማድረግ፤ እንዲት ሴት በባሏ ላይ ማመፅዋን የሚያሳይ ነበር። ጳውሎስ ይህ እግዚአብሔር ባል የሚስቱ ራስ እንዲሆን የወሰነውን ትእዛዝ እንደ መጣስም ነው ሲል ገልጾአል። በዘመናችን ራስን መከናነብ የተለየ ትርጉም ሳይረው ይችላል። መሠረታዊ መርሑ ግን ስምምነት ያለው ግንኙነት ለመመሥረት መዋቅር ስለሚያስፈልግ፤ እግዚአብሔር ባል የሚስት ራስ እንዲሆን መወሰኑን የሚያሳይ ነው።

በሌላ በኩል ጳውሎስ ባሎች የራስነትን አስተሳሰብ በማዛባት ወንዶች ሚስቶቻቸውን ወይም ሌሎች ሴቶችን እንደ ፈለጉ ሊያደርጉ ይችላሉ የሚል መልእክት ሳለማስተላለፍ ጥንቃቄ አድርጓል። ወንዶችና ሴቶች የተያያዙ ስለሆኑ፤ እንዱ ሌላው ያስፈልገዋል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጸው ትክክለኛ ግንኙ ነት ባልና ሚስት አንድነትን ለመመሥረት ተባብው የሚሠሩበት ነው። ባል ባለ ሥልጣን ሆኖ ሚስቱን የሚያዝበትና ሚስትም ምንም ዓይነት ጥያቄ ሳታነሣ የታዘዘችውን የምትፈጽምበት ትዳር ግንኙነት ነው ሊባል አይችልም። የባልና ሚስት አንድነት ከአብና ወልድ አንድነት ጋር ተመሳሳይ ነው። ኢየሱስን ማየት ማለት እግዚአብሔርን ማየት ነው (ዮሐ. 14:8-11)። ኢየሱስ አብን አክብሯል። አብም ወልድን አክብሯል (ዮሐ. 17:1-5)።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሌሎች ምንባቦችን በምንተረጉምበት ጊዜ ልናስታውሰ የሚገባን ነገርም አለ:: በ1ኛ ቆሮንቶስ 11:5 «የምትጸልይ ወይም ትንቢት የምትናገር ሴት» ይላል:: የዚህ ምንባብ ዐውድ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚካሄድ አምልኮ ነው:: አንዲት ሴት ራሷን እስከ ሸፈነች ድረስ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ልትጸልይና ትንቢት ልትናገር ትችላለች ማለት ነው:: ስለሆነም፣ በ1ኛ ቆሮንቶስ 14:34 ውስጥ ሴት ዝም እንድትል የተሰጠው ትእዛዝ፣ ሴት በምንም ዓይነት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መናገር የለባትም ማለት አይደለም:: ስለ 1ኛ ቆሮንቶስ 14:34 የሚኖረን ማንኛውም ግንዛቤ ይህንን ምንባብ ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አለበት::

ጳውሎስ ወንድ የሴት ራስ መሆኑ እግዚአብሔር ዓለምን በፈጠረበት ጊዜ ያደረገው ነገር እንደ ሆነ አመልክቷል:: እግዚአብሔር መጀመሪያ ወንድን፣ ከዚያም ሴትን ፈጠረ:: ሁሉንም እንስሳት የፈጠረው በአንድ ጊዜ ሲሆን፣ ሰውን ሲፈጥር ግን ወንድን መጀመሪያ ነበር የፈጠረው:: ሴትን የፈጠረው አዳም እንደ እርሱ ያለ ረዳት እንዲኖረው ነበር:: ጳውሎስ ይህ የእግዚአብሔርን የግንኙነት መስመር፣ ማለትም ወንድ (ባል) የሴት (ሚስት) ራስ መሆኑን ያመለክታል ብሏል:: ይህ ጳውሎስ በአንድ ቦታና ጊዜ የተወሰነን ባህላዊ ጉዳይ እየዳሰሰ ነው እንዳንል የሚያደርግ ነው:: ጳውሎስ ለትምህርቱ ፍጥረትን ምክንያት ማድረጉ ምንም ዓይነት ባህል ከመኖሩ በፊት እግዚአብሔር የግንኙነትን ሥርዓት እንደ መሠረተ የሚያሳይ ነው:: ስለዚህ፣ በየትኛውም ባህልና ትውልድ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ይህንን መከተል አለባቸው::

ሴት በመሪነት ቦታ ላይ መቀመጥ የለባትም የሚሉ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከእግዚአብሔር የሚመነጭና በባልና ሚስት ግንኙነት ውስጥ የተገለጠ የሥልጣን ተዋረድ አለ ብለው ያምናሉ:: ባል የሚስቱ «ራስ» ነው:: እንዲሁም ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወንድ ሽማግሌዎች በሴቶች ላይ ሥልጣን አላቸው ብለው ያምናሉ:: እግዚአብሔር ከኢየሱስ ወይም ኢየሱስ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ባለው የራስ ምሳሌ፣ ወንዶችም በሴቶች ላይ ተመሳሳይ የሆነ የፍቅር ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባል:: ሴቶች



በዚህ ሥልጣን ሥር እስካሉ ድረስ፣ እንደ መጸለይና ትንቢት መናገር የመሳሰሉትን አገልግሎቶች ማካሄድ ይችሉ ነበር::

34ኛ ጥያቄ:- ሀ) አብዛኞቹ ኢትዮጵያውያን ወንዶች «ወንድ የሴት ራስ ነው» የሚለውን ሐረግ የሚረዱት እንዴት ነው? ለ) ስለ «ራስ» ያለን ግንዛቤ የመነጨው እግዚአብሔር የኢየሱስ ራስ መሆኑን ከመመልከት ከሆነ፣ ይህ ባል የሚስቱ ራስ ነው የሚለውን አሳብ እንድንረዳ የሚመራን እንዴት ነው? ሐ) አብዛኞቹ ወንዶች ራስነት የሥላሴን ግንኙነት ምሳሌነት የሚከተል መሆኑን ቢገነዘቡ የጋብቻ ግንኙነቶች እንዴት ሊቀየሩ የሚችሉ ይመስልሃል?

2) 1ኛ ቆሮንቶስ 33:35:- በ1ኛ ቆሮንቶስ 14፣ ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያን አምልኮ «ተስማሚ» እና «ሥርዓት» ያለው እንዲሆን የሚያስችሉትን ትምህርቶች ሲሰጥ እንመለከታለን (1ኛ ቆሮ. 14:40):: ትንቢትንና ልሳንን በተመለከተ ተገቢው አምልኮ ምን ዓይነት እንደ ሆነ መመሪያዎችን ሰጥቶአል:: ነገር ግን በአጭሩ ከጠቀሳቸው ነገሮች አንዱ በአምልኮው ውስጥ የሴቶች ሚና ምን መሆን እንዳለበት ነው:: ሴቶች «ዝም» እንዲሉ ነበር ያዘዘው:: ከዚያም ሴቶች «እንዲገዙ« አዝዟል:: ይህንን ትእዛዝ ሴቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲጸልዩና ትንቢት እንዲናገሩ ከሚያበረታታው የ1ኛ ቆሮንቶስ 11:5 አሳብ ጋር ስናነጻጽር፣ የጳውሎስ መልእክት ሴቶች ትንፍሽ እንዳይሉ ማዘዝ አይመስልም:: ይህ «የመገዛት» ጉዳይ ነው:: ጳውሎስ ሁለት ችግሮችን በመግለጽ ላይ ነው::

በመጀመሪያ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሥርዓት-አልባነት ችግር ነበር:: አንዳንድ ምሁራን እንደሚሉት፣ ትምህርት ያልነበራቸው የቆሮንቶስ ሴቶች የተሰጠው ትምህርት እንዳልገባቸው ወይም እግዚአብሔር ስለሚያደርጋቸው ነገሮች የራሳቸውን አሳብ ለመሰንዘር ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ይጮሁ ነበር:: ይህ ደግሞ አምልኮውን ይረብሽ ነበር:: ጳውሎስ ሴቶች በቤታቸው ከባሎቻቸው መረጃዎችን ሊያገኙና አሳባቸውን ሊገልጹላቸው እንደሚገባ ተናግሯል:: እግዚአብሔር በአምልኮ ውስጥ ነገሮች በሥርዓትና በአገባብ በሚከናወኑበት ጊዜ ይከበራል::

ሁለተኛ፣ ጳውሎስ ሴቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚናገሩት ስባሎቻቸውና ለወንድ ሽማግሌዎች ሥልጣን በመገዛት መሆን እንዳለበት ይገልጻል:: ስለሆነም፣ ሴቶች ሲጸልዩና ትንቢት ሲናገሩ (ወይም ማንኛውንም ዓይነት አገልግሎት ሲሰጡ) የዐመፀኝነትን መንፈስ በመላበስ ወይም ለእኩልነት በመጋፋት ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ለሰጠው ሥርዓት ተገዥ መሆን አለባቸው:: ባሎቻቸው ወይም የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች በሚያጸድቁላቸው መንገድ አገልግሎታቸውን ያከናውናሉ:: ሴቶች ትሕትናን በመላበስ ወንድ ሽማግሌዎች የሚናገሩትን እሳብ እንዲገመግሙና የተሳሳተ ነገር ካለም እንዲያርሟቸው መፍቀድ አለባቸው:: ሽማግሌዎች ወይም ባሏ ፍርድ በሚሰጡበት ጊዜ፣ አንዲት ሴት መገዛት አለባት::

35ኛ ጥያቄ:- ሀ) አንዳንድ አማኞች በአምልኮ ወቅት የሚያደርጓቸው አግባብነትና ሥርዓት የጎደላቸው ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? ለ) አንዲት ሴት ለባሏና ለሽማግሌዎች በመገዛት እንዴት ልታገለግል እንደምትችል ግለጽ::

ኤፌሶን 5:22-24:- ይህ ምንባብ ሴት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለሚኖራት ተግባር የሚናገር አይደለም:: ነገር ግን በ1ኛ ቆሮንቶስ 11:1-16 ስለ «ራስ»፣ እንዲሁም በ1ኛ ጢሞቴዎስ 2:11 ሴቶች በ«መገዛት» መማር እንዳለባቸው የሚያስረዳው አሳብ በዚህም ክፍል ውስጥ ተመልክቷል:: ጳውሎስ በባልና ሚስት መካከል ሊኖር የሚገባውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሕ ነበር የገለጸው:: በዚህ ክፍል የጳውሎስ ትምህርት የሚያተኩረው በትዳር ውስጥ ባል ስለሚኖረው ሚና እንጂ፣ ስለ ሚስት አይደለም:: ኢየሱስ እንደ ሞተልን ሁሉ፣ ባልም ራሱን በመሠዋት ፍቅሩን ሊገልጽላት ይገባል:: ሴት ለባሏ «እንድትገዛ» እና «እንድታከብረው» ታዝዛለች (ኤፌ. 5:33):: ሚስት መገዛት ያለባት ልክ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን «ራስ» በሆነበት መንገድ ባል የሚስት ራስ ስለሆነ ነው:: ቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር እኩል ናት ወይም ትበልጠዋለች ማለቱ ትክክል እንደማይሆን ሁሉ፣ ሴትም በሥልጣን ከባሏ ጋር «እኩል» እንዳልሆነች ጳውሎስ ያስረዳል:: በእግዚአብሔር ፊት ባላት እሴትነት እኩል ብትሆንም፣



እግዚአብሔር ባል በሚስቱና በቤተሰቡ ላይ ሥልጣን የሚይዝበትን ሥርዓት መሥርቷል:: (ማስታወሻ:- ልጆች ለወላጆቻቸው «እንዲታዘዙ» ሲጠየቁ፣ ሚስት ግን ለባሏ «እንድትገዛ» ነው የታዘዘችው::) ጳውሎስ መገዛት ሲል፣ ሚስት (ሴት) የምታደርገው ማንኛውም ተግባር ባሏ (ሽማግሌ) በእርሷ ላይ ያለውን ሥልጣን የሚቃወም መሆን የለበትም ማለቱ ነው:: (ይህ በምእመናንና በቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች መካከል ያለውን ግንኙነትም ይመለከታል::) በፍቅርና በውይይት ሲፈቱ የማይችሉ አከራካሪ ጉዳዮች በሚኖሩበት ጊዜ፣ ሚስት መብቶቿን (አሳቦቿን) በመተው ባሏ (ሽማግሌዎች) ውሳኔ እንዲሰጥ ማድረግ አለባት:: ነገር ግን ይህ ምንባብ በቤተ ክርስቲያንና በሴቶች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚመለከት ከሆነ፣ ሽማግሌዎች በሴቶች ላይ ሥልጣናቸውን መጠቀም ያለባቸው ልክ ባሎች ለሚስቶቻቸው በፍቅር በሚራሩበት መንገድ መሆን እንዳለበት ያስረዳል:: ባል ወይም ሽማግሌ ሥልጣን አለው ማለት ሴቶች የሚናገሩትን መስማትም ሆነ አመለካከታቸውን ለመረዳት መጣር የለባቸውም ማለት አይደለም:: ነገር ግን የማይታረቁ አመለካከቶች በሚኖሩበት ጊዜ፣ ሴት የሽማግሌውን ውሳኔ መቀበል አለባት:: ሴቶች የሚያደርጉት ማንኛውም ነገር ሽማግሌዎች በእነርሱ ላይ ያላቸውን ሥልጣን የሚቃወም መሆን የለበትም::

36ኛ ጥያቄ:- ሀ) እብዛኞቹ ወንዶች ኢየሱስ በመስቀል ላይ በመሞት ባሳየው ዓይነት ፍቅር ሚስቶቻቸውን እንዲወዱ ታዝዘው ሳለ፣ ሴቶች ለባሎቻቸው መገዛት አለባቸው በሚለው አሳብ ላይ ትኩረት የሚያደርጉት ለምንድን ነው? ለ) ባሎች ሚስቶቻቸው እንዲገዙላቸው ለማስገደድ ከመሞከር ይልቅ፣ ሚስቶቻቸውን በማፍቀር ላይ ትኩረት ቢያደርጉ ጋብቻ ምን ያህል የሚለወጥ ይመስልሃል? ሐ) ሽማግሌዎች በሴቶች ላይ ያላቸውን ሥልጣን ከማሳየት ይልቅ፣ ፍቅር በመስጠት ላይ ትኩረት ቢያደርጉ፣ የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ እንዴት የሚለወጥ ይመስልሃል?

4) 1ኛ ጢሞቴዎስ 2:11-15ን:- ጳውሎስ አሁንም የሚናገረው ስለ ቤተ ክርስቲያን አምልኮ ነው:: (1ኛ ጢሞ. 2:1 እንብብ::) ከጠቀሳቸው ነገሮች አንዱ ሴቶች በሕዝባዊ አምልኮ ላይ ምን ማድ

ረግ እንዳለባቸው ነው። ሴቶቹ ያሉበት ባህል በሚጠይቀው መንገድ በአግባቡ መልበስ እንዳለባቸው ከገለጸ በኋላ (1ኛ ጢሞ. 2:9-10)፣ ሴቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስላላቸው ሥልጣን ማስተማሩን ይቀጥላል። የሚከተሉትን ነጥቦች እጢን፡-

ሀ) ሴት እንድትማር ትበረታታለች። ጳውሎስ ሴቶች ልክ እንደ ወንዶች የእግዚአብሔርን ቃል እንዲያውቁ ያበረታታቸዋል።

ለ) ሴት በ«ጸጥታና በመገዛት» እንድትማር ታዝዛለች። «ጸጥታ» የሚለው ቃል በግሪኩ ጭራሽ አለመናገርን ሳይሆን፣ አለመረበሽን የሚያሳይ ነው። ሴት የተከራካሪነት አስመለካከት ሊኖራት አይገባም። ሴት ከሚያስተምራት ወንድ የተለየ አመለካከት በሚኖራት ጊዜ አሳቧን መግለጽ ብትችልም፣ ለሚያስተ ምራት ወንድ (ምናልባትም ሽማግሌ) አሳብ መገዛት አለባት።

ሐ) ሴት «እንድታስተምር» አልተፈቀደላትም። ቀደም ሲል በ1ኛ ቆሮንቶስ 11:5 ላይ ሴት ትንቢት መናገር እንደምትችል ስለ ተመለከትን፣ አለማስተማር ማለት ዝም ማለትን አያመለክትም። ጳውሎስ ማስተማርን ከሥልጣን ጋር ያገናኘው፣ ሴት የቤተ ክርስቲያን መሪ የሆነው ሽማግሌ የያዘውን ሥልጣን ያዘለ የማስተማር ተግባር እንድታከናውን ባለመፈለጉ ነው።

መ) ሴት በወንድ ላይ ሥልጣን የላትም። ከላይ የተመለከተ ውን አመለካከት የሚይዙ ሰዎች ይህንን እንደ ዋንኛ ጥቅስ ይጠቀማሉ። እነዚህ ወገኖች ጳውሎስ በመልእክቶቹ ሁሉ ባለማቋ ረጥ የሚናገረው ነገር ቢኖር ሴት በመሪነት ወይም በሥልጣን ስፍራ ላይ መሆን እንደሌለባት ነው። ስለዚህ በወንዶች ላይ ሥልጣን በመያዝ ሽማግሌ ወይም አስተማሪ መጋቢ ልትሆን አትችልም ይላሉ። (የሴቶች ወይም የልጆች መጋቢ ልትሆን ትችላለች። የወንዶች መጋቢ ግን ልትሆን አትችልም። ቲቶ 2:3-5 አረጋውያን ሴቶች ወጣት ሴቶችን እንዲያስተምሩ ያበረታታል።) (ማስታወሻ፡- አንዳንድ ምሑራን ጳውሎስ ሥልጣን ያለውን የማስተማር ተግባር ማከናወን ያለበት ሽማግሌ ነው የሚል አቋም እንደ ነበረው ያስረዳሉ። ስለሆነም፣ ሴቶች ብቻ ሳይሆኑ፣ ሽማግሌ ያልሆኑ ወንዶችም ማስተማር የለባቸውም ይላሉ።) ጳውሎስ ሴት ያዘዛትን ወንድ ሁሉ መታዘዝ አለባት የሚል አቋም የነበረው አይመስልም። መታዘዝ ያለባት ባሏንና የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌን፣ በተለይም አስተማሪ ሽማግሌን ነው።

ሠ) ጳውሎስ ሴቶች በወንዶች ላይ ሥልጣን ሊኖራቸው አይገባም ያለው በፍጥረት መጀመሪያ ላይ በተከሰተው ሁኔታ ላይ በመመሥረት ነው።

አንደኛ፣ የፍጥረትን ቅደም ተከተል ጠቅሶአል። እግዚአብሔር መጀመሪያ ወንድን፣ በመቀጠል ደግሞ ሴትን የፈጠረበት ምክንያት ሥልጣን (አመራር) የወንዱ (የባል ወይም የሽማግሌ) እንዲሆን በመፈለጉ ነው።

ሁለተኛ፣ ሴት መጀመሪያ በኃጢአት መውደቋና ወንድ ደግሞ እርሷን ተከትሎ ኃጢአት መሥራቱ መንፈሳዊ ሥልጣን የወንድ መሆን እንዳለበት ያሳያል።

ጳውሎስ ክርክሩን በፍጥረት ላይ መመሥረቱ በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለውን አካባቢያዊ ችግር ወይም ከሌሎች ባህሎች ወይም ዛሬ ከእኛ ጋር የማይዛመድ አንድ የሆነ ባህላዊ ጉዳይ ስማስተካከል እየሞከረ ነው እንዳንል ያደርገናል።

ይህንን አመለካከት የሚያዙ ሰዎች ሴቶች እንዳያስተምሩ የተ ሰጠው ትእዛዝ ዓለም-አቀፍ መሆኑን ይዘኑጋሉ። አንዳንዶች ጳውሎስ ሴት በጭራሽ ማስተማር የለባትም የሚል አቋም እንደ ነበረው ያስረዳሉ። ሌሎች ደግሞ ጳውሎስ ሥልጣን ባለው የማስተ ማር ስፍራ፣ ማለትም የቤተ ክርስቲያን መጋቢ ወይም በቤተ ክርስቲያን ላይ ሥልጣን ያላቸውን ሰዎች ስለምታስተምር ሴት ነው የሚናገረው ይላሉ። እንዲሁም ደግሞ እግዚአብሔር በሕይወቷ ውስጥ ያደረገውን ነገር የምትመሰክር ሴት፣ «እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው ይህ ነው» የሚል ሥልጣናዊ የማስተማር አገልግሎት ከምትሰጥ ይለያሉ።

ሠ. ገላትያ 3:28 ስለ ሴቶች እኩልነት ቢናገርም፣ ሴቶች በቤተ ክርስቲያንና በአመራር ውስጥ ስለሚኖራቸው ስፍራ አልገለጸም። ነገር ግን እኩል የደኅንነት ወራሾች መሆናቸውን ይገልጻል። ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በክርስቶስ ላይ ባላቸው እምነት የአብርሃም

መንፈሳዊ ዘሮች ይሆናሉ። በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ልጆች አይበላለጡም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መሪነት ለወንዶች ብቻ የተሰጠ መሆኑን የሚያሳዩ ሌሎች ጥቅሶች ስላሉ፣ ይህንን ጥቅስ በመጠቀም ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እኩል የመሪነት ተሳትፎ ሊያደርጉ ይችላሉ እንዳንል ይቃወማሉ።

37ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በዚህ ጉዳይ ላይ የምትስማማባቸው ነጥቦች የትኞቹ ናቸው? ለ) የማትስማማባቸውስ? ለምን?

2. መጽሐፍ ቅዱስ ሴቶችና ወንዶች እኩል በመሆናቸው፣ ሴት እግዚአብሔር ስጦታውን እስከ ሰጣት ድረስ የትኛውንም ዓይነት ሥልጣን ልትይዝ ወይም አገልግሎት ልትሰጥ ትችላለች። ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስና በ1ኛ ጢሞቴዎስ ውስጥ ያስፈራቸው መመሪያዎች ሴቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እኩልነታቸውን እየገለጹ ባሉበት ጊዜ ለተፈጠሩት ባህላዊ ወይም ጊዜያዊ ችግሮች መፍትሔ ለመስጠት ሲባል የቀረቡ ናቸው።

(ማስታወሻ፡- ይህንን አቋም የያዙ ሰዎች የተለያዩ ጥቅሶችን እንዴት እንደሚረዱ አብራራለሁ። እነዚህ አሳቦች የግድ የግል አቋሜን የሚያሳዩ ላይሆኑ ይችላሉ።)

ከዚህ በታች ይህንን አመለካከት የሚይዙ ሰዎች ሴት ልታገለግልና ሥልጣን ልትይዝ እንደምትችል የሚሰጡትን ማብራሪያ እንመለከታለን፡-

ሀ. በገላትያ 3:28 ጳውሎስ በክርስቶስ አይሁድ የለም፣ የግሪክ ሰው የለም (የጎሳ ልዩነት አይኖርም)፣ ባሪያ የለም፣ ጨዋ ሰውም የለም (የኢኮኖሚ ልዩነት አይኖርም)፣ ወንድ የለም፣ ሴትም የለም (የጾታ ልዩነት አይኖርም) ሲል በግልጽ አስተምሯል። ነገር ግን ሁሉም አንድ ናቸው። በርግጥ ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት ሰዎች ከተለያዩ ጎሳዎች ወይም ከተለያዩ የኢኮኖሚ ደረጃዎች የመጡ አይደሉም እያለ አልነበረም። ወንዶችና ሴቶች መኖራቸውንም አልካደም። ነገር ግን በዓለም ውስጥ ሰዎችን የሚለያዩት ክፍፍሎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስፈላጊዎች አይደሉም ማለቱ ነው። ኢየሱስ ካደረገልን ነገር የተነሣ ሁላችንም የእግዚአብሔር ልጆች ነን።



በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚታዩ ክፍፍሎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቦታ የላቸውም የሚለው ትምህርት የአዲስ ኪዳን ዐቢይ እውነት ነው። ይህ እውነት ሌሎች ጥቅሶችን (ለምሳሌ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሴቶች የሚኖራቸውን ሚና) የምንረዳበትን ሁኔታ ሊያሳየን ይገባል። ገላትያ 3:28ን በመጥቀስ ጳውሎስ መሪነት መያዝ ያለባቸው አይሁዶች ብቻ እንጂ አሕዛብ አይደሉም የሚለውን አቋም አይደግፍም ብለን ልንከራከር እንችላለን። መሪነት መያዝ ያለባቸው ሀብታም ባሪያ አሳዳሪዎች ብቻ እንጂ፣ ባሪያዎች አይደሉም የሚለውንም አቋም መፈታተን ይቻላል። (በቤተ ክርስቲያን ክርስቲያን ባሪያ በአማኝ ጌታው ላይ መንፈሳዊ መሪ ሊሆን ይችላል።) እንግዲህ ጳውሎስ አመራር በጾታ ላይ ይመሰረታል የሚል አቋም አለው እንድንል የሚያደርገን ምንድን ነው? ይህ ጳውሎስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲኖር ከሚፈልገው አንድነት የተለየ እንደሚሆን ግልጽ ነው። ስለሆነም፣ ወንዶች ብቻ በቤተ ክርስቲያን ሥልጣን ሊይዙ ይገባል የሚል አመለካከት ያላቸው የሚመስሉ ጥቅሶች የሁልጊዜ መመሪያዎች ሳይሆኑ፣ ጊዜያዊ አገዳዎች ተደርገው መወሰድ አለባቸው።

ለ. 1ኛ ቆሮንቶስ 11:5፡- ጳውሎስ ሴቶች ሲጸልዩና ትንቢት ሲናገሩ ራሳቸውን መሸፋፈን እንዳለባቸው ያዘዘበትን ምክንያት ስለማናወቅ፣ ምን ለማስተማር እንደ ፈለገ መረዳቱ አስቸጋሪ ነው። የዚህ ክፍል ትኩረት በሴቶች መሪነት ላይ ሳይሆን፣ ሴቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ «እንዴት» መልበስ እንዳለባቸው የሚያሳይ ነው። ጳውሎስ ሴቶች በማኅበረሰቡ ባህል ውስጥ ስለሚኖሩ ወንጌሉን እንዳያሰድቡ ይፈልጋል። በግሪክ ባህል ሴቶች ጸጉራቸውን ያስይዛሉ እንጂ ከትከሻቸው ላይ ለቅቀው አይሄዱም። (ማስታወሻ፡- ጳውሎስ ስለ አውሮፓ ሴቶች ጸጉር ነው የሚናገረው። የእነዚህ ሴቶች ጸጉር አይጠቀለልም። በተለይ ረዘም በሚልበት ጊዜ ከትከሻቸው ላይ ይዘናፈላል።) ለቆሮንቶስ ሴቶች በባህላቸው ተቀባይነት ያላቸውን የጸጉር አያያዝ በመተው መሸፋፈናቸውን አቁመው ጸጉራቸውን ከትከሻቸው ላይ ማዘናፈላቸው እንደ ሴተኛ አዳሪዎች ስለሚያስቆጥራቸው፣ ለወንጌሉ እንቅፋት ነበር። ሌሎች ምሁራን ጳውሎስ ትኩረት ያደ

ረገው ወንዶች የሴቶች ራስ በመሆናቸው ጉዳይ ላይ ሳይሆን፣ በሴቶችና በወንዶች የአለባበስ ልዩነት ላይ ነው ይላሉ:: ሴት እንደ ሴት፣ ወንድ እንደ ወንድ መልበስ አለባቸው የሚል ትምህርት ያስተላልፋል:: እኩልነት ማለት ሴት እንደ ወንድ ትለብሳለች ማለት አይደለም::

ጳውሎስ ባል የሚስቱ «ራስ» ነው ሲል ምን ማለቱ ነው? በሚለው ጥያቄ ሳይም የተለያዩ አመለካከቶች ተንጸባርቀዋል (1ኛ ቆሮ. 11:3-5)::

1) አንዳንድ ምሁራን ጳውሎስ የቆሮንቶስን ሰዎች አስተሳሰብ እየጠቀሰ እንጂ፣ የራሱን አመለካከት እየገለጸ አይደለም ይላሉ:: በመሆኑም፣ የቆሮንቶስ ወንድ አማኞች እግዚአብሔር በሴቶች ላይ የመሪነትን ሥልጣን ሰጥቶናል ብለው ያምኑ ነበር:: ጳውሎስ ሴቶች አላግባብ መልበሳቸው ትክክል ያልሆነበትን ምክንያት ለማሳየት የእነዚህን ወገኖች እምነት ተጠቅሟል ይላሉ:: እግዚአብሔር (ወይም ጳውሎስ) ወንዶች በሴቶች ላይ ሥልጣን አላቸው የሚል ትምህርት አለመስጠታቸውን ያስረዳሉ::

2) የባል «ራስ» መሆን ማለት፣ በታሪክ ሁሉ እንደ ተገመተው፣ ባል በሚስቱ ላይ «ሥልጣን አለው» የሚል ትርጉም አይሰጥም:: «ራስነት» የሚያሳየው ለማክበር መፈለግን ነው:: ስለዚህ፣ እግዚአብሔር የክርስቶስ ራስ ነው ማለቱ ክርስቶስ እግዚአብሔርን «ለማክበር» ይፈልጋል ማለት ነው:: ባል የሚስቱ ራስ ነው ማለትም ሚስት ባልን ለማክበር ትፈልጋለች ማለት ነው::

3) ሌሎች ምሁራን ይህ ጥቅስ መተርጎም ያለበት «ሴት በራሷ ላይ ሥልጣን ሊኖራት ይገባል» በሚል ነው ብለው ያስባሉ:: ስለሆነም፣ ጳውሎስ ሴት ራሷን በተገቢው መንገድ መሸፈን አለባት የሚል መልእክት እንደሚያስተላልፍ ያስረዳሉ::

ጳውሎስ ስለ ፍጥረት ያቀረበው አሳብ ወንድ ከሴት በፊት ስለ ተፈጠረ መሪ ይሁን አይልም:: በዘፍጥረት ታሪክ ውስጥ አዳም የሔዋን መሪ መሆን አለበት የሚል ቃል አልተጠቀሰም:: የፍጥረት ቅደም ተከተል ሴትና ወንድ የተለያዩ መሆናቸውንና ሴት ወንድን ለመከረጅ መሞከር እንደሌለባት የሚገልጽ ነው:: ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 11:11



-12 ያቀረበው ትምህርት ወንድና ሴት እኩል መሆናቸውን የሚያሳይ ነው:: ይህም በገላትያ 3:18 ከተጠቀሰው ጋር አንድ ዓይነት ነው::

ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 12 ስለ መንፈሳዊ ስጦታዎች ባቀረበው ትምህርት መንፈስ ቅዱስ ያለ ጾታዊ ልዩነት ለወደደው ስጦታን እንደሚሰጥ ይናገራል:: እንደ ትንቢት፣ ልሳናት ወይም ማስተማር የመሳሰሉትን የንግግር ስጦታዎች ወንዶች ብቻ እንደሚቀበሉ የሚያሳይ ነገር አልተጠቀሰም:: መንፈስ ቅዱስ ሴቶች እነዚህን ስጦታዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲያገለግሉ ካልፈለገ ለምን ይሰጣቸዋል? ዛሬ ሴቶችም ልክ እንደ ወንዶች መንፈሳዊ ስጦታቸውን በእኩል ደረጃ መጠቀማቸው ሴቶች ያለ ምንም ገደብ ስጦታዎቻቸውን እንዲጠቀሙ ይፈቅዳል ሲሉ ያስረዳሉ::

ሐ. 1ኛ ቆሮንቶስ 14:33-35:- ጳውሎስ ሴቶች በቤተ ክርስቲያን ጭራሽ እንዳይናገሩ አልከለከለም:: በ1ኛ ቆሮንቶስ 11 ውስጥ ሴት ትንቢት ልትናገርና ልትጸልይ ትችላለች::. በ1ኛ ቆሮንቶስ 14 ጳውሎስ ሰዎች ስጦታቸውን በአግባቡ ባለመጠቀማቸው ምክንያት አምልኮ እንዲረበሽ የሚያደርጉ ሦስት ዓይነት ሁኔታዎች መኖራቸውን ይገልጻል:: ስለዚህ፣ ጳውሎስ በማኅበር አምልኮ ላይ ምን ማድረግ እንደሚገባ ይገልጻል:: ሦስቱም ቡድኖች ለሌሎች ሲባል ራሳቸውን መቆጣጠር አለባቸው:: ልሳናት ወይም ትንቢት የሚናሩ ሰዎች ራሳቸውን እንዲቆጣጠሩና በየስብሰባው ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች ብቻ እንዲናገሩ ይመክራል:: አነስተኛ ትምህርት ያላቸው ሴቶች በአምልኮው ጊዜ እየጮሁ ያልገቧቸውን ነገሮች መጠየቅ የለባቸውም:: ጳውሎስ የሚናገረው ሥርዓት ያለው አምልኮ ስለ ማካሄድ ነው:: ስለዚህ፣ ሴቶች አምልኮን ከመረበሽ እንዲቆጠቡ ያሳስባቸዋል:: ነገር ግን፣ ቆይተው ይበልጥ ከተማሩት ባሎቻቸው ማብራሪያ እንዲጠይቁ ይመክራቸዋል:: ዛሬ ሴቶች የወንዶችን ያህል ትምህርት ስላላቸው፣ የባሎቻቸውን አመለካከት መጠየቅ አያስፈልጋቸውም:: አንዳንዶች ለግሪክና አይሁዳዊ ሴቶች በአደባባይ መነጋገር በባህላቸው ተገቢ ስላልሆነ፣ ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያን ልምምድ ባህልን ያገናዘበ መሆን አለበት

የሚል አመለካከት እንዳለው ያስረዳሉ:: ሴቶች በአደባባይ መናገራቸው የማያምኑ ሰዎች ወንጌሉን በተሳሳተ መንገድ እንዲረዱና ቤተ ክርስቲያንን እንዲንቁ ስለሚያደርግ፣ ይህ መደረግ የለበትም:: ጳውሎስ ባህሉ የሚቀበላቸው ከሆነ፣ ሴቶች ምንጊዜም መናገር የለባቸውም አላለም::

መ. 1ኛ ጢሞቴዎስ 2:11፡- ጳውሎስ በኤፌሶን ተዋረዳዊ አስተምህሮን እየገለጸ ነው:: ከወንዶች ያነሰ ትምህርት ያላቸው ሴቶች ለማስተማር ከሚሞክሩ፣ መጀመሪያ መማር ይኖርባቸዋል:: ስለሆነም፣ በእነዚህ ጥቅሶች ጳውሎስ ወንዶች በሴቶች ላይ የበላይ እንዲሆኑ ሳይሆን፣ ሴቶችም ልክ እንደ ወንዶች መማር እንዳለባቸው ማመልከቱ ነው::

ጳውሎስ ሴቶች «በሚማሩበት» ጊዜ ምን ዓይነት ባሕርይ ሊኖራቸው እንደሚገባ ለማመልከት ይፈልጋል:: ከመከራከር ይልቅ፣ በጥንቃቄ («በጸጥታ») መስማት አለባቸው:: ለሚሰጣቸው ትምህርት አክብሮት («መገዛት») ሊኖራቸው ይገባል:: የሐሰት አስተማሪዎችን እያዳመጡ ግራ ከመጋባት ይልቅ፣ የእውነትን አስተማሪዎች በሚገባ ማዳመጥ አለባቸው::

አንዳንዶች ጳውሎስ በአካባቢው ባህል ትክክለኛ የሆነውን ነገር እያብራራ ነው ይላሉ (1ኛ ጢሞ. 2:9-10):: ሴቶች እንዳያስተምሩና የቤተ ክርስቲያን ሥልጣን እንዳይይዙ ያስተማረው በባህሉ ሴቶች በእንዲህ ዓይነት ስፍራ ላይ መቀመጣቸው ትክክል ስላልሆነ ነው:: «አልፈቅድም» የሚለው ከአገባቡ እንደምንረዳው ጊዜያዊ እንጂ፣ ዘለቄታዊ እገዳ አይደለም ሲሉ ያስረዳሉ::

ሌሎች ጳውሎስ የከለከለው ሴቶች እንዳያስተምሩና ሥልጣንን በአጥፊ መንገድ እንዳይይዙ ነው ይላሉ:: በዘፍጥረት 2 እና 3 የተመለከተው የአዳምና የሔዋን ታሪክ አዳም በሔዋን ላይ ሥልጣን እንዳለው አያሳይም:: ነገር ግን ሔዋን በወደቀች ጊዜ፣ አዳም በኃጢአት እንዲወድቅ ተጽዕኖ አሳድራበታለች:: ጳውሎስ የሚናገረው አንድ ሰው ሌላ ሰው የተሳሳተ ነገር እንዲያምን ተጽዕኖ እንዳያሳድር ነው:: ስለዚህ፣ ሴቶች እንደ ሔዋን ባሎቻቸውን ለክፉ



ነገር እንዳይቀሰቅሱ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት መማር አለባቸው::

38ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በዚህ ጉዳይ ላይ የምትስማማባቸው ነጥቦች የትኞቹ ናቸው? ለ) የማትስማማባቸውስ? ሐ) ከሁለቱ አመለካከቶች የመጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ ድጋፍ ያለው የትኛው ነው? መ) በሴቶችና አመራር ላይ ያለህን አቋም ግለጽ::

## የማጠቃለያ ምክር

ሴቶች በቤተ ክርስቲያን አመራር ውስጥ ስለሚኖራቸው ስፍራ የሚደረገው ክርክር ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ የሚቀጥል መሆኑ አያጠራጥርም:: እያንዳንዳችን ሰዎች ለእግዚአብሔር ቃል የሚሰጡትን አተረጓጎም በጥንቃቄ በማጤን የምናምነውን መወሰን አለብን:: አቋምህን በምትወስንበት ጊዜ የሚከተሉትን ነገሮች ማስተዋሉ ጠቃሚ ነው:-

1. «አቋምህ» መሆን ያለበት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እንጂ፣ የዓለም አመለካከት መሆን እንደሌለበት ተገንዘብ:: እግዚአብሔር ዓለም እንደ ሴቶች መሪነት ያሉትን ነገሮች የሚረዳበትን መንገድ በመጠቀም የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንድንከተል ሊያግዘን ይችላል:: (ለምሳሌ፣ በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ኅብረተሰቡ ስለ ባርነት የነበረው አመለካከት በመለወጡ ነበር ቤተ ክርስቲያን ባሪያ አሳዳሪነት ትክክል ነው ብላ የያዘችውን አቋም መመርመርና ስሕተት መሆኑን መረዳት የጀመረችው::) ነገር ግን የምንጠየቀው የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት በመከተላችን እንጂ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች ትክክል ነው ወይስ ስሕተት ነው የሚሉትን ነገር በመያዛችን አይደለም::

2. መጽሐፍ ቅዱስ ቀደም ሲል በአእምሮህ ውስጥ ያለውን አሳብ እንዲደግፍልህ አትጠምዝዘው:: ሁላችንም በተወሰነ ደረጃ ይህንን ጥፋት እንፈጽማለን:: በተቻለን መጠን ግን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ መጥተን፣ «ጌታ ሆይ፣ የአንተ አመለካከት ምንድን ነው? ስለዚህ ጉዳይ ልታስተምረን የምትፈልገው ምንድን ነው?» ልንል ይገባል:: የምናነበውን ግልጽ ፍች ለመለወጥ ሳንሞክር እንቀበላለን::

ለባህላችን ከሚመች ነገር ጋር ለማስማማት ከመሞከር ይልቅ፣ የምንባቡን ግልጽ አሳብ መቀበሉ ከሁሉም የተሻለ ነው።

መንፈስ ቅዱስ አያስተማረኝ ነው ብለህ የምታምነውን ነገር ለመታዘዝ ቆርጠህ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ቅረብ። አንድ ክርስቲያን ሊይዝ የሚችለው እጅግ አስከፊ አቋም «መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን አውቃለሁ፣ ነገር ግን አልስማማበትም» ማለት ነው። ጳውሎስ ጸረ-ሴት አቋም ስላለው፣ እርሱን መስማት የለብንም የሚሉ ክርስቲያኖች አሉ። ይህ እውነት ከሆነ፣ ጳውሎስ የጻፈው በመንፈስ ቅዱስ ምሪት አይደለም ማለት ነው። እርሱ የጻፈውም ሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ነገር ሁሉ የሰዎች አመለካከት ብቻ ነው ማለት ነው። ይህ የእግዚአብሔር ሳይሆን፣ የሰው ቃል ነው ማለት ነው። ይህ ደግሞ ፍጹማዊ እውነት እንደሌለና፣ ሁሉም ነገር የሰዎች አመለካከት ብቻ እንደ ሆነ የሚያመለክት ነው። እንደ ፈለግን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ልንስማማም ሳንስማማም እንችላለን ብለን እናስባለን። እንዲህ ዓይነቱ አመለካከት ለእግዚአብሔር ቃል ከመገዛትና ከመታዘዝ ይልቅ በቃሉ ላይ «ፈራጆች» እንድንሆን ያደርገናል።

4. ከአንተ የተለየ አመለካከት ያላቸውን ሌሎች ክርስቲያኖች በትሕትናና በትዕግሥት አስተናግድ። በተለይም የእግዚአብሔርን ቃል በግልጽ ለመረዳትና ለመታዘዝ የሚፈልጉ ከሆነ፣ ይህ አስፈላጊ ነገር ነው። የእነርሱን አቋም በመገምገምና መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው በዚህ መንገድ ነው ብለህ በምታስበው መንገድ በመመርመር የምታምነው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነገር መሆኑን ወስን። ከዚያም በፍቅርና በታጋሽነት እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያኑ ሁሉ እንዲገልጽ ጸልይ።

## ማጠቃለያ

አሁን የቤተ ክርስቲያን አመራር ጥናታችንን አጠናቅቀናል። የቤተ ክርስቲያን አመራርን ከተለያዩ አቅጣጫዎች በመመልከት ጠቃሚ ትምህርት እንዳገኘህ እምነቴ ነው። እግዚአብሔር ይህንን መጽሐፍ በመጠቀም ሁላችንም ውጤታማ የቤተ ክርስቲያኑ መሪዎች እንድንሆን ይርዳን። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን



በመውደዱ ምክንያት ኢየሱስ እንዲሞትላት ካደረገ፣ እኛስ በተቻለን መጠን የእግዚአብሔርን ሕዝብ በአግባቡ ለመምራት መጣር አይገባንም? መሪዎች እንደ መሆናችን፣ ለክርስቶስ ያለንን ፍቅር ለማሳየት ትልቁ መንገድ እያንዳንዱ አማኝ በመንፈሳዊ ብስለትና በአገልግሎት ብቃት እንዲያድግ መጣር አይደለምን?

ምናልባት በዚህ መጽሐፍ የማትስማማባቸው አቋሞች ይኖራሉ። ወይም ደግሞ ከአኔ ሁኔታ ጋር አይሄዱም የምትላቸው ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ። ይህ ከሆነ፣ ጠቃሚዎች ሆነው ያገኘሃቸውን አሳቦች ተግባራዊ ከማድረግ ሊያቅብህ አይገባም። ከሁሉም በላይ፣ ሁላችንም መንፈስ ቅዱስ ዓለምን ለመለወጥ የሚጠቀምበት እውነተኛነትና መንፈሳዊ ባሕርይ ያለን ሰዎች እንድንሆን እግዚአብሔር ይርዳን። ሐዋርያት በዘመናቸው ሳይ ያመጡትን ዓይነት ለውጥ ለማምጣት እንድንችል ጌታ ይርዳን!

## አራተኛ ቀን፡- ለሳምንታዊ ውይይት በመዘጋጀት የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስ።

# ሳምንታዊ ስብሰባ

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. እያንዳንዱ አማኝ ወደ መንፈሳዊ ብስለት ለማደግ የሚያስችል መረዳት እንዳለው ማረጋገጥ የሽማግሌዎች ኃላፊነት ነው። ሀ) የቤተ ክርስቲያናችሁ ሽማግሌዎችና አስተዳደራዊ መዋቅር ለእያንዳንዱ አማኝ የእረኝነትን አገልግሎት በመስጠት በኩል ምን ያህል የተዋጣላቸው ናቸው? ለ) ሁሉም ምእመናን የሚያስፈልጋቸውን ያህል እጥጋቢ ክትትል እንዲያገኙ ለማስቻል በሽማግሌዎች አገልግሎትና በመዋቅሩ ላይ ምን ዓይነት ለውጥ ቢደረግ መልካም ይሆናል ትላለህ?

2. ሀ) ለሽማግሌዎች፣ ለወንጌላውያን ወይም ለመጋቢዎች የሚደረጉት ሥርዓተ-ሲመቶች ምን ዓይነት ጥቅም አላቸው? ለ) ሥርዓተ-ሲመቶች በአገልጋዩ ወይም በቤተ ክርስቲያን ላይ

# ዋቢ መጻሕፍት


Anderson, Dr. Lynn, They Smell Like Sheep. Howard Publishing Co., Inc., 1997.

Bingham, Robert E.Traps to Avoid in Good Administration. Broadman Press, 1979.

Blackaby, Henry & Richard, Spiritual Leadership. Broadman & Holman Publishers, 2001.

Clinton, Dr. J. Robert, The Making of a Leader. NavPress, 1988.

Cousins, Don; Anderson, Leith; DeKruyter, Arthur, Mastering Church Management. Multnomah Press, 1990.

Covey, Stephen R., The Seven Habits of Highly Effective People. Simon & Schuster, 1989.

Elliston, Edgar J., Home Grown Leaders. William Carey Library, 1992.

Fenton, Horace L. Jr, When Christians Clash. Intervarsity Press, 1987.

Grenz, S. Women in the Church.

Haggai, John, Lead On. Word Publishing, 1986.

McKinley, Steve; Maxwell, John; Asimakoupoulos, Greg. The Time Crunch: What to Do When You Can't Do it All., Multnomah Books, 1993.

McNeal, Reggie, A Work of Heart: Understanding how God Shapes Spiritual Leaders., Jossey-Bass, 2000.

Miller, Samuel, An Able and Faithful Minister. Presbyterian Heritage Publications, 1987.

Miller, Samuel, The Ruling Elder. Presbyterian Heritage Publications, 1984.

Myra, Harold, ed, Leaders: Learning Leadership from Some of Christianity's Best. Word Books, 1987.

Reinhart, Stacy T., Upside Down: The Paradox of Servant Leadership. Navpress, 1998.

Richards, Lawrence O. & Hoeldtke, Clyde, Church Leadership. Zondervan Corporation, 1980.

Rush, Myron, Management: A Biblical Approach. Victor Books, 1983.

Sander, J. Oswald, Spiritual Leadership. Lakeland: Marshall, Morgan, Scott, 1967.

Schaller, Lyle E., The Change Agent. Abingdon Press, 1972.

Stott, John R. W., The Preacher's Portrait. Billing & Sons, Inc. 1967.

Strauch, Alexander, Biblical Eldership: An Urgent Call to Restore Biblical Church Leadership. Lewis and Roth Publishers, Littleton, Co. 1988.


Swindoll, Chuck. Moses. Word Publishing, 1999.

«የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ፣ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ» (2ኛ ጢሞ. 2:15)

ተፈትኖ ያለፈ የእግዚአብሔር አገልጋይ ለመሆን ትሻለህ? እንደዚህ ለመሆን የምትሻ ከሆነ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ተግተህ ልታጠና ይገባል። ይህ የጥናት መምሪያና ማብራሪያ መጽሐፍ የእግዚአብሔርን ቃል ጠለቅ ብለህ እንድታጠናና ከሕይወትህ ጋር እንድታዛምድ በእጅጉ ይረዳሃል። በተለይም ለሚከተሉት ወገኖች ይህ መጽሐፍ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡-

. ለመዘምራን ቡድን አገልጋይ
. ለወጣቶች መሪ
. ለቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ
. ለሰንበት ትምህርት ቤት መምህር
. ለመጋቢ
. ለወንጌላዊ
. ለመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት መምህር
. ለትጉሕ የእግዚአብሔር ቃል ተማሪ።

ይህ መጽሐፍ ተማሪው በእግዚአብሔር ቃል ላይ ሰፊ ግንዛቤ እንዲኖረውና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለማገልገል ይችል ዘንድ ለመርዳት የሚዘጋጁት ተከታታይ መጻሕፍት አካል ነው።



Church Leadership,Book 2
Printed by SIM Press

BIBLE BASED BOOKS
SIM PUBLISHING